LAW
EDUCATION
DISCUSSION
OPPORTUNITY
A STRONGER
SOCIETY

*"Where there is no law, there is no freedom."*
*J. Locke*

# TINSAE LEGAL FORUM

*"ignorance of law is no excuse"*

## KEEP LEARNING.
## STAY CONNECTED.

Join Tinsae Legal Forum for legal insights, learning materials, and practical resources.

**TELEGRAM**
Legal updates & discussions
OPEN →

**YOUTUBE**
Legal education videos
OPEN →

**FACEBOOK**
Community & announcements
OPEN →

LAW | ETHIOPIA | A BETTER TOMORROW

# የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ ለመገንዘብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች

(ቅጽ አንድ)
ሁለተኛ እትም

በሙሐሪ ረዳኢ.
2002 ዓ.ም.

Generated by CamScanner

# ማውጫ


መግቢያ ገጽ

ምእራፍ አንድ - አጠቃላይ vii

1.1 የአዋጁ ትርጉ 1
1.2. የአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን 3
1.3 የአዋጁ ይዘት 7

1.3.1. ስለ ወንጀል ድንጋጌዎች 7
1.3.2. ስለ መተጫጨት 8
1.3.3 ስለ የሥጋና የጋብቻ ዝምድና 11

ምእራፍ ሁለት - ስለ ጋብቻ አፈጻጸም

2.1. የጋብቻ ምንነት 11
2.2. ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች 18

2.2.1. ፈቃደኝነት 19
2.2.2. እድሜ 20
2.2.3. ዝምድና 23
2.2.4. በጋብቻ ላይ ጋብቻ 27
2.2.5. በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ 29

2.3 ጋብቻ እንዳይፈፀም ስለመቃወም 32
2.4. ስለጋብቻ ምዝገባ 38
2.5. የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት 41

ምእራፍ ሦስት - የጋብቻ ውጤት 49

3.1 ስለጋብቻ ውል 49

3.2. ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት 56
3.3. ጋብቻ በንብረት በኩል ስሚኖረው ወጤት 64

ምእራፍ አራት - ጋብቻ መፍረስና ውጤቶቹ 83

4.1. ጠቅላላ 83
4.2. በስምምነት ስለመፋታት 91
4.3. የፍቺ ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ 95
4.4. የባልና ሚስትን ሃብት ስለማጣራት 110

ምዕራፍ አምስት - ጋብቻ ስለመፈፀሙ የሚቀርብ ማስረጃ 115

5.1. የጋብቻ ምስክር ወረቀት 115
5.2. የትዳር ሁኔታ 118

ምእራፍ 6 - ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር 122

አባሪ አንድ 131 - 158
አባሪ ሁለት 159 - 183



# መግቢያ

ይህ ፅሁፍ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ዙሪያ አንዳንድ ለግንዛቤ የሚረዱ ነጥቦችን ለመጠቆም ታቅዶ የተዘጋጀ ነው:: በዚህ ህግ ዙሪያ የሚቀርቡት ሃሣቦች በሁለት ክፍል ተለይተው እንዲቀርቡ የታሰበ ሲሆን አንደኛው ክፍል እነሆ በዚህ መልክ ቀርቧል::

አንደኛው ክፍል የጋብቻ አፈጻጸምና ፍቺንጿ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን አስመልክቶ እንዲሁም ከእነዚህ ጉዳዮች ጋር ተዛማጅነት ያለቸው ነጥቦች ላይ የሚያተኩር ሲሆን ከትርብ ጊዜ በኋላ ታትሞ ይወጣል ተብሎ በሚታሰበው ሁለተኛ ክፍል ደግሞ ተወላጅነትን (filiation) ጉዲፈቻ (adoption) እንዲሁም አሳደሪነትና ሞግዚትነትን በሚመለከት በዋነኝነት በህፃናት ለይ አትኩረው የተደነገጉትን የአዋጁ ምእራፎች የሚሸፍን ይሆናል::

እንደሚታወቀው በሃገራችን ህጎች ላይ የተጻፉ ማብራሪያዎችም ሆነ ትችቶች በጣም ጥቂት ናቸው:: በተለይም በሃገሪቱ ቋንቋ የተፃፉት በጣት የሚቆጠሩ ናቸው:: ከሁሉም በላይ ግን የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዲስ በመሆኑ ለመነሻ የሚሆን ሃሣብ ማቅረብ ተገቢ መሆኑ አምንንበታል:: ምክንያቱም ወደፊት በህጉ ዙሪያ ለሚደረጉ ምርምሮችና ማሻሻያዎችም እንደግብአት ሆኖ ያገለግላል የሚል ተስፋ አለን::

የፅሁፉ አቀራረብ በሃገሪቱ ቋንቋ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በቀላል አቀራረብ ለማዘጋጀት ጥረት ተደርጓል:: የቤተሰብ ጉዳይ የህግ ጉዳይ ብቻ ባለመሆኑ ሌሎች ከህግ ሙያ ውጪ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችም

አንባቢው እንዲረዱት ለማስቻል በተቻለ መጠን "የህግ ቋንቋዎች" (legal jargons) ላለመጠቀም ጥረት ተደርጓል::

የዚህ ዕሁፍ አቅራቢ የቤተሰብ ህጉ ሲቀረፅ በኮሚቴ አባልነት ተሳታፊ ስለነበር ህጉ አሁን ያለውን ቅርጽና ይዘት ይዞ እንዲወጣ ታሳቢ ተደርገው የተወሰዱ ነጥቦች የመረዳት እድል አጋጥሞታል:: እነዚህን ነጥቦች መግለጽ ህጉን በተሻለ ሁኔታ ለመገንዘብ ይረዳል ከሚል እምነት በዚህ ዕሁፍ ውስጥ እንደየአግባብነታቸው ለማስቀመጥ ተሞክሯል:: በርግጥ ይህ ማብራሪያ ከህግ አውጪው አካል የወጣ አይደለምና አስገዳጅ (authoritative) አይሆንም:: ሆኖም የህጉ ረቂቁ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከቀረበ በኋላ ከሞላ ጎደል በቀረበበት ሁኔታ የፀደቀ ስለሆነ ህግ አውጪው የአርቃቂዎቹ ሃሳብና ፍላጎት የራሱ አድርጎ ተቀብሎታል ሊባል ይቻላል:: ስለዚህም በዚህ ረገድ የአርቃቂዎች አባል የነበረው የዚህ ዕሁፍ አቅራቢ ማብራሪያ ከዚህ አንፃር ፋይዳ ያለው ይመስለናል::

በመጨረሻም ዕሁፉን በተቻለ መጠን በአማርኛ ቋንቋ ተጠቅሞ ለማዘጋጀት ጥረት የተደረገ ቢሆንም የአማርኛ ቋንቋ በአግባቡ አይገልፀው ይሆናል የሚል ሥጋት በተፈጠረበት ቦታ ሁሉ በቅንፍ የእንግሊዝኛ ቃል ወይም ሃረግ ለመጠቀም ተገደናል:: ዕሁፉ የተሟላ እንዲሆን በማሰብም በዚህ ማብራሪያ የተካተቱትን የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎችና የፍትህ ሚኒስቴር አዘጋጅቶት ከነበረው ረቂቅ ውስጥ ማብራሪያው የሚሸፍነው የረቂቁ ክፍል በአባሪነት እንዲያያዙ ተደርገዋል:: ይህም ከፍትሐብሄር ህጉ የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች ወደ ፍትህ ሚኒስቴር ረቂቅ ከዚያም ወደ ተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የመጨረሻው ቅርጽና ይዘት የተደረጉትን ሽግግሮች ለማንፀባረቅ ይረዳል የሚል እምነት አለን::



# ምዕራፍ 1 - አጠቃላይ

## 1.1 የአዋጁ ቅርፅ

በፍትሐብሄር ህጉ ውስጥ ተካትቶ የሚገኘው የቤተሰብ ህግ ለአርባ ዓመታት ያህል ሥራ ላይ ከቆየ በኋላ የፌደራል መንግስት እነሆ ከሰኔ ወር 1992 ዓ.ም ጀምሮ ህጋዊ ኃይል ያገኘ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አውጇል::

አንድ ህግ ለማውጣት ሲታሰብ ምን ዓይነት ቅርጽ ሊይዝ እንደሚገባ መወሰን አንዱ ጉዳይ ነው፤ ማለትም በነጠላ አዋጅ (piece of legislation) መልክ ወይስ በመጽሐፍ (code) መልክ ሊወጣ ይገባል ብሎ አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ የግድ ይላል:: ነባሩ የቤተሰብ ህግ በፍትሐብሄር ህጉ ውስጥ የመጽሐፉ አንድ አካል ሆኖ ሲሠራበት እንደነበረ አይዘነጋም:: የፍትህ ሚኒስቴር አዘጋጅቶ አቅርቦት በነበረው ረቂቅ ህግ ግን ከፍትሐብሄር ህጉ ውስጥ ወጥቶ ራሱን ችሎ ግን ደግሞ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት እንዲሁም ጉዲፈቻን የመሰሉ ከቤተሰብ ህግ ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ጉዳዮችን ያካተተ ስለነበር የነጠላ አዋጅ ቅርጽ እንጂ የኮድነት ባህርይ ነበረው ለማለት ያስቸግራል::

በአንፃሩ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ራሱን ችሎ በኮድ መልክ እንዲወጣ ተደርጓል:: በመሆኑም የተሟላ ይሆን ዘንድ በ1952 የወጣው የፍትሐብሄር ህግ አካል የነበሩትን በ"ሁለተኛ መጽሐፍ" "አንቀጽ አራት" ሥር የነበሩትን ድንጋጌዎች/ ከቁጥር 550 - 825/ እንዲሁም ከ"አንደኛው መጽሐፍ" "አንደኛው" አንቀጽ

/ከቁጥር 198 - 338/ ያሉትን ድንጋጌዎች በማጣመርና አስፈላጊ ማሻሻያዎች በማከል የተደራጀ ነው::

የቤተሰብ ህጉ ከአጠቃላይ የፍትሐብሄር መጽሐፍ ተገንጥሎ ራሱን ችሎ በኮድ መልክ መውጣቱ የፍትሐብሄር ኮዱን አንድነት የሚያናጋ መሆኑን ቢታመንም ቢያንስ በሁለት ምክንያቶች ብቻውን ነጥሎ ማውጣቱ ተመራጭነት አግኝቷል::

አንደኛ የፍትሐብሄር ህጉ አጠቃላይ ክለሳና ማሻሻያ እስኪጠናቀቅ ድረስ መጠበቁ የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎች በሴቶችና በህጻናት መብት ላይ የነበራቸውን አሉታዊ ተጽእኖ ላልተወሰነ ጊዜ ማስቀጠል ስለሚሆን የሚመረጥ መንገድ አልሆነም:: አዲስና ከህገ መንግስቱ ጋር የተጣጣመ ህግ በአስቸኳይ መውጣት አለበት የሚለው የህብረተሰብ ግፊትም በቸልታ የሚታለፍ አልሆነም:: ሁለተኛ በአሁኑ ወቅት ሃገራችን እየተከተለች ባለችው ፌዴራላዊ አወቃቀር የፍትሐብሄር ህጉ አንድነቱን ጠብቆ መቀጠል የሚያስችለው አይደለም ምክንያቱም የተወሰኑት ክፍሎቹ በፌደራላዊ መንግሥቱ ሥልጣን ሥር የተቀሩትም በክልሎች ሥልጣን የሚወድቁ ሊሆኑ ስለሚችሉ ዞሮ ዞሮ የፍትሐብሄሩ መጽሐፍ መከፋፈሉ የማይቀር ነው:: ስለዚህ የኮዱን አንድነት ጠብቆ የማይኬድ ከሆነም አጣዳፊነት ያላቸው ጉዳዮች በተቻለ ፍጥነት ማወጁ ተመራጭ ይሆናል:: ሲታወጅም አጠቃላይ (Comprehensive) በሆነ መልክ ሆኖ የቤተሰብ ግንኙነቶች ማለትም የጋብቻ አፈጻፀምና ፍቺን፤ የህፃናት አስተዳደግና የጋራ ንብረት ክፍፍልን ፤ አካለመጠን ያልደረሰን ሰው አሳዳሪነትና የሞግዚትነት



እንዲሁም ጉዲፈቻንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የሚገዛ አንድ ወጥ ለነድና አንድ መጽሐፍ (ኮድ) አዘጋጅቶ በዚህ ዙሪያ የሚነሱትን ክርክሮች በተቻለ መጠን ወደሌላው የህግ ዘርፍ መሄድ ሳያስፈልግ በዚሁ ኮድ መሠረት ለመፍታት ያስችል ዘንድ በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጅቶ እንዲወጣ ተደርጓል::

## 1.2. <u>የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን</u>

በኮድ መልክ ራሱን ችሎ የወጣው የተሻሻለው የቤተሰብ ህጉ ግን አሁን ባለው ሁኔታ አገር አቀፍ ተፈጻሚነት የለውም::

በአሃዳዊ ቅርፀ መንግስት ውስጥ ህግ አውጪው አካል ራሱ የአዋጁን የተፈጻሚነት ወሰን በግልጽ ካልገደበው በቀር በሃገሪቱ በሞላ ተፈጻሚነትና አስገዳጅነት ይኖረዋል:: በፌደራል ሥርዓተ መንግስት ግን ሁኔታው የተለየ ነው:: በፌደራላዊ ሥርዓት መንግስታዊ ሥልጣን በሁለት ደረጃዎች ይከናወናል:: ዋና ዋናዎቹ መንግስታዊ ሥልጣኖች ማለትም የህግ አውጭነት፤ የህግ አስፈፃሚነትና የዳኝነት ሥራዎች በፌዴራል መንግስት ደረጃና በአባል መንግስታት ደረጃ የሚካሄዱ ናቸው:: በፌዴራል መንግስቱ የሥልጣን ክልል ውስጥ በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግስቱ ህግ አውጥቶ በሃገሪቱ በሞላ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል:: በአንጻሩ በአባል መንግስታት የሥልጣን ክልል በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ ግን ህግ የማውጣት ሥልጣን አይኖረውም ቢያወጣም ህገ-መንግስታዊ አይሆንም::

በመሆኑም የህጉን የተፈጻሚነት ወሰን ለመለየት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት

ነው? ወይስ የክልል መንግስታት? የሚለው ጉዳይ ማየቱ አግባብነት አለው፡፡ ለዚህም መልስ የሚሰጠን ህገ-መንግስቱ ነው፡፡

ህግ በማውጣት ረገድ የፌደራሉ ህግ አውጪ አካል የሠራተኛ ጉዳይ ህግን ፤ የንግድ ህግን እንዲሁም የወንጀለኛ መቅጫ ህግን የማውጣት ሥልጣን እንዳለው በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 55(3)(4) እና (5) ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በመርህ ደረጃ የፌደራል መንግስቱ የፍትሐብሔር ህግ የማውጣት ሥልጣን እንዳለው አልተመለከተም፡፡ የቤተሰብ ህግ ደግሞ የፍትሐብሔር የህግ ዘርፎች ከሚባሉት አንዱ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 52(1) መሠረትም ለፌደራል መንግስቱ በግልፅ ያልተሰጠ ሥልጣን የክልል ሥልጣን እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የፍትሐብሔር ህግ የማውጣት ሥልጣን በዋናነት የክልሎች ነው ማለት ነው፡፡

በርግጥ የፌደራሉ ህግ አውጪ አካል በልዩ ሁኔታ "አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን ለመፍጠር ሲባል በፌደራል መንግስት ህግ እንዲወጣላቸው የሚያስገድዱ ስለመሆናቸው በፌዴሬሽን ምክር ቤት የታመነባቸው የፍትሐብሔር ህጎች ያወጣል" በሚል በህገ መንግስቱ አንጽ55(6) የተደነገገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የቤተሰብ ህግ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሲባል አንድ ወጥ ህግ ያስፈልገዋል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ የቤተሰብ ህግ በባህርዩ ከባቢያዊ (local) ነው፡፡ በመሆኑም ክልሎች ህገ-መንግስቱን መሠረት አድርገውና ህገ መንግስቱን ሳይጥሱ ግን ደግሞ ባህላዊና



ሃይማኖታዊ ሁኔታቸውን ግምት ውስጥ አስገብተው ህግ ሊያወጡበት የሚገባ ዘርፍ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ አንድ ወጥ የፌደራል ህግ ያስፈልገዋል የሚባል ቢሆን እንኳ ይህ የሚወሰነው በፌደሬሽን ምክር ቤት እንጂ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አይደለም፡፡ የፌደሬሽን ምክር ቤት ደግሞ እስከአሁን ድረስ በዚህ ረገድ አንድ ወጥ የፌደራል የቤተሰብ ህግ ሊወጣ ይገባል ብሎ የወሰደው አቋም የለም፡፡ ስለዚህ ነገሩን በማጠቃለል ሲታይ የቤተሰብ ህግ የማውጣቱ ሥልጣን የክልሎች ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ እምነት በመነሳትም ይመስላል የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የራሱ የቤተሰብ ህግ አውጥቶ በሥራ ላይ አውሎ ይገኛል፡፡

እዚህ ላይ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ጉዳይ ግን አሁን ባለው የኢትዮጵያ አስተዳደራዊ አወቃቀር መሠረት አገሪቱ በሙሉ በክልሎች ያልተሸነሸነች መሆኗ ነው፡፡ ይልቁንም የክልልነት ደረጃ ያልተሰጣቸው ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለፌደራሉ መንግስት የሆኑ መስተዳድሮች አሉ፡፡ በእነዚህም መስተዳድሮች ውስጥ ጋብቻ ይፈፀማል፤ ቤተሰብ ይመሰረታል፤ ፍቺም ይከናወናል፡፡ ለእነዚህ የሚሆን አዋጅ የሚያወጣው ደግሞ በፌደራሉ መንግስት ህግ አውጪ አካል ነው፡፡ ስለዚህ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ይህን ህግ ሲያወጣ ተፈጻሚነቱ ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለፌደራል መንግሥት ለሆኑት ለአዲስ አበባ አስተዳደርና ለድሬዳዋ ካውንስል እንደሆነ በግልጽ ደንግጓል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በፌደራላዊ አወቃቀሩና የሥልጣን ክፍፍሉ መሠረት የፍትሐብሔር ጉዳዮች በመርህ ደረጃ በክልሎች ሥልጣን ስር የሚወድቁ በመሆናቸውና የቤተሰብ ህግ ደግሞ ከፍትሐብሔር የህግ ዘርፎች አንዱ በመሆኑ



Generated by CamScanner

በክልሎች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ በመሆኑ የፌደራል ህግ አውጪው አካል /የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት/ በዚህ ዘርፍ አገር አቀፍ ህግ ለማውጣት ህገ መንግሥታዊ ሥልጣን እንደሌለው ስለተገነዘበ እንደሆነ ይገመታል:: በመሆኑም ለጊዜውም ቢሆን የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ተፈጻሚነት አዋጅ ለማውጣት ስልጣን ባልተሰጣቸውን ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለፌደራል መንግስቱ በሆኑት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ መስተዳድር ላይ የተወሰነ ነው::

ዞሮ ዞሮ ግን በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ዝግጅት ወቅት በነበሩት ተከታታይ አውደ ጥናቶች ክልሎችም ተወካዮቻቸውን እየላኩ ሃሣብ የሰጡበትና ያዳበሩት ስለሆነ ብዙዎቹ ክልሎች ይህን ህግ ከመጠነኛ ማስተካከያዎች ጋር በምክር ቤቶቻቸው በኩል ተቀብለው የህጎቻቸው አካል ያደርጉታል የሚል እምነትና ተስፋ አለ:: በርግጥ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳደር የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ከመታወጁ አንድ ዓመት ያህል ቀደም ብሎ በፍትሐብሔር ህጉ ላይ ያሉትን የቤተሰብ ህጉን ድንጋጌዎች በማሻሻል የራሱ የቤተሰብ ህግ ያወጀ ሲሆን ሌሎች ክልሎችም በዚህ ረገድ በእንቅስቃሴ ላይ እንደሆኑ ይነገራል::



## 1.3. የአዋጁ ይዘት

### 1.3.1 ስለ ወንጀል ድንጋጌዎች

ሌላው በአጠቃላይ ክፍሉ ሥር ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ጉዳይ ቀደም ሲል በፍትሐብሔር ህጉ ሥር የነበሩት የወንጀል ቅጣት ድንጋጌዎች ከተሻሻለው የቤተሰብ ውስጥ እንዲካተቱ አለመደረጋቸው ነው:: ለዚሁ ምክንያቱ አንደኛ በፍትሐብሔር ህጉ ውስጥ የነበሩት የወንጀል ድንጋጌዎች ወንጀሉን ከነቅጣቱ ያስቀመጡ ሳይሆኑ እንዲሁ በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ መሠረት የሚያስቀጡ መሆናቸው የሚጠቁሙ ብቻ ነበሩ:: በወንጀል ህግ መሠረታዊ መርህ መሠረት ግን አንድ ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑን መደንገግ አስፈላጊ ቢሆንም በቂ ግን አይደለም:: ምን ያህል እንደሚያስቀጣም በህግ ሊመላከት ይገባል:: የቅጣቱ መጠንና ዓይነት በህግ ባልተመለከተበት ሁኔታ ፍርድ ቤት ራሱ የራሱ ቅጣት ሊወስን አይችልም:: ስለሆነም በቤተሰብ ህጉ ውስጥ የነበሩት የወንጀል ድንጋጌዎች ከወንጀል ህጉ ጋር ተገናዝበው ካልታዩ በቀር ለብቻቸው ተፈጻሚ የሚሆኑ አልነበሩምና ወደ ወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ከመሄድ የማያድኑ ስለነበሩ ብዙም ፋይዳ አልነበራቸውም:: ሁለተኛ የፍትሐብሔር ህግ ዓላማ የግለሰቦችን ፍትሐብሔራዊ መብትና ግዴታን መደንገግ እንጂ የወንጀል ቅጣት መደንገግ ባለመሆኑ፤ ሦስተኛ በኮድ በሚተዳደሩ ነገሮች በወንጀል የሚያስቀጡ ድርጊቶች በወንጀለኛ መቅጫ ኮድ ውስጥ ተጠቃልለው ሊገኙ ስለሚገባቸው የወንጀል ህጉ ሲሻሻል እዚያው ሊጠቃለሉ እንደሚገባ በማመን እዚህ መግለጻቸው



Generated by CamScanner

አላስፈለገም::[1] በመሆኑም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የፍትሐብሄር ሃላፊነቶችና ውጤታቸው ከመደንገግ ባሻገር ለጋብቻ አስፈላጊ ሁኔታዎች ሳይሟሉ በመተረታቸው ለሚያስከትሉት የወንጀል ሃላፊነት የተደነገገ ነገር አይገኝም::

### 1.3.2 ስለመተጫጨት

ሌላው በዚህ ክፍል ሥር መወሳት ያለበት ጉዳይ መተጫጨትን አስመልክቶ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የወሰደው አቋም ነው:: በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሄር ህግም ሆነ በቅርቡ በፍትህ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በቀረበው ረቂቅ የቤተሰብ ህግ መተጫጨት ህጋዊ እውቅና ተሰጥቶት ምንነቱና ውጤቱ በህግ ተደንግጎ ነበር::[2] በርግጥ በፍትሐብሄር ህጉ ስለመተጫጨት የነበረው ፅንሰ-ሃሣብና በፍትህ ሚኒስቴሩ ረቂቅ በመተጫጨት ጽንሰ ሃሳብ ላይ የተወሰደው አቋም ልዩነት ነበራቸው::

በፍትሐብሄር ህጉ መሰረት መተጫጨት ሲባል የእጮኛውና የእጮኛይቱ ቤተ ዘመዶች በልጆቻቸው መካከል ጋብቻ ይኖራል ብለው በእነዚሁ የሁለቱ ቤተዘመድ አባሎች መካከል የሚደረግ ውል ሲሆን /አንቀጽ 560/1/ በዋነኛነት ወላጆች ለአካለመጠን ባልደረሱ ልጆቻቸው ላይ ያላቸውን ፍፁማዊ ሥልጣን የሚገነዘቡበት ነበር ማለት ይቻላል:: በፍትህ ሚኒስቴር በቀረበ ረቂቅ ግን "መተጫጨት ማለት እጮኛውና እጮኛይቱ በመካከላቸው ለወደፊት ጋብቻ ለመፈጸም የሚያደርጉት ስምምነት ነው:: /የረቂቁ አንቀጽ 8/:: በርግጥ በሁለቱም ህጎች "መተጫጨቱ በእጮኛውና በእጮኛይቱ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ካልሆነ በቀር ህጋዊ ውጤት አይኖረውም" ተብሏል:: /ፍትሐብሄር ቁጥር 565 እና ረቂቅ ህጉ አንቀጽ 8/2/ ይመለከተዋል/ ቢሆንም በፍትሐብሄር ህጉ መሠረት መተጫጨት በዋናነት በእጮኛዎቹ ቤተ ዘመዶች መካከል የሚደረግ ስምምነት መሆን ሲገባው በፍትሕ ሚኒስቴር ቀርቦ በነበረው ረቂቅ ግን መተጫጨት የቤተዘመድ ጉዳይ ሳይሆን መነሻና መድረሻው የእጮኛውና የእጮኛይቱ ስምምነት ነው:: ሁለቱንም የሚያመሳስላቸው ግን ስምምነቱ በቤተዘመድ መካከልም ተደረገ በእጮኛውና በእጮኛይቱ መካከል፤ ይዘቱ ወደፊት ጋብቻ ለመፈጸም የሚደረግ ስምምነት እንጂ ጋብቻ አይደለም:: በመሆኑም የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ይህንኑ በህግ ማካተት አስፈላጊ ሆኖ ስላላገኘው እንዲወጣ አድርጎታል:: ምክንያቱም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ እምነት መተጫጨት መጋባት ሳይሆን ለወደፊቱ ይጋባሉ ወይም እንጋባለን ብሎ "መስማማት" ስለሆነ፤ የተጫጩ ስምምነት እንዲጋቡ ስለማይገደዱ፤ መተጫጨት ሳይከናወንም በቀጥታ ጋብቻ መፈጸም የሚቻል በመሆኑ መተጫጨት ለጋብቻ ቅድመ ሁኔታ አይደለም:: ስለዚህ ለጋብቻ ወሳኝና አስፈላጊ ያልሆነን ስርዓት በቤተሰብ ህጉ ውስጥ ማካተቱ አስፈላጊ አልሆነም::

---

[1] የወንጀለኛ መቅጫ ህጉም በአሁኑ ወቅት የማሻሻያ ሥራ እየተከናወነበት ያለ በመሆኑ ይህንኑ ግምት ውስጥ ያስገባ ይዘት ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል::

[2] ለበለጠ ግንዛቤ የፍትሀብሄር ህጉ ከቁጥር 560-576 እና በፍትሕ ሚኒስቴር የተዘጋጀው ረቂቅ የቤተሰብ ህግ ከአንቀጽ 8-17 ያሉትን ድንጋጌዎች መመርመር ይቻላል::

በርግጥ ትጭጭት የወደፊት ተጋቢዎችን እንደመከዋወቂያና መጠናኛ መድረክ ሊያገለግላቸው ይችላል ሊባል ይችል ይሆናል። አኩሪና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህላችን ስለሆነ ይዘነው ልንቀጥል ይገባል የሚል ክርክርም አልፎ አልፎ ይደመጣል። ሆኖም የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በህግ እውቅና አይሰጠውም ብሎ ከቤተሰብ ህጉ ሠረዘው እንጂ ክልክል ነው ስላላለው ህገ መንግሥቱን እስካልተጻረረ ድረስ በመጠናኛ መድረክነቱ ሊቀጥል ይችላል። ባህሉችን ነው ስለሚባለውም በመሠረቱ አንድ ወጥ የሆነ የመተጫጨት ስርዓት በሀገሪቱ ውስጥ ያለ አይመስልም። የሰሜኑ ከምዕራቡ ወይም ከመሃሉ የሃገሪቱ ክፍል በእጅጉ ይለያል፤ ሌላውም እንዲሁ፤ በየሃይማኖቶቹም እንዲሁ ልዩነት አለው። በመሆኑም አንድ ወጥ የመተጫጨት ስርዓት በሌለበት ሁኔታ በአንድ ወጥ ህግ ለመደንገግ መሞከር አስቸጋሪ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል። ስለሆነም መተጫጨትን እንደተቋም በህግ እውቅና ማስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። በተለይም የዚህ ህግ ተፈጻሚነት በአዲስ አበባና ድሬዳዋ መስተዳድሮች መሆኑ አብሮ የጎላ ያደርገዋል። በክልሎች ሲታይ የተቋሙ አላስፈላጊነት የቤተሰብ ህጎች ተቋሙን የሚያካትቱ ህጎች ሲኖሩ በሚወጡ እንደሚችሉ ይገመታል። ያም ቢሆን ግን ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል የሚለውን ህገ-መንግስታዊ በር መርህ እንዳይሸረሽርና ለህፃናት ጋብቻ (Child Marriage) እንዳይከፍት ጥንቃቄ ሊደረግለት ይገባል።



### 1.3.3. ስለ የሥጋና የጋብቻ ዝምድና

በመጨረሻም ቀደም ሲል ፍትሐብሔር ህጉ ውስጥ እንደ አንድ ክፍል ተቆጥሮ ቦታ ተሰጥቶት የነበረው ስለ ሥጋና ጋብቻ ዝምድና የሚደነግገው ነበር።[1] በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ ይህ አልተካተተም። ለዚህም ምክንያቱ የሥጋ ዝምድናውም ሆነ የጋብቻ ዝምድናው በአቆጣጠሩ ላይ የተለያዩ አመለካከቶችና ስልቶች እየቀረቡ ከግልጽነት ይልቅ ውዥንብር ሲፈጥር መቆየቱ በማስታወስ ዓላማውን የሚያመለክት አቀራረጽ መከተሉ ተመርጧል። በመሆኑም የሥጋና የጋብቻ ዝምድና ህጉ ጠቃሚነቱ በዋነኛነት ለጋብቻ ክልከላና ቀለብ የመስጠት ግዴታ ለመጣል ስለሆነ ማን ከማን ጋር መጋባት እንደማይፈቀድለት ማን ለማን ቀለብ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት መጥቀሱ የተሻለ እንደሚሆን ታምኖበታል በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በዚሁ መልክ እንዲቀመጥ ተደርጓል።

## ምዕራፍ 2 - ስለጋብቻ አፈጻጸም

### 2.1. የጋብቻ ምንነት

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የመጀመሪያ ምእራፍ ሆኖ የተቀረጸው በጋብቻ አፈጻጸም ዙሪያ ያሉትን ድንጋጌዎች የሚያካትተው ክፍል ነው። ህጉ በተለምዶ እንደሚደረገው የጋብቻ ትርጉምን በመግለጽ አልጀመረም።

[1] የፍትሕ ሚኒስቴር አዘጋጅቶት በነበረው ረቂቅ የቤተሰብ ሀግም ከአንቀጽ 1-7 ይህንኑ የሚመለከት ነበር።



Generated by CamScanner

አንዳንድ ሃገሮች የቤተሰብ ህጎቻቸውን የጋብቻን ምንነት በመተርጎም ይጀምራሉ። ለምሳሌ በኢንዶኔዥያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ (1) "ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል መንፈሳዊና ቁሣዊ ጥምረት በመፍጠር በፈጣሪ ፈቃድ ዘላቂና ደስተኛ ቤተሰብ ለመመስረት የሚደረግ ስምረት ነው" በሚል ይተረጉመዋል። ጋብቻን ዘር ለማፍራት በማሰብ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረግ ግንኙነት ነው ብለው የሚተረጉሙት ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ ዘር ለማፍራትና የጋራ ኑብረት ለመመስረት የሚደረግ ጥምረት በመሆኑ ላይ ይስማማሉ። እንዲህ ዓይነት ትርጓሜዎች ግን ጋብቻን በአግባቡ አይገልጹትም። ምክንያቱም አንደኛው ወይም ሁለቱም መሃን መሆናቸው እያወቁ በትዳር ውስጥ የሚኖሩ የመገናኘታቸውን ያህል፤ የኑብረት ግንኙነታቸውን በጋብቻ ውል መሠረት የየግላቸው እንዲሆን ደንግገው እንዲሁ በትዳር ዓለም የሚቀጥሉ ብዙ ናቸው። ስለዚህ ጋብቻን ከዘር ማፍራትን የጋር ኑብረት ከመፍጠር ጋር አያይዞ መተርጎሙ የተሟላ ትርጉም አያደርገውም[4]።

በመሆኑም በትርጉም መልክ የሚቀረጸው አንቀጽ የጋብቻን ሙሉና ዋነኛ ይዘቶችን በአጥጋቢ ሁኔታ ሊገልጽ ስለማይችል ትርጉሙ ከመስጠት በመታቀብ አጠቃላይ ትርጉሙ ከተለያዩ የህጉ አንቀጾች ግንዛቤ ቢወሰድበት እንደሚሻል በመታመኑ ጋብቻን የሚተረጉም አንቀጽ አስፈላጊ አልሆነም።

[4] የፍትሕ ሚኒስቴር አዘጋጅቶት በነበረው ረቂቅ የቤተሰብ ህግም "ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በእኩልነትና በፈቃደኝነት ቤተሰብ ለመቋቋም የሚመሠረቱት ስምረት ነው" በሚል ተተርጉሞ ነበር። (የረቂቅ አንቀጽ 31 ይመለከታል።) ይህም ቢሆን የጋብቻን ዘላቂነትን (Permanency) ስለማያመለክት የተሟላ ትርጉም ነበር ለማለት አያስደፍርም።



በ1952ቱ የፍትሐብሔር ህግ "ልዩ ልዩ የጋብቻ ዓይነቶች" በሚል ተደንግጎ የነበረው በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ "ልዩ ልዩ የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓቶች" በሚል ተሸሽሏል። ለዚህም ምክንያቱ ልዩነቱና ልዩ ልዩ ዐይነት የሚሆነው በአፈጻጸሙ ላይ እንጂ የተለያዩ የጋብቻ ዓይነቶች ሊኖሩ አይገባም ምክንያቱም የአፈጻጸም ስርዓታቸው ቢለያይም ውጤታቸው አንድ ዓይነት ነውና። ስለሆነም "ልዩ ልዩ ዓይነት ጋብቻዎች" የሚለው አቀራረጽ አግባብ ስላልነበር አዲስ አቀራረጽ ማለትም "ልዩ ልዩ የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቶች" የሚለው ተመራጭ ሆኖአል።

በዚሁ ክፍል ሥር በተሻሻለው ህግ በዋናኛነት ለሶስት ዓይነት የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሥርዓቶች እውቅና ሰጥቷል። እነዚህም በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈጸም ጋብቻ፤ በሀይማኖት ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻና በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻ ናቸው።[5]

በአሁኑ ህግ ቀደም ሲል ማለትም በነባሩ ህግ ብሔራዊ ጋብቻ፤ የሀይማኖት ጋብቻና የልማድ ጋብቻ በመባል ሲታወቁ የነበሩት መጠነኛ የይዘትና የስያሜ ማሻሻያዎች ተደርጎባቸው መቀጠላቸውን ለመገንዘብ የሚያዳግት አይመስልም።

[5] የፍትህ ሚኒስቴር አዘጋጅቶት በነበረው ረቂት የቤተሰብ ህግ ውስጥ የሃይማኖትና የባህል ጋብቻዎች እንዲካተቱ አልተደረገም ነበር። በረቂቱ ላይ በተካሄዱት ሰፋፊ የህዝብ ውይይቶች ግን ህጉ የሃይማኖትና የባህል

ጋብቻዎችን አለማካተቱ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እያንፀባረቅም ተብሎ በሰተተቸ እነዚህኑ የማካተት ሥራ ተከናውኗል።

ብሄራዊ ጋብቻ ሲል የተደነገገው ህግ የሰየመው በተሻሻለው ህግ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈጸም ጋብቻ በሚል እንዲጠራ ተደርጓል:: ለዚህ ውሳኔ ከምክንያቶቹ ጥቂቶቹም ብሄራዊ ጋብቻ ቀድሞውኑ የአፈጻጸም ሥርዓቱ ጋብቻውን በክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ ስለነበር ይህንኑ በግልጽ ለማመልከት በማሰብ፤ ብሄራዊ የሚለው ቃል አሁን ባለንበት የፖለቲካ ሥርዓት ሃገሪቱን በአጠቃላይ የሚያመለክት ሳይሆን የተለያዩ የሃገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦች ሊያመላክት ስለሚችል 'ብሄራዊ ጋብቻ' የሚለው ትክክለኛውን መልእክት የሚያስተላለፍ ስለማይመስል፤ በመጨረሻም 'ብሄራዊ' የሚለው ቃል ሃገሪቱን በሞላ ይገልጻል ቢባል እንኳ የዚህ ዓይነቱ የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓት በጥቂት ትላልቅ ከተሞች ብቻ በሥራ ላይ የዋለ እንጂ አብዛኛው የሃገሪቱ ተጋቢ በሌሎች የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሥርዓቶች ጋብቻው እንደሚያከናውን ይታመናል:: በመሆኑም "ብሄራዊ" ለማለኘት ስፋና በቂ ሽፋን ያለው አይደለም::[6]

---

ጋብቻዎችን አለማተቱ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አያንፀባርቅም ተብሎ ስለተተቸ እነዚህን የማካተት ሥራ ተከናውኗል::

[6] የቤተሰብ ህጉን ለማሻሻል በተካሄዱት ተከታታይ አውደ ጥናቶች አንዳንድ ተሳታፊዎች ይህ ዓይነት የጋብቻ ማስፈፀሚያ ስርዓት "ብሄራዊ ጋብቻ ከሚባል ይልቅ "የከተሜ ጋብቻ" ተብሎ ቢጠራ የተሻለ ገላጭ እንደሚሆን ሃሣብ ሲያቀርቡ ይደመጡ ነበር::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጋብቻን ለማበረታታት ሲባል በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በአንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አስተባባሪነትና ድጋፍ በመቶ የሚቆጠሩ ጥንዶች በጋራ ሠርጋቸውን ሲያደምቁ ይስተዋላል:: ይህ ዓይነት የጋብቻ አፈጻጸም በየትኛው ሥር ሊፈረጅ ነው? የሚል ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል:: በርግጥ በየትኛውም የሃገራችን ባህል በመቶ የሚቆጠሩ ጥንዶች አብረው ጋብቻ የሚፈጽሙበት ሥርዓት ስለሌለ በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻ ነው ብሎ



የሃይማኖት ጋብቻ ተብሎ ይጠራ የነበረውም ሥርዓቱ ሃይማኖቱ በሚፈልገው መሠረት መከናወኑን እንጂ ከተጋቢዎቹ የሃይማኖት እምነትና የእምነት ጥንካሬ ጋር የሚያይዘው ነገር የለውም:: ስለሆነም ከሃይማኖት ጋር የሚያገናኛቸው የአፈጻጸም ሥርዓቱ ብቻ በመሆኑ ይህንኑ በሚያንጸባርቅ መንገድ መቅረጹ የተሻለ እንደሚሆን ታምኖበታል:: 'በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻ' በሚልም እንዲስተካከል ተደርጓል::

በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ 'የልማድ ጋብቻ' በሚል የሚታወቀው የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓት ከመጠነኛ የይዘት ማስተካከያ ጋር 'በባህላዊ ሥርዓት የሚፈጸም ጋብቻ' በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል:: ልማድ ከሚለው አገላለጽ ይልቅ "ባሕል" የሚለው የተሻለ ዘላቂነትና ሰፊ ማህበረሰባዊ ተቀባይነት ይጠቁማል ከሚል እምነት ይህንኑ ማሻሻያ ተደርጓል:: ከዚህም በተጨማሪ በነባሩ ህግ የልማድ ጋብቻ እንዲባል የጋብቻው ሥርዓት "በአንድ ወንድና አንዲት ሴት በጎሣቸው ልማድ ወይም ከነርሱ በአንደኛው ጎሳ ልማድ" እንዲከናወን ይጠበቅበታል:: በዚህ አቀራረጽ መሠረት አንድ የጉራጌ ተወላጅና አንዲት ትግሬ በኦሮሞ ባህል መሠረት በኦሮሚያ ውስጥ ቢጋቡ የልማድ ጋብቻ ሳይባል ነው ማለት ነው

---

ለመፈረጅ ያስቸግራል:: በሃይማኖት ሥርዓት የሚፈጸም ጋብቻ ነው እንዳይባልም ጥንዶቹ ሃይማኖት የተለያየ ከመሆኑም ባሻገር በየትኛውም የሃይማኖት አባቶች ፊትና በየትኛውም የሃይማኖት ስርዓት መሠረት የሚከናወን አይደለም:: ሆኖም ሠርጉና ድግሱ በጋራ መከናወኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ጥንድ በከተማው ማዘጋጃ ቤት የጋብቻ አስፈጻሚ ሠራተኛ ፊት እየቀረበ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈጸም ዓይነት ሥርዓት ስለሚከተሉና ከዚሁ ክፍል የጋብቻ ምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ስለሆነ ቢያንስ የክብር መዝገቡ ጽ/ቤት እስኪቋቋም ድረስ



Generated by CamScanner

ምክንያቱም የተጋቡበት ባህል የሁለቱም ወይም ከሁለቱ የአንዱም አይደለም። ነገር ግን በህዝባችን የእንቅስቃሴ ስፋትና ከክልል ወደ ክልል በነጻነት መንቀሳቀስና መስራት የመቻል መብት እንዲህ ዓይነት ሁኔታና ጋብቻ ሊያጋጥም ስለሚችል አዲሱ ህግ "ጋብቻ በባህል ሥርዓት መሠረት ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሚኖሩበት አካባቢ ባህል ወይም በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል መሠረት የሚጸና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው።"[7] /ሠረዝ የተጨመረ/ በሚል እንዲተረጎም ተደርጓል።

ሌላው በነባሩ ህግ ያልነበረና አዲሱ ሕግ እውቅና የሰጠው የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓት ከኢትዮጵያ ውጪ በተፈጸመበት ሃገር የአፈጻጸም ሥርዓት መሠረት የተፈጸም ጋብቻን ነው። አሁን ባለንበት ሁኔታ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከረዥምም ዓመታት የስደት ኑሮ በኋላ ወደ አገር ቤት በመመለስ ኑሮአቸውን በመምራት ላይ ስለሚገኙ በስደት በነበሩበት ጊዜና ቦታ የፈጸሙአቸው ጋብቻዎች በነበሩበት አገር የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓት መሠረት እስከተፈጸመ ድረስ እውቅናና ህጋዊ ፋይዳ መስጠት አስፈላጊ ይሆናል። ለወደፊቱም ቢሆን የዜጎች ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት ባለበት ሁኔታና የውጭ ዜጎችም መውጣት መግባት ብሎም በሃገሪቱ ውስጥ መኖር በሚችሉበት ሁኔታ እንዲህ ዓይነት ድንጋጌ ስለማስፈለጉ አጠያያቂ አይመስልም።

---

[7] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 4



በአንዳንድ አገሮች ጋብቻቸውን በውል አዋዋይ ፊት፤ በሌሎችም በዳኛ ፊት እንዲሁም በከተማው ከንቲባ ፊት እንደሚፈጸሙ ይታወቃል። መመዘኛችን የኢትዮጵያ ህግ ቢሆን ኖሮ እነዚህ ዓይነት ጋብቻዎች እውቅና ላያገኙ ነበር ማለት ነው ምክንያቱም ከሶስቱም የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሥርዓቶች በአንዱም ሥር ሊወድቁ አይችሉምና። ቢሆንም ከኢትዮጵያ ውጭ የሚፈጸሙ ጋብቻዎችን እውቅና የሚሰጥ አንቀጽ በአዲሱ ህግ በመካተቱ በዚህ ረገድ ችግሩን ያስወገደዋል ተብሎ ይታመናል።

እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ግን በአዲሱ ህግ መሠረት እውቅና የሚሰጠው ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈጸመ ጋብቻ አፈጻጸሙን አስመልክቶ (formality) እንጂ ይዘቱን (substance) የሚመለከት አይደለም። ይህም ማለት በተጋቡበት አገር የሚፈቀድ ሆኖ ሁለት ወንዶች ወይም ሁለት ሴቶች እርስ በርሳቸው "ተጋብተው" መጥተው ለምዝገባ ቢቀርቡ የኢትዮጵያ ህግ እውቅና አይሰጠውም ምክንያቱም በኢትዮጵያ ህግ ህጉ አሁን ባለበት ሁኔታ ጋብቻ ለመፈጸም የሚቻለው በወንድና ሴት መካከል እንጂ በወንድና በወንድ ወይም በሴትና በሴት መካከል ባለመሆኑ ነው። በሌሎችም ይዘትን አስመልክቶ የሚነሡ ጉዳዮች ለምሣሌ ወንድምና እህት ውጭ አገር ተጋብታው ቢመጡ ተመሳሳይ አቋም ይወሰዳል ማለት ነው።



Generated by CamScanner

## 2.2. ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ጋብቻን ለመፈጸም ሶስት ዓይነት ስርዓቶች ማለትም በክብር መዝገብ ሹም ፊት፤ በሃይማኖት ወይም በባህል ስርዓት ማከናወን እንደሚቻል ቀደም ሲል ተመልክተናል:: ይህ የአፈጻጸም ስርዓትና ልዩነት እንዳለ ሆኖ ጋብቻው በየትኛውም ስርዓት ቢፈጸም ሊታለፉ የማይችሉ መሠረታዊ ሁኔታዎች ግን አሉ:: እንግዲህ በዚህ ክፍል ሥር ያሉት አንቀጾች እነዚህን ሁኔታዎች የሚያመለክቱ ናቸው:: "ተጋቢዎቹ ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት የኤድስ መርምራ ማከናወን አለባቸው" የሚል ለጋብቻ እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊቀመጥ ይገባል በማለት በአንዳንድ የአውደጥናት ተሳታፊዎች ሃሣቦች ሲቀርቡ የነበረ ቢሆንም የኤድስ ምርመራ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋሞች ውሱን መሆናቸው፤ አፈጻጸሙና ክትትሉ ውስብስብ እንደሚያደርገው በመታመኑ፤ እንዲሁም በዚህ ረገድ ራሳቸውን የሚጠራጠሩ ወገኖች የኤድስ ምርመራ አድርገው ጋብቻ ከመመስረት ይልቅ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ለመኖር ሊወስኑ ስለሚችሉ የታሰበውን ግብ እንዲመታ አያደርገውም:: በመሆኑም ይህ ጉዳይ አስፈላጊነቱ ቢታመንበትም በህግ እንደግዴታ ከሚቀመጥ ይልቅ ለተጋቢዎቹ የጋር ውሳኔና ፈቃደኝነት ቢተው ይሻላል የሚል ሃሣብ ስላመዘነ ይህ ነጥብ እንደ ቅድመ ሁኔታ እንዲቀመጥ አልተደረገም::



### 2.2.1 ፈቃደኝነት

በዚህ ክፍል ሥር በቀደምትነት የተቀመጠው ሁኔታ ፈቃድ ነው:: የሚጸና ጋብቻ ተፈጸመ የሚባለው ተጋቢዎቹ ለመጋባት ነጻና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ እንደሆነ ተመልክቷል::[*] ይህ አንቀጽ በዚህ ክፍል ሥር በአንደኛ ተራ ቁጥር መቀመጡ የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም:: ከሁኔታዎቹ ዋነኛው እንደሆነ ለማመልከት ነው::

በአንዳንድ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ባህሎች ለመጋባት የተጋቢዎች ፈቃድ እምብዛም አስፈላጊ አይደለም:: የተጋቢዎቹ ቤተዘመዶች ከተፈቃቀዱ ተጋቢዎቹ ተያይተው የማያውቁ ቢሆኑም እንኳ ለጋብቻው መፈጸም እንቅፋት አልነበረም:: እኔ ላንቺ /ላንተ/ የማይበጀውን አልመርጥልሽም /አልመርጥልህም/ ከፈቃዱ ከወጣሽ /ከወጣህ/ እረግምሽና /እረግምህና/ አስረግምሻለሁ /አስረግምሃለሁ/ ወዘተ እያሉ ቤተዘመዶች በልጆቻቸው ላይ በሚፈጥሩት የሞራል ተጽእኖ ምክንያት ከማያውቁት ጋር መጋባት ከማይወዱት ጋር መኖር የተለመደ ነበር:: በዚህ ሁኔታ የተጋቡም ሳይተዋወቁና ሳይፈላለጉ ትዳር የመሠረቱ ናቸውና ኑሮአቸው የጭቅጭቅና የንዝንዝ ቢሆን ብዙም አያስደንቅም::

ዘመናዊ አስተሳሰብና እምነት በእንደ እስከ አሁኑ እንዲቀጥል የሚፈቅድ አልሆነም:: ስለሆነም በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 34/2/2 "ጋብቻ በተጋቢዎች ነጻና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ

[*] ገቢ. ከማሁ አንቀጽ 6

ይመሰረታል" በሚል ተደንግጎ እናገኘዋለን:: በዚህ የቤተሰብ ህግም ይህንኑ ህገ መንግሥታዊ መርህ ነው አጽንኦት ለመስጠት በማሰብ እንዳለ እንዲቀመጥ የተደረገው::

### 2.2.2. እድሜ

በሁለተኛ ደረጃ እንዲቀመጥ የተደረገው የጋብቻ ቅድመ ሁኔታ የእድሜ ጉዳይ ነው:: በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ ወንድ በአስራ ስምንት ዓመት ሴት ደግሞ በአስራ አምስት ዓመት በህግ ተቀባይነት ያለው ጋብቻ መመስረት እንደሚችሉ ተቀምጦ እንደነበር አይዘነጋም::[9]

ለዕድሜው መለያየት ከሚቀርቡት ምክንያቶች ጥቂቶቹ፤ ለአካለ መጠን በመድረስ ላይ የተፈጥሮ ጉዳይ ሆኖ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ቀድመው ይደርሳሉ፤ የወሊድ አደጋም ወሊድ ከአሥራ አምስት ዓመት እድሜ በታች ሲሆን እንጂ አሥራ አምስትና ከዚያ በላይ አደጋ እንደሌለው በተግባር እየታየ ነው:: ከዚህም አልፎ ሴቲቱ የምታገባበት እድሜ ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር የጋብቻ እድልዋን ሊያስናክሉ የሚችሉ እንደ ጠለፋና መደፈር፤ ከጋብቻ ውጭ የመውለድ አደጋ ሊያጋጥምዋት ስለሚችሉ ቶሎ ማግባትዋ ለራስዋም የሚበጅ ነው:: በተለይም የጽንስ መከላከያ እድልና የትምህርት እድል የሌላቸው የገጠር ሴቶች ገና ባለ እድሜ እንዲያገቡ መደረጉ አግባብ ነው የሚል አመለካከት የነበረበት ወቅት ነበር::

[9] የፍትሐ ብሄር ህግ ቁጥር 581



ይህ ዓይነቱ አመለካከት የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ለመትረቅ ይረዱ ዘንድ ሃሣብ ለማሰባሰብ ይዘጋጁ በነበሩ የተለያዩ አውደ ጥናቶችም በስፋት ሲስተጋባ የነበረ አስተያየት ነበሩ::[10] ሆኖም ይህ አመለካከት በሚከተሉት ምክንያቶች ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል::

ጋብቻ ራሱን የቻለ ሃላፊነት መሆኑ እየታወቀ ወንድ በአስራ ስምንት ዓመቱ እንዲያገባ ሲደረግ ሴቲቱ ግን በአሥራ አምስት ዓመቷ ይህንን ሃላፊነት እንድትሸከም መፍቀድ ተጋቢዎች በጋብቻው አፈጻጸም ላይ እኩል መብት አላቸው የሚል ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌ የሚከተል አይደለም ከዚህም ሌላ ሴቶች እንዳይጠለፉና እንዳይደፈሩ የመከላከል ከተደፈሩና ከተጠለፉም ድርጊቱን በሚፈጽመት ላይ ጠንከር ያለ ቅጣት መወሰን የህብረተሰብና የመንግስት ሃላፊነት ሊሆን ይገባል እንጂ እንዳይደፈሩና እንዳይጠለፉ ተብሎ ቶሎ ያግቡ ማለት ተቀባይነት ያለው ክርክር አይደለም::

ከዚህም አልፎ የፌደራል ህገ መንግሥቱ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ነጻና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ መመስረት እንዳለበት የደነገገ ስለሆነ አሥራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው የሚሰጥ ፈቃድ ነጻና ሙሉ ስለመሆኑ አጠያያቂ ነው:: ሌሎች ህጋዊ ድርጊቶች ·

[10] እነዚህ ነጥቦች ፍትህ ሚኒስቴር ባቀረበው ረቂቅ የጋብቻ ማስፈጸሚያ ገቅተኛው እድሜ ለወንዱም ሆነ ለሴቲቱ 18 ዓመት እንዲሆን ደንግጎ የነበረ ሲሆን በተካሄዱት ተከታታይ አውድ ጥናቶች ይህንኑ ወደ ነባሩ የፍትሐብሄር ህግ የዕድሜ አቀማመጥ ለመውሰድ ሲባል ሲቀርቡ የነበሩ መከራከሪያዎች ናቸው:: ሆኖም በዚህ ጉዳይ በመጨረሻ ተቀባይነት ያገኘ ው የፍትህ ሚኒስቴሩ ረቂቅ ነው::



Generated by CamScanner

ለማግኘቱን አካለ መጠን መድረስን /የአሥራ ስምንት ዓመት እድሜ መድረስን/ አስፈላጊ ሆኖ እያለ ጋብቻን በመሰለ ዘላቂ ግንኙነት በሚፈጥር ተቋም ለሴቲቱ ዝቅ ያለ የጋብቻ እድሜ ማስቀመጥ ለሴቲቱ ፈቃድ ዝቅተኛ ግምት የተሰጠው መሆኑን ይጠቁማል:: የሚሉ መከራከሪያዎች ሲቀርቡ ነበር::

ከጤና አንጻርም ሲታይ የህክምና ጠበብት ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሚፈጸም ወሊድ የሴቲቱን የወሊድ አካላት የሚፈለገውን ያህል ሳያድጉና ሳይዳብሩ ስለሚሆን በአብዛኛው የእናቲቱም ሆነ የህጻኑን ጤናና ሕይወት ለአደጋ እንደማያጋልጥ ጥናቶችን በማጣቀስ ያብራራሉ::[11] በተጨማሪም በዘመናችን የአሥራ ስምንት ዓመት እድሜ ባብዛኛው ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁበት ወቅት ነው:: አገሪቱ እየተከተለች ባለው የትምህርት ፖሊሲም በገጠር ያለው ኑሮም በመጠኑም ቢሆን የትምህርት ጭላንጭል እየገባበትና ደረጃ በደረጃ እየተሻሻለ ይሄዳል ተብሎ ስለሚታመን፤ ከዚሁ የእድሜ ክልል በታች ጋብቻ እንዲፈጽሙ መፍቀድ የትምህርት እድላቸውን በእጅጉ ያሰናክለዋል:: ስለሆነም በትምህርት ደረጃና በውድድር ሥራ በሚያገዙበት ዓለም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሳያጠናቅቁ ሥራ ለማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ ስለሚመጣ የሴት እህቶቻችንን የኢኮኖሚ ነጻነትን የሚጎዳ አሠራር ሊሆን እንደሚችልም ተፈርቷል::

[11] በእውደ ጥናቶቹ የተሳተፉት የህክምና ባለሙያዎች ይህንኑ ጉዳይ በአጽንኦትና በተደጋጋሚ ይገልጹና ያስጠንቅቁ ነበር::



ለነገሩ በብዙ ሃገሮች የጋብቻ ማስፈፀሚያ ዝቅተኛው እድሜ ለሁለቱም ጾታዎች አሥራ ስምንት ወይም ከዚያ በላይ እያደረጉት ነው:: ለምሳሌ በክሮሺያ ቀደም ሲል ከአሥራ ስድስት ዓመት በላይ ጋብቻ መፈጸም የሚቻል የነበረ ቢሆንም፤ በአዲሱ ህጋቸው ግን ዝቅተኛው የጋብቻ እድሜ ወደ አስራ ስምንት ከፍ አድርገውታል:: በሁንጋሪና በአይስላንድም እንዲሁ ዝቅተኛ የጋብቻ ማስፈፀሚያ እድሜ ለሁለቱም ጾታዎች አሥራ ስምንት ዓመት ነው:: እንዲያውም በሩዋንዳ ዝቅተኛው የጋብቻ እድሜ ለሁለቱም ጾታዎች ሃያ አንድ ዓመት መሆኑ በፍትሐብሄር ህጋቸው አንቀጽ 171 ደንግገውት እናገኛለን ::

በመሆኑም እነዚህን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የጋብቻ መመስረቻ ዝቅተኛ እድሜ /minimum marriageable age/ ለሁለቱም ጾታዎች አሥራ ስምንት ዓመት እንዲሆን፤ ሆኖም ልዩ ሁኔታ ቢያጋጥም ለምሳሌ ሴቲቱ አስራ ስምንት ዓመት ከመድረሷ በፊት ብታረግዝ ወይም የወደፊት ባልዋ ወደ ግዳጅ የሚንቀሳቀስ ቢሆን ጋብቻ ሳይኖር መውለድዋ የሚፈጥረው ህጋዊ፤ ማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ ተጽእኖው ቀላል ስለማይሆን በልዩ ፈቃድ የጋብቻ እድሜ ወሰኑ እስከ ሁለት ዓመት ዝቅ ሊል እንደሚችል ተደንግጓል::[12]

### 2.2.3. ዝምድና

በተጋቢዎች መካከል የሥጋም ሆነ የጋብቻ ዝምድና ሊኖር እንደማይገባ በቀድሞው የቤተሰብ ህግም የተመለከተ እንደነበር

[12] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 7



Generated by CamScanner

አይዘነጋም::[13] በተለይም በሥጋ ዝምድናው አቆጣጠር የጋራ ከሆነው የግንድ ወላጅ እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ለጋብቻ ክልከላ እንደሚያገለግል ተመልክቶ ነበር::

ለዚህ ክልከላ መሠረቱ የክርስትና ሃይማኖትና የሰሜኑ የሃገሪቱ ክፍሎች ባህል እንጂ በሌላው ሃይማኖትና በሌሎች የሃገሪቱ ባህሎች እንጻር ተቀባይነት ያለው ምክንያት እንዳልሆነ ሲስተጋባ ቆይቶአል:: የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ለመቅረጽ በተካሄዱት አውደጥናቶችም ይህ ጉዳይ በየመድረኩ ሲወሳ ነበር::

ከአውደጥናቶቹ የተገኘው ግንዛቤ ግን የክልከላው መሠረት የክርስትና ሃይማኖትን የሰሜን ባህል ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስደፍር አልሆነም:: የህክምና ሣይንስ መሠረትም እንዳለው ተመልክቶአል:: በየአውደ ጥናቶች የተሳተፉት የህክምና ባለሙያዎች በአጽንኦት እንደገለጹት ከሆነ አንዳንድ እንደ እስምና የስኳር በሽታ የመሳሰሉ በዘር የሚተላለፉ በሽታዎች በመሆናቸው የትርብ የሥጋ ዘመዳሞች በተጋቡ ቁጥር የበለጠ አደገኛና ውስብስብ እንደሚሆኑ አስገንዝበዋል:: ይህን በመገንዘብና መሠረት በማድረግም ክልከላው እንዲቀጥል የተሻሻለው የቤተሰብ ህግም ካለፈው ህግ አንጻር መጠነኛ አቋም ወስዶበታል ቢሆንም ማሻሻያዎች አድርጎበታል::

በነባሩ ህግ የዝምድና ደረጃው እስከ ሰባት ትውልድ እንደሚዘልቅ ተመልክቶ የነበረው ሻላስፈላጊና ረቻም እንዲሁም

[13] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥሮች 582 እና 583



በአቆጣጠሩ ላይ ግልጽነት ያልነበረው ስለነበረ በተሻሻለው ህግ በዝምድና ደረጃ መቁጠር ቀርቶ ከእህት፤ ከአክስት፤ ከወንድም፤ ከእኅት በሚል የተሻለ ግልጽነት ባላቸው ቃላት መጠቀም ተመርጦአል::[14] ደረጃውም እስከ ሰባት ትውልድ የሚዘልቅ ሳይሆን የጤና ችግር እንዳያስከትል በሚያሰጋው በቅርብ የሥጋ ዝምድና እንዲወሰን ተደርጓል:: በርግጥ አንዳንድ ሃይማኖቶችና ባህሎች መሠረት በማድረግ ክልከላው በጣም ውሱን ሆነ ሰፋ ማለት ነበረበት ሊባል ይችል ይሆናል:: ቢሆንም ይህ ህግ ለሁሉም ሃይማኖቶችና ባህሎች የሚያገለግል (secular and neutral) መሆን ስላለበት በተቻለ መጠን በሁሉም ተቀባይነት ሊኖረው እንደሚችል አድርጎ መቅረጹ አግባብነት ያለው ይመስለናል:: ሰፋ ያለ ክልከላ የሚስቀምጡ ሃይማኖቶች ወይም ባህሎች ካሉ ተከታዮቻቸውን በዚያው መሠረት ጋብቻቸውን እንዲፈጽሙ ከማስተማርና ከመቀስቀስ አይከለከሉም:: የህብረተሰብ ባህርይ በህግ ደንቦች (legal norms) ብቻ ሳይሆን ከዚያ ውጭ በሃይማኖትና በሞራል ደንቦችም (religious and moral norms) እንደሚገዛ መገንዘብ የሚገባ ይመስለናል:: ስለሆነም በዚህ ረገድ የተወሰነው የባህርይ

[14] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 8(2)! ለነገሩ ረቂቁ ለህግ አውጭው አካል ሲቀርብ ይህ ንኡስ አንቀጽ "ወደ ጎን በሚቆጠር የሥጋ ዝምድና አንድ ወንድ ከእህቱ ከአክስቱ እንዲሁም ከእኅቱ ልጅ ወይም ከአክስቱ ልጅ ጋር፤ አንዲት ሴት እንዲሁ ከወንድሟ፤ ከእኅቷ፤ ከእኅቷ ልጅ ወይም ከአክስቷ ልጅ ጋር ጋብቻ መፈጸም የተከለከለ ነው::" (ሠረዝ የተጨመረ) በሚል ተቀርጾ ነበር:: አዋጁ ፀድቆ ሲወጣ ግን የተሠመሩት ሃረጎች አልተካተቱም:: ይህ ተራ የታይፐ ግድፈት ነው ወይስ ህግ አውጪው ሆን ብሎ ያደረገው ነው ለሚለው በቂ ማብራሪያ አልተገኘም:: ምናልባትም ከዚያ በላይ ያሉት ክልከላዎች ለየተጋቢዎቹ ሃይማኖታዊ እምነትና ባህላዊ አመለካከት ወይም ሞራላዊ አስተሳሰብ ቢተው ይሻላል የሚል ግንዛቤ ስለተወሰደ ሊሆን ይችል ይሆናል::



Generated by CamScanner

ክፍል ለሃይማኖትና ለባህል መተው ይበጃል:: የቀጥታ ዝምድናው ግን ማለት አንድ ሰው ከእናቱ፤ ከአያቱ ወይም ከልጁ ጋር ጋብቻ መፈጸም እንደማይገባ በማመን በቀጥታ የሥጋ ዘመዳሞች መካከል ክልከላው ፍጹም መሆኑን ለማመላከት "በቀጥታ የሥጋ ዘመዳሞች መካከል ጋብቻ መፈጸም ክልክል ነው" በሚል እንዲቀረጽ ተደርጓል::[15]

የጋብቻ ዝምድናም ለጋብቻ ክልከላ መሠረት እንደነበረ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 552, 553 እና 583 የተመለከተ ሲሆን ወደ ጎን በሚቆጠሩ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ክልከላው እስከ ሶስተኛ ደረጃ ድረስ እንደሆነ ተመልክቶ ነበር:: ይህም ቢሆን እላይ እንደተመለከተው በአቆጣጠር ረገድ ግልጽነት የጎደለው በመሆኑና በክልከላው ስፋትና ጥበትም ላይ የተለያዩ አመለካከቶች በመኖራቸው ክልከላው የሚመለከታቸውን ወገኖች በግልጽ ጠቅሶ ማመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: በመሆኑ የጋብቻ ክልከላ በቀጥታ ከሚቆጠሩ የጋብቻ ዘመዳሞች ማለትም አንድ ወንድ ከሚስቱ እናት ወይም ከሚስቱ ልጅ ወይም አንዲት ሴት ከባልዋ አባት ወይም ከባልዋ ልጅ በተጨማሪ ወደ ጎን በሚቆጠር የጋብቻ ዝምድናም ባል ከሚስቱ እህት ጋር፤ ሚስት ከባልዋ ወንድም ጋር ጋብቻ መፈጸም የተከለከለ መሆኑ ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል::[16]

[15] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ - 8(1)
[16] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ - 9-



2.2.4. <u>በጋብቻ ላይ ጋብቻ</u>

ሌላው ለጋብቻ ክልከላ መሠረት ተደርጎ በነባሩ የቤተሰብ ህግም ሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የተቀመጠው በጋብቻ ላይ ጋብቻ መመስረት እንደማይገባ የሚደነግገው አንቀጽ ነው::[17]

በተከታታይ በተካሄዱት አውደ ጥናቶችም ይህ አንቀጽ በሰፊው ያወያየ መሆኑ አይዘነጋም:: በአንዳንድ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ወገኖቻችን በኩል 'ይህ አንቀጽ በእምነታችን የተጎናጸፍነውን መብት የሚያጣብብ ስለሆነ በአዲሱ ህግ ሊካተት አይገባውም' የሚል መከራከሪያ ሲያቀርቡ በአንዳንድ ለሴቶች መብት መከበር በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በኩል ግን በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተቀባይነት የሌለው ድርጊትና 'ሴቲቱ በጋብቻ ዘመን እኩል መብት ይኖራታል' የሚለውን ህገ መንግሥታዊ ጥበቃ የሚሸረሽር ድርጊት ስለሆነ በህግ ሊከለከል ይገባል ባዮች ነበሩ:: በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችም በኩል በጋብቻ ላይ ጋብቻ በጋብቻ ውስጥ ሊኖር የሚገባውን መተማመን የሚንድና የሃጥአን ድርጊት ስለሆነ ሃጥያት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በህግም ሊከለከል ይገባል ሲሉ ተደምጠዋል::

ለነገሩ በእስልምና ሃይማኖት ሊቃውንትም በኩል በዚህ ረገድ የነበረው አቋም አንድ ወጥ አልነበረም:: አንዳንዶቹ ቅዱስ መጽሐፍ ቁርዓን በጋብቻ ላይ ጋብቻ የሚፈቅደው አግቢው ያገባቸውን ሚስቶች እኩል ፍቅርና እኩል መተዳደሪያ እስከሰጠ

[17] በፍትህ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በቀረበው ረቂቅም ይህ ነጥብ ተካትቶ ነበር (የረቂቁ አንቀጽ 23 ይመለከቷል::)



Generated by CamScanner

ድረስ ብቻ ነው:: እኩል መተዳደሪያ ማቅረብ ቢችል እንኳ እኩል ፍቅር ሊሰጣቸው ስለማይችል ቁርአን በእጅ አዙር በጋብቻ ላይ ጋብቻ ይከለክላል ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በቁርአን የተፈቀደ ቢሆንም ተፈጻሚ የሚሆነው ግን የመጀመሪያዋ ሚስት ከፈቀደች ብቻ ነው ብለዋል:: ሌሎች ደግሞ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ለመፈጸም የቃዲ ፈቃድ ያስፈልጋል:: የቃዲ ፈቃድ ማግኘትም አሳማኝ ምክንያት /የፊተኛዋ ሚስት የአልጋ ቁራኛ መሆን/ ወይም ለመውለድ አለመቻል ወዘተ የመሳሰሉት/ ሊቀርቡ ይገባል እንጂ እንዲሁ በዘፈቀደ የሚከናወን አይደለም የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ::

በዚህ ረገድ በእስልምና ሃይማኖት አማኞች ብዛት በዓለም ቀዳሚነት መያዝዋ በሚነገርላት ኢንዶኔዥያም ሁኔታው የሚከተለውን ይመስላል:: ከአንድ ሚስት በላይ ሚስት እንዲኖረው የሚፈልግ ወንድ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት በጽሁፍ ሊያቀርብ ይገባል:: (የኢንዶኔዥያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 4(1) ይመለከተዋል::) በዚህ ጉዳይ የመጀመሪያዋ ሚስቱም ፈቃድ ያሰፈልጋል (የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 5(1)(ሀ) ይመለከተዋል) ፈቃዱም በጽሁፍ ወይም በቃል ልትገልጸው የምትችል ቢሆንም በቃል የምትገልጽ ከሆነ ፍርድ ቤት በግንባር ቀርባ ልትገልጸው ይገባል (የኢንዶኔዥያ መንግስታዊ ደንብ ቁጥር9/1975/ አንቀጽ (41):: አመልካቹ ሁሉንም ሚስቶቹና ልጆቻቸው በመተዳደሪያ ረገድ በብቃት ሊያስተዳድራቸው የሚችል ስለመሆኑ በቃለ መሃላ ለፍርድ ቤቱ ያረጋግጣል (የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 5(1) (ለ)) በዚህ መነሻነት ፍርድ ቤቱ ሁለተኛ ሚስት ለመፍቀድ አሳማኝ ምክንያቶች ስለመኖራቸው የጣራል ፤ ማለትም የመጀመሪያ ሚስቱ የሚስትነት ግዴታዋን



ለመወጣት አለመቻልዋ (incapable of performing her duties as a wife) ወይም በሰውነትዋ ላይ ጉዳት ስለመድረሱ (physically disfigured) ወይም የማይድን በሽታ የያዛት ስለመሆኑ (contracted an incurable disease) ወይም ለመውለድ የማትችል መሆንዋ (incapable of producing children) ሲያረጋግጥ አቤቱታውን ይቀበላል (የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 4(2) (ሀ) (ለ) (ሐ) ይመለከተዋል):: በተግባር እንደሚታየው አቤቱታው ተቀባይነት ከሚያገኝበት ይልቅ ውድቅ የሚደረግበት ጊዜ እንደሚበዛ መፀሐፍት ያስረዳሉ::

በመሆኑም በጋብቻ ላይ ጋብቻ ከህገ መንግሥቱ ጋር ያለው መጣጣም አጠያያቂ መሆኑን በመገንዘብ፤ በአንዳንድ ሃይማኖቶችም ተቀባይነት እንደሌለው ግምት ውስጥ በማስገባት፤ የተፈቀደ ነው በተባለበት ሃይማኖትም የቅድስ ቁርአን አተረጓጎምንና የድርጊቱ አፈጻጸም አስመልክቶ አንድ ወጥ አቋም አለመኖሩን በማየት፤ በአዲሱ የቤተሰብ ህግ ድርጊቱን በህግ መከልከል የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ታምኖበታል::[18] ምናልባት አስፈላጊነቱ ከታመነበትና ህገ መንግስታዊ ችግርም ከሌለበት የሃይማኖትና የባህል ጋብቻዎች እውቅና በሚሰጡ ህጎች በልዩ ህግ መሟላት ያለባቸውን ድንጋጌዎች አካትቶ ሊወጣ ይገባል::

2.2.5. <u>በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ</u>

ሌላው በዚህ ክፍል ማብራሪያ ያስፈልገዋል ተብሎ የሚገመተው አንቀጽ "በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ"

[18] የተሻሻለው የቤተሰህ ህግ አንቀጽ - 11



Generated by CamScanner

የሚደነግገው የአዲሱ ህግ ድንጋጌ ነው:: በነባሩ ህግ ውስጥ አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ አንድ መቶ ሰማንያ ቀናት ካላለፈ በስተቀር እንደገና ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸም አትችልም"[19] የሚል ነበር::

በአንዳንድ ወገኖች ይህ ድንጋጌ የጾታ እኩልነትን የማያከብርና አድሉአዊ በመሆኑ በአዲሱ ህግ መካተት እንደሌለበት በጥናት ሲወሳ ቆይቶአል:: "ወንዱ የፊተኛው ጋብቻውን ባፈረሰ በማግስቱም ቢሆን ሌላ ጋብቻ ሊፈጽም እየቻለ ሴቲቱ ግን አንድ መቶ ሰማንያ ቀናት እንድትጠብቅ ማስገደዱ ተገቢ አይደለም":: በተለይም ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሴቶች ትዳር የሥራ መስክና የገቢ ምንጭ ነው:: በመሆኑም ለስድስት ወራት ያህል ከሥራ መስክ እንዲገለሉ ማድረግ በኑሮአቸው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ጫና ያስከትልባቸዋል የሚሉ መከራከሪያ ነጥቦች በየአውደ ጥናቶቹ መቅረባቸው የሚታወስ ነው::

ጠለቅ ብሎ ሲታይ ግን ይህ አንቀጽ በሴቶች ላይ አሳስፈላጊ ጫና ለማሳረፍ ተብሎ የተቀረጸ አይመስልም:: ይልቁንም የህጻናትን መብት ለመጠበቅ የተቀመጠ አንቀጽ እንደሆነ ይታመናል:: በተለይ በአሁኑ ወቅት በፌደራላዊው ህገ መንግሥትና ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ህጻናት

[19] የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር - 596



ወላጆቻቸውን የማወቅና ከወላጆቻቸው እንክብካቤ የማግኘት መብት እንዳላቸው ተመልክቷል::[20]

ይህንኑ መብታቸውን ለማስከበርም በተቻለ መጠን በወላጆቻቸው ማንነት ላይ አከራካሪ ሁኔታ እንዳይፈጠር ማድረግ ተገቢ ነው:: ልጁ የተወለደው ከቀድሞው ጋብቻ ነው? ወይስ ከኋለኛው? የሚለውን ለመወሰን ካስቸገረ ልጁ እንክብካቤ ማግኘት የሚኖርበት ከየትኛው ስለመሆኑ የማወቅ እድሉ ይጣበባል:: ይህ እንዳይሆን እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል:: ከነዚሁም አንዱ እርምጃ የአባትነት ግጭት እንዳይፈጠር ማድረግ ነው:: ይህ አንቀጽም ለዚሁ ዓላማ የተቀመጠ ነው:: የተፈጥሮ ጉዳይ ሆኖ የማርገዝ ኃላፊነት በሴቲቱ ላይ የሚወድቅ በመሆኑ በዚሁ የተፈጥሮ ግዴታዋ ምክንያት የመቶ ሰማንያ ቀናት የግዜ ገደብ ግዴታ እንድትጠብቅ ተደርጓል እንጂ በሴት ላይ የፆታ አድልዎ ለመፈጸም የተቀረፀ አይመስለንም::

ስለሆነም ይህንኑ የአባትነት ግጭት የማይፈጠርበት ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ የመቶ ሰማንያ ቀናት የግዜ ገደብ የመጠበቅ ግዴታ አይኖርባትም:: እነዚህም ሁኔታዎች በተሻሻለው ህግ አንቀጽ 16/2/ ተመልክተዋል:: ጥቂቶቹም ሴቲቱ መቶ ሰማንያ ቀናት ከመሙላቱ በፊት የወለደች እንደሆነ ማለትም ይህ የግዜ ገደብ ከመድረሱ በፊት ከወለደች የተወለደው ህጻን የፊተኛው ባል መሆኑ ስለሚታመን የአባትነት ግጭት ስለማይኖር ሌላ ጋብቻ ከመፈጸም የምትከለከልበት ሁኔታ አይኖርም:: ጋብቻውን

[20] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 36(10 (ሐ) እና የሕፃናት ኮንቬንሽን አንቀጽ-7(1)

ለመፈጸም ያቀደችው ከቀድሞ ባልዋ ጋር ከሆነም ዞሮ ዞሮ ልጅ ከተወለደም አባትየው እርስ ራሱ ስለሚሆን አባትነት በመወሰን ረገድ ችግር ስለማይኖር የግዜ ገደቡ መጠበቅ አይኖርባትም። በአሁኑ ዘመን እርግዝና መኖር አለመኖሩ እንዳንዴም የሽሉ ፆታም ሳይቀር በሳይንሳዊና አስተማማኝ መንገድ በምርመራ ማረጋገጥ ስለሚቻል ከፊተኛው ትዳር የያዘችው እርግዝና አለመኖሩ በምርመራ ከተረጋገጠም ሙቶ ስማያ ቀናት ሳለመጠበቅ በቂ ምክንያት ነው። በመጨረሻም ሁሉም ምክንያቶች ዘርዝሮ ማስቀመጥ አስቸጋሪ በመሆኑ ፍርድ ቤት ከዚህ በላይ የተመለከተውን የግዜ ገደብ ከመጠበቅ ነፃ የሚያደርግበት ሁኔታም ተመልክቷል።[21]

## 2.3. ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወም

በዚህ ክፍል ሥር ሊፈጸም የታቀደን ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት እንዴት መቃወም እንደሚቻል፤ ተቃዋሚ ሆነው ለመቅረብ የሚችሉት እነማን እንደሆኑ፤ ተቃውሞአቸው መቼና በምን ዓይነት ..ሰርዓት እንዲሁም ለማን ማቅረብ እንዳለባቸው በመጨረሻም የተቃውሞው ውጤት ምንነት የሚደነግጉ አንቀጾች ተካትተውበት ይገኛሉ።

---

[21] ለምሳሌ ሴትዮዋ መውለድ የማትችል (መሃን) መሆንዋ ከተረጋገጠ ወይም ከተመሰከረ ወይም በእስልምና ሃይማኖት እንደሚታመነው የፊተኛ ው ትዳር ከፈረሰ በኋላ ለሦስት ተከታታይ ወራት የወር አበባ ካየች ከፊተኛው ትዳር እርግዝና እንደሌለ ስለሚያመለክት ፍርድ ቤት የማስረጃው ክብደት አመዛዝኖ የግዜ ገደቡን እንዳትጠብቅ ሊወስን ይችላል። ከእነዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ ሃገሮች ሴትዋ ከፊተኛው ባልዋ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት አለመፈጸምዋ ከተረጋገጠ በብቸኝነት የመኖሩ የጊዜ ገደብ ተፈጻሚ አይሆንም (የኢንዶኔዢያ የመንግስት ደንብ ቁጥር 9/1975 አንቀጽ 39(2)።



ወደ ይዘታቸው ከመግባታችን በፊት የዚህ ክፍል አስፈላጊነት አስመልክቶ ጥቂት ነጥቦች ማንሳት አስፈላጊ ይመስለናል።

በርግጥ ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ መመስረት እንዳለበት ቀደም ሲል ተመልክቶአል። ይህ ሲባል ግን የተጋቢዎቹ የግል ጉዳይ ነው ማለት አይደለም። እንዲያውም ጋብቻ የህብረተሰብ መሠረት በመሆኑ የመንግስትና የህብረተሰብ ጥበቃና እንክብካቤ የሚጠይቅ ተቋም ነው። ስለሆነም የጋብቻ ጉዳይ የመንግስት ክትትል እንዲሁም የህብረተሰብ በተለይም የተጋቢዎቹ ቤተዘመዶች ትኩረት የሚሻ ነጥብ ነው።

ህግ ከደነገገው እድሜ በታች ጋብቻ እንዳይፈጸም፣ በዘመዳሞች መካከል ጋብቻ እንዳይፈጸም፤ በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዳይፈጸም ክትትል እንዲሁም የማድረግና ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት ለመንግስትና ለህብረተሰብ የተሰጠ አደራ ነው። ይህንን ኃላፊነት መንግስት በዓቃቤ ህግ መስሪያ ቤቱ በኩል የሚከታተለው ሲሆን ህብረተሰቡም በተጋቢዎች ዘመዶችና በሌሎች በጉዳዩ ያገባናል በሚሉ የህፃናትና የሴቶች መብት አስከባሪ ድርጅቶች በኩል የሚያከናውነው ይሆናል።

ለጋብቻ አስፈላጊ ሁኔታዎች ሳይሟሉ የተፈፀመ ጋብቻ በፍርድ እንዲፈርስ የማስወሰን አማራጭ እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻው ሊፈፀም ዝግጅት በመደረግ ላይ ባለበት ጊዜም ተቃውሞ በማቅረብ እንዳይፈፀም ማስከልከል ይቻላል። ስለሆነም የዚህ ክፍል አስፈላጊነት ጋብቻው ከመፈፀሙ በፊት እርምጃ እንዲወሰድ



Generated by CamScanner

ማስቻል ነው፡፡ ምክንያቱም ጋብቻው ከተፈፀመ በኋላ እንዲፈርስ ከማስወሰን ይልቅ ከመፈፀሙ በፊት እንዳይፈጸም ማድረጉ በሁሉም አንፃር ለሁሉም ወገኖች የሚበጅ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

ጋብቻው እንዳይፈፀም መቃወም የሚችሉት ወገኖች ማንነት በመወሰን ረገድ የተቃውሞ መሠረት የሆነውን ጉዳይ ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ የተቃውሞው መሠረት በሕግ ከተወሰነው የእድሜ ወለል (minimum marriageable age) በታች ጋብቻ እንዳይፈጸም ለማስከልከል ከሆነ የተጋቢዎቹ ወላጆች በጋራ ወይም በተናጠል መቃወሚያቸውን ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን፣ መንግስትም ከጋብቻ እድሜ በታች ጋብቻ መፈጸም (child marriage) ህገ መንግስቱን፣ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶችና ሌሎች የሃገሪቱ መደበኛ ህጎች የሚጥስ ድርጊት በመሆኑ በዓቃቤ ህግ በኩል ተቃውሞውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ከዚህም አልፎ በዘመናችን ከጋብቻ እድሜ በታች ጋብቻ መፈጸም ህብረተሰቡን በአጠቃላይ የሚያሳስብ ጉዳይ በመሆኑ በህጻናትና በሴቶች መብት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጥልቀትና በስፋት የሚሠሩበት ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል እነዚህ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዚህ ረገድ ትርጉም ያለው እንቅስቃሴ ማድረግ ይችሉ ዘንድ ተቃውሞ ማቅረብ የሚችሉበት ህጋዊ ስርዓት ማመቻቸት አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ለማካተት በማሰብ "ማንኛውም ያገባኛል የሚል" ሰው የሚል ሃረግ እንዲገባ ተደርጓል፡፡



በሌላ ቋንቋ "ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው" የሚለው ሃረግ እንዲህ 'በዚህ ጉዳይ እኔንም ያገባኛል' ብሎ የሚመጣን አካል እንደሚ ለማለት ሳይሆን በእንግሊዝኛው "interested party" ማለትም የጉዳዩ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ መወሰን በአሉታዊ ወይም በአዎንታዊ ሁኔታ ጥቅሙ የሚነካበት ማለት ነው፡፡ እነዚህ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከጋብቻ እድሜ በታች ጋብቻ እንዳይፈፀም በመቃወም እንዳይፈፀም መከላከል ከቻሉ በህፃናትና በሴቶች መብት መከበር ዙሪያ ለሚያደርጉት ጥረት መሳካት አመቺ መንገድ የሚፈጥርላቸው በመሆኑ ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው (interested party) በሚለው ሥር ይካተታሉ ተብሎ ይታመናል በመተዳደሪያ ደንባቸው ተመልክቶ ይገኛልና፡፡

የተቃውሞው መሠረት በዘመዳሞች መካከል ሊፈፀም የታቀደውን ጋብቻ እንዳይፈጸም በመከላከል ያተኮረ ከሆነ የተቃዋሚዎቹ ማንነት እላይ ከተመለከቱት በመጠኑ ይለያል፡፡ ጉዳዩ በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዳይፈጸም ለመቃወም ከሆነም እንዲሁ በተቃዋሚዎቹ ማንነት ላይ ልዩነት እንዳለ መገንዘብ ይገባል፡፡[22] የልዩነቱ መሠረትም ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህንን ተቃውሞ ለማንሳት አግባብነት የሚኖራቸው እነማን ሊሆኑ ይገባል የሚለውን ነጥብ በመውሰድ ነው፡፡

[22] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 18(ለ) (ሐ)



Generated by CamScanner

ቀጥሎ መነሣት ያለበት ጉዳይ ተቃውሞው ለማን መቼና በምን ዓይነት ሥርዓት ሊቀርብ ይገባል የሚለው ነው። እንደሚታወቀው ለጋብቻ አስፈላጊ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ጋብቻ ተፈፅሞ ቢገኝ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄ እንዲያቀርቡ በህግ መብት የተሰጣቸው ወገኖች አቤቱታቸውን የሚያቀርቡት ለፍርድ ቤት ነው[23]።

ሊፈፀም የታቀደን ጋብቻ የመቃወም ጉዳይ ከሆነ ግን ለመቃወም በህግ መብት የተሰጣቸው ወገኖች መቃወሚያቸውን የሚያቀርቡት ለጋብቻ አስፈጻሚው ባለስልጣን ነው።[24] ይህ ባለስልጣን እንደጋብቻ ማስፈፀሚያው ሥርዓት ሊለያይ ይችላል። ጋብቻው ሊፈፀም የታቀደው በክብር መዝገብ ሹም ፊት ከሆነ መቃወሚያው ለክብር መዝገብ ሹሙ ሊቀርብ ይገባል። በአንፃሩም ጋብቻው ሊፈፀም የታቀደው በሃይማኖት ሥርዓት ወይም በባህል ሥርዓት የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ጋብቻውን ለሚያስፈፅሙ የሃይማኖት አባቶች ወይም የባህል አባቶች ወይም የሃገር ሽማግሌዎች ይሆናል ማለት ነው።

መቃወሚያው ለጋብቻ አስፈፃሚው መቅረብ ያለበት በጽሁፍ ሲሆን መቅረብም ያለበት እጅግ ቢዘገይ ጋብቻው ሊፈፀም

---

[23] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 19



ቀን ቀጠሮ ከተያዘበት ከአሥራ አምስት ቀናት በፊት መሆን እንዳለበት ተደንግጓል።

በጽሁፍ የቀረበ ነገር በተሻለ ሁኔታ የታሰበበት፤ የተሻለ ግልጽነት ያለው በማስረጃነት ለመያዝ የሚያመች በመሆኑ መቃወሚያው ይህ ዓይነት ቅርጽ እንዲኖረው ተፈልጓል። ጊዜውን በተመለከተም የተቃውሞ ማቅረቢያ ጊዜው ወደ ጋብቻ ማስፈፀሚያው ዋዜማ በተጠጋ ቁጥር ተጋቢዎቹን ለአላስፈላጊ ወጪና ጫና ሊዳርጋቸው ስለሚችል ተቃውሞው ቀደም ብሎ ቀርቦ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ እንዲሰጠው ሊደረግ እንደሚገባ በማመን ነው።

በተለይ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀሙ ጋብቻዎችን "ተጋቢዎቹ ጋብቻ ለመፈፀም ማቀዳቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን ለመፈፀም ከወሰኑበት ቀን ከአንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማስታወቅ ስላለባቸው"[25] የክብር መዝገብ ሹሙም ጋብቻው የሚፈፀምበትን ቀን በመግለጽ አመቺ በሆነው መንገድ ማስታወቂያ ስለሚያወጣ ተቃውሞ አቅራቢዎች የተቀመጠላቸውን የአሥራ አምስት ቀናት ሊጠቀሙ የሚችሉበት እድል አለ።

የተቃውሞ ጉዳይ ሲነሣ ጋብቻው ከመፈጸሙ ከአሥራ አምስት ቀናት በፊት እንዲቀርብ መደረጉ በአንድ በኩል ለጋብቻ አስፈላጊ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ጋብቻ እንዳይፈጸም ለመከላከል እንዲያግዝ የተቀመጠ ነው። በሌላ በኩል ግን ተቃውሞ አለን የሚሉ ወገኖች የተጨበጠ ወይም ያልተጨበጠ ማስረጃ እየያዙ

---

[24] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 23

እንዲሁ ጋብቻው ቀሪ ይሁን የተጋቢዎችን ትዳር የመመስረት መብት በመጋፋት ተጋቢዎችን እንዳያገለግሉ በማለት ከአምስ እምነት ቀን ያለፈ ጊዜ ከሆነ ጋብቻውን ለማፍረስ የቀረበ ምርጫ መከተሉን እንጂ በተቃውሞ ምርጫ ማፍረስ ተመልሶ ሀቀ አልተገኘም። በዚህ ለተቃውሞ ጊዜ ያለፈበት ወገን ከሌ ጋብቻው ከተፈጸመ በኋላ ጋብቻውን ለማፍረስ ሊንቀሳቀስ ይችላል እንጂ በጋብቻው ቅሬታ ተጋቢዎቹን ለመበተን አይችልም ማለት ነው።

ከዚህም ሌላ ተቃውሞው የቀረበት የጋብቻ አስፈጻሚው ባለስልጣን በሚሰጠው ውሳኔም ላይ የቀረበ ክርክር እንዲሰጠው ተደርጓል። ጋብቻ አስፈጻሚው ባለስልጣን ተቃውሞው ተቀባይነት የለውም ብሎ ከወሰነ ውሳኔው የመፈጸሚ ይግባኝ የሚያቀርብበት ሊሆን ተቃውሞው ተቀባይነት አግኝቶ ጋብቻው እንዳይፈፀም ከወሰነ ግን ተጋቢዎቹ ይግባኝ የመጠየቅ መብት እንዲኖራቸው ተደርጓል።[18] ይህም የተደረገበት ምክንያት የተጋቢዎችን ትዳር የመመስረት መብት ከበድ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን በማመን በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዳይዘጋ በማለት በፍርድ ቤት ታይቶ እንዲወሰን ለማስቻል ነው። ተቃውሞው ተቀባይነት የለውም ተብሎ መወሰኑ ግን መጋባት አይችሉም የማለት ያህል ከባድ ውጤት እንደሌለው በማመን ከሁለቱ በአንዱ እንዲቀም ተደርጓል።

### ፫.፬ ስለ ጋብቻ ምዝገባ

ነባሩ የቤተሰብ ሕግ ከሃይማኖት ጉባዔ እንጂ የወሰደው የጋብቻ ምዝገባ በተሟላ አለማደራጀቱ ነበር። ምንም እንኳ የጋብቻ

[18] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 20(2) (3) እና አንቀጽ 21



ምዝገባ እንዲሟላ በሃገሩ ህግም ተመልክቶ የነበረ ቢሆንም የምዝገባ ተቋማት ባለመደራጀታቸው ግን ሊሳካ አልቻለም።[19]

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በዚህ ረገድ ግልጽነትና ተግባራዊነቱን ሊያሟሉት የሚችሉ ድንጋጌዎች አካትቶም ይገኛል።

በመጀመሪያ ደረጃ የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሰርተፊኬት የተሰጠው አካል እንዲሟላ ተደም ሲል የተመለከተ ቢሆንም የምዝገባ ስርዓት ግን እንደገና እንደ ብዙ ነው። ስለዚህም የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሰርቲፊኬት የምዝገባ ኃላፊነት የተሰጠው ለክበር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ነው። ይህ ጽ/ቤት ከሃይማኖትና ባህል ባለስልጣናት የተሻለ አደረጃጀትና አቅም ይኖረዋል ተብሎ ስለሚገመት ይህንን ኃላፊነት እንዲወጣ ተመርጧል። ጽ/ቤቱ መንግሥታዊ ተቋም ነውና እንዲህ ዓይነቱ ግዴታ በመንግሥት ላይ መጣሉ ተመራጭ ሆኗል።[20] በተጨማሪ የሰው ሃይል ይመደብለታል ተብሎም ይታመናል። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር ግን ጋብቻው በሃገር የተመለከተውን ውጤት ማስከተል የሚጀምረው ግን ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ጋብቻው ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ነው።[21] ስለዚህ

[19] የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3361 (1)
[20] ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች በሴቶች ላይ የሚፈፀሙትን አድልዎ የሚከለክል ስምምነት አንቀጽ 16(2) ላይ የጋብቻ ምዝገባ አስገዳጅ በሚሆን የተመለከተ ስለሆነ መንግሥት ይህንን ኃላፊነት የማስፈፀም ግዴታ አለበት
[21] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 28(1) መሠረት በሃይማኖት ወይም በባህል ሥርዓት የተፈፀሙ ጋብቻዎች በክበር መዝገብ ሹም ቀርበው እንዲመዘገቡ መደረጉ አንድ ወጥ መዝገብ ለሚያደርጉት እንጂ እንዲህ ዓይነት የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሥርዓቶችን ተቀባይነት ለማሳጣት ባለመሆኑ ጋብቻዎቹ ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትሉት ከተፈጸመበት ጊዜ እንጂ



Generated by CamScanner

የምዝገባው አስፈላጊነት ለማስረጃነትና ለሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች እንጂ ጋብቻ የሚፀና ነው አይደለም ብሎ (validity) ለመወሰን አይደለም።

በሁለተኛ ደረጃ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሠረት የሚደራጀው የምዝገባ ስርዓት ጋብቻ ፈጽመው ለማስመዝገብ የሚመጡትን ብቻ ሳይሆን የክብር መዝገቡ ሹሙ ጋብቻ መፈፀሙን ካወቀ ተጋቢዎቹን በመጥራትና በማስጠራት ምዝገባ ማከናወን እንደሚገባው የሚያመለክት ነው። የምዝገባ አስፈላጊነት አጠያያቂ ባይሆንም ህብረተሰባችን ካለው የእድገት ደረጃ አኳያ ብዙዎች አስበውበትና ተዘጋጅተው ለምዝገባ ይመጣሉ ተብሎ ስለማይገመት መዝጋቢው አካል የራሱን ተነሳሽነት እየወሰደ ምዝገባ እንዲያከናውን መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል[30]።

በሦስተኛ ደረጃ የምዝገባ ተቋሙ መቋቋም አርግጥ ይሆን ዘንድ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የፌዴራል መንግስቱን በሚያስገድድ ሁኔታ የምዝገባ ህግና የምዝገባ ተቋሞች የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በሥራ ላይ በዋለ ቢረዝም በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የምዝገባ ህግ እንዲያወጣና የምዝገባ ተቋማት እንዲያቋቁም ኃላፊነት

ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ እንዳልሆነ በግልጽ መደንገግ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

[30] በዚህ ረገድ በሴቶችና በህፃናት መብት ዙሪያ የሚሠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የጋብቻ ምዝገባ አስፈላጊነትን በማስተማርና የተፈፀሙ ጋብቻዎች እንዲመዘገቡ ለማስቻል ይረዳ ዘንድ ለክብር መዝገብ ሹሙ መረጃ በመስጠት ውጤታማ ሥራ እንዲሰሩ ይጠበቃል። ምክንያቱም አሁን ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የጋብቻ ምዝገባ ባለመከናወኑ ይበልጥ ተጎጂ የሚሆኑት ሴቶችና ህፃናት ናቸውና።



ተጥሎበታል[31]። ክፍተት እንዳይፈጠር በማሰብም የምዝገባ ተቋሙ ተደራጅቶ ሥራውን እስኪጀምር ድረስ ህጉ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው መስተዳድሮች ውስጥ በማዘጋጃ ቤቶች የተሰጡ ወይም የሚሰጡ የልደት የጋብቻና የመሳሰሉት የምስክር ወረቀቶች በክብር መዝገብ ሹም የተሰጡ ያህል ህጋዊ ፋይዳ እንደሚኖራቸው ተመልክቷል[32]።

ለነገሩ የጋብቻ ምዝገባ የማደራጀት ጉዳይ ለሃገራችን አለምአቀፋዊ ግዴታም ጭምር ነው። ኢትዮጵያ ያፀደቀችው በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውንም ልዩነቶች የማጥፋት ኮንቬንሽን አንቀጽ 16(2) የጋብቻ ምዝገባ ግዴታ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። ኢትዮጵያ ያፀደቀችው አለም አቀፍ ስምምነትም የሀገሪቱ ህግ አካል ስለመሆኑ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 9(4) ተመልክቷል። በመሆኑም የምዝገባ ሥርዓቱ የማደራጀት ጉዳይ ለነገ የሚባል አይደለም ሊሆንም አይገባም።

### 2.5 የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት

ቀደም ሲል ህጋዊና በህግ ፊት የሚፀና ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት የሚገባቸው ከፈቃድ ጋር፣ ከእድሜ ጋር፣ እንዲሁም ከዝምድናና ከመሳሰሉት ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ነጥቦች ማንሳታችን ይታወሳል። ቢሆንም በዚያ ክፍል ሥር ሁኔታዎቹ ሳይሟሉ ጋብቻው ተፈጽሞ ቢገኝ የጋብቻው እጣ ፈንታ ምን

[31] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 321(1) ሆኖም አዋጁ ከወጣ ሁለት ዓመት የሞላው ቢሆንም የምዝገባ ህጉና የምዝገባ ተቋሞቹ እስከአሁን ድረስ እንዳልወጡና እንዳልተቋቋሙ ለማወቅ ተችሏል። በመሆኑም ይህ ሁኔታ የህጉን አፈጻጸም እንዳይጎዳው ሥጋት አለ።
[32] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 321(2)



Generated by CamScanner

ይሆናል? የሚለውን አልተዳሰሰም ነበር:: በዚህ ክፍል ሥር ይህንኑ ለማየት እንሞክራለን::

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ይህ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የፍትሐብሔር ሕግ እንጂ የወንጀል ህግ ባለመሆኑ የወንጀል ቅጣቶችን አስመልክቶ የሚለው ነገር አይኖርም:: ይህንኑ በተመለከተ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ በተመለከተው መሠረት የሚታይ ይሆናል:: ስለሆነም በዚህ ክፍለ ሥር የምናገኛቸው ድንጋጌዎች የሁኔታዎቹ አለመሟላት የሚኖረው ፍትሐብሔራዊ ውጤት የተመለከተ ነው:: በወንጀል ህጉ መሠረት የሁኔታው አለመሟላት የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል ቢሆን እንደተጨማሪ ውጤት ይወሰዳል ማለት ነው::

ለጋብቻ የሚሆን ዝቅተኛው እድሜ ለወንዱም ሆነ ለሴቷ አሥራ ስምንት ዓመት ሲሆን እንደሚገባ የተደነገገ ቢሆንም በተለይ ለሴቶች ከዚህ እድሜ በታች ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል:: ለነገሩ የልደት ምዝገባ በሌለበት ሁኔታ ይህንኑ ማረጋገጥና መቆጣጠርም አስቸጋሪ እንደሚሆን ይገመታል::[23] ሆኖም ከእድሜ በታች ካጋጠመና ከተረጋገጠ ምን ይደረጋል? ለሚለው ግን ህጉ መልስ ሰጥቶ ማለፍ ይገባዋል::

ህጉ በህግ ከተመለከተው እድሜ በታች ጋብቻ ተፈጽሞ ቢገኝ ማንኛውም ባለጉዳይ ወይም ዓቃቤ ህግ ጋብቻ እንዲፈርስ

[23] ኢትዮጵያ ያፀደቀችውን የሃገሪቱ ህግ አካል የደረገችው የህፃናት መብት ኮንቬንሽን በአንቀጽ 7(1) ሥር ህፃናት እንደተወለዱ ወዲያውኑ መመዝገብ የሚያስችላቸው ሥርዓት እንዲያመቻቹ ለንዱ በፈራሚ ሃገሮች ላይ ግዴታ ጥሎባቸዋል::



ፍርድ ቤትን መጠየቅ እንደሚችሉ ደንግጓል::[24] ማንኛውም ባለጉዳይ ሲባል ቀደም ሲል እንደተመለከተው ከተጋቢዎቹ ዘመዶች በተጨማሪ በህፃናትና ሴቶች ዙሪያ የሚሠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንም ይጨምራል::

እዚህ ላይ ሊወሳ የሚገባው ጉዳይ ትዳሩ ጥያቄ ቀርቦ እስከፈረሰ ድረስ እንደማንኛውም ህጋዊ ትዳር ተቀባይነትና ህጋዊ ውጤት ይዞ የሚቀጥል መሆኑን ነው (valid unless and until invalidated):: በመሆኑም ሁኔታው አለመሟላቱ ትዳሩን ውድቅ ሊሆን (voidable) የሚችል ትዳር ያደርገዋል እንጂ ከመነሻው ዋጋ የሌለው አያደርገውም::

በአንዳንድ ሃገሮች የህግ ሥርዓት በህግ የተመለከቱትን አስገዳጅ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ተፈጽመው የተገኙ ጋብቻዎች ከመጀመሪያውም ጋብቻ እንዳልተፈጸመ (void abinitio) ተብለው ሊፈረጁ ይገባል ምንም ህጋዊ ውጤትንም ሊያስከትሉ አይገባም የሚል አቋም ይወስዳሉ:: በዚህ በያዝነው ህግ ግን እንዲህ ዓይነቱ አቋም መወሰድ አልተመረጠም:: ምክንያቱም ጋብቻው ከተፈጸመ በኋላ የጋራ ንብረት ባለሃብትነትና ልጆች ሊፈጠሩ የሚችሉበት እድል ሰፊ በመሆኑ ጋብቻ እንዳልነበረ መቁጠሩ በጋራ ንብረቱም ላይ ሆነ በተለይም ፈቅደው ባልተወለዱት ህፃናት ላይ አላስፈላጊና ውስብስብ ሁኔታዎች ስለሚፈጥር አልተመረጠም:: የተመረጠው

[24] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 31(1)



Generated by CamScanner

አቋም ጋብቻው ችግር የነበረው ቢሆንም እስከፈረሰ ድረስ ህጋዊ እንደነበር በመገመት ጋብቻ በፍርድ ውሳኔ ሲፈርስ የሚኖረው ሥርዓትና ውጤት መቀበል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ትዳሩ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚቻለው በህግ የተመለከተው እድሜ በተጋቢዎቹ ወይም በአንዳቸው እስካልተሟላ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ዝቅተኛው የጋብቻ እድሜ በሂደት መሟላቱ ከተረጋገጠ ትዳሩ እንዲፈርስ ሊጠየቅ አይቻልም፤ ቢጠየቅም ፍርድ ቤቶች እንዲፈርስ ሊወስኑ አይችሉም ጉድለቱ በሂደት (validation) ተስተካክሏልና፡፡[35]

በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና የተመለከተው ክልከላ በመተላለፍም ሆነ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሞ ከተገኘም እላይ እንደተመለከተው ትዳሩ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡[36] በዚህም ቢሆን ጥያቄ ቀርቦ እስካልፈረሰ ድረስ ህጋዊ ውጤቱ የፀና ሆኖ ይቆያል ማለት ነው፡፡ በርግጥ በዚህ ረገድ ትዳሩ እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ በጊዜ የተገደበ አይደለም፡፡ በማናቸውም ጊዜ ትዳሩን ለማፍረስ ጥያቄ ሊቀርብም እንዲፈርስም ሊወሰን ይችላል፡፡ የሚኖረው ገደብ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሞ የነበረ ከሆነ የመጀመሪያው ተጋቢ ከሞተ፣ የመጀመሪያው ጋብቻ በሞት ምክንያት ስለሚፈርስ ሁለተኛው ጋብቻ በጋብቻ ላይ ጋብቻ መሆኑ ስለሚቀር ሁለተኛውን ትዳር ለማፍረስ ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም፤ ቢቀርብም እንዲፈርስ አይወሰንም፡፡[37] በተለይም በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሞ ሲገኝ የኋለኛው ጋብቻ እንዲፈርስ

[35] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 31(2)
[36] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 32 እና 33(1)
[37] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 33(2)



መጠየቅ የሚችሉት የመጀመሪያዋ ተጋቢ ወይም ሁለተኛዋ ተጋቢ ወይም ዓቃቤ ህግ እንጂ ማንኛውም ባለጉዳይ ይህ መብት እንዲኖረው አልተደረገም፡፡[38] ይህ የተደረገበት ምክንያት አንዳንድ ሃይማኖቶችና ባህሎች በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተቀባይነት ሰጥተውት ስለሚገኙ ከባህሉና ከሃይማኖቱ ውጭ ያሉ ያገባናል ባዮች ጣልቃ እንዳይገቡ ለመገደብ በማሰብ ነው፡፡ በዚሁ ረገድ የሃይማኖትና የባህል ጉዳዮች ብርቱ ጥንቃቄ የሚሹ በመሆናቸው በጋብቻ ላይ ጋብቻን እንዳይፈጸም ለመቃወምና ለማፍረስ መጠየቅ የሚችሉ ወገኖች አጥብቦ መቅረጽ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው በዚሁ ክፍል ሥር የተደነገገው የተጋቢዎች ፈቃድ ለጋብቻ ምስረታ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጠ ስለሆነ የፈቃድ ጉድለት ማለትም ሙሉና ነፃ ፈቃድ ሳይሰጡ ጋብቻ ከተፈጸመ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለው ነው፡፡

ሰዎች በተለያየ ምክንያት ሙሉና ነፃ ፈቃድ የማይሰጡበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ አንዳንዴ በሃይል ተገደው ፈቃድ እንዲሰጡ ይደረጋሉ፤ በሌላ ጊዜም በአንዳንድ ሁኔታዎች በመሳሳት ወይም በመታለል ወይም የአእምሮአቸው ሁኔታ ባልተስተካከለበት ወቅት ፈቃዳቸው የሚሰጡበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ጥያቄው እንግዲህ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የተሰጠ ፈቃድና በዚህ ፈቃድ ተመስርቶ የተፈጸመ ጋብቻ የወደፊት እጣው ምን ሊሆን ይገባል? የሚል ይሆናል፡፡

[38] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 33(1)



Generated by CamScanner

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ከአንቀጽ 34 - 36 ያሉት ድንጋጌዎች ለዚህ ሁኔታ መፍትሄ ይሰጣሉ በሚል የተቀመጡ ናቸው:: በዚህም መሠረት በእንዲህ ዓይነት ፈቃድ ላይ ተመስርቶ የተፈጸመ ጋብቻ የመፍረስ እጣ ሊያጋጥመው ይችላል። ቢሆንም የማፍረስ ጥያቄው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል። የማፍረስ ጥያቄው የሚያቀርበውም ማንኛውም ባለጉዳይ ወይም ዓቃቤ ህግ ሳይሆን እንደነገሩ ሁኔታ በሃይል ተግባር ተገዶ ፈቃዱን የሰጠ፤ የተሳሳተ ወይም የተጭበረበረ[39] ሰው ወይም ፈቃዱን ባግባቡ ያልሰጠው ሰው ብቻ ሊሆን ይገባል:: የጊዜ ገደቡም እንደነገሩ ሁኔታ የኃይል ተግባሩ ከቀረ ወይም መሳሳቱን ካወቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጋብቻውን ለማፍረስ መንቀሳቀስ እንደሚኖርበት የተመለከተ ሲሆን በአጠቃላይ ግን በእንዲህ ዓይነት የፈቃድ ጉድለት ሁለት ዓመት ካለፈ ጋብቻውን ማፍረስ እንደማይቻል ተመልክቷል::[40] ለዚህም ምክንያቱ በሁለት ዓመት ውስጥ በጋብቻው ውስጥ ግንኙነቱን የሚያጠናክሩ እንደልጅ መውለድና የጋራ ሃብት ማፍራት የመሳሰሉት ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ጋብቻው የሚጠገን ቢሆን እንዲጠገን እድል ለመስጠት ነው::

እዚህ ላይ ግን ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ሁለት ዓመት ካለፈ ጋብቻውን ማፍረስ አይቻልም ሲባል መሳሳቱን ወይም የኃይል ተግባሩን ወይም ሌላ የፈቃድ ጉድለት የፈጠረን ነገር

[39] በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ በማታለል የተፈፀመ ጋብቻ ውጤቱ ምን እንደሚሆን የተቀመጠ ነገር ባይኖርም መታለል በአንድ መልኩ ሲታይ መሳሳት በመሆኑ "በስህተት ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻን ስለማፍረስ" በሚለው ሥር ይወድቃል ተብሎ ይታመናል:: በፍትሐብሄር ጉዳይ በይመስላል (analogy ) መስጠት የሚከለከል አይደለም።



Generated by CamScanner

መሠረት በማድረግ ጋብቻው እንዲፈርስ መጠየቅ አይቻልም ለማለት እንጂ በሌላ ሁኔታ ለምሳሌ በፍቺ ምክንያት ጋብቻውን ማቋረጥ አይቻልም ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል:: ስለሆነም ትዳሩ እስካልተፈለገ ድረስ የአካሄዱ ስርዓት ይለያል እንጂ ትዳሩን በሌላ የህግ ምእራፍ የማፍረሱ እድል አሁንም ክፍት ነው ማለት ነው::

በመጨረሻም በዚህ ክፍል ሥር ከአንቀጽ 37 - 39 ያሉት ድንጋጌዎች ምንም እንኳ በሰፊው ሲታዩ 'የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት' በሚለው ስር ይወድቃሉ ሊባል የሚችል ቢሆንም ከይዘት (substance) ይልቅ የሥነ-ስርዓት (procedural irregularities) ግድፈቶች ተብለው የሚወሰዱ ስለሆነ ጋብቻውን የማፍረስ ውጤት ሊያስከትሉ አይገባም በሚል ተቀምጠዋል:: ይዘታቸውም የሚከተለውን ይመስላል::

እንዲት ሴት የፊተኛው ጋብቻ ከፈረሰ እስከ 180 ቀናት ድረስ ሌላ ጋብቻ መፈጸም አትችልም የሚል ድንጋጌ ቀደም ሲል የተቀመጠ ቢሆንም ዓላማው ምናልባት ከፊተኛው ጋብቻ እርግዝና ኖሮ ቢሆን የልጁን አባት በመወሰን ረገድ ችግር እንዳይፈጠር ለመከላከል ስለሆነ እንዲሁ 180 ቀናት አልጠበቀችም ተብሎ የኋለኛው ጋብቻ እንድታፈርስ ጥያቄ ማቅረቡ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም::[41]

[40] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጾች - 35 እና 36
[41] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 37

ከዚህም ሌላ ጋብቻው በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀም ከሆነ ሥልጣን የሚኖረው የክብር መዝገብ ሹም ከተጋቢዎች አንዱ ወይም ከተጋቢዎቹ ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች አንዱ ጋብቻው ከሚፈጸምበት ጊዜ በፊት ቢያንስ ለስድስት ወራት ሳያቋርጥ በሚኖርበት ቦታ የሚገኘው የክብር መዝገብ ሹም እንደሆነ ተመልክቷል::[42] ሆኖም ተጋቢዎች ከዚህ ክብር መዝገብ ሹም ውጪ በሌላ የክብር መዝገብ ሹም ፊት ጋብቻቸውን ከፈፀሙ ጋብቻውን ያስፈጸመው ክብር መዝገብ ሹም መሆኑ እስካላወገዘ ድረስ የሌላ ቦታ የክብር መዝገብ ሹም እንጂ የእነርሱ አይደለም በሚል ብቻ ጋብቻቸውን ለማፍረስ መንቀሳቀስ አይገባም አይቻልም::[43]

ሌላውና የመጨረሻው በዚህ ክፍል ሥር የተመለከተው ድንጋጌ ርእሱም ራሱ 'የሥነ-ስርዓት አለመጠበቅ' በሚል የተቀረፀ ነው:: በአንቀጽ 25 ሥር የክብር መዝገብ ሹም ጋብቻ ሲያስፈጽም መከተል ስለሚገባው ሥነ-ስርዓት ተቀምጦዋል:: ይህን ሥነ-ሥርዓት ሳይጠብቅ ጋብቻውን ቢያስፈጽም ይህንን ሥርዓት ግድፈት በመጥቀስ ብቻ ጋብቻውን እንዲፈርስ መወሰን አይቻልም::[44] በርግጥ ይህ የሥነ-ስርዓት ግድፈት ያስከተለው ሌላ የጋብቻ ሁኔታ አለመሟላት ተከትሎ ከሆነ በዚሁ መሠረት ጋብቻውን ለማፍረስ ጥያቄ ማቅረብ ግን ይቻላል:: ለምሳሌ የክበር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹንና ምስክሮቻቸው ማስፈረም ሲገባው

---

[42] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 22
[43] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 38
[44] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 39



ተጋቢዎቹን ሳያስፈርማቸው ከቀረ ፈቃዳቸው ስለመስጠታቸው ማረጋገጥ ስለማይቻል የጋብቻ ሁኔታ አለመሟላት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::

## ምእራፍ 3 - የጋብቻ ውጤት

### 3.1 ስለ ጋብቻ ውል

ጋብቻ ህጋዊ ድርጊት እንደመሆኑ መጠን ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ስለመሆኑ የታወቀ ነው:: እነዚህም ህጋዊ ውጤቶች በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ወይም በተጋቢዎች የንብረት ግንኙነት ላይ ወይም በሁለቱም ላይ ተጽእኖ የሚኖራቸው ናቸው:: በርግጥ አንዳንዱ ውጤቶች በውል ሊቀየሩ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ ቢሆኑም አንዳንዶቹ ግን ሊቀሩ ወይም ሊሻሻሉ የማይችሉ አስገዳጅ ውጤቶች ናቸው::[45]

እነዚህም ውጤቶች የጋብቻው የአፈጻጸም ሥርዓት ምንም ይሁን ምንም ተመሳሳይ ውጤት እንደሚኖር በግልጽ ተመልክቷል::[46] በተለይም በሃይማኖትና በባህል ስርዓት የተፈጸሙ ጋብቻዎች ውጤታቸውም ሃይማኖቱ ወይም ባህሉ በሚያዘው መሠረት የተመሠረተ ሊሆን ይገባል በሚል አልፎ አልፎ የሚያመጠው ክርክር ህጋዊ መሠረት እንደሌለው ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል::[47] አንዳንድ ሃይማኖቶችና ባህሎች የጋብቻ

---

[45] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 42(3)
[46] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 40
[47] የቤተሰብህጉን ለማሻሻል በተካሄዱት ተከታታይ አውደ ጥናቶች ሲቀርቡ ከነበሩት አስተያየቶችአንደ ገንዘብነው "ጋብቻ የተፈፀመው በሸሪዓ ህግ



Generated by CamScanner

ውጤትን ከግብረስጋ ግንኙነት መፈጸም ጋር ወይም ከክብረንፅህና መገኘት ጋር ለማያያዝ እንደሚሞከሩ ይታወቃል::[47] ሆኖም ህ የጋብቻ ውጤትን የጋብቻው ስርዓት ከመፈጸም ጋር እንጂ ከእነዚህ ጉዳዮች ጋር ሊያያይዘው አልፈቀደም::

እላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የጋብቻ ውጤት በውል ሊቀር ወይም ሊሻሻል ይችላል:: ይህም ውል የጋብቻ ውል ተብሎ ይጠራል:: በነባሩ የቤተሰብ ህግ የጋብቻ ውልና የጋብቻ ጽሁፍ የተባሉ ጽንሰሃሳቦች እየተምታቱ አንዳንዴም አንደ ዓይነት እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠሩ እንደነበር አይዘነጋም::[49]

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ችግሩን በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ፡ በማሰብ የጋብቻ ጽሁፍ የሚለው ጽንስ ሃሳብ ከህጉ ውስጥ በማውጣት የጋብቻ የምስክር ወረቀት በሚል ተተክቶ ሲገኝ የጋብቻ ውል ግን በነበረበት እንዲቀጥል ተደርጓል:: በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አገላለጽ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ጋብቻ ከተፈፀመ በኋላ ወይም ሲመዘገብ ጋብቻ ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ከክብር መዝገብ ሹም የሚሰጥ ማስረጃ ሲሆን የጋብቻ ውል ግን ተጋቢዎች

ከሆነ ውጤቱም በዚያው በሸሪዓ ህግ መሠረት የሚታይ ይሆናል እንጂ ወደ ፍትሐብሔር ህጉ የሚመጡበት ሁኔታ ሊኖር አይገባም የሚሉና የመሳሰሉት ሃሳቦች ይደመጡ ነበር::

[48] በአንዳንድ ኢትዮጵያዊ ባህሎች እንዲት ሴት በጋብቻው ወቅት ከንክብረንፅህናዋ ካልተገኘች ጋብቻው እንዳልተፈፀመ የመቁጠር አመለካከትና አዝማሚያ አለ

[49] የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሲ.ች.ፍ.መ.ቁ 287/81 ሥር በዚሁ ነጥብ በሰሬው የተቸበት ጉዳይ ነው:: (የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ምርጥ ፍርዶች የፍትሐብሔር ጉዳዮች ሁለተኛ መጽሐፍ ከገጽ 409 - 412 ይመልከቱ፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋኩልቲ የተጠረዘ - መጋቢት 1992)



የንብረት ግንኙነታቸው አልፎ አልፎም ግላዊ ግንኙነታቸውን እስመልክተው የሚፈራረሙት የጽሁፍ ሰነድ ነው::[50]

የጋብቻ ውል እንደማንኛውም ውል ሁሉ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን ሊቃረን እንደማይችል ተቃርኖ ቢገኝም ፈራሽ እንደሚሆን በግልጽ ተመልክቷል:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ከመፈጸማቸው በፊት ወይም ጋብቻቸው በሚፈጸምበት ዕለት ጋብቻው በንብረት ግንኙነታቸውና በግላዊ ግንኙነታቸው ላይ ስለሚኖረው ወጤት በጋብቻ ውል ሊወስኑ እንደሚችሉ በህግ ተመልክቷል:: እንዲህ ሲባል ለምሣሌ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በጋብቻ ላይ ጋብቻ የተከለከለ እንደሆነ ተገልጿል:: በመሆኑም ሚስት ባሏ ሁለተኛ ሚስት እንዲያገባ በጋብቻ ውል ብትስማማም ህጋዊ ሊሆን አይችልም ማለት ነው:: ምክንያቱም ከቤተሰብ ህጉ ውስጥ አስገዳጅ ከሆኑት ድንጋጌዎች አንዱ የሆነውን አንቀጽ 11 ይቃረናልና::

ከዚህም አልፎ የጋብቻ ውሉ በጽሁፍ እንዲሆንና በአራት ምስክሮች ምስክሮቹም ሁለት በባልየው በኩል ሁለት ደግሞ በሚስቲቱ በኩል የቀረቡ እንዲሆኑ ያስገድዳል:: ይህ ካልተሟላም የጋብቻ ውል እንዳልተደረገ ይቆጠራል::[51] በተጨማሪም የጋብቻ ውሉ አንድ ቅጅ በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ሊቀመጥ ይገባል::[52]

[50] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 42(1) እና 94

[51] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 44

[52] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 45



Generated by CamScanner

በጽሁፍ የተያዘ መረጃ ከአስተማማኝነትና ማስረጃዊ ፋይዳ አንፃር ከሌላው የተሻለ እንደሆነ ስለሚታመንና በጽሁፍ የተደረገ ነገር በበለጠ የታሰበበት ነገር (seriousness of commitment) ነው ተብሎ ስለሚገመት ይህንኑ ለማረጋገጥ የጋብቻ ውል በጽሁፍ እንዲደረግና ተጋቢዎች ግዴታ ተጥሎባቸዋል። ውሉም በምስክሮች ፊት እንዲደረግ ይፈልጋል ብቻ ሳይሆን ምስክሮቹም ከሁለቱም ወገን የተውጣጡ እንዲሆኑ ተፈልጓል።[53] ባልና ሚስቱ ለሁለቱ ተፈራርመዋል ቢሉ ነገ ውሉ ፈቃድ የነበረበት ስለመሆኑ አከራካሪ ስለሚሆን በሰዎች ፊት እንዲያደርጉት፤ አግባብ ካለው ድርድር በኋላ የተፈፀመ ውል መሆኑን ለማረጋገጥ ደግሞ በነድም እንዲሁ አላፊ አግባቢ ምስክር ሳይሆን የተጋቢዎቹ ወገኖች እንዲሆኑ ተፈልጓል። የውል ሰነዱም በአንድ በኩል ለጥንቃቄ ሲባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከተጋቢዎች ወይም ከአንዳቸው ጋር ለመጣላት የሚፈልጉ ሦስተኛ ወገኖች ሰነዱን ለማየት እንዲችሉ አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር በመንግስት ተቋም (በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም) እንዲቀመጥ የሚያስችል የህግ ድንጋጌ ተቀምጦላቸዋል።[54]

[53] ለነገሩ ይህ ግዴታ ድንጋጌ በፍትሐብሔር ህጉ ውስጥም ሆነ የፍትሕ ሚኒስቴር አዘጋጅቶት በነበረው ረቂቅ የቤተሰብ ህግ ተካትቶ የነበረ ነው። (የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 620 እንዲሁ የፍትሕ ሚኒስቴር ረቂቅ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 49 ይመልከቱ) በረቂቁ በፍትሕ ሚኒስቴር ረቂቅ "የጋብቻ ውል" ሳይሆን "የጋብቻ ስምምነት" በሚል ተተርጉሞ እንደነበር መገንዘብ ይገባል።
[54] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 45(1)



እዚህ ላይ ምናልባት ሊነሳ የሚችል ተገቢ ጥያቄ የጋብቻ ውል በእነዚህ መንግስታዊ ተቋማት በአንዱ ባይቀመጥ ህጋዊ ፋይዳው ምን ይሆናል የሚል ነው? በአንድ በኩል ሊያዝ የሚችለው የክርክር መስመር የውሉ ሰነድ በእነዚህ ተቋማት እንዲቀመጥ በህግ የተደነገገ በመሆኑ ይህ ካልተፈጸመ ሰነዱ ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው አይገባም የሚል ነው። ሁለተኛው የክርክር መስመር ደግሞ ሰነዱ እነዚህ ተቋማት ዘንድ እንዲቀመጥ የተፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ለጥንቃቄና ለሶስተኛ ወገኖች ጥቅም ተብሎ በመሆኑ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዳይኖረው በማድረግ በተጋቢዎች ላይ ግን ህጋዊ ሃይሉን እንደጠበቀ እንዲቀጥል ማድረግ ይገባል የሚል ነው። ከሁለት አቀራረቦም ሲታይ በአንቀጽ 44 መሰረት የውሉ ፎርም ካልተሟላ ውጤት እንደማይኖረው ሲገልጽ በመንግስት ተቋም ዘንድ ባለመቀመጡ የሚያስከትለው ውጤት ግን በአንቀጽ 45 የተባለ ነገር ስለሌለ ውጤት አልባ ለማድረግ ታስቦ ቢሆን ኖሮ ይህንኑ በግልጽ ማስቀመጥ ይቻል ስለነበር ሁለተኛው የክርክር መስመር ሚዛን የሚደፋ ይመስለናል።

ሌላው በጋብቻ ውል ዙሪያ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ እንደሌላው ውል ሁሉ በሶስተኛ ወገኖች ግዴታን የሚያስከትሉ ድንጋጌዎችን ማካተት እንደማይችል በአስገዳጅ መግለጽ ብቻ ሳይሆን የጋብቻ ውሉም በጥቅሉ ለምሳሌ እንደሚስት በስማንያ እንደገለጸ በቁርባን ተጋብተናል በሚል ወይም የጋብቻ ግንኙነታችን በሸሪዓ ህግ መሰረት ይገዛ በሚል ወይም የጋብቻ ግንኙነታችን በነባሩ የቤተሰብ ህግ መሰረት ይገዛል በሚል ወይም

የመሳሰሉት ጥቅል ሃረጎች በመጠቀም መዋዋል እንደማይቻል መገንዘብ ይገባል:: እንዲህ ዓይነቶቹ ጥቅል ሃረጎች ከርክር ሲያጋጥም ለተለያየ ትርጉም የተጋለጡ በመሆናቸው ይህ መሰሉ የጋብቻ ውል አቀራረጽ እንዲወገድ ህጉ ይፈልጋል ያስገድዳልም::[8] በመሆኑም እንዲህ ዓይነት የጋብቻ ውል በህግ ተቀባይነት አይኖረውም ማለት ነው::

ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን ለማቋረጥም ሆነ ለማሻሻል ሙሉ ነፃነት እንዳላቸው የውል መሠረታዊ መርህ ያስገነዝባል:: የጋብቻ ውል በዚህ ረገድ ከውል መርህ በተለየ መልክ እንዲታይ ተደርጓል:: ተጋቢዎች የጋብቻ ውላቸውን ለማሻሻልም ሆነ በጋብቻቸው ዘመን የጋብቻ ውል ቢፈረም እንዲሁ ዓይነቱ ማሻሻያ ወይም ውል ፍርድ ቤት ካላፀደቀው ተቀባይነት እንደማይኖረው በአዋጁ አንቀጽ 47 እና 73 ተመልክቷል::

ይህን ዓይነት ውል የማፅደቅ ኃላፊነት በነባሩ የቤተሰብ ህግ ለቤተ ዘመድ ሽምግልና ዳኞች ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የሽምግልና ዳኞቹ ሚና በተወሰነ ጉዳዮች ላይ የተገደበ ስለሆነ በዚህ ረገድ የነበራቸው ኃላፊነት ወደ ፍርድ ቤት እንዲተላለፍ ተደርጓል:: እዚህ ላይ ባልና ሚስቱ እርስ በራሳቸው የመዋዋል ነፀነታቸውን መገደብ ለምን አስፈለገ? የሚል ጉዳይ ሊነሳ ይችል ይሆናል::

---

[8] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 46



የመዋዋል ነፃነት ፋይዳ የሚኖረው ተዋዋዮቹ በነፃነትና በእኩልነት ለመዋዋል ሲችሉ ነው:: ባልና ሚስት ሆነው ውል ሲፈጽሙ ህጉ የሚፈልገው ዓይነት ነፃነትና እኩልነት (arms length transaction) ስለመኖሩ በእጅጉ ያጠያይቃል:: ባልና ሚስቱ ባላቸው ልዩ ግንኙነት ምክንያት በነፃነት ሳይደራደሩና በእኩልነት ስሜት ሳይተያዩ ውል ለመፈረም የሚኖረው እድል ሰፊ ነው:: ለዚህም ባህላዊ ሃይማኖታዊና ሞራላዊ እሴቶቻችን የየራሳቸው ተጽእና ማሳደራቸው አይቀርም:: ከዚህም አልፎ ውላቸውን የሶስተኛ ወገኖች ጥቅም ለሚጎዳ ዓላማ ሊያውሉት ይችላሉ:: በመሆኑም የተሻሻለው ውል ወይም አዲስ የተመሰረተው ውል የተጋቢዎቹ የራሳቸው ወይ.ም የቤተሰቡ ጥቅም ወይም የሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ጥቅም የመጎዳት ውጤት ሊኖረው ይችላል:: ስለዚህ ይህ አላስፈላጊ ውጤት እንዳይከተል መንግስት ጣልቃ ገብቶ መቆጣጠር እንደሚገባው ይታመናል:: ፍርድ ቤትም ከመንግስት ተቋሞች አንዱ በመሆን ይህንኑ ኃላፊነት እንዲያከናውን ተመርጧል::

በመጨረሻም በዚህ ክፍል ሥር መወሳት ያለበት ነገር ተጋቢዎች የጋብቻ ውል ካልመሠረቱ ወይም የጋብቻ ውሉ በህግ ተቀባይነት ካጣ የተጋቢዎቹ ግላዊና የንብረት ግንኙት ምን መልክ ይኖረዋል? የሚለው ህጉ መልስ የሰጠበት መሆኑን ነው:: በህጉ እምነት ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ውጤት በውል ከወሰኑና የጋብቻ ውሉም አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን ያልተቃረነ ከሆነ የጋብቻ ውሉ ግንኙነታቸውን እንዲገዛ ይደ.ጋል:: አልፎ አልፎ ግን እንዲያውም ብዙውን ጊዜ ተጋቢዎች የጋብቻ ውል ሲፈራረሙ አይታይም:: ቢፈራረሙም በህጉ የሚፈለግበትን መመዘኛ የማያሟላበት ጊዜ



Generated by CamScanner

ጥቂት አይደለም። በዚህ ግዜ ህጉ የተፈጠረውን ክፍተት (gap filling mission) የመድፈን ኃላፊነት ተጥሎበታል።[56] ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ ከአንቀጽ 49-73 ያሉትን ድንጋጌዎች ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም ወደነዚህ የህግ ድንጋጌዎች መሄድ የግድ የሚሆነው የጋብቻ ውል በሌለ ጊዜ ወይም የጋብቻ ውል ቢኖርም አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች ከተቃረነ ወይም በህግ የሚጠበቅበት አስገዳጅ መስፈርቶች ሳይሟላ ሲቀር ነው። በመሆኑም ይህ ክፍል የመጨረሻ አማራጭ (last resort) መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ግን በዚህ ክፍልም ሥር አስገዳጅ ሆነው የተቀመጡ ድንጋጌዎች ካሉ እነርሱም ቢሆኑ ሊከበሩ ይገባቸዋል ማለት ነው ምክንያቱም የህጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች ናቸውና ነው።

### 3.2. <u>ጋብቻው በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት</u>

ማግባት ከወንደላጤነት ወይም ከሴተላጤነት ተወጥቶ የተለየ ማህበረሰባዊ ቦታ ማለትም 'አባወራነት' ወይም 'እማወራነት' የሚያገኙበት ማህበራዊ ቁርኝት በመሆኑ በተጋቢዎች ግላዊ አቋም (status) ላይ ለውጥ ማስከተሉ አይቀርም። በዚህ ረገድ እንደአገራችን ህጋዊ ውጤት ተደርጎ የሚወሰደው ባልና ሚስቱ እርስ በራሳቸው መከባበር መተጋገዝና መደጋገፍ እንዳለባቸው የሚመለከተው ነው። ለነገሩ በሞራልም ቢሆን ትዳር የሚመሠረተው በጎና ክፉውን ለመጋራት እንደሆነ ይታመናል። እንዲያውም በአንዳንድ ጋብቻ

[56] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 48



ማስፈፀሚያ ስርዓቶች ተጋቢዎች "ታማኝ (ታማኝ ብዬ) ላልከዳው (ላልከዳት)፣ ችገረው (ቸገራት) ብዬ ላልከደው (ላልከዳት) እንዲምሉ ይደረጋል። ቃል እገባለሁ" ብለው በእድምተኛው ፊት እንዲምሉ ይደረጋል። ይህ ግዴታ መኖሩ ብቻም ሳይሆን ግዴታውንም በጋብቻ ውል ማስቀረት (ማስወገድ) የማይቻል መሆኑም ጭምር ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል ማለትም 'አንተጋገዝም አንረዳዳም እኛን የሚያገናኘን መኝታ ብቻ ነው' ብለው መስማማት አይችሉም።

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ከነባሩ ህግ በተለየ መልኩ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ዙሪያ ከወሰደው አቋም አንዱ የቤተሰብ አመራርን የተመለከተው ነው። በቀድሞው ህግ "ባል የቤተዘመድ ሹም ነው" "ባል ለሚያዛት ህጋዊያን ድርጊቶች ሁሉ ሚስት መታዘዝ አለባት" የሚሉ ድንጋጌዎች እንደነበሩ አይዘነጋም።[57] ከዚህም አልፎ የፍትሐብሄር ህጉ "ባልና ሚስት የሚኖሩበት ሥፍራ የሚወስነው ባልየው"[58] እንደሆነ እንዲሁም" ባል ሚስቱን የመቆጣጠር ጠባይዋንና ግንኙነትዋንም የመወሰን ሥልጣን እንዳለው ተመልክቷል።[59] ይህን መሰል ድንጋጌዎች ይዞ የወጣው የፍትሐብሄር ህግ በትዳር ጓደኛሞች መሐከል ሹምና ጭፍራ፣ አለቃና ምንዝር፣ አዛዥና ታዛዥ በመፍጠር በትዳር ዘመን የወንዱን የበላይነት የሚያረጋግጥ የህግ ሰነድ ሆኖ አገልግሎአል ተብሎ ሲወገዝ እንደነበር አይዘነጋም።

[57] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 635
[58] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 641(1)
[59] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 641(2)



Generated by CamScanner

በርግጥ አንዳንድ ወገኖች ይህ ሁሉ ሥልጣን ባልየው በሚስቲቱ ላይ እንዲኖረው የተደረገበት ምክንያት ህጉ በወጣበት ዘመን በባልና ሚስት መካከል በነበረው አጠቃላይ የሥራ ክፍፍል መሠረት ነው:: ባል በቀጥታ ገቢ በሚያስገኙ ሙያዎች ተሰማርቶ የሚያመጣውን ጥሪት የሚስት ሲሆን የሥራ ድርሻ ቤት ተቀምጣ አብስላ ማቅረብ ስለነበር ይህን የባልየው የኢኮኖሚ የተሳትፎ የበላይነት ድርሻ ለማንፀባረቅ የወጣ ህግ እንደሆን ለማሳመን ይሞክራሉ::

ሆኖም ይህ ዓይነቱ የሥራ ክፍፍል በሁሉም የሃገራችን ክፍሎች የሚሠራ አይደለም:: በተለይም በአርብቶ አደሩ ህብረተሰባችንና በቆላማው የሃገራችን ክፍል የውጪውንም ሆነ የጓዳውን ሥራ ከሞላ ጎደል አጠቃልላ የምትሰራው ሚስቲቱ ሆና እያለች ህጉ ግን አሁንም የበላይነቱን የሰጠው ለባልየው ነው:: የሚስት ስራ ቤት ተቀምጣ የቀረበላትን አብስላ ማቅረብ ነው የሚባልለት የሃገራችን ክፍልም ቢሆን ሚስት አብስላ የማቅረቡን ስራ የምታከናውነው ከባልየው ጋር በምርት ሥራ ደፋ ቀና ስትል ውላ ከተመለሰች በኋላ እንደተጨማሪ ሥራ የምታከናውነው እንጂ ብቸኛ ሥራዋ አይደለም:: በመሆኑም ህጉ ያንፀባረቀው የባልና ሚስቱን የኢኮኖሚ ድርሻና ተሳትፎ ነው የሚለው አባባል ሚዛን የሚደፋ ክርክር አይመስልም:: እንዲሁ ህጉ ሲወጣ የነበረውን የፊውዳል ሥርዓት አጠቃላይ እምነትና አስተሳሰብ ለማንፀባረቅ የወጣ ነበር ቢባል የተሻለ አሳማኝ ይመስላል:: ለነገሩ በኢንዶኔዥያ የቤተሰብ ህግም "ባልየው የቤተ-ዘመድ ሹም ሲሆን ሚስትየው ደግሞ የቤቱ ሥራ አስኪያጅ ናት (The husband is the head of the



family and the wife is the manager of the household)" በሚል ተደንግጎ እናገኛለን (አንቀጽ 31(2) (3) ይመለከቷል::)

ያም ሆነ ይህ እንዲህ ዓይነቱ ህግ አሁን ከደረስንበት የእድገት ደረጃና በቅርቡ ከፀደቀው ፌደራላዊ ህገ-መንግስት ጋር ስለማይጣጣም በዚህ ረገድ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ ለውጥ ተደርጓል:: "በተለይም ተጋቢዎች በጋብቻ አፈጻጸም በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው::"[60] የሚለውን ህገ መንግስታዊ መርህ መከበር ስለሚገባው በጋብቻው ዘመን ወንዱን የበለይ አመራር ሰጪ ሴቷን ታዛዥ የሚያደርግ ህግ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም ስለዚህም የቤተሰብ አመራር እኩልና የጋራ የሚያደርግ አንቀጽ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ እንዲካተት ተደርጓል:: በመሆኑም በቤተሰብ አመራር ረገድ ባልና ሚስት እኩል መብት እንዳላቸው በማረጋገጥ የቤተሰቡን ደህንነትና ጥቅም ማእከል ያደረገ የቤተሰብ አመራር በመመካከር እንዲያከናውኑ ግዴታ ተጥሎባቸዋል::[61]

ሳንዳንዴ የሚነሣው ሃሳብ በሁሉም ነገር በትንሹም በትልቁም እንዴት ይመካከራሉ? ግላዊ ውሳኔ እንዲወስዱ መብት ሊሰጣቸው አይገባም ወይ? የሚል ነው:: እዚህ ላይ ግን መታወቅ የሚኖርበት ጉዳይ ህጉ ግላዊ ውሳኔ እንዳይወስዱ በትንሹም ነገር ወደ ምክክር እንዲሄዱ ለማስገደድ የተቀረጸ ሳይሆን በህግ የተቀመጠ ሹምና የቤተሰብ ሃላፊ እንዳይኖርና ተጋቢዎቹ ራሳቸው

[60] ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 34(1)
[61] የሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 50



Generated by CamScanner

የቤተሰብ አስተዳደራቸውን በውስጥ የሥራ ክፍፍል እንዲያከናውኑት ለማድረግ ለማስቻል ብቻ ነው:: ስለሆነም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ሲታመንበት የግል ውሳኔ ሰጪነትን የማያስቀር አይደለም::

ሌላው ጋብቻ በተጋቢዎች የግል ግንኙነት የሚፈጠረው ውጤት አብሮ የመኖር ግዴታ የሚጥል መሆኑን ነው:: በመሠረቱ ህግ ጋብቻን ለመጠበቅ ከተነሣባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋናው የህብረተሰብ መሠረት መሆኑ ነው:: የህብረተሰብ መሠረትነቱ የሚገለጽበት መንገድም ተተኪዎች በመውለድ የህብረተሰብ ቀጣይነት የሚረጋገጥበት መንገድ ስለሆነ ነው:: ይህም አብሮ በመኖርና ለጤና አደገኛ እስካልሆነ ድረስ ባልና ሚስቱ መደበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ የሚሳካ ይሆናል:: ስለዚህም ይህ ግዴታ ተጋቢዎቹ እንዳለባቸው በህይወት ልማድ እንደሚታወቅ ቢገመትም በህግም ማስገንዘብ እንደሚገባ ታምኖበታል::[62] ይህ ግዴታ በህግ መቀመጡም በአንዳንድ ሃገሮች ውስጥ የሚያጋጥመው ባል ሚስቱን ደፈረ (marital rape) ተፈጸመ ዓይነት ውዝግቦች በኛ አገር የህግ መሠረት አይኖራቸውም ማለት ነው:: እንዲህ ዓይነት ጉዳዮች ወደፊት በጊዜ ሂደት ምን መልክ እንደሚይዙ በመጪው ትውልድ ዘመን የሚታይ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን የኢትዮጵያ ሴቶች ቀዳሚ አጀንዳ አይመስልም የሚል እምነት አለ:: ከዚህ የጠጠረ ችግር በስፋት አለንና::

[62] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 53



በባልና ሚስት መካከል አብሮ የመኖር ግዴታ ያለ ቢሆንም ይህንኑ ግዴታ በሁለቱም ስምምነት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ሊያስወግዱት ይችላሉ:: አብሮ መኖሩ ለኑሮአቸው መደጎሚያ ከሚሠሩት ሥራ ጋር ላይስማማ ስለሚችል በሥራ ምክንያት ተለይቶ መኖር የሚያስፈልግበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ይህንኑ በተጋቢዎች ስምምነት ሥር ማስተናገድ ይቻላል::[63]

አብረው መኖር ካለባቸው የመኖሪያ ስፍራቸው እንዴት ይወሰናል? የሚለው ጉዳይ ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት የሚገባው ነው:: በነባሩ ህግ አብረው የሚኖሩበት ሥፍራ የሚወስነው ባልየው እንደሆነ ተመልክቶ እንደነበር አይዘነጋም::[64] በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን እላይ ለመግለጽ በተሞከሩት ምክንያቶች በመመስረት የመኖሪያ ስፍራ በጋራ /በባልና ሚስቱ/ መወሰን እንደሚገባው ተደንግጓል:: እዚህ ላይ ባይስማሙስ ምን ይደረጋል? ሊባል ይችል ይሆናል::

የህጉ ግምት ጉዳሩን እስከፈለጉት ድረስ ጉዳዩን በቅን ልቦናና በሰከነ ህሊና ይወያዩበታል የሚል እምነት ይኖራል የሚል ነው:: ተወያይተው መስማማት ካልቻሉም በዚህ ምክንያት ወደ ፍቺ እስካላመሩ ድረስ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠር አለመግባባት ስለሚሆን ባልና ሚስቱ በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት እንዲወሰን ይደረጋል::[65]

[63] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 54
[64] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58
[65] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 118



Generated by CamScanner

በነባሩ ህግ በጋብቻ ግላዊ ግንኙነት ውጤት ሥር የነበሩት "ባል ሚስቱን መጠበቅ አለበት፤" ሚስቱ የምታደርጋቸውን ግንኙነቶች ለመቆጣጠርና የጠባይዋንም አመራር ለመጠበቅ ይችላል፤"[66] ከተጋቢዎች እያንዳንዱ የመረጠውን የሞያ ሥራ ወይም የጥበብ ሥራ ለማከናወን ይችላል፤"[67] ቢሆንም ለትዳራቸው የማይጠቅም መሆኑን ከተገነዘበ ሌላኛው ተጋቢ ሊቃወመው ይችላል፤" "ባል አሽከር ለመቅጠር ችሎታ የሌለው እንደሆነ ሚስቲቱ የቤት አያያዝ ሥራ እንድታከናውን ግዴታ አለባት"[68] የሚሉት ድንጋጌዎች በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ እንዲካተቱ አልተደረገም።

እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ መውሰድ ያስፈለገበት ምክንያት ባል ሚስቱን መጠበቅ እንዳለበትና ግንኙነትዋንም እንዲቆጣጠር መፍቀዱ ሚስት ራስዋን የማትጠብቅና ጠቃሚ ግንኙነትዋን ለመገምገም የማትችል አስመስሎ የሚያቀርብና ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው አንቀጾች ጋር ተዳምሮ ሲታይ በተለይም ለሚስት በተመሳሳይ ባልዋን የመግራት መብት ባልተሰጠበት ሁኔታ የወንዱን የበላይነት ብቻ ሳይሆን በእውቀት የላቀ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ ይታያል።[69] በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሠረት ባልና ሚስቱ ጋብቻው ለአካለ መጠን ከደረሱ በኋላ የሚፈጽሙት ህጋዊ ድርጊት በመሆኑ ራሳቸውን በራሳቸው ይጠብቃሉ ተብሎ

[66] የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 644
[67] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 645
[68] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 646
[69] የፍትህ ሚኒስቴር አዘጋጅቶት በነበረው ረቂት የቤተሰብ ህግ አንቀጽ - 62! ሥር "ለትሮአቸው መልካም ጥቅም ከሆነ ባል ሚስቱ የምታደርገውን እንዲሁም ሚስት ባልዋ የሚያደርገውን ግንኙነት ለመቆጣጠርና የየጠባያቸውንም አመራር ለመጠበቅ ይችላሉ። በሚል ተደንግጎ ነበር።



ይገመታል። ስለሆነም አንዱ የሌላውን ግንኙነትና ጠባይ እንዲቆጣጠር በህግ መብት መስጠቱ አስፈላጊ አልሆነም። አንዱ የሌላውን ግንኙነት መቆጣጠር ለጋብቻቸው ስምረት አስፈላጊ መሆኑ ከታመነበትም የህግ ድንጋጌ ሳያስፈልግ በእለት ተእለት ኑሮአቸው ቢተገበሩት የሚሻል ይመስላል። መቼም ቢሆን ሁሉንም ግንኙነታቸውን በህግ ደንግጎ ማስቀመጥ የሚቻልም ተገቢም አይደለም። በርግጥ "በሰዎች ህግ" መጽሃፍ ውስጥ አሳዳሪው አካለመጠን ላልደረሰ ሰው ግንኙነቱን እንደሚጠብቅ የአካልና የደብዳቤ ግንኙነቱን እንደሚቆጣጠርና ገደብ ሊያበጅ እንደሚችል ተመልክቷል።[70] የባልና ሚስት ግንኙነት ግን የአሳዳሪና አካለመጠን ያልደረሰ ሰው ዓይነት ግንኙነት ባለመሆኑ ተመሳሳይ ድንጋጌ አስፈላጊ አይደለም።

ተጋቢዎቹ የመረጡትን ሞያ ወይም ሥራ የማከናወን ጉዳይም ቢሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፤ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት እንዳለው በህገ-መንግስቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ[71] በጋብቻ ምክንያት የሌላውን ተጋቢ የሞያ ሥራን መቃወም በህገ መንግሥት የተረጋገጠን መሠረታዊ መብት የሚጻረር ስለሆነ የዚህ አንቀጽ በተሻሻለው ህግ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም።

ሚስቲቱ የቤት አያያዝ ሥራ እንድታከናውን የህግ ግዴታ መጣሉንም ቢሆን የቤት ውስጥ የሥራ ክፍፍልን ለተጋቢዎቹ መተው ሲገባ በህግ ለመወሰን መሞከሩ ተገቢ አይሆንም (It is too

[70] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 268
[71] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 41(1).(2)



Generated by CamScanner

domestic to be regulated by law):: ይልቁንም ሴቲቱ በማጀት ውስጥ አስሮ የሚያስቀራት እንዳይሆንም ያሰጋል:: በመሆኑም ቀደም ሲል ባልና ሚስቱ መከባበር መተጋገዝና መከባበር እንዳለባቸው የተገለጸ ስለሆነ ይህም የቤት ሥራውንም የሚመለከት በመሆኑ ተጨማሪ አንቀጽ ማካተት ሳያስፈልግ በቀድሞው ህግ የነበረው አንቀጽ ግን እንዲቀር ተደርጓል::

### 3.1 ጋብቻ በንብረት በኩል ስሚኖረው ውጤት

በአንዳንድ የሃይማኖት አባቶች እምነት ጋብቻ ተጋቢዎችን ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ንብረታቸውንና ገንዘባቸውንም የሚቀላቅል ተፈጥሮአዊና እምላካዊ ተግባር መሆኑን ያስምናብታል::[72] በዚህ እምነት መሠረትም ጋብቻ ሌላ ተጨማሪ ድርጊት ወይም ስርዓት ሳያስፈልገው በመፈጸሙ ብቻ የጋራ ንብረት ባለቤትነት ይፈጥራል ብለው ያምናሉ:: በአንዳንድ ባህሎችም ጋብቻ የአንደኛው ተጋቢን ንብረት ከሌላኛው ጋር የሚቀላቀልበት ሥርዓት ሲሆን ለዚህም መገለጫው ጋብቻቸው ሲፈጸም "ሀብትሽ ከሀብቴ" የሚለው መሃላ መሆኑን አብዛኛው የገጠር ነዋሪ የሚመራበት ሥርዓት እንደሆነ ያስገነዝባሉ:: በአንጻሩ በሌሎች ሃይማኖቶችና ባህሎች መሠረት ጋብቻ ተጋቢዎችን "አንድ ሥጋ" ያደርጋል እንጂ በንብረታቸው ላይ የሚያስከትለው ውጤት አይኖርም ንብረታቸውን በተመለከተ በጋብቻ ውል የሚገዛ ይሆናል ይላሉ::

[72] በቤተሰብ ህጉ ዙሪያ በተካሄዱት አውደ ጥናቶች ተሳታፊ የነበሩት የሃይማኖተ አባቶች በተለይም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሪዎች ይህንኑ ጉዳይ በአፅንኦት ሲገልጹ ይደመጡ ነበር::



በዚህ ረገድ ነባሩ ህግም ሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ከዚህ የተለየና የጋራ አቋም አላቸው:: ተጋቢዎቹ በጋብቻ ውላቸው ውስጥ "ከዚህ በፊት ያፈራነውም ሆነ ለወደፊቱ የምናፈራው ንብረት የጋራ ሃብታችን ይሆናል በሚል" ወይም በሌላ ተመሳሳይ አገላለጽ በጋራ ባለሀብትነት ካልፈጠሩ በቀር ባልና ሚስቱ ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሩአቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው ይቀጥላሉ::[73] ይህ ብቻም አይደለም ከተጋቡም በኋላ ቢሆን በውርስ ወይም በስጦታ መልክ ለግላቸው የተላለፈላቸው ንብረት ካለም የግላቸው ሆኖ ይቀጥላል:: ስለሆነም በሁኑ ዓይን ጋብቻ በመፈጸሙ ብቻ የጋራ ንብረትን ይፈጥራል የሚለው የአንዳንድ ሃይማኖቶችና ባህሎች አቋም የህግ መሠረት ያለው አይደለም:: ይህ አባባል የህግ መሠረት 'የሚኖረው በጋብቻ ውስጥ ለተፈጠሩ ንብረቶችና የእነዚህን ጉዳይ የሚመለከት የጋብቻ ውል በሌለበት ሁኔታ ነው:: ማለትም በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ ሆነውም የጋብቻ ውሉ በግል ባለሀብትነት እንዲቀጥሉ ተቀባይነት ያለው ድንጋጌ ካስቀመጠ የግል ሀብት ሆነው የሚቀጥሉበት እድል ይኖራል ማለት ነው::

የንብረት ጉዳይ የኢኮኖሚ ጉዳይ በመሆኑ በተጋቢዎች መካከል በተለይም በፍቺ ጊዜ ወይም አንደኛው ተጋቢ ሲሞት በወራሾችና በህይወት በቀረው ተጋቢ መካከል ከፍተኛው የውዝግብ ምንጭ እንደሆነ ይታወቃል:: ህጉ የታሰበውን ያህል ግልጽ

[73] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 647 እና የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 57 ለነገሩ በፍትህ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በነበረው ረቂቅ የቤተሰብ ህግም በአንቀጽ 64(1) ተመሳሳይ ድንጋጌ ነበር::

ለማድረግ የሚደረገው ጥረት /የቋንቋ ችግር ነው/ የማይሳካ መሆኑ አንድ ችግር ሆኖ፤ ተጋቢዎቹም ከሀገሩ ድንጋጌዎች ለማምለጥ የሚያደርጉት ጥረት ተጨምሮበት ጉዳዩን ውስብስብ እንደሚያደርገው ብዙ የፍርድ መዛግብት ይመሰክራሉ።

በተለይም ትዳር ሲመሠረት የእድሜ ልክ ጽምረት በመሆኑ ተጋቢዎች ለብዙ ዓሥርት ዓመታት በዚህ ህጋዊ ትስስር ሥር እንደሚኖሩ ይታወቃል። በዚህ ሂደትም የግል ንብረት ዓይነቱ የሚለወጥበት፤ ተሸጦ ሌላ የሚገዛበት፤ ብሎም ከጋራ ንብረት ጋር በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚቀላቀልበት እድል በጣም ሰፊ ነው። እንዲህ ሲሆን ምንም እንኳ የመጀመሪያው ንብረት የግል ከሆነ በዓይነት የተለወጠው ወይም ተሸጦ በሽያጭ የተገዛው የግል ስለመሆኑ የማያጠያይቅ ቢሆንም በጋብቻ ውስጥ ከተፈራ ንብረት ጋር የመቀላቀል እድሉ ስለሚኖር የግል እንዲባልለት የሚፈልገው ወገን ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብና ፍርድ ቤት ሊያጸድቀው ይገባል።[74] ይህ ካልሆነ ግን የኋለኛው ንብረት የጋራ የመሆን እድል ሊያጋጥም ይችላል። በነባሩ ህግም ቢሆን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ንብረቱ የግል ይባልልኝ የሚል ወገን ጥያቄውን ለቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ አስቀርቦ ማፀደቅ ይጠበቅበት እንደነበረ ማስታወስ ይገባል። በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤውን ሥልጣን የመቀነስ እርምጃ ስለተወሰደ ይህም ሃላፊነት ወደ ፍርድ ቤት እንዲዛወር ተደርጓል።

እላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በትዳርም ውስጥ ሆና የግል ሃብት ሊኖር እንደሚችል አይተናል። ይህም ሃብት ወይም

[74] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 58



ከጋብቻ በፊት የተፈራ ወይም በውርስ ወይም በስጦታ ለግል የተላለፈ በጋብቻ ውል የተገለለ ወይም በፍርድ ቤት እንዲገለል የተደረገ ሀብት ሊሆን ይችላል። እንዲህ ከሆነ እንግዲህ ሃብቱ እንዴት ይተዳደራል? የሚል ጥያቄ ቢነሣ አግባብነት አለው።

ኑሮው በትዳር ውስጥ ቢሆንም ሃብቱ የግል እስከሆነ ድረስ የሚተዳደረው በግል ይሆናል። ባለሀብቱ በዚሁ ሀብት አስተዳደር ሙሉ ነጻነት አለው።[75] ከዚህም አልፎ የዚህ ሃብት አስተዳደር በሙሉ ወይም በከፊል ሌላኛው ተጋቢ ያከናውን ዘንድ በጋብቻ ውል ማስተላለፍ ይቻላል።[76] በጋብቻ ውል ይህንኑ ሳያደርግ ቀርቶ ቢሆንም በትዳር ውስጥ እያሉ የግል ሃብቱን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት ሌላኛው ተጋቢ ውክልና መስጠት ይችላል።[77]

እዚህ ላይ ምናልባት ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 73 መሠረት "ባልና ሚስቱ ተጋብተው በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሚያደርጉአቸው ውሎች ፍርድ ቤት ካላፀደቃቸው በስተቀር ውጤት አይኖራቸውም" የሚል ተደንግጎ ይገኛል። ውክልና መስጠት ደግሞ ውል ነው፤ ውሉም እየተከናወነ ያለው በባልና ሚስቱ መካከል ነው። ስለዚህ በአንቀጽ 61 ያለው ውል በአንቀጽ 73 መሠረት የፍርድ ቤት የማፅደቅ እርምጃ ያስፈልገዋል ወይ? የሚል ይሆናል።

[75] (ገዚ ከማሁ አንቀጽ 59) ተጋቢው የማዘዝ መብት የሚኖረው በሃብቱ ላይ እንጂ በገቢው ላይ ግን አይደለም። ምክንያቱም ከግል ሃብትም ቢሆን የተገኘ ገቢ የጋራ መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 62(1) የተደነገገ ስለሆነ በገቢው ላይ የማዘዝ ስልጣን የጋራ መሆኑን ሊታወቅ ይገባል።
[76] ገዚ ከማሁ አንቃጽ 60



Generated by CamScanner

የውክልና ውል የራሱ የሆኑ ልዩ ባህርያት እንዳሉት ይታወቃል። ወካዩ ለተወካዩ ሰጥቶት የነበረውን ሥልጣን መልሶ መውሰድ ይችላል።[78] ተወካዩ በወካዩ ስምና ለወካዩ ጥቅም የሚሠራ ሲሆን ኃላፊነትም የሚያስከትል ድርጊት ቢፈጽም ከውክልና ሥልጣኑ እስካላለፈ ድረስ ወካዩ የሚጠየቅበት ይሆናል።[79] በመሆኑም ይህን የውክልና ውል ልዩ ባህርይ ግምት ውስጥ በማስገባት እንደልዩ ሁኔታ የፍርድ ቤት ይሁንታ ሳያስፈልገው በተጋቢዎቹ ስምምነት ብቻ የሚከናወን ይሆናል። በመሆኑም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 61 የህጉ አንቀጽ 73 ልዩ ሁኔታ ተደርጎ መውሰድ ይኖርበታል የሚል እምነት አለ።[80]

ቀደም ሲል እንደገለጽነው ጋብቻ በመፈጸሙ ብቻ የጋራ ባለሀብትነት እንደማይፈጥር ተገንዝበናል። ይህ ከሆነ ታዲያ የባልና የሚስት የጋራ ሀብት የሚባል ነገር አይኖርም ማለት ነውን? እንዲህ ከሆነም የትዳር ወጪዎች እንዴት ሊስተናገዱ ነው? ባልና ሚስቱን የሚያስተሳስር ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት የለም ማለት ነውን? ሊባል ይችላል።

በዚህ ረገድ ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 57 እና 58 ለመገንዘብ የምንችለው ነገር በትዳር ውስጥ የተፈሩ ሃብቶችና ለተጋቢዎች በጥቅሉ በውርስ ወይም በስጦታ የተሰጡአቸው

77 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 61
78 ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2183
79 ዝኒ ከማሁ ቁጥር 2189(1)
80 በርግጥ በ1995 በወጣው የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አዋጅ ሥር ውክልና በውል አዋዋይ ፊት ቀርቦ መከናወንና መረጋገጥ እንዳለበት የተደነገገ ስለሆነ ወደ ፍርድቤት መቅረብ ባያስፈልገውም ወካዩ ውል ክፍል ቀርቦ ውክልናውን መስጠት ግን አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።



ሃብቶች እንዲሁም የግል ሃብት ተሸጦ ወይም ተለውጦ የተገኘ ንብረት ሆኖ በፍርድ ቤት የግል እንዲሆን ያልተደረገ ሃብት ሁሉ የጋራ ሀብት ስለሚሆን ኢኮኖሚያዊ ትስስር ከሚፈጠርበት ህጋዊ መሠረቶች አንድ ክፍል ነው። ሌላው የኢኮኖሚ ትስስሩ መሠረት የሚሆነው ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው መሆኑ ነው።

እዚህ ላይ ህጉ በግል ጥረት /እውቀት/ እና በዚህ ጥረት ተመስርቶ በሚገኝ ገቢ መካከል ልዩነት ያደረገ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ በግል ንብረትና ከንብረቱ በሚገኝ ገቢ መካከል ልዩነት ፈጥሯል። እውቀቱ የግል ቢሆንም ከዚሁ የሚገኝ ደመወዝ ወይም ሌላ ገቢ ግን እሁንም የጋራ ነው።[81] በህጉ እምነት ከዚህ መሰሉ ምንጭ የሚገኙት ገቢዎች የጋራ ሃብት እንዲሆኑ ካልተደረገ ሌላው ይትርና የትዳር ወጪን ለመሸፈን እንኳ እንዳያስቸግር ስጋት አለ። እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው የሚለውንም ህጋዊ ግዴታ ማስፈጸም ያስቸግራል። በመጨረሻም በገቢው መፈጠር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሌላው ተጋቢም አስተዋጽኦ አለው ተብሎ ስለሚታመን ይህ ገቢ የጋራ ሀብት ማድረጉ አግባብ ነው ተብሎ ይታመናል።

81 የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 62(1)

በነባሩ የቤተሰብ ህግ "የባልና ሚስት ደመወዝና ገቢዎች የጋራ ሀብቶቻቸው ናቸው"::[82] የሚለው አገላለጽ በአንድ በኩል ደመወዝ ገቢ እንዳልሆነ አስመስሎ የሚያቀርብ በመሆኑ በሌላም በኩል ገቢው ከግል ወይስ ከጋራ ንብረት ወይስ ከሁለቱም የተገኘ ገቢ የሚለውንም በግልጽ የማያመለክትና ለተለያዩ ትርጉም የተጋለጠ ስለነበር የተሻለ ግልጽነት በሚያሣይ አገላለጽ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 62/1/ ማስቀመጥ አስፈልጓል::

ሌላው ስለ ጋራ ንብረት ሲነሣ መወሳት ያለበት ጉዳይ ንብረቱ የጋራ ሆኖ የተመዘገበው በአንደኛው ተጋቢ ስም ከሆነ ውጤቱ ምን እንደሚሆን የመወሰን ጉዳይ ነው:: አንዳንድ ንብረቶች በተለይም እንደቤትና መኪና የመሳሰሉት ንብረቶች ባለቤትነት የሚረጋገጠው በይዞታ ምስክር ወረቀት ወይም ባለቤትነት የምስክር ወረቀት መሆኑ ይታወቃል:: የሚያጋጥመው ችግር ግን ንብረቱ በትዳር ውስጥ የተፈራ ሆኖ ምዝገባው ግን በአንደኛው ተጋቢ ስም የተዘጋጀ ይሆናል:: በኢትዮጵያችን ተጨባጭ ሁኔታም ብዙውን ጊዜ የጋራ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ማዘጋጀትና ማውጣት የተለመደ አይደለም:: ይህ ጉዳይ ስሙ ያልተመዘገበውን የጋራ ባለሀብት መብት አልፎ አልፎ የሚያጣብብ ሆኖ ስለተገኘ[83] በዚህ ረገድ ግልጽ የህግ ድንጋጌ ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል::

---

[82] ፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 562(1)

[83] በአንድ ወቅት የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 947/74 ታህሳስ 15 ቀን 1975 በሰጠው ውሳኔ የባለቤት መታወቂያ ደብተሩ (ሊብሬ) በአንደኛው ተጋቢ ስም ከሆነ ሌላኛው ተዋዋይ ወገን ሌላኛው ተጋቢ የጋራ ባለቤት ነው ብሎ መገመት የለበትም፤ መኪናው በባልና ሚስቱ ስም አይደለምና የሚል አቋም ይዞ ነበር:: (የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ



በመሆኑም በህጉ ግምት "አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳ የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል" የሚል ድንጋጌ ሰፍሮ እናገኛለን:: ስለዚህም የአስተዳደር አካሉ ከሚሰጠው የባለቤትነት ወይም የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ይልቅ በዚህ ረገድ የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎች የበላይነት እንዳላቸው መገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል::

ገቢ ማለት ደመወዝም ሆነ ሌላ፤ ከግል ንብረት የመነጨም ሆነ ከጋራ የጋራ ሃብት መሆኑን እላይ ተመልክተናል:: ሆኖም አስተዳደሩን ማለትም አቀባበሉም ሆነ አቀማመጡ የገቢው ምንጭ የሆነው ወገን በመሰለው መንገድ የሚወስነው ይሆናል:: ቢሆንም ሌላኛው ወገን ሲጠይቅ የተገኘው የገቢ መጠንና የተቀመጠበት ሁኔታ የማስታወቅ ግዴታ ግን ይኖርበታል:: በርግጥ በብዙዎቻችን አልተለመደም እንጂ አንዳንዶቹ ባልና ሚስት የጋራ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ገቢያቸውን የሚያስቀምጡበትና የሚያንቀሳቅሱበት ሁኔታ አለ:: ህጉም ይህ ዓይነት አሠራር ለማበረታት በአንቀጽ 64(2) ሥር ጠቀስ አድርጎ አልፏታል::

በመርህ ደረጃ ገቢውን የሚቀበለው የገቢው ምንጭ የሆነው ወገን ነው ቢባልም በልዩ ሁኔታ ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበለው ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል:: እንዲህ ዓይነቱ ሥልጣንም ከውል ወይም ከፍርድ ቤት ውሣኔ ሊመነጭ ይችላል::

---

ቤቶች ምርጥ ፍርዶች የፍትሐብሄር ጉዳዮች አንደኛ መጽሐፍ ገጽ 128-135 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋኩልቲ መጋቢት 1992 ይመልከቱ::)



Generated by CamScanner

አንደኛው ተጋቢ ለእርሱ መክፈል የነበረበት ገቢ ለሌላኛው ተጋቢ እንዲሰጥለት ውክልና ሲሰጠው ይህንኑ ተፈጻሚ ይሆናል። ሌላው ከተጋቢዎቹ አንዱ ገቢውን ከተቀበለ በኋላ ለትዳር በሚያገለግል መልኩ የማይጠቀምበት ከሆነና የአባካኝነት ልምድ የሚታይበት ከሆነ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሌላኛው ተጋቢ ገቢውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲቀበል የሚታዘዝበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል:: በመጨረሻም ገቢው በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከበር ትእዛዝ ሊሰጥበት የሚቻል መሆኑን መገንዘቡ ይገባል:: ይህ ሲባል ግን በሌላ ህግ መከበር የሌለባቸው ገቢዎችና ንብረቶች የተመለከተ ስለሆነ ውሳኔው ይህንኑ ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል::[84] ለምሣሌ የጡረታ አበል ሊከበር እንደማይቻል በጡረታና በሌሎች ህጎች የተመለከተ ሲሆን በፍትሀብሄር ሥነ-ሥርዓት ህጉም ውስጥ ሊከበሩ የማይችሉ የንብረት ዓይነቶችና የደመወዝ መጠን ተመልክቷል::[85] ሌሎች የህግ ዘርፎችን ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ሆነው ቢገኙ በዚህ ጉዳይ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ግምት ውስጥ እንዲገቡ ይጠበቃል::

በዚህ ህግ ከነባሩ የቤተሰብ ህግ በተለየ ሁኔታ አቋም የተወሰደበት ሌላው ጉዳይ በተሻሻለው ህጉ አንቀጽ 66 የተመለከተው ነው:: በቀድሞው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 656/1/ መሠረት የተጋቢዎቹ የጋራ ሃብት የሚያስተዳድረው ባልየው እንደሆነ ተደንግጎ እንደነበር አይዘነጋም:: ቀደም ሲል 'ባል የቤተ

[84] የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 59 የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር አንቀጽ 9 ለምሣሌነት መግለጽ ይበቃል



ዘመድ ሹም ነው' ይል ለነበረው ድንጋጌ በሰጠነው ትችት ላይ እንደተመለከተው ይኸኛውም አንቀጽ የወንዱን የበላይነት ይንጸባርቁባቸው ነበር ከሚባሉት ድንጋጌዎች አንዱ ነው:: ህገ መንግሥቱ ተጋቢዎች በትዳር ዘመናቸው እኩል መብት ይኖራቸዋል ስለሚልና[86] ሴቶች ንብረት በማስተዳደር ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው[87] በማለት በግልጽ የደነገገ ስለሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ህጉ ከህገ መንግስቱ ጋር በተጣጣመ መንገድ መቀረፅ ስለሚኖርበት "ባልና ሚስቱ የጋራ ሃብታቸውን በጋራ ያስተዳድራሉ" የሚል ድንጋጌ ተቀምጦላቸዋል::[88] በርግጥ የጋራ ሀብቱን አስተዳደር በውል ለአንደኛው ወገን ሊሰጥ ይችላል:: ያም ቢሆንም ግን ሌላኛው ወገን በጠየቀ ቁጥር ስለሃብቱ አስተዳደር መረጃ የመስጠት ግዴታ እንዲጣልበት ተደርጓል::

የጋራ ንብረቶችን በጋራ የማስተዳደር መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ ንብረቶቹን ለሌላ ሦስተኛ ወገኖች የማስተላለፍ ወይም ሦስተኛ ወገኖች በጋራ ንብረቱ ላይ መብት እንዲኖራቸው የማድረግ ጉዳይ ሲነሣ ግን የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ መሆኑ በአንቀጽ 68 ተመልክቶ ይገኛል:: ሆኖም በአንዳንድ የህግ ዘርፎች ልዩ ሁኔታና ድንጋጌ እንደሚኖር በመገንዘብ "በሌላ ህግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በቀር" የሚል ሃረግ እንዲካተትበት ተደርጓል:: ይህም ሲባል ሌላ ህግ የተጋቢዎች ስምምነት አላስፈላጊ የሚያደርገው ሲሆን ይህንኑ ተፈጻሚ ማድረግ ይገባል ማለት ነው:: በዚህ ረገድ እንደ ምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ በንግድ ህጋችን መሠረት "ባል

[85] የፍትሐብሀር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 404
[86] ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34(1)
[87] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 35(7)

ወይም ሚስት ካልተቃወመ በቀር ያላገባ ሰው የንግድ ሥራ ለመስራት እንደሚችለው ሁሉ ያገባም ሰው የንግድ ሥራ መሥራት ይችላል" ስለሚልና እንደዚህ ያለው መቃወም በንግድ መዝገብ ካልገባ በቀር ሦስተኛ ወገኖችን መቃወሚያ ሊሆን አይችልም" ተብሎ የተደነገገ ስለሆነ አንቀጽ - 68 በዚህ ረገድ ባዝ ነገሮች ላይ የሚኖረው ጫና በጣም ውሱን መሆኑን ያሳያል::[88]

የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት እንዲኖር የሚጠይቅ የህግ ድንጋጌ በነባሩ የቤተሰብ ህግም በአንቀጽ 658 ተመልክቶ እንደነበር አይዘነጋም:: ዋነኛ ዓላማውም የጋራ የሆነውን ንብረት ከተጋቢዎች አንዱ ያለ ሌላኛው ፈቃድ በፈለገው መጠንና ጊዜ ለሌሎች ሦስተኛ ወገኖች አሳልፎ እንዳይሰጥ ወይም መብት እንዲያገኙ እንዳያደርግ ለመከላከል ይመስላል:: ሆኖም ይህ ድንጋጌ ካልተከበረ ውጤቱ ምን እንደሚሆን በነባሩ ህግ ያልተመለከተ ስለነበር ለተለያዩ የፍርድ ውጤቶች ምክንያት ሆኖ ቆይቶአል::[89]

በአንድ ወቅት በዚህ ጉዳይ ውሳኔ እንዲሰጥ ጥያቄ የተረበለት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፓነል ችሎት ዳኞችን አራት መስመር ላይ እንደከፈላቸው[90] ነባር የፍርድ መዛግብት

[88] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 66(1)
[89] በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የንግድ ህግ ከአንቀጽ 16 እስከ 21 ድረስ ማየትና ከቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎች ጋር አዛምዶ መመልከቱ ጠቃሚነት ይኖረዋል::

[90] ይግባኝ ባይ አበባ ገ/መድህንና፲ መልስ ሰጭ ተስፋዬ ኪዳኔ በሚል የተከፈተው የፍ.ይ.መ.ቁ. 367/74 በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፓነል ችሎት



ያከረዳለ:: ጉዳዩ ባጭሩ እንዲህ ነው:: ባል የጋራ ንብረት የሆነውን የቤት አውቶሞቢል በብር 20,000 ሽጦ ገንዘቡን ከተቀበለ በኋላ መኪናውንና የባለቤትነት ማስረጃውን ለገዢው ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት ክስ ያቀርባል:: ሻጭ ካቀረባቸው መከላከያዎች አንዱ 'ባለቤቴ እኔ ሳላውቅ ለምን የሽያጭ ውል ፈፀምክ?' በማለት ተቃውማኝ በትዳሬ ላይ ከባድ ችግር ያስከተለብኝ በመሆኑ ውሉን መፈጸም አልቻልኩም የሚል ነበር:: የሻጭ ሚስትም ጣልቃ ለመግባት ጠይቃ ተፈቅዶላት ባቀረበችው ማመልከቻ መኪናው የባልና ሚስት የጋራ ሀብትና ለቤተሰብ አገልግሎት ብቻ እንዲውል የተገዛ በመሆኑ ያለ እኔ ፈቃድ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል የተደረገው ውል በፍትሐብሔር ቁጥር 658 የተደነገገውን የሚቃረን በመሆኑ ውሉ ውድቅ ነው ይባልልኝ በማለት ክርክሯን አቀረበች:: ገዥውም ለዚሁ በሰጠው መልስ ሻጭ በንግድ ሚኒስቴር የተመዘገበ ነጋዴ በመሆኑ እስተድሞ ሌሎች መኪናዎች ሲገዛ ወይም ሲሸጥ ባለቤቱ በመስማማት የፈቀደችበት ጊዜ የለም:: አሁን ያቀረበችው ተቃውሞ በሻጩ አነሳሽነት ሽያጩን ለማሰናከል በመሆኑ ተቃውሞዋን ፍርድ ቤት ሊቀበላት አይገባም ሲል አጥብቆ ተከራከረ::

ጉዳዩ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ "ለተባለው መኪና በተናጠል በባለንብረትነት የተመዘገበው ሻጭ ብቻ ስለሆኑ የባለቤት ንብረት መተውቂያው የሁለት ወይንም ከዚያ በላይ የሆነ የጋራ ባለመብትነትን

የሰጠው ውሳኔ ይመልከቱ:: (የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድቤቶች ምርጥ ፍርዶች የፍትሀብሔር ጉዳዮች አንደኛ መጽሐፍ ገጽ 82-85)



Generated by CamScanner

የሚረጋገጥ እስካልሆነ ድረስ አንድን ንብረት የሚገዛ ሰው በንብረቱ ላይ መብት ያለው ሌላ ሰው ስለመኖሩ የሚያውቅበት መንገድ የለውም:: ንብረቱ በሻጩ ስም ብቻ ተመዝግቦ ከተገኘ ገዥው ምናልባት ሚስት ይኖረው ይሆናል ወይም የጋራ ንብረት ይሆናል ብሎ ከመንደር መንደር እየዞረ የመጠየቅና የማጣራት ግዴታ የለበትም:: የተጠቀሰውም የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 658 ይህን ግዴታ አይጥልበትም" በማለት የሚስትን ተቃውሞ ውድቅ ያደርገዋል::

በዚህ ውሳኔ ላይ ሚስት ይግባኝ ታቀርባለች ይግባኙን የመረመረው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ ችሎት በአንድ በኩል "ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ያላቸውን የጋራ ሃብት ባል ሚስቱ ሳትስማማ ሊሸጥ ሊለውጥ ወይም ሊሰጥ ሊያስተላልፍ እንደማይችል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 658 ተደንግጓል:: የዚህ ድንጋጌ ዓላማ አንደኛው ተጋቢ ወገን ሌላው ወገን ሳያውቅ በሚፈጽመው ተግባር ምክንያት ትዳራቸው እንዳይፈርስ ለማድረግ ጭምር ነው:: በዚህ መሠረት ሚስት ሳታውቅ ባሏ የፈጸመውን ውል እንዲፈርስላት መጠየቅ ትችላለች:: በዚህ ጉዳይም መኪናው የተሸጠው ሳትስማማ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስላት ለመጠየቅ መብት አላት" የሚል ነው:: ሌላኛው የዳኞች ወገን ደግሞ "በመሠረቱ አንደኛው ተጋቢ ወገን ሌላኛው ወገን ሳያውቅ የፈጸመው ውል መቃወሚያ ሊያቀርብበት የሚችል መሆኑን አምኖ በተያዘው ጉዳይ ላይ ግን የመኪና ሽያጩ ውል ሚስት ሳታውቅ የተደረገ ነው የሚያሰኝ ባለመሆኑ ጥያቄውን ሚስት ሳታውቅ የሚያስመሰክር አቋም ወሰዷ:: እንደማይቀበል



የአብልጫው ድምፅ አቋም ደግሞ ከዚህ ለየት ያለ ነበር "ሚስት ያለእኔ ፈቃድ የጋራ ንብረታችን የሸጠው ከህግ ውጭ ነው በማለት በከፍተኛ ፍ/ቤት ተቃውሞ ያቀረበችው ባሏ በውሉ መሠረት መፈጸም አይገባኝም በማለት በሚከራከርበት ጊዜ ሲሆን ለመቃወም ያነሳሳት ምክንያት ምን እንደሆነ ተጠይቃ በሰጠችው መልስ በዋጋ የተጎዱ መሆናቸውን ገልጻለች:: የመኪና ሽያጭ ዋጋ በአንድ ወቅት ገቅ በአንድ ወቅት ከፍ እንደሚል የታወቀ ነው:: በዝቅተኛ ዋጋ ከተሸጠ በኋላ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የገበያው ዋጋ ከፍ ሲል ባል ሚስቱን እየቀሰቀሰ ሽያጩ እንዲፈርስ ካደረገ በቅን ልቦና ላይ የተመሠረተ የንግድ ልውውጥ ዋስትና አይኖረውም::" በማለት ጥያቄውን ውድቅ አደረገው:: በመሠረቱ ከዚህ ውሳኔ ጋር ተስማምቶ በምክንያት የተለየው ሌላ የዳኞች ወገንም እንዲህ "አንድ ውል እንዲፈርስ የሚጠየቅባቸው ምክንያቶች፣ ማን መጠየቅ እንደሚችል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1808 በዝርዝር ተገልጧል:: በቁጥር 658 የተጠቀሰው ሁኔታ ውልን ለማፍረስ ያስችላል ተብሎ በቁጥር 1808 በተጠቀሱት ምክንያቶች በአንዱ ሥር እንኳ የሚመደብ አይደለም:: ቁጥር 658 የሚገኘው በፍትሐብሔር ህጉ በሁለተኛው መጽሐፍ ጋብቻን በሚመለከተው ክፍል ነው:: በዚህ ድንጋጌ ሥር የተጠቀሱትን ተግባራት ለመፈጸም የሁለቱ ወገኖች ስምምነት እንደሚያስፈልግ ተገልጧል:: የዚህ ድንጋጌ ዓላማ፣ ውጤት በሁለቱ ወገኖች መካከል ሊኖረው የሚገባውን የሥልጣን ክልል የሚወስን ነው:: የድንጋጌው ተፈጻሚነት በሁለቱ ወገኖች መካከል እንጂ የሦስተኛ ወገኖችን መብት የሚነካ አይደለም::



Generated by CamScanner

የድንጋጌው ውጤት በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 686 በግልጥ ተጠቅሷል፡፡ ይኸውም አንደኛው ተጋቢ ወገን በቁጥር 658 የተጣለበትን የሥልጣን ገደብ ተላልፎ የጋራ ንብረትን የሚጎዳ ተግባር ፈፅሞ ቢገኝ የጋብቻው ግንኙነት በሚቋረጥበት ጊዜ በካሣ ተጠያቂ መሆኑ ነው፡፡

በቁጥር 685(ለ) የተጻፈው ድንጋጌ በምንም ዓይነት አንዱ ተጋቢ ወገን ከሶስተኛ ወገን ጋር ያደረገው ውል ለማፍረስ ምክንያት አይሆንም፡፡ሕርቃቂው ክፍል ይህን ድንጋጌ ከህጉ ውስጥ ያስገባው የውል ማፍረሻ ምክንያት እንዲሆን አስቦና አቅዶ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ አንዱ ተጋቢ ወገን ከሶስተኛ ሰው ጋር ያደረገው ውል ይህ ንዑስ አንቀጽ እየተጠቀሰ በሌላኛው ተጋቢ ውሉ እንዲፈርስ የሚጠይቅና ፍርድ ቤቶችም ይህን ጥያቄ የሚቀበሉ ቢሆን የሽያጭንና የንግድ ልውውጥን የሚመለከቱ፤ውሎች እንዳችም ዋስትና አይኖራቸውም፡፡ በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1161 መሠረት ዋጋ ከፍሎ በቅን ልቦና ባለይዞታ የሆነ ሰው ንብረቱን ያስተላለፈለት ሰው መብት ባይኖረውም ከሀብትነት አይነቀልም ተብሎ የተደነገገው ህጉ የባለ ሃብትነት መብት የሌለው ሰው በሽያጭ ለሌላ ሰው አስተላልፎ ገኘው ዋጋውን ከከፈለና የንብረቱ ባለይዞታ ከሆነ ቅን ልቦና የለውም ካልተባለ በቀር ሀብትነቱን አይነቀልም እያለ የንብረቱ የጋራ ባላሀብትና አስተዳዳሪ የሆነው ባለቤት ዋጋ ተቀብሎ ለሶስተኛ ሰው በሽያጭ ያስተላለፈው ንብረት ውሉ ፈርሶ ንብረቱ ተመላሽ ይሆናል ለማለት እንዴት ይችላል? በማለት በአንክሮ ይጠይቃል፡፡ይህም ለብዙ ነገሮች ቀዳዳ የሚከፍትና የህጉን ዓላማ የሚያደናቅፍ ነው" በሚል የውል ማፍረሻ ምክንያት ሊሆን እንደማይገባ ደምድሟል፡ ፡



በፍትሐብሄር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 832/75 እንዲሁ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፓነል ችሎት በተመሳሳይ መልኩ በዳኞች መካከል የሃሣብ ልዩነት ተከስቷል፡፡[91] በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ አንድ ዓይነት አተረጓጎም በሌለበት ሁኔታ በበታች ፍርድ ቤቶች ደረጃ ጉዳዩ ምን ያህል ከባድና ውስብስብ እንደሚሆን መገመት የሚከብድ አይመስልም፡፡

ስለሆነም የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ችግሩን በባንዱ ወይም በሌላ መልክ መፍትሄ ሰጥቶ ማለፍ እንዳለበት በማመን ውጤቱን አስመልክቶ ግልጽ የህግ ድንጋጌ አስቀምጦ ይገኛል፡፡

ለችግሩ መፍትሄ በመስጠት ረገድ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ሁለት ጥቅሞቹን (intersts) ለማስታረቅ ጥረት አድርጓል፡፡ በአንድ በኩል የተጋቢዎች የጋራ ንብረት በተቻለ መጠን በተጋቢዎች የጋራ ውሳኔ ብቻ እጅ መቀየር እንዳለበት የማድረግ ፍላጎት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሽያጭና የንግድ ልውውጥን ዋስትና የመስጠት አስፈላጊነት (security or transaction) ጉዳይ ነው፡፡

በዚህም መሠረት አንደኛው ተጋቢ የሌላኛው ተጋቢ ፈቃድ ሳይቀበል በህጉ በአንቀጽ 68 ከተመለከቱት ድርጊቶች አንዱ ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ፈቃዱ ያልሰጠው ተጋቢ ውሉ እንዲፈርስ ፍርድ ቤትን የመጠየቅ መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡[92] ከዚህ አንፃር ይህ ድንጋጌ በአጠቃላይ የውል መጽሐፍ ከተመለከቱት የውል ማፍረሻ ምክንያቶች እንደተጨማሪ ምክንየት ሆኖ ያገለግላል ማለት

[91] አላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 83 ተመልክቷል
[92] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 69(1)



Generated by CamScanner

ነው:: በሌላ በኩል ግን ፈቃዱ ያልሰጠው ወገን ይህንን መብት ባልተወሰነ ጊዜ እንዲሠራበት መፍቀድ የንግድ ልውውጥን ዋስትና የሚፃረን መሆኑን በመገንዘብ በጊዜ ገድቦ ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል:: ስለሆነም ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ ግዴታው መገባቱን ባወቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ግን ግዴታው ከተገባ ሁለት ዓመት ካለፈው መጠየቅ እንደማይቻል ተመልክቷል::[93] በዚህ ዓይነት አቀራረጽ አላይ የተመለከቱትን ሁለት ጥቅሞች ለመጠበቅ ጥረት ተደርጓል የሚል እምነት አለ::

ቀደም ሲል ባልና ሚስቱ በጋብቻቸው ዘመንም ቢሆን የግል ንብረት ይዘው ሊቀጥሉ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ ተመልክተናል:: በመሆኑም ይህ የግል ንብረት ገቢ የሚያመነጨውን ያህል እዳም ሊያመጣ ይችላል:: የተጋቢዎቹ የግል ጥፋቶችም ቢሆኑ የዕዳና የኃላፊነት ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ ለትዳሩ አጠቃላይ ጥቅም ሲባል የሚገቡ እዳዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በነባሩ ህግ መሠረት እነዚህ እዳዎች በአከፋፈላቸው ላይ ልዩነት አልነበረም:: ሁለቱም እዳዎች ከተጋቢዎቹ የግል ሀብት ላይ ወይም ከጋራ ንብረታቸው ላይ ሊጠየቅ እንደሚቻል ተመልክቶ ነበር::[94] ይህ ዓይነት መፍትሄ አግባብ አይደለም፤ የግል እዳ እንዴት ከጋራ ሃብት እንዲከፈል ይደረጋል የሚልና የመሳሰሉ ጥያቄዎች አልፎ አልፎ

[93] ገጽ ከማሁ አንቀጽ 69(2)
[94] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 659



ሲነሡ ቆይተዋል::[95] ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ይመስላል ቀደም ሲል የፍትህ ሚኒስቴር ባዘጋጀው ረቂቅ የቤተሰብ ህግ ላይ በአንቀጽ 74 በሚከተለው መልክ ተቀርጾ ነበር:: "ከባልና ከሚስት ከአንደኛው የሚጠየቀው እዳ ከግል ሀብት ላይ ሊጠየቅ ይችላል፤ የግል ሀብት በማይኖርበት ጊዜ ዕዳው ከባለእዳው ድርሻ ከጋራ ሃብታቸው" ሊጠየቅ ይችላል ይል ነበር::[96] (ሠረዝ የተጨመረ)

ሆኖም ይህ መፍትሄ የአፈጻጸም ችግር የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ የዕንስ ሃሣብ ችግርም ሳይኖርበት አይቀርም:: ምክንያቱም የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ጋብቻው እስካልፈረሰ

[95] የቤተሰብ ህጉን ለመሻሻል ሲታሰብ ሃሳቦች ለማሰባሰብ እንዲረዳ በተደረጉ ተከታታይ አውደጥናቶች እንዲህ ዓይነት ሃሣቦች በተደጋጋሚ ሲቀርቡ ነበር:: በተለይም በኢትዮጵያችን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ወንዱ ከተለያየ የወንጀልም ሆነ የፍትሐብሔር ጥፋቶች በመነጨ የግል እዳ ይዞ እየመጣ የጋራ ሃብቱ ለእዳው መክፈያነት የሚውል ከሆነ የሌላኛው ተጋቢ ጥቅም ይጎዳል በሚል ጠንካራ ክርክር ሲቀርብ ነበር:: በምሳሌነትም የሚከተለው ጉዳይ ቀርቦ ነበር:: ባል የመንግስት ሠራተኛ ነው፤ በሥራው አጋጣሚ ያገኘውን የመንግስት ገንዘብ ይመዘብራል:: በዚህ ገንዘብ ምክንያትም አኗኗሩና ጠባዩም ይለወጣል፤ ሌላ ሴትም ይለምዳል:: የትዳር ኑሮውም ይደፈርሳል:: በስተመጨረሻ ግን የምዝበራው ጉዳይ ይደረስበትና በወንጀል ተከሶ ይፈረድበታል:: ከእስራት በተጨማሪ የመዘበረው የመንግስት ገንዘብ እንዲመልስ ይፈረድበታል:: በዚህ ወቅት ባል የግል ንብረት ከሌለው ወይም የግል ንብረቱ ለእዳ መክፈያው በቂ ካልሆነ የጋራ ሃብታቸው ለእዳ መክፈያ ሊውል ነው ማለት ነው:: ሚስት ከምዝበራው ያገኘችው ጥቅም ሳይኖር ይልቁንም ምዝበራው ትዳርዋን እንዲፈረስባት እየታወቀ ይባስ ብሎ እዳው ከጋራ ሃብትሽ ተቀንሶ ይከፈል ማለቱ ፍትሐዊ አይደለም በሚል ስሜት በሚነካ አቀራረብ መልክ ቀርቦ ነበር::
[96] የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ባፀደቀው የክልሉ የቤተሰብ ህግም በአንቀጽ 97(1) ሥር ተመሳሳይ ድንጋጌ ይገኛል:: እንደሚከተለውም ይነበባል:: "ከባልና ሚስት ከአንደኛው የሚጠየቀው እዳ ከባለእዳው የግል ሃብት ተቀንሶ ይከፈላል:: የግል ሃብቱ እዳውን ለመክፈል በቂ ካለልሆነ ከጋራ ንብረቱ የባለእዳው ድርሻ ተቀንሶ ዕዳው እንዲከፈል ይደረጋል::" (ሠረዝ የተጨመረ)



Generated by CamScanner

ድረስ አንድ ሃብት (single patrimony) ስለሆነ የያንዳንዱ ድርሻ በእርግጠኝነት የሚታወቅበት ሁኔታ የለም። በሌላም በኩል ድርሻቸው ይታወቃል ቢባል እንኳ ከድርሻው ለእዳው ከተከፈለ በኋላ ትዳሩ እስከልፈረሰ ድረስ በቀሪው ንብረት ላይ የጋራ ባለሀብትነቱ ስለሚቀጥል ዞሮ ዞሮ ከጋራ ሀብት የተከፈለ ያህል ነው። በመሆኑም ይህ መፍትሄ የእዳ ጠያቂ ሦስተኛ ወገኖች መብትና ጥቅም የሚያጣብብ ብቻ ሳይሆን ጋብቻውንም የማፍረስ አደጋ ሊጋርጥ ስለሚችል በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ተመራጭ ሆኖ አልተገኘም።

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ተቀባይነት ያገኘው መፍትሄ በመርህ ደረጃ በግል የሚጠየቅ እዳ ከባለእዳው የግል ሃብትና ለትዳር ጥቅም የመጣ እዳ ደግሞ ከጋራ ሃብት መከፈል ያለባቸው ሲሆን የግል ሃብቱ በቂ በማይሆንበት ጊዜ የግል እዳውም ቢሆን ከጋራ ሃብት እንዲከፈል በአንፃሩም ለትዳር ጥቅም የመጣ እዳ ሆኖ የጋራ ሃብቱ ለእዳ መክፈያነት በቂ ሳይሆን ሲቀር ከተጋቢዎች ቱየግል ሃብትም ቢሆን ሊከፈል እንደሚገባ ተደንግጓል።[97] እንዲህ ሲሆን የእዳ ጠያቂዎች መብትም ሰፋ ያለ ይሆናል። ተጋቢዎችም በትዳር ዘመናቸው መረዳዳትና መተጋገዝ እንደየአቅማቸው አስተዋጽኦ ማድረግ ይገባቸዋል የሚለውንም መርህ የሚያጠናክር ይሆናል።

[97] የተሻሻለው ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 70



በርግጥ የግል እዳ ከጋራ ሀብት ከተከፈለ በኋላ ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰ በንብረት ክፍፍሉ ጊዜ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ከጋራ ሃብቱ ለእዳው የተከፈለውን መጠን የሌላውን ወገን ድርሻ ከባለእዳው ድርሻ በካሣ መልክ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብት ማመቻቸት ይገባ ይሆናል። ይህም በተሻሻለው ህግ በአንቀጽ 87 በተመለከተው ሥር ይወድቅ ይሆናል የሚል እምነት አለ።

## ምዕራፍ 4 - ስለ ጋብቻ መፍረስና ውጤቶቹ

### 4.4 ጠቅላላ

ጋብቻ ሲፈጸም በህግ የተደነገገ ሥርዓት መከተል ያለበትን ያህል ሲፈርስም ህጋዊ ሥርዓት ተከትሎ ሊሆን ይገባዋል። በመሠረቱ ጋብቻ ሲፈፀም እስከ እለተ ሞት ድረስ በዚሁ ግንኙነት ተሳስሮ ለመቀጠል በማሰብ ነው ተብሎ ይታመናል። ከሌሎች የውል ግንኙነቶች (contractual relations) የሚለየውም አንዱ ይህ ነው። እንዲያውም በአንዳንድ ሃይማኖቶች አመለካከት ትዳር በሞትም ቢሆን አይፈርስም። በህይወት የቀረው ተጋቢ ሟቹን እያሰበ በምናኔ ወይም በምንኩስና ቀሪው እድሜውን ለመግፋት ይወስናል እንጂ ሌላ ትዳር አይመሰረትም የፊተኛው እንዳልፈረሰ ይታመናል።

ይህ ዓይነት እምነትና አመለካከት እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ ዓይን ግን የአንደኛው ተጋቢ ሞት ለጋብቻው መፍረሻ በቂ ምክንያት



Generated by CamScanner

ተደርጎ ይወሰዳል::[98] ሞት ብቻ ግን አይደለም ለትዳር መፍረስ እንደ ብቸኛ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው፤ ከሞት በመለስ በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥም ጋብቻ ይፈርሳል::[99]

የመጥፋት ውሳኔ የሚሰጠው በፍርድ ቤት ሲሆን አንድ ሰው የጠፋና ከሁለት ዓመት ወዲህ ወሬውን ያልሰጠና ያልተገኘ እንደሆነ በባለጉዳዮች አመላካችነት ፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ እንደሚያስተላልፍ ይታወቃል::[100] ብዙውን ጊዜ ፍርድቤቶች ውሳኔውን የሚሰጡት የሰውየው መጥፋት የሞተ የሚመስል ሆኖ የሚያሳይ መረጃ ሲቀርብላቸው ነው::[101] ይህ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው በትዳር ውስጥ የነበረ ሰው ከሆነ በጋብቻው ላይ ስለሚኖረው ውጤት በነባሩ ህግ ግልጽ አልነበረም::

"ስለሰዎች" በሚለው መጽሐፍ በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 163(1) መሠረት "ከተጋቢዎች አንዱ የጠፉ እንደሆነ የመጥፋቱ ማስታወቅ ፍርድ የመጨረሻ በሆነበት ቀን ጋብቻው እንደሚፈርስ" ተደንግጎአል:: በአንጻሩ "ስለቤተዘመድና ስለውርስ" በሚለው መጽሐፍ ደግሞ በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 670(ለ) መሠረት ከባልና ከሚስት ያንደኛው ከአገር መጥፋት በፍርድ ውሳኔ ተገልጾ እንደሆነ ለፍቺ መጠየቂያ እንደከባድ ምክንያት እንደሚቆጠር ተመልክቶ ይገኝ ነበር:: በመሆኑም በህግ ባለሙያዎች አካባቢ የመጥፋት ውሳኔ መስጠቱ በቁጥር 163(1) መሠረ የጋብቻ ማፍረሻ

[98] የፍትሐ ብሄር ህግ ቁጥር 663(1) እና የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 75(ሀ)
[99] ዝኒ ከማሁ 75(ሀ)
[100] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 154(1)
[101] ዝዝኒ ከማሁ 157 (1)



ምክንያት ነው? ወይስ በቁጥር 670(ለ) መሠረት ለፍቺ መጠየቂያ ምክንያት ነው? በሚለው ጭብጥ ላይ አንድ ወጥ አቋም አልነበረም"::

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ይህንን ውዥንብር በሚያስወግድ መልክ ለመትረጽ ጥረት ተደርጓል:: ስለሆነም በተሻሻለው ህግ በአንቀጽ 75(ሀ) ከተጋቢዎች በአንዱ ላይ በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ መስጠት ለጋብቻ መፍረስ እንደ አንድ ምክንያት ተደርጎ ተቀምጧል:: ይህም ማለት በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ መስጠቱ ተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት ሳያስፈልገው ጋብቻውን ቀሪ ለማስደረግ እንደበቂ ምክንያት ተወስዷል ማለት ነው:: በመሆኑም በአሁኑ የህጉ አቀራረጽ የመጥፋት ውሳኔ መስጠቱ ለፍቺ ምክንያት ሳይሆን ራሱን የቻለ የጋብቻ ማፍረሻ ምክንያት ሆኖ ቀርቧል ምክንያቱም ጠፋ የተባለ ሰው ጠባብ የመመለስ እድል ቢኖረውም በህጉ ዓይን የጠፋ ሰው ከሞላ ጎደል የሞተ ሰው ያህል ነውና::

ሌላው ለጋብቻ መፍረስ እንደ ህጋዊ ምክንያት ተወሰደው ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት የሚወሰን የጋብቻ መፍረስ ነው:: ቀደም ሲል ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ አይተናል:: ከተወሰነ እድሜ በታች ጋብቻ መፈፀም እንደማይቻል፤ በሥጋና በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ጋብቻ መፈፀም እንደማይቻል፤ በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈፀም የተከለከለ መሆኑን፤ አሳስቶና በኃይል አስገድዶ ጋብቻ መፈፀም እንደማይቻል ተመልክተናል:: ሆኖም ከዚህ አልፎ እነዚህን ሁኔታዎች ሳያሟሉ ወይም ሁኔታዎቹን



Generated by CamScanner

በመሃል ጋብቻ ተፈጽሞ ሲገኝ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለውንም መመለስ ተገቢ ነው::

በመሠረቱ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች ሲጣሱ ኃላፊነት መከተሉ አይቀርም:: ኃላፊነቱም የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር ወይም ሁለቱም ሊሆን ይችላል:: አሁን በያዝነው ጉዳይም የወንጀልና የፍትሐብሔር ኃላፊነት እንደሚኖር የሚታመን ቢሆንም የወንጀል ኃላፊነቱን በተመለከተ በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ መሠረት የሚታይ ሲሆን የፍትሐብሔር ኃላፊነቱና ውጤቱን ብቻ በቤተሰብ ህጉ ውስጥ ማመላከቱ አግባብነት አለው:: በመሆኑም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 75(ሰ) መሠረት ይህንኑ ዓይነት ጉድለት ያለበት ጋብቻ ለፍርድ ቤት በማመልከት እንዲፈርስ ማስወሰን እንደሚቻል ተመልክቷል:: ጋብቻውን ለማፍረስ አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት እነማን ናቸው፤ በምን ያህል ጊዜስ አቤቱታቸውን ሊያቀርቡ ይገባል? የሚሉ ነጥቦች ቀደም ብለው የተነሱ ስለሆነ እዚህ ላይ መድገሙ መደጋገም ስለሚሆን ፋይዳ አይኖረውም::

ሦስተኛውና የመጨረሻ ጋብቻ መፍረሻ ምክንያት ፍቺ[102] ነው:: በነባሩ የቤተሰብ ህግ ፍቺ የተፈቀደ ቢሆንም ምክንያት ሊኖር ይገባል ነበር:: ተጋቢዎች አልፈልግህም አልፈልግሽም ተባብለው

---

[102] በፍትሐብሔር ህጉ መሠረት ለፍቺ ከባድና ሌሎች ምክንያቶች ተብለው የተከፋፈሉ ድርጊቶች ወይም ክንዋኔዎች የነበሩ ሲሆን እንደየምክንያቱ ዓይነት የፍቺ ውጤቶቹም የተለያዩ እንደነበር አይዘነጋም:: የፍትህ ሚኒስቴር አዘጋጅቶ ለውይይት ባቀረበው ረቂቅ የቤተሰብ ህግም ለፍቺ ከባድና ሌሎች ምክንያቶች የሚለው ክፍፍል እንደተጠበቀ ነበር:: በርግጥ የፍትህ ሚኒስትሩ ረቂቅ በከባድ ምክንያቶቹ ዝርዝር ላይ በፍትሐብሔር ህጉ ውስጥ ያልነበረ ተጨማሪ ምክንያት አካቶ ነበር:: (የረቂቁ አንቀጽ 85(ሐ) ይመለከታል::)



መለያየት (መፋታት) እንደማይችሉ ተደንግጎ ይገኛል:: ህጉ ራሱ ለፍቺ ከባድ ምክንያት ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን ከዚያ ውጪ ያሉት ሌሎች (ቀላል) ምክንያቶች እንደሆኑ ይቆጥራቸዋል::

የፍቺ መጠየቂያው ምክንያት ከባድ ከተባሉት በአንዱ ከሆነ ለማስታረቅ የሚደረገው ጥረት ብዙም የሚገፋበት ባይሆንም፤ ፍቺ የተጠየቀው በሌሎች ምክንያቶች ከሆነ ግን የሽምግልና ዳኞች ባልና ሚስቱ እንዲታረቁና የመፋታት ሃሳባቸውን እንዲተዉ ለማድረግ መጣርና መድከም እንደሚገባቸው ህጉ ይደነግጋል::[103] ይህም ጋብቻን ለመጠበቅና ፀንቶ እንዲቀጥል ለማድረግ ካለ እምነት የመነጨ እንደሆነ ይገመታል:: ከዚህም በተጨማሪ ከከባድ ምክንያት ውጪ በሆነ ምክንያት ፍቺ የሚጠይቅ ወገን ከጋራ ንብረቱም ጭምር ተቀጥቶ ፍቺው ይከናወናል:: ለዚህም እንደምክንያት ሆኖ የሚቀርበው ጋብቻ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ተቋም ነውና በሆነው ባልሆነው ፍቺ እየተጠየቀ ይህ የህብረተሰብ መሠረት የሆነውን ተቋም እንዳይናጋ ለመከላከል እንደሆነ ይነገራል::

የቤተሰብ ህጉ ለማሻሻል የሚረዱ ሃሳቦች ለማሰባሰብ በተካሄዱት ተከታታይ አውደጥናቶች እንደተመለከተው ግን፤ በርግጥ ጋብቻ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ተቋም ነው፤ ሆኖም ጥበቃው መከናወን ያለበት እንዳይፋቱ በመከላከል ወይም እንፋታ ሲሉ በንብረታቸው በመቅጣት አይደለም:: ለመፋታት ቁርጥ

---

[103] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 676(1)

ሃሣብ ከተወሰደ የነበረት ቅጣት መፋታቱን እያስቀረውም፡፡ ይልቁንም ድህረ ፍቺ ያላቸውን የተጋቢዎች ግንኙነት በእጅጉ ያሻክረውና በተለይ ከጋብቻው የተፈሩ ልጆች ቢኖሩ በእነርሱም ላይ አሉታዊ ጫና ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ለጋብቻ የሚደረግ ጥበቃ ወደመፋታት ከማምራቱ በፊት የሚደረግለትን ድጋፍና እንክብካቤ ሊታሰብ ይገባል እንጂ ፍቺ መከልከሉ ፋይዳ አይኖረውም የሚል ሃሣብም ይቀርብ ነበር፡፡

ሌሎች ወገኖች ደግሞ የቀድሞው የፍቺ ህግ ችግር የለበትም፤ ቢኖርበትም አፈጻጸሙ ላይ ነው፡፡ መንግስት ለጋብቻ ጥበቃ እንደሚደረግ ቃል ገብቷል፡፡ የጥበቃው አንዱ መገለጫ መሆን ያለበትም በዘፈቀደና ያለምክንያት ፍቺ እንዳይከናወን ማድረግ ነው፡፡ ጋብቻ በአብዛኛው ህፃናት ስለሚፈጥር ትዳር ሲበተን ፈቅደው ከዚያ ቤተሰብ ባልተወለዱት ህፃናት ላይ አሉታዊ ጫና ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም ከሁለቱም ወላጆቻቸው ማግኘት የሚገባቸውን እንክብካቤ ያጣሉ፡፡ በመሆኑም የፍቺ ጉዳይ ሲነሣ የህፃናቱ ጥቅምና መብትም አብሮ መታየት ይኖርበታል፡፡ በርግጥ በህጉ ከባድ ምክንያቶች ተብለው የተቀመጡት በቂ አይደሉም፤ ዝርዝሩ ሰፋ ማለት ይገባዋል ቢባል አግባብነት አለው፡፡ በተረፈ ግን ለፍቺ ከባድና ሌሎች ምክንያቶች ብሎ መከፋፈሉ ተገቢ ነው፡፡ ፍቺን ልቅ ማድረግ የጋብቻን ክቡርነት አሳንሶ እንደተራ ሸርክና ያስመስለዋል በማለት አጥብቀው ሲከራከሩ ነበር፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ሲዘጋጅ እነዚህና ሌሎች የተለያዩ አመለካከቶች ታሳቢ ተደርገው ተይዘዋል፡፡ በተቻለ መጠን እያንዳንዱ አቋም ውስጥ ያሉትን ጠንካራ ጎኖች በአዲሱ ህግ



ለማካተት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ፍቺ በሁለት መንገዶች ሊከናወን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

እነሊህም:-

ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑና ይህንኑ ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ[104] ወይም

1. ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ተጋቢዎች በአንድነት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው፡፡[105]

በመሆኑም በአሁኑ ህግ ለፍቺ ከባድና ሌሎች ምክንያቶች ብሎ መከፋፈል ሳያስፈልግ ተጋቢዎች ጋብቻቸውን በስምምነትም ቢሆን የሚያፈርሱበት ሥርዓት ተቀምጦላቸዋል፡፡[106] ህጉ እንዲህ ዓይነት

[104] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 76(ሀ)
[105] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 76(ለ)
[106] እንዲህ ያለ ለቀቅ ብሎ የተቀረፀ የፍቺ ሥርዓት (no fault divorce) በአብዛኛው የሚሠራበት በበለፀጉት ሃገሮች ነው፡፡ በእነዚሁ አገሮች ውስጥ ወንዱም ሆነ ሴቱ የመቀጠር፤ ገቢ የማመንጨትና ባለቤት የመሆን አቅማቸው ከሞላ ጎደል ተመጣጣኝ በመሆኑ ከፍቺ በኋላም ቢሆን በየራሳቸው ገቢ የመኖር እድላቸው ሰፋ ያለ በመሆኑ ድህረ ፍቺ የከፋ ኢኮኖሚያዊ ችግር አያጋጥምም፡፡ እንደኢትዮጵያ ባሉ በእድገት ወደኋላ በቀሩ አገሮች ግን የሴት እህቶቻችን የገቢ ባለቤትነትና የመቀጠር እድል በእጅጉ ጠባብ በመሆኑ፤ ለብዙ ሴቶች ትዳር እንደ ሥራ መስክ የሚቆጠር ነው፡፡ ስለሆነም በኛ አገር ሁኔታ ለቀቅ ያለ የፍቺ ስርዓት የሴቶችን የኢኮኖሚ አቅም በማጎልበት እንቅስቃሴ (economic empowerment) ካልታገዘ ውጤቱ አደገኛ ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክትና ትኩረት የሚሻ ሥጋት አለ፡፡ በመሆኑም ህብረተሰቡ በአጠቃላይ በተለይም መንግስትና በሴቶች መብት ዙሪያ የሚሠሩ ድርጅቶች በዚህ ረገድ በንቃት እንዲንቀሳቀሱ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ለቀቅ ያለ የፍቺ ህግ ለመቀበል ከገፋፉት ምክንያቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።[107]

- መጋባት ከፍት የሆነውን ያህል መፋታት ደግሞ ድፍን ሳይሆን ሥርዓት ባለው መልኩ መከናወን ይገባዋል እንጂ የሚፋቱበትን መንገድ በምክንያት ማጥበብና መንገድ መዝጋት የተጋቢዎቹን ቅራኔ ይበልጥ ያሰፋልᏤ እንዲሁም የወደፊት ተጋቢዎች ተስፋ ያጨልማል ወደጋብቻ ለመግባትም ይሰጋሉ።
- የጋብቻ መሠረቱ ፍቅርና ስምምነት ሆኖ እያለ ፍቅርና ስምምነት ባይኖርም እንኳን በህግ ጫና አብራችሁ ኑሩ ብሎ መደንገጉም ሆነ ፍቺ ጠያቂውን ወገን እንዲቀጣ ማድረጉ አግባብነት አይኖረውም።
- መንግስት ለጋብቻ ጥበቃ ያደርጋል ማለት ተጋቢ ወገኖች እንዴ ተጋብተው መኖር ከጀመሩ በኋላ ጋብቻው እንዳይፈርስ መንገዶችን ይዘጋል ወይም ፍቺ ጠያቂው ይቀጣል ማለት ሳይሆን መንግሥት በተለያዩ እቅዶቹ ለቤተሰብ የሚደርጋቸውን ቁሳዊና ህጋዊ ድጋፎች ያስፋፋል ማለት ነው።
- ህፃናት የወላጆቻቸውን ፍቅርና እንክብካቤ እንዲያገኙ ሲባል ጋብቻው ፀንቶ እንዲቆይ ይደረግ ከተባለ ህፃናቱ ፍቅር ተሟጦ ያለቀበትና በህግ ግዴታ እንዲቀጥል ከተደረገ ትዳር ጭቅጭቅና ንትርክ ብሎም ጥላቻን ይማራሉ እንጂ ፍቅርና እንክብካቤ ያገኛሉ ተብሎ አይጠበቅም።

[107] የፍትህና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት ቦርድ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ውስጥ የፍቺ ሥርዓቱ እንዴት ሊሆን ይገባል የሚለውን የፖሊሲ ሃሣብ ሲቀርጽ ካቀረባቸው ምክንያቶች በጥቂቱ የተወሰደ ነው።



- በመሆኑም ፍቺን ከሚፈለገው በላይ ማጥበብ ወይም ፍቺ እንዳይፈፀም መከልከል ለተጋቢዎቹም ለልጆቻቸውም የሚበጅ ስላልሆነ ለቀቅ ያለ የፍቺ ህግ መቅረጽ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል።

## 4.4 በስምምነት ስለመፋታት

በቀድሞው የቤተሰብ ህግ ሚስት ባልዋን ወይም ባል ሚስቱን አልፈልግም ማለትን ህግ አይፈቅድም ነበር።[108] ከዚህም አልፎ በባልና በሚስት ስምምነት የሚደረግ መፋታት በህጋዊ መንገድ ካልተፈጸመ በቀር አይፈቀድም ተብሎ መደንገጉ አይዘነጋም።[109] በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን ባልና ሚስት በስምምነት ተፋትተው ውሳኔያቸውን ይፀድቅላቸው ዘንድ ለፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችሉ ተደንግጎ ይገኛል።

ይህ ሲባል ግን ተጋቢዎች ለመፋታት ተስማምተናል ባሉ ቁጥር መንግስት እየተቀበለ ያፀድቃል ማለት አይደለም። መንግስት አስገድዶ አብረው እንዲኖሩ አያስገድዳቸውም እንጂ ጣልቃ በመግባት አብረው እንዲኖሩ ለማግባባት አይጥርም ማለት አይደለም። መንግስት በፍርድ ቤት በኩል የፍቺ ስምምነታቸውን ለማስፀደቅ የሚመጡትን ባለትዳሮች በርግጥ አስበውበትና ውጤቱን ተገንዝበው የወሰኑት ውሳኔ ስለመሆኑ የመጠየቅና የማጣራት ግዴታ እንደሚኖርበት ተመልክቷል። ከዚህም አልፎ የመፋታት ሃሣባቸውን እንዲለውጡ ብሎም የበለጠ አስበውበትና በሰከነ አእምሮ እንዲመጡ ለማስቻል እስከ ሦስት ወር የማሰላሰያ

[108] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 664
[109] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 665



Generated by CamScanner

ጊዜ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል::[110] በርግጥ የማሰላሰያ ጊዜ የመስጠቱ ጉዳይ እንደነገሩ ሁኔታ እየታየ የሚወሰን ነው:: ለምሳሌ ባልና ሚስቱ የዲቪ እድል አጋጥሞአቸው ሚስት አሜሪካ ሄደን እንኑር፣ ባል ደግሞ በዚህ እድሜ በዚህ ዘመን ከአገሬ አልወጣም በሚል የሃሳብ ልዩነት ፈጥረው እንግዲያውስ በፍቺ እንለያይና በየውሳኔአችን እንቀጥል ብለው በስምምነት ተፋትተው ለማስፀደቅ ቢቀርቡ የማሰላሰያ ጊዜ መስጠቱ ብዙም ውጤት ሊያመጣ አይችልም ሊባል ይችል ይሆናል ምክንያቱም በአግባቡ ያስቡበትና የተወያዩበት ይመስላልና:: በሌላ ጊዜና ሁኔታ ደግሞ የማሰላሰያ ጊዜው ውጤታማ ሊሆን ይችላል የሚል እምነትና ተስፋ ሊኖር ይችላል:: ስለሆነም ጉዳዮች የሚቀርቡት ለፍርድ ቤቶች ስለሆነ እንደነገሩ ሁኔታ እያየ እንዲወስን ሥልጣን ለፍርድ ቤት መስጠቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል::

[110] ፍርድ ቤቶች በሚቀርቡላቸው ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም በህጉ ተመስርተው ረቺና ተረቺ ከመወሰን አልፈው ባለጉዳዮችን ለማግባባትና ለማስታረቅ መሞከር ዋነኛ ኃላፊነታቸው እንዳልሆነ ይታወቃል:: ስለሆነም ይህ ጉዳይ ከተለመደው የፍርድ ቤቶች ሚና ወጣ ያለው ነው:: ከዚህ አንፃር ሲታይ እንዲህ ዓይነት ጉዳዮች የሚያስተናግዱ ችሎቶች ተጨማሪ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል ማለት ነው:: በተለይም በተሻሻለው የቤተሰብ ህጉ የተለያዩ ድንጋጌዎች ውስጥ በፍቺ ሂደት ባልና ሚስቱን በጋራና በተናጠል ማነጋገር የሚቻል ስለመሆኑ (አንቀጽ 77 እና 82) ውሳኔ ሲሰጥ የተጋቢዎቹን ወይም የቤተዘመዶቻቸውን መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ዝርዝር ህጉ ጉዳዮችን ከመተቸት መቆጠብ የሚቻል መሆኑና (አንቀጽ 111) የመሳሰሉት ሲታይ ከመደበኛው የፍትሐብሄር ሥነ-ስርዓት ህግ ወጣ ያለ አካሄድ ስለሚጠይቅ የቤተሰብ ጉዳዮችን የሚስተናግድ የተለየ ችሎት የመቋቋም አስፈላጊነትን የሚያጎላ ይመስላል::



እላይ እንደተመለከተው ጋብቻን በተቻለ መጠን ሀንዶ ለማስቀጠል የመንግስት ፍላጎት በመሆኑ ለመፋታት ተስማምተው ከመጡ "እኔ ምንቸገረኝ" የሚል አቋም ሊወሰድ እንደማይገባ ለማስገንዘብ ህጉ ለፍርድ ቤቶች አንዳንድ የድርጊት መርሐ ግብሮች (guide lines) አስቀምጦላቸዋል::[111] እነዚህም ጋብቻ በዘፈቀደ እንዳይፈርስ ለመከላከል የተቀመጡ አስፈላጊ መሰናክሎች እንደሚሆኑ ስለሚታመን በአግባቡና በኃላፊነት ስሜት ተግባራዊ ከተደረጉ በስምምነት መፋታት አትችሉም ብሎ በመደንገግ ከሚገኝ ውጤት ይልቅ በዚህ መልክ የተሻለና ፋይዳ ያለው የጋብቻ ጥበቃ ይገኛል ተብሎ ይታመናል::

በስምምነት የሚደረግ ፍቺ እላይ ከተመለከቱት ገደቦች በተጨማሪ ሁሉም ተጋቢዎች የሚገለገሉበት ሥርዓት እንዳልሆነ መገንዘብም ይገባል:: ለምሣሌ አዲስ ተጋቢዎች በስምምነት መፋታት አይፈቀድላቸው:: አዲስ ተጋቢዎች የሚባሉት ጋብቻ ከፈፀሙ ስድስት ወር ያልሞላቸው ጥንዶች ናቸው::[112] በህጉ ዓይን እነዚህ ወገኖች ተጋብተው ለአጭር ጊዜ ብቻ የቆዩ በመሆናቸው በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ለመፋታት ይስማማሉ ተብሎ ስለማይታመን ነው:: ይህ ሲባል ግን እነዚህ ጥንዶች መፋታት አይችሉም ማለት አይደለም:: ለማለት የተፈለገው የእነዚህ ወገኖች የመፋታት ጉዳይ በአዋጁ ከአንቀፅ 77 እስከ 80 ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት ሳይሆን በአዋጁ 81-84 መሠረት የሚታይ ይሆናል ለማለት ብቻ ነው::

[111] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 78 እና 80)
[112] ገኒ ከማሁ አንቀጽ 77(2



Generated by CamScanner

ሌላው በስምምነት በሚደረግ ፍቺ የተቀመጠው ገደብ ፍርድ ቤቱ የፍቺ ስምምነቱን የሚያፀድቀው "ስምምነቱ የባልና ሚስቱ ትክክለኛ ፍላጎት መሆኑን እና ባልና ሚስቱ ፈቃዳቸው በነፃ የሰጡ መሆኑን እንዲሁም ስምምነቱ ከህግና ሞራል ጋር የማይቃረን መሆኑን ሲያምን ብቻ ነው::"[113] አንዳንዴ የፍቺው ስምምነት አንደኛው ወገን በጤና ችግር እያለ ወይም በተመሳሳይ ከባድ ችግር ውስጥ ወድቆ ባለበት ሁኔታ ችግርን አብሮ ለመጋፈጥ ካለመፈለግ በመነጨ ስሜት ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ በክርሽያ የቤተሰብ ህግ ባል ሚስቱ በእርግዝና ወቅት ባለችበት ጊዜ ወይም ልጃቸው ተወልዶ አንድ ዓመት ሳይሞላው ፍቺ ሊጠይቅ አይችልም የሚል ግልጽ ክልከላ አለ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ባልና ሚስቱ እርስ በርሳቸው መተጋገዝና መከባበር አለባቸው የሚለውን የህግ ድንጋጌ የሚጥስና በሞራል ተቀባይነት ስለሌለው የፍቺውን ስምምነት ላለማጽደቅ በቂ ምክንያት ሊሆን ይችላል ማለት ነው::

በመጨረሻም በስምምነት የመፋታት ጉዳይ ሲነሣ ውጤቱም አብሮ መታየት ያለበት ነው:: ከጋብቻው የተወለዱ ልጆች፣ በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት፣ ለትዳር ጥቅም የተገባ እዳና አከፋፈሉ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ሊኖሩ ስለሚችሉ የፍቺው ስምምነት እነዚህ ጉዳዮች እንዴት እንደሚተዳደሩ ሊገልጽ

113 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 80(1) ከዚህ ጋር በተያያዘ የፍትህ ሚኒስቴር አዘጋጅቶ ባቀረበው ረቂቅ የቤተሰብ ህግ "ባልና ሚስት አብሮ ለመኖር የሚያስችል ከባድ ሁኔታ ካጋጠመ በቀር ሚስቲቱ ነፍሰ ጡር በሆነችበት ጊዜ ወይም ወልዳ ስድስት ወር ከማለፉ በፊት ባልየው የሚያቀርበው የፍቺ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም" የሚል ድንጋጌ ተካትቶበት ነበር (የረቂቁ አንቀጽ 87 ይመለከቷል::) በስምምነት ለሚደረግ ፍቺም ግምት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይመስላል::



ይገባል:: እንዲህ ባለ ጉዳይ የስምምነት ምንጩ የተጋቢዎች ፍላጎት ቢሆንም ፍርድ ቤትም ሰፊ ሚና አለው:: ስምምነቱ የልጆቻቸውን ደህንነትና ጥቅም የሚያስከብር ስለመሆኑ መመርመር፣ የጋራ ንብረቱ ፍትሐዊ በሆነ መልክ ለማከፋፈል ጥረት ስለመደረጉና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት:: ፍርድ ቤቱ ባደረገው ማጣራት ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ነጥቦች የማያሟላ ስምምነት መሆኑን ከተገነዘበ እንዲያስተካክሉት የማዘዝ ወይም ራሱ ማስተካከል የሚችልበት ህጋዊ ስልጣን ተሰጥቶታል::[114]

ሲጠቃለልም ምንም እንኳ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በስምምነት መፋታት የሚፈቀድ ቢሆንም የፍቺው ስምምነት ሆነ በፍቺው ውጤት የተደረገው ስምምነት ለፍርድ ቤት ቁጥጥርና ምርመራ (court supervised agreement) የተጋለጠና እልፎ አልፎም ስምምነቱ ውድቅ ሊደረግ እንደሚችል መገንዘብ የሚገባ ይመስለናል::

### 4.3. <u>የፍቺ ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ</u>

በስምምነት በሚደረግ ፍቺ ተጋቢዎቹ ብዙውን ሥራ ማለትም በፍቺውና በውጤቱ ላይ ስምምነት ፈጥረው ፍርድ ቤት

114 ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 80(3)

እንዲያፀድቅላቸው የሚጠይቁበት ሥርዓት ሲሆን በዚህ ክፍል ሥር ግን ሁኔታው የተለየ ነው::[115]

በስምምነት በሚደረግ ፍቺ ሁለቱም ተጋቢዎች ለፍቺው ፈቃዳቸውን የገለጹ ሲሆን አሁን በያዝነው ጉዳይ ግን ፍቺው የፈለገውና የጠየቀው አንደኛው ተጋቢ ብቻ ሊሆን ይችላል:: ለነገሩ በዚህም ቢሆን ፍቺውን የፈለጉት ሁለቱም ተጋቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ ግን ስለፍቺአቸው ሆነ ስለውጤቱ ያደረጉት ስምምነት የለም:: ስለሆነም በዚህ ክፍል ሥር የፍርድ ቤቱ ሚና ስምምነትን የማፅደቅ ሳይሆን በተጋቢዎቹና በሽማግሌዎች በመታገዝ ቢቻል ጉዳዩን ማቃናት ካልሆነ ግን ፍቺውና የሚያስከትለው ውጤት መወሰን ይሆናል:: በዚህ ረገድ የፍርድ ቤቱ ሚና በዚህ ክፍል ሰፋ ያለ ነው:: የፍርድ ቤቱ የሥራ ልዩነትና ስፋት የተሻሻለው የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 78 እና አንቀጽ 82 በማነፃፀር መገንዘብ የሚቻል ይመስለናል::

በአንቀጽ 82 ስር ፍርድ ቤቱ ዘርዘርና ሰፋ ያሉ ሃላፊነቶች የተሰጡት ሲሆን ከፍርድ ቤቱ በተጨማሪ በተጋቢዎች የሚመረጥ ወይም የሚመረጡ አስታራቂ ሽማግሌዎችም በጉዳዩ ላይ እንዲገቡበት የማድረግ እድል አለ:: የአስታራቂ ሽማግሌዎቹን የስራ ክንውን ሪፖርት የመቀበልና ለሽማግሌዎቹ የሥራ መመሪያ መስጠት የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ስለመሆኑ ከአንቀጽ 119 እስከ

[115] አንዳንድ ወገኖች በስምምነት በሚደረግ ፍቺና የፍቺ ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት በሚወሰን ፍቺ መካከል ልዩነት የለም ምክንያቱም ሁለቱም የሚቀርቡት ለፍርድ ቤት እስከሆነ ድረስ ልዩነት አልነበረም ይላሉ:: ህጉ ልዩነት ፈጥሮ እንደቀረፃቸው ሊታወቅ ይገባል::



አንቀጽ 122 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ተመልክቶ ይገኛል:: የሦስት ወሩ የማሰላሰያ ጊዜም በዚህ ክፍል ሥርም እንዳለ ነው::

አንዳንድ ወገኖች . የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ባልና ሚስቱ ፍርድ ቤት ድረስ መቅረብ ሳያስፈልጋቸው በጠበቆቻቸው አማካይነት መፋታት የሚያስችል ነው ሲሉ ይደመጣሉ:: በኛ በኩል ግን ህጉን በዚያ መልክ አናየውም:: ፍርድ ቤቱ የፍቺ ጥያቄው ሲቀርብለት ባልና ሚስቱን በተናጠል ወይም በጋራ በማነጋገር የመፋታት ሃሣባቸውን እንዲተዉ ለማግባባት መሞከር እንዳለበት ተመልክቷል:: እነርሱን በተናጠል ወይም በጋራ ማነጋገር የሚቻለው ደግሞ በግባንር ሲቀርቡለት ብቻ ነው:: ከዚህም አልፎ ጋብቻ ግላዊ (Personality) ስለሆነ በእንደራሴ ሊፈጸም እንደማይቻልና ተጋቢዎቹ በግንባር ቀርበው ፈቃዳቸውን ሊገልጹ እንደሚገባ ቀደም ሲል አይተናል:: በእንደራሴ ማግባት የሚቻለው በጠባብና ልዩ ሁኔታ ነው:: (የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 12(2) ይመለከቷል:: ስለሆነም የፍቺውም ጉዳይ የተጋቢዎቹ በግንባር መቅረብ በልዩ ሁኔታ ካልተወገደ በቀር ግዴታ ነው ብለን እናምናለን:: በመጨረሻም በፍትሐብሄር ጉዳይ ምንም እንኳ በግንባር መቅረብ ሳያስፈልግ በጠበቃ መከራከር የሚቻል እንደሆነ ቢታመንም ፍርድ ቤቱ የዋናው ባለጉዳይ መቅረብ ለፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ እንዲቀርብ ከማዘዝ የሚከለክል አይመስለንም:: በዚህ ጉዳይ ደግሞ የባለጉዳዮች የመቅረብ አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይደለም የሚል እምነት አለን::

በዚህ ክፍል ሥር የፍርድ ቤት ትኩረት የሚያሻው ሌላው ነጥብ የጊዜያዊ ትእዛዝ ጉዳይ ነው:: ፍቺውም የተጠየቀበት

ምክንያት የተጋቢዎቹ ትራኔ በመስፋቱ ሊሆን ስለሚችል የእስተራቂ ሽማግሌዎች የጥረት ውጤት እሲኪታይና የማስላሰያ ጊዜው ምናልባት ውጤት ካስገኘ ለመጠባበቅ ሲባል ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩበት ሁኔታ፤ ስለልጆቻቸው አጠባበቅ፤ ስለሚኖሩበት ስፍራና ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ስለጋራ ንብረታቸው አስተዳደር ግልጽና ጊዜያዊ ትእዛዝ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ በዚህ የአለመግባባት ወቅት ንብረቶች ይባክናሉ፤ እጅ ይለውጣሉ፤ ይደበቃሉ፡፡ የንብረት አስተዳደር ኃላፊነት የያዘው ተጋቢ ይህንን ሥልጣኑን የሌላውን ተጋቢ ጥቅም ለሚጎዳ ግብ ሊያውለው እድል አለ፡፡ የልጆች አኗኗርና አስተዳደግ ችግር ሊገጥመው ይችላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ወቅት የመንግስት (ፍርድ ቤት) ጣልቃ ገብነት እጅግ ተፈላጊ ሆኖ ስለሚገኝ የጊዜያዊ ትእዛዝ ጉዳይ ጊዜ የሚሰጥ አይደለም፡፡[116]

ከሁሉም በላይ የመጠለያ ጉዳይ ቁልፍ ነጥብ ነው፡፡ አንዳንዶ ፍቺው እስኪከናወን ድረስም ባልና ሚስቱ አብረው

[116] ለነገሩ የንብረት አስተዳደርና ክፍፍል እንዲሁም የልጆች አኗኗር የሚሸ ጉዳይ በጊዜያዊ ትእዛዝ ላይ ብቻ ሳይሆን በፍቺ ጊዜም ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም የልጆች አኗኗር፤ ትምህርት፤ ቀለብና ጤንነት ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም የልጆች አኗኗር፤ ትምህርት፤ ቀለብና ጤንነት ግልጽና የማያሻማ ውሳኔ የሚጠይቅ ነጥብ ይመስለናል፡፡ ይህ ውሳኔ ሲሰጥም የወላጆቹን ገቢ፤ የዕድሜ፤ የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የልጆቹን እድሜ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸውን ያገናዘበ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ ውስጥ ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት በተቻለ መጠን ከእናታቸው ጋር እንዲቆዩ ማድረግ እንደሚገባ ተመልክቶ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን ፍርድ ቤቶች የቀረቡላቸውን ጉዳዮች በማመዛዘን እንደ ሁኔታው እያዩ ለመወሰን ያስችላቸው (flexibility) ዘንድ ህጉ ሰፋና ጠቅለል ባለመልክ ተቀርጿል፡፡ ሲሰጡ ዞሮ ዞሮ ግን "ፍርድቤቶች ህፃናትን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ሲሰጡ የህፃናትን ደህንነት በተደምትነት ማሰብ እንዳለባቸው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 36(2) የተደነገገ ስለሆነ የህፃናቱን ጥቅም እንደማይጎዳ ይታመናል፡፡



በአንድ መጠለያ ሥር መቆየት የማይችሉበት ትራኔ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በተለምዶ 'አባወራው' ከጋራ መኖሪያ ቤት ሳይፈናቀል እንዲቆይ ይደረግ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ በዚህ ረገድ ለውጥ ለማምጣት ጥረት አድርጓል፡፡

በመሠረቱ በዚህ ረገድ ቀዳሚውና ተመራጩ እርምጃ ሁለቱም ተጋቢዎች ከጋራ መኖሪያቸው ሳይፈናቀሉ እንዲቆዩ ጥረት ማድረግ ነው፡፡ ይህም ተቻችለው እንዲቆዩ በማግባባት ወይም መኖሪያ ቤቱ ተከፋፍሎ በር ለይተው እንዲወጡ እንዲገቡ በማድረግም ሊከናወን ይችላል፡፡ ይህ ሁሉ አማራጭ ተሞክሮ የማይሳካ ቢሆን ግን ከአስፈላጊነት የመነጨ (need based) ውሳኔ እንዲሰጥ ለፍርድ ቤት ግዴታ ተጥሎበታል፡፡[117] ይህም ማለት ተጋቢዎች ያላቸው ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት በማድረግ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ የበለጠ የሚጎዳው የትኛው መሆኑን በመመርመርና የልጆቻቸውን አጠባበቅና ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን ይገባዋል እንጂ የመጠለያ ቅድሚያ አባወራው በአባወራነቱ እንደመብት የሚያገኘው አይሆንም ማለት ነው፡፡[118]

[117] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 82(6)

[118] የቤተሰብ ህጉን ለማሻሻል የሚረዱ ሃሣቦችን ለማሰባሰብ በተካሄዱት ተከታታይ አውደ ጥናቶች ሲቀርቡ የነበሩት አንዳንድ ሃሣቦች "ፍቺው እስኪወሰን ድረስ ባልና ሚስቱ አብረው መቆየት የማይችሉ መሆናቸው ከተረጋገጠ ከጋራ መኖሪያ ቤት ውስጥ የመቆየት መብት ለሚስት ይሰጣል" የሚል ግልጽ ድንጋጌ በአዲሱ የቤተሰብ ህግ እንዲቀመጥ ሃሣብ ቀርቧል፡፡ በሌሎች አገሮችም የተለመደና ተቀባይነት ያለው አሰራር እንደሆነም ተጠቅሶ ነበር፡፡ ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ ቁርጥ ያለ ድንጋጌ ፍርድቤቶች የቀረቡላቸውን ጉዳዮች በማመዛዘን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ውሳኔ ለመስጠት ስለማያስችላቸው ሚስት መቆየት አለባት የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ካለ ይህንኑ እንዲወስኑ ለማስቻል በአንፃሩም ባል መቆየት ይገባዋል የሚያሰኝ አሳማኝ ምክንያት ከተገኘም ይህንኑ



Generated by CamScanner

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ሌላው ነጥብ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የፍቺ ምክንያቶች ከባድና ሌሎች ብሎ መክፈል ተቀባይነት ያላገኘ ቢሆንም የፍቺው ምክንያት ምንነት በአሁኑ ሕግ ፋይዳ የለውም ማለት አይደለም። የፍቺ ምክንያት ለፍቺው መወሰን ወይም ላለመወሰን አስፈላጊ ባይሆንም ለውጤቱ በተለይም ለጋራ ንብረት ክፍፍሉ ግን ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል። ለምሳሌ ፍቺው የተጠየቀው አንደኛው ወገን በፈፀመው ዝሙት ወይም ድብደባ ምክንያት ከሆነ ፍቺው ተወስኖ በሚደረገው የንብረት ክፍፍል ወቅት ንብረቱ በእኩል መክፈሉ ቀርቶ ይህንኑ ጥፋት ግምት ውስጥ ያስገባ ክፍፍል ሊከናወን ይችላል ማለት ነው። ምክንያቱም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 84 «ከባልና ከሚስት አንዱ ለፍቺው ምክንያት የሆነውን በደል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ ለፍትህ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሌላው ተጋቢ ላይ ለደረሰው ጉዳት በዳዩ ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ እንዲከፍል ሊወስን ይችላል» በማለት ተደንግጎ ይገኛልና።

በርግጥ በፍቺ ወቅት የሚኖረው የጋራ ሃብት ክፍፍል በአንቀጽ 90 እንደተመለከተው የጋራ ሃብቱ ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ አንቀጽ 84 የአንቀጽ 90 ልዩ ሁኔታ (exception) መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል። በሕግ



አተረጓጎም መርህ ደግሞ ልዩ ሁኔታ በጠባቡ መተርጎም ስላለበት (exceptions should be interpreted restrictively) አንቀጽ 84 ከሚፈለገው በላይ ተለጥጦ ሊተረጎም አይገባም። «...ፍርድ ቤቱ ለፍትህ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው...» የሚለው ሃረግን በጠባቡ መተርጎም እንደሚኖርበት አንዱ መገለጫ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ካሣ መክፈል ተገቢ ሆኖ ከተገኘ በዚህ አንቀጽ ሥር የሚከፈለው ካሣ የሞራል ጉዳት ካሣ ብቻ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። የሞራል ጉዳት ካሣ አሁን በሥራ ላይ ባለው የፍትሐብሔር ህግ ጣሪያው አንድ ሺህ ብር መሆኑን በመገንዘብ በዚህ አንቀጽ የሚከፈለው ካሣ በዚህ መጠን ለመገደብ ስላልተፈለገ በአንቀጹ ውስጥ በጥቅሉ «ካሣ» በሚል እንጂ የሞራል ጉዳት ካሣ በሚል እንዲተረጸ አልተፈለገም።

እዚህ ላይ የካሣው መጠን እንዴት ይወሰናል? የሚለው ጥያቄ ቢነሣ አግባብነት አለው። በውል ሳይኖር የሚደርስ ሃላፊነት ሕግ በአንድ ሰው ጥፋት ምክንያት የደረሰበትን የጉዳት መጠን የማስረዳት ሃላፊነት ያለው ተጎጂው እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህ አንፃር በሌላኛው ተጋቢ ጥፋት ምክንያት ፍቺ የጠየቀ ወገን ካሣ እንዲቆረጥለት የሚጠይቅ ቢሆን የደረሰበት ጉዳት መጠን የማሳየት ኃላፊነት ይኖርበታል ማለት ነው። ሆኖም ጉዳቱ ስለመድረሱ ታምኖ መጠኑን ለመገመት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ የአካባቢ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የካሣውን መጠን በርትዕ



Generated by CamScanner

መወሰን እንዲችል ሥልጣን የተሰጠው ስለሆነ በዚሁ ሥልጣኑ ቢሠራበት ህጋዊ ነው የሚል እምነት አለ::[119]

በመጨረሻም ስለፍቺ ጉዳይ ሲነሣ ስለ ቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ጉባኤ አንዳንድ ነጥቦች አንስቶ ማለፉ ተገቢ ነው:: ምክንያቱም በነባሩ ህግ መሠረት በፍቺ ጉዳይ ውሳኔ የሚሰጠው ይህ ተቋም ስለነበር ነው::[120]

በፍትሐብሄር ህጉ መሠረት ማናቸውም የባልና ሚስት አለመግባባት (ፍቺን ጨምሮ) መቅረብ የሚገባው ለቤተ-ዘመድ ሽምግልና ዳኞች ነበር:: ባልና ሚስቱ ወደ ፍርድ ቤት ቢመጡ እንኳ ፍርድ ቤቱ ወደ ሽምግልና ዳኞች እንዲመራቸው ይጠበቅበታል:: የሽምግልና ዳኝነት አባላት ቀደም ሲል ጋብቻው ሲፈፀም ምስክሮች የነበሩ ከባል ወገን ሁለት ከሚስት ወገንም ሁለት ሆነው እነርሱ በስምምነት የሚመርጡት ሰብሳቢ ጨምሮ የሚዋቀር ጉባኤ ነበር::[121] እነዚህ ሰዎች በቅርብ የማይገኙ ከሆነ ግን ባልና ሚስቱ ሁለት ሁለት ሰዎች ለዚሁ ዓላማ እንዲመርጡ

---

[119] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 2102(1) ይመለከቷል:: እዚህ ላይ "ጋብቻ ውል ስለሆነ የውል ሳይኖር የሚደርስ ኃላፊነት ህግ ለጋብቻ ጉዳይ አግባብነት አይኖረውም" የሚል ክርክር ሊቀርብ ይችል ይሆናል:: ሆኖም "ጋብቻ ውል (contract) ነው ወይስ ማህበራዊ ተቋም" (institution) የሚለው የሰንስ ሃሳብ ክርክር እልባት ያላገኘ ስለሆነ ጋብቻ ውል ነው ብሎ ደፍሮ መናገር የሚቻል አይመስልም:: ጋብቻ ውል ነው ብለንም እንኳ ብንነሣ፤ በውል አለመፈጸም ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ወገን የጉዳት ካሣ ለመጠየቅ እንደሚችልና የጉዳት ኪሣራውና ልክ በፍትሐብሄር ህግ ከቁጥር 2090-2123 ባሉት የውል ሳይኖር የሚደርስ ኃላፊነት ድንጋጌዎች መሠረት እንደሚታይ በቁጥር 1790 የተደነገገ ስለሆነ የውል ሳይኖር ድንጋጌዎች ለውልም ጉዳይ አግባብነት እንዳላቸው መገንዘብ ይገባል::

[120] የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 677-679

[121] ገዚ ከማሁ ቁጥር 725



ይደረጋል ወይም ፍርድ ቤት የቤተ ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ይሸምላቸዋል::

ከጋብቻ የሚመነጩ አለመግባባቶች በቤተ-ዘመድ ሽምግልና ዳኞች እንዲታይ ካስፈለገበት ምክንያቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

- ሽማግሌዎቹ የባልና ሚስቱ የቅርብ ዘመዶች ስለሚሆኑ ለማስታረቅ በትእግስትና በሃላፊነት ስሜት ይጥራሉ ተብለው ስለሚገመቱ፣ አለመግባባቱን አስወግደው ጋብቻውን ያቃኑታል፣ ካልተሳካም ባልና ሚስቱን ሳይጉላሉ ፍቺ ይወስናሉ የሚል ግምት በመኖሩ፤
- የጋብቻ ጉዳይ አደባባይ ወጥቶ መሳቂያ መሳለቂያ ከሚሆን ይልቅ በጥቂት የቅርብ ዘመዶች በሚስጥር እንዲያዝ ለማስቻል፤ እንዲሁም ለማስታረቅም ቢሆን ከፍርድ ቤት ይልቅ ሽማግሌዎች የተሻለ ብቃት ስለሚኖራቸው፤
- ባልና ሚስቱ በሽማግሌዎች ፊት ጠበቃ መቅጠር ሳያስፈልጋቸው ጉዳዮቻቸውን በእነስተኛ ወጪ ራሳቸው መከታተል እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፤
- አለመግባባቶች በሽማግሌ የመፍታት ልምድ ከኢትዮጵያ ባህላዊ እሴቶች አንዱ በመሆኑ ቀጣይነቱን ለማረጋገጥና ለማበረታታት፤
- በመጨረሻም የጋብቻ አለመግባባቶች ከፍርድ ቤት ውጪ እንዲያልቁ በማድረግ የፍርድ ቤቶችን የሥራ ጫና ለማቃለል በማሰብ እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል::



Generated by CamScanner

የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ ለማዘጋጀትና ሃሣቦች ለማሰባሰብ በተካሄዱት ተከታታይ አውደጥናቶች ወቅት የቤተ-ዘመድ ሽምግልና ጉባኤን አስመልክቶ የተለያዩ አስተያየቶች ሲቀርቡ ተስተውለዋል::

አንዳንድ ወገኖች ህጉ በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ላይ አሳድሮት የነበረው እምነት ሊሳካ አልቻለም:: ይህ ተቋም በተለይ በከተሞች አካባቢ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ አመዝኖአል:: በከተሞች አካባቢ የሰዎች ዝውውር ሰፊና ፈጣን በመሆኑ ጋብቻ ከፈፀሙበት ቦታ ርቆ መኖር የተለመደ ነው:: ስለዚህ ጋብቻውን በምስክርነት ያከናወኑ የቅርብ ዘመዶች በአብዛኛው በአካባቢው አይገኙም::

በመሆኑም አለመግባባቱ ሲከሰት በሽምግልና ዳኝነት የሚመደቡት ከጥላ ጎደል በፍርድ ቤት የሚሾሙና በዚህ «ሙያ» ከሚያገኙት ዳጎስ ያለገቢ ኑሮአቸውን የሚመሩ «ፕሮፌሽናል» ሽማግሌዎች ናቸው:: እነዚህ ሽማግሌዎች የተጋቢዎቹ የቅርብ ዘመድ መሆን ቀርቶ ተጋቢዎቹን ጨርሶ የማያውቁዋቸው ስለሚሆኑ ጋብቻውን ለማቃናት ሞራላዊ ኃላፊነት አይኖራቸውም:: ሽማግልናውም ብዘውን ጊዜ ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ቤተ በሉቶች ቅጥር ግቢ የሚካሄድ ስለሚሆን በሚስጢር እንዲያዝ የሚፈለገው የጋብቻ አለመግባባት የአደባባይ ሚስጥር እየሆነ መጥቷል:: ፍቺም የሚወሰን ቢሆን ባለጉዳዮቹ ሳይጉላሉ ፍቺው በአጭር ጊዜ ውስጥ መከናወን ሲገባው የሽምግልና ዳኞቹ አበል የሚቆረጥላቸው ስብሰባ በተቀመጠባቸው ቀናት ብዛት ነውና በጉዳዩ መጓተት ተጠቃሚ ስለሚሆኑ ሂደቱን ከሚፈለገው በላይ ያራዝሙታል:: ስለዚህም ህጉ



ለተቋሙ መመስረት ያስቀመጣቸው ዓላማዎች አንዱንም ሊያሳካ ስላልቻለ ተቋሙ አስፈላጊነት የለውም::

ከዚህም በተጨማሪ ድሮውኑም ቢሆን የህግ እውቀት የሌላቸው የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ህግን መሠረት አድርገው እንዲወስኑ ማዘዝ አግባብ አይደለም:: እንዲያውም የቤተ-ዘመድ ሽምግልና ዳኝነት የዳኝነት ሥልጣንን ከፍርድ ቤቶች የሚነጥቅ በመሆኑ ህገ-መንግስታዊ አይደለም:: ስለሆነም የቤተ-ዘመድ የሽምግልና ዳኝነት የሚባል ተቋም ፈርሶ ለዚሁ ተቋም በህግ ተሰጥተው የነበሩት ሥልጣንና ሃላፊነቶች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት እንዲተላለፉ ሊደረግ ይገባል በማለት አጥብቀው የሚከራከሩ ወገኖች በስፋት ታይተዋል::

ሌሎች ወገኖች ደግሞ አለመግባባቶችን በሽምግልና የመፍታት ጥረት የፍትሐብሄር ህጉ የፈጠረው ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ በሃገራችን ባህል ሲሠራበት የነበረ ስለመሆኑ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ:: ይህንንም አኩሪ ባህላችንን ይዘነው ልንቀጥል ይገባል:: ተቋሙ በከተሞች አካባቢ ሊሠራ ያልቻለበት ምክንያት ሊኖር ይችላል፤ ከዚህ ተነስቶ ግን በአጠቃላይ አይሰራም ብሎ መደምደም ተገቢ አይደለም:: ለነገሩ በከተማም ቢሆን የተሳኩ ሽምግልናዎች እንዳሉ ማመን ይገባል:: ዋናው ነገር ግን ተቋሙ በገጠሩ የሃገራችን ክፍል እየሠራና እየተሠራበት ያለ ስለመሆኑ ሊሠመርበት ይገባል:: በተለይም ተቋሙና በተቋሙ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለያይተን ማየት ይኖርብናል:: ግለሰብ የሽምግልና ዳኝነት አባላት ችግር ስለፈጠሩ ተቋሙ ይፍረስ ማለት አይገባም::

ይልቁንም በአባላቱ አመራረጥ ላይ ማስተካከያ በማድረግ ተቋሙን ማስቀጠል ይበጃል ባዮች ናቸው።

ከዚህም አልፎ የህግ እውቀት የሌላቸው ሰዎች በህግ መሠረት ሊዳኙ ስልጣን ሊሰጣቸው አይገባም ለተባለውም ህጎቻችን ወደፍርድ ቤት ይግባኝ የመጠየቅ መብትን በማመቻቸት ለተለያዩ የህግ እውቀት አይኖራቸውም ተብለው ለሚገመቱ ተቋሞች መለስተኛ ቅራኔዎችን የመዳኘት ሥልጣን የሚሰጡበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ለምሳሌ እንደማህበራዊ ፍ/ቤቶች፣ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ፣ የአስተዳደር ፍ/ቤት እንዲሁም የግብር ይግባኝ ጉባኤ የመሳሰሉት ተቋሞች መጥቀስ ይቻላል። ስለዚህ የቤተ-ዘምድ ሽምግልና ዳኝነት ጉዳይ ከነዚህ በተለየ ሁኔታ ሊታይ አይገባም። ተቋሙ ህገ-መንግስታዊ አይደለም ለሚለውም በህገ መንግስቱ መሠረት ለፍርድ ቤቶች ወይም በህግ የመዳኘት ሥልጣን ለተሰጣቸው ተቋሞች የመዳኘት ሥልጣን የተሰጠ ስለሆነ ይህ ተቋም ፍርድ ቤት ባይሆንም በህግ የመዳኘት ስልጣን ከተሰጠው የህገ-መንግስታዊነት ጥያቄ አያስነሣም። በመጨረሻም ሁሉም ከጋብቻ የሚመነጩ አለመግባባቶች ወደ ፍርድ ቤቶች እንዲመጡ ማድረግ የፍርድ ቤቶችን የሥራ ጫና አክብዶ የተጋቢዎቹን ጉዳይ ስለሚያጓትት ችግሩ የባሰ ይሆናል የሚሉ መከራከሪያ ነጥቦች ሲያቀርቡ ነበር።

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ሲዘጋጅ እንደተለመደው እዚ ከተመለከቱት የተለያዩ ሃሣቦች አንዳንድ ጠቃሚ ነጥቦች ለማካተት ጥረት ተደርጎአል። በዚህ ህግ መሠረት ከጋብቻ የሚመነጩ



አለመግባባቶች በሁለት እንዲከፈሉ ተደርጓል። እነዚህም ፍቺና ከፍቺ በመለስ ያሉ ሌሎች አለመግባባቶች ተብለው ተቀምጠዋል። ፍቺና ውጤቶቹን የመወሰን ጉዳይ የፍርድ ቤት ሥልጣን ሲሆን ከዚህ በመለስ ያሉ የጋብቻ ውስጥ አለመግባባቶች ግን በሽማግሌዎች እንዲታዩ ተደርጓል።[122] ይሁን እንጂ በሽማግሌዎች ጥንቅርም ለውጥ ተደርጓል በነባሩ ህግ መሠረት በቤተ ዘመድ ሽምግልና አባልነት የሚሾሙት ሁለት ከባል ወገንና ሁለት ከሚስት ወገን የሚወጣጡና ሰብሳቢያቸውን በጋራ የሚመርጡ ነበሩ። ይህ ዓይነት አደረጃጀት በባል ወገን የመጡት ባልየውን በመደገፍ በሚስት ወገን የመጡትም ሚስቲቱን በመደገፍ ሲወግኑ ሂደቱን ውስብስብ የማድረግ ውጤት እንደነበረው ይነገራል። የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ይህንኑ ስጋት ለማስወገድ ያመች ዘንድ ተጋቢዎቹ እስከተስማሙ ድረስ ሽማግሌዎች አንድም ሁለትም ከዚያ በላይም ሊሆኑ ይችላሉ። አመጣጣቸውም ከዚህ ወገን ከዚያ ወገን ተብለው ሳይሆን በተቻለ መጠን ሁለቱም ተጋቢዎች የተስማሙባቸው እንዲሆኑ ይጠበቃል።[123] ይህም በሽማግሌዎች አካባቢ ሊኖር የሚችለው ውጥረት ሊያረግበው ይችላል የሚል እምነት አለ።

እዚህ ላይ ሊሠመርበት የሚገባው ሌላው ነጥብ የፍቺ ጉዳይ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የፍርድ ቤቶች ሥልጣን ነው ቢባልም ሽማግሌዎች ምንም ዓይነት ሚና የላቸውም ማለት

---

[122] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 117 አንቀጽ 118(1)ይመልከቱ።
[123] በነባሩ ህግ ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች ወይም ሰብሳቢ የሚሾምበት ሥርዓትና ሥልጣን የነበረው ቢሆንም በአዲሱ ህግ ይህ ነገር እንዲቀር ተደርጓል። ምክንያቱም ፍርድ ቤት የሚሾሙዋቸው ሽማግሌዎች ከአለ

አይደለም፡፡ በርግጥ በዚህ ህግ መሠረት ሽምግሌዎች ካላፈነገጡ የማስታረቅ ወይም የማስታረቅ ጥረት ማድረግን እንጂ ማፈንገጥን አይጨምርም፡፡[124] ሆኖም የፍቺ ጥያቄ ይዘው የቀረቡ ተጋቢዎች ፍርድ ቤቱ ባደረገው ጥረት ጉዳያቸውን በዕርቅ ለመጨረስ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ቀጥረናቸውን ማንነታቸው በተጋቢዎቹ በሚወሰኑ ሽምግሌዎች አማካኝነት የዕርቅ ጥረት ሊደረግ ይችላል፡፡ በነባሩ ህግ እንደ የፍቺ ጉዳይ በቤተ-ዘመድ ሽምግልና ጉባኤ እጅ ከገባ ውሳኔአቸውን ለማስፈጸም ወይም በይግባኝ መልክ ለፍርድ ቤት ይቀርባል እንጂ ከዚህ ውጪ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የሚከታተልበት እድልና ሥልጣን አልነበረውም፡፡[125] በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሠረት ግን ሽምግልናም የሚከናወን ቢሆን በፍርድ ቤት የመፍትሄ አተጣጥ ጠበቅ ያለ ክትትል (court superivised arbitration) እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የዚህ መገለጫ ከሆኑት ድንጋጌዎች ጥቂቶቹ

ከፍያ ጋር የተያያዘ ስለሚሆኑ በዚህ ረገድ በነባሩ ህግ የተከለከሉ "የፕሮፌሽናል" ሽምግሌዎች ችግር እንዳይደገም በማሰብ ነው፡፡

[124] በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ121(3) ይመለከቷል፡፡ ሆኖም ከፍቺ በመለስ ባሉ የጋብቻ ውስጥአለመግባባቶች ግን ሽምግሌዎች ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን እንዳላቸው መገንዘብ ይገባል (የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 118(1)

[125] በርግጥ በፍትሐብሔር ህጉ ቁጥር 737 መሠረት ሽምግሌዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ሊቋጩት ካልቻሉ እንደገና ወገን በሚያቀርበው ጥያቄ ዳኞች ነገሩን ሊመረምሩ እንደሚችሉ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ይህ ጉዳይ ልዩ ሁኔታ (exception) እንጂ አጠቃላይ መርህ (rule) ባለመሆኑ በጠባቡ የሚፈጸም ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ግን ከሽምግሌዎች ጉዳዩን የሚወስደው የትኛው ፍ/ቤት ነው በሚለው ጉዳይ ላይ አንድ ወጥ አቋም ያለ አይመስልም፡፡ በዚህ ጭብጥ ላይ በወረዳ ፍ/ቤት ጋናል ችሎት ዳኞች መካከል የሃሳብ ልዩነት ተከስቶ እንደነበር ማውሳቱ ተገቢ ነው፡፡ (የፍ.ብ.መ.ቁ 697/74 የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ምርጥ ፍርዶች የፍትሐብሔር ጉዳዮች አንደኛ መጽሐፍ ገጽ 80-92



በመጀመሪያ የዕርቅ ጥረቱ ሲጀመር ፍርድ ቤቱ ለሽምግሌዎች ዕርቁ የሚከናወንበትን የመፍትሄ አተጣጥ የሚጠቁም ምክርና መመሪያ (Terms of reference) ይሰጣቸዋል ወይም እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡[126] ቀጥሎም የዕርቁ ወይም የዕርቅ ሙከራው ውጤት በተወሰነ የጊዜ ገደብ (በሦስት ወር ውስጥ) ሪፖርት እንዲያደርሱ ያዛል፡፡ ከዚህም አልፎ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሦስት ወሩ የጊዜ ገደብ መጠበቅ ሳያስፈልገው የዕርቁ ሂደት የደረሰበትን ደረጃ የሚያመለክት ወቅታዊ ሪፖርት (Progress report) እንዲቀርብለት የማዘዝ ሥልጣን አለው፡፡[127] የሽምግልናው ሂደት ከፍርድ ቤት ጋር እንዲተሳሰር ማድረጉ የፍቺ ጉዳዮች በሽምግሌዎች እጅ ከሚፈለገው በላይ እየተጓተቱ የባለጉዳዮችን ችግር ምክንያት ስለነበር አዲሱ አሰራር ይህንን ችግር ለመቅረፍ ያግዛል የሚል እምነት አለ፡፡

የዕርቅ ጥረቱ ውጤት ሳያመጣ ቀርቶ ፍቺ ከተወሰነ በኋላም[128] የፍቺ ውጤቶችን ለመወሰን የሽምግሌዎች እገዛ ትልቅ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋኩልቲ መጋቢት 1992 ይመልከቱ፡፡)

[126] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 119(2)

[127] ዝኒከማሁ አንቀጽ 119(3)

[128] በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ፍቺ በመወሰኑ ይግባኝ አይጠየቅበትም (አንቀጽ 112) ይህ ማለት ከተጋቢዎቹ ሁለቱም ወይም አንዱ የፍቺ ጥያቄ ቢያቀርቡና የፍርድ ቤቱና የሽምግሌዎች የማስታረቅ ጥረት ሳይሳካ ቀርቶ ፍቺ እንዲከናወን ከተወሰነ ከተጋቢዎች አንዱ መፋታት አይገባንም የሚል አቋም በመያዝ ይግባኝ በመጠየቅ የበታች ፍርድ ቤት ውሳኔውን ማስለወጥ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የበታች ፍ/ቤት ፍቺውን የወሰነው ቢያንስ ከተጋቢዎች አንዱ ጋብቻውን እንዲፈርስ በመጠየቁ ነው ተብሎ ስለሚታመን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ቢሆን ተጋቢዎችን በፍርድ አስገድዶ አብረው እንዲኖሩ ማድረግ ስለማይችል ቢወስነውም አፈጻጸሙ ስለሚያስቸግር ፍቺ መወሰኑ ለይግባኝ መሠረት

አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ በተለይም የፍርድ ቤቶች የሥራ ጫና ዝርዝር የንብረት ክፍፍልና ሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮችን ለመከታተል ስለማያስችላቸው በሽማግሌዎች መታገዛቸው ተገቢነት አለው፡፡ ህጉም እንዲህ ማድረግ በሚያስችል መልክ ተቀርጾ ይገኛል፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ግን በዚህ ነጥብ ላይም ቢሆን የሽማግሌዎች ውሳኔ ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ መሆኑ ነው፡፡[129] በአጠቃላይ ሲታይ ግን በተሻሻለው የቤተሰብ ህግም ቢሆን ሽማግሌዎች አወቃቀራቸውና ሚናቸው የተለየ ሆነ እንጂ ጨርሰው እንዲወገዱ ማድረግ ተመራጭ ሆኖ አልተገኘም፡፡ እንዲህ ከተደረገበት ምክንያቶች አንዱ ከፍርድ ቤት ውጪ በአማራጭ ያለመግባባቶች መፍቻ መንገድ (alternative dispute resolution) መጠቀም ለባለጉዳዮቹም ሆነ ለህብረተሰቡና ለመንግስት ጠቃሚ እንደሚሆን በመታመኑ ነው፡፡

### 4.4 የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት

ጋብቻ ፈርሶ የመፍረሱ ውጤት ሲወሰን ከሚነሡት ነጥቦች አንዱ የጋራ ንብረት ክፍፍል ጉዳይ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው ጋብቻ ሲፈፀም ተጋቢዎቹ የንብረት አስተዳደራቸውን በተመለከተ

እንዳይሆን ተደርጓል፡፡ ሆኖም በፍቺው ውጤቶች ላይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ግን የይግባኝ መብት እንደተጠበቀ መሆኑን አብሮ መገንዘብ ይገባል፡፡

[129] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 83(2) እ 83(3)፤ የፍቺ ውጤቶችን የመወሰን ጉዳይ ፍቺ ከመወሰን የበለጠ ሰፋ ያለ ጊዜ የሚፈጅ መሆኑ ይታመናል፡፡ የንብረት ክፍፍል፤ የጋር እዳ አከፋፈል፤ የልጆች አጠባበቅና አስተዳደግ የመሳሰሉት ጉዳዮች ለመወሰን ረዘም ያለ ጊዜ መውሰዱ ስለማይቀር ፍቺው ከተወሰነ በኋላ እስከ ስድስት ወር ጊዜ ሰጥቶ እንዲከናወን የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 83(4) ይፈቅዳል፡፡



የጋብቻ ውል ሲፈራረሙ እንደሚችሉና ይህም በተጋቢዎቹ ላይ የሆነ ያህል አስገዳጅነት እንዳለው ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ጋብቻው ፈርሶ የንብረት ክፍፍል ሲደረግም የጋብቻ ውሉ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ ምናልባትም ጋብቻው ሲፈፀም የተደረገ የጋብቻ ውል ካልነበረ ወይም ውሉ በህግ የማይፀና ሆኖ ከተገኘ በፍቺው ወቅትም ቢሆን የጋራ ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ ተጋቢዎቹ ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡[130] በርግጥ በፍቺ ወቅት የሚደረገው የዚህ ዓይነት ስምምነት በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 83(3) እንደተመለከተው ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ እንደሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

ይህ ዓይነት ቅድመ ዝግጅት ወይም ስምምነት በሌለበት ሁኔታ በተጋቢዎቹ እጅ ያሉ ንብረቶች ሁሉ የጋራ ንብረት እንደሆኑ ይቆጠራሉ የሚል ግምት ስላለ እያንዳንዱ ተጋቢ ይህ ንብረት የግሌ እንጂ የጋራ ንብረታችን አልነበረም፤ አይደለም እያለ የማስረዳት ሸክም ይጣልበታል ማለት ነው፡፡ ይህንን የማስረጃ ግዴታውን የተወጣ ተጋቢ ከጋራ ንብረት ክፍፍሉ በፊት የግል ሃብቱ የሆነውን ንብረት የመውሰድ መብቱ ይጠበቅለታል፡፡[131] የግል

[130] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 83(1)

[131] በፍትሐብሔር ህጉ ውስጥ በፍቺ ንብረት ክፍፍል ወቅት ተጋቢዎቹ የግል ንብረታቸው ቀደመው እንዲወስዱ ሲደረግ "ሚስት የግል ሀብቷን ከባሏ አስቀድማ መውሰድ ይገባታል፡፡" የሚል ድንጋጌ እንደነበር አይዘነጋም (የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 685(2) ይመለከቷል፡፡) ሆኖም የፍትሕ ሚኒስቴር አዘጋጅቶ ለውይይት ባቀረበው የቤተሰብ ህግ ረቂቅ ይህ ለሚስት ተሰጥቶ የነበረው የቅድሚያ መብት እንዲካተት አልተደረገም ነበር፡፡ ላለመካተቱ በወቅቱ የቀረበው ምክንያትም በረቂቁ ህግ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት በጋራ አስተዳደር እንዲመራ የተደረገ ስለሆነ ለሴቷ የተለየ የቅድሚያ መብት መስጠት አይገባም፡፡ ለሴቷ የቅድሚያ መብት

ንብረቱ በዓይነቱ (in kind) ያልተገኘ ይልቁንም ከጋራ ሃብቱ ጋር ስለመቀላቀሉ የተረጋገጠ ሲሆን ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሃብቱ በቅድሚያ እንዲሰጠው ይደረጋል::

ይህ ከተደረገ በኋላ ቀጥሎ የሚወሰደው እርምጃ ከጋራ ሃብቱ ክፍፍል በፊት የጋራ ዕዳዎችን መክፈል ይሆናል:: ለትዳር ጥቅም ሲባል የተገቡ እዳዎች የጋራ እዳዎች መሆናቸው ቀደም ሲል የተገለጸ ስለሆነ ከጋራ ሃብት ክፍፍል በፊት መስተናገድ ያለባቸው ናቸው::

ከተሰጠም ባልና ሚስቱ በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው የሚለውን ህገ-መንግስቱዊ ድንጋጌ የሚፃረር ይሆናል የሚል ነበር::

በሌላ በኩል ሲቀርብ የነበረው የመከራከሪያ ነጥብ ግን ምንም እንኳ በረቂቁ ህግ የጋራ ንብረት አስተዳደር በጋራ እንዲከናወን ቢደነገግም የሴቶች ችግር የህግ ችግር ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ የባህልና የመሳሰሉት ችግሮች የሚጨምር ስለሆነ በህግ ንብረታቸውን እኩል ያስተዳደራሉ መባሉ ብቻ ወዲያውኑ እኩል ስለማያደርጋቸው አሁንም በነገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለሴቶች የተለየ ጥበቃ ያስፈልጋል የሚል ነበር:: በህገ-መንግስቱም ቢሆን ሴቶችን ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ ማድረግ የሚፈቅድ በመሆኑ (ህገ-መንግስት አንቀጽ 35(3)) ህገ መንግስቱን የሚፃረር አይሆንም የሚል ነበር:: ከዚሁ እምነት በመነሣትም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው ረቂቅ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 86(3) ሚስት ከባል በፊት ይህን ዓይነት ንብረት በቅድሚያ የማንሳት መብት ይኖራታል የሚል የነበረ ቢሆንም በመጨረሻው ይህ ንኡስ አንቀጽ አሁን አንቀጽ 86(3) ባለበት መልክ እንዲተረጎም ተደርጓል:: በዚህ መልክ ለመቀረጹ ምናልባት ህግ አውጪው በዚህ ረገድ በፍትህ ሚኒስቴር በኩል የቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ የበለጠ አሳማኝ ነው ብሎ ስለወሰደ ይሆናል የሚል ግምት አለን::



ይህ ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ቀሪው የጋራ ንብረት በመርህ ደረጃ[132] እኩል የሚከፋፈል ይሆናል:: ተመራጩ የንብረት ማከፋፈያ መንገድም ንብረቶቹን በዓይነት ማከፋፈል ነው:: ይህም ሲባል እቃዎቹ ሳይሸጡ ሳይለወጡ ባሉበት ሁኔታ ተጋቢዎች ድርሻቸውን እንዲወስዱ ማስቻል ነው::ይሁን እንጂ በንብረት ክፍፍሉ ወቅት ለያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸውን ንብረቶች እንዲያገኝ ጥረት እንዲደረግ ይጠበቃል[133] ለምሳሌ ልብስ ሰፊ የሆነ አባወራ የቤት እመቤት የሆነች ሚስት የነበረችው ቢሆንና በጋብቻ ወቅት ከተፈራው የጋራ ንብረት አንዱ የልብስ ስፌት መኪና ቢሆን ይህ ትዳር የመፍረስ እድል ቢያጋጥመው በተቻለ መጠን የልብስ ስፌት መኪናው ለልብስ ሰፊው እንድትደርስ ማድረግ ይገባል:: ምክንያቱም የልብስ ስፌት መኪናው ከቤት እመቤትዋ ከሚሰጥ ይልቅ ለልብስ ሰፊው የበለጠ ጠቃሚነት እንዳለው ይገመታል:: በርግጥ ልዩነቱ በገንዘብ ሊካካስ እንደሚገባ መዘንጋት የለበትም:: ስለሆነም የጋራ ንብረቱን በሁለት ላይ ከፍሎ እጣ ከማጣጣል ይልቅ ንብረቶቹ ለያንዳንዱ ተጋቢ ያላቸውን ጠቃሚነት ግምት ውስጥ ያስገባ ክፍፍል ቢደረግ የተሻለ ተቀባይነትና ፍትሐዊነት እንደሚኖር ይታመናል::

በመጨረሻም አንዳንድ ንብረቶች በባህሪያቸው በዓይነት ለማከፋፈል አዳጋች ወይም ከተከፋፈሉ ጠቀሜታቸው እጅግ የሚቀንስ ይሆናል:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ምን ሊደረግ

[132] በመርህ ደረጃ የተባለበት ምክንያት በልዩ ሁኔታ ማለትም በአንቀጽ 84 በተመለከተው ሁኔታ የጋራ ሃብቱን አበላልጦ ማከፋፈል የሚቻልበት እድል ስለሚኖር ነው::

[133] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 91(3)



Generated by CamScanner

ይገባል? የሚለውን ለመወሰን እልፍ እልፍ ችግር ያጋጥማል። ለምሳሌ ባልና ሚስት ቀደም ሲል በጋራ ሀብት የሠሩት 105 ካሬ ሜትር ያረፈ ቤት የነበራቸው ቢሆንና ጋብቻው ከጥቂት ዓመታት ቆይታ በኋላ በፍቺ ቢፈርስ፤ ይህ የጋራ ቤት ምን ይደረግ የሚል ነገር ሊያወዛግብ ይችላል። ይህ በጠባብ ቦታ ያረፈ ቤት ለማከፋፈል አዳጋች ነው። ለማከፋፈል ይቻላል የሚባል ቢሆን እንኳ ሁለት ላይ ከተከፈለ ጠቀሜታው እጅግ ይቀንሳል። በዚህ ወቅት ምናልባት ከጋብቻው የተፈሩ ህፃናት ያሉ ቢሆን ህፃናቱን ይዞ እንዲቆይ የሚወስንለት ተጋቢ በዚህ ቤት ውስጥ የመቆየት እድል ፍርድ ቤት ሊወስንለት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በሽማግሌዎች ይህ ዓይነት ሃሳብ ቀርቦለት ፍርድ ቤቱ ሊያፀድቅ ይችላል። ከዚህ ውጪ ግን የመጀመሪያው እርምጃ በተጋቢዎቹ ስምምነት (እጣ ለማውጣትም ሊስማሙ ይችላሉ) አንዱ ለሌላው የቤቱን ግምት ግማሹን ከፍሎ ቤቱን እንዲያስቀር ማድረግ ነው። በዚህ ዓይነት የመፍትሔ አቅጣጫ መስማማት ካልቻሉ ግን ንብረቱ ለአንዳቸውም ሳይሰጥ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ተሸጦ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ ማድረግ ነው። ንብረቱ መሸጥ ካልቀረ ከዚህ ንብረት በተቻለ መጠን ከፍተኛ ገንዘብ ማግኘት ይችሉ ዘንድ በመሐንዲስ ወይም እንደ ዕቃው ዓይነት በሌላ ገለልተኛ ገማች አካል ግምት ሳይወሰን ንብረቱን በግልጽ በጨረታ እንዲሸጡ መብት ተሰጥቶአቸዋል። ንብረቱን በግልጽ ጨረታ መሸጥ ገበያው ሊሰጠው የሚችል ከፍተኛ ዋጋ ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል።



ምዕራፍ 5. <u>ጋብቻ ስለመፈፀሙ የሚቀርብ ማስረጃ</u>

5.1 <u>የጋብቻ ምስክር ወረቀት</u>

ጋብቻ በጥቅሉ ሲታይ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በግብረ ሥጋ ግንኙነት በቋሚነት አብሮ ለመኖር የሚያደርጉት ስምምነት ሲሆን ከዚህም ግንኙነት በህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ ህጋዊና ማህበራዊ ተቀባይነት ያገኙ በርካታ ውጤቶች ሲከተሉ ቆይተዋል። ከእነዚህም ውስጥ ዘር ማፍራት፤ የጋራ ንብረት መመስረት፤ እርስ በርስ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ግዴታዎች ይገኙበታል። ከዚህም አልፎ ጋብቻ ህጋዊ ወጤት የሚያስከትል የጋብቻ ዝምድናም ይፈጥራል። እነዚህ ጉዳዮች በሰዎች ላይ መብትና ግዴታ ስለሚያስከትሉ ይህ መብትና ግዴታ ይጣል ዘንድ ጋብቻው ስለመኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል። ይህ ሳይረጋገጥ በሰዎች ላይ ከጋብቻ የሚመነጩ ግዴታዎችን መጣሉ አግባብነት አይኖረውም።

በነባሩ ህግ ውስጥ የጋብቻ ማስረጃ አወዛጋቢ ከሚባሉት የቤተሰብ ህግ ክፍሎች ውስጥ አንዱ እንደነበር አይዘነጋም።[134] ነባሩ ህግ "ጋብቻ ለመኖሩ ማስረጃ የሚሆነው ጋብቻው በተፈፀመበት ጊዜ ወይም ጋብቻው ከተፈፀመ በኋላ በህጉ መሠረት የተደረገውን በጽሁፍ የተቋቋመውን የጋብቻ ጽሁፍ በማቅረብ ነው"

[134] የጉዳዩን አወዛጋቢነት በመገንዘብ በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወቅት የነበረው ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጋብቻ ማስረጃ ዙሪያ በፍርድ ቤቱ ዳኞ የቀረበውን ጥናታዊ ጽሁፍ መሠረት በማድረግ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤው በኩል መመሪያ አውጥቶ እንደነበር አይዘነጋም። (ዝርዝር ጥናታዊ ፅሁፉና መመሪያው ህግና ፍትሕ ቅጽ-1-1 ቁጥር 2 ነሐሴ 1981 ይመልከቱ) የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ሲቀረጽ በጋብቻ ማስረጃ ረገድ ከሞላ ጎደል በዚያ ጥናታዊ ጽሁፍ የቀረበውን የመፍትሔ አቅጣጫ በመቀበል ለመቅረጽ ጥረት ተደርጓል።



Generated by CamScanner

ቢልም የጋብቻ ጽሁፍ እንዲያዘጋጅ በህጉ ሃላፊነት የተሰጠው የክብር መዝገብ ጽ/ቤት ሳይቋቋም በመቅረቱ ዋነኛው የጋብቻ ማስረጃ እንዲሆን የታሰበው ሰነድ ሊቀርብ የማይችል መሆኑ ገሃድ ሆነ:: በመሆኑም የጋብቻ መኖርን ለማረጋገጥ በሌሎች ማስረጃዎች መመርኮዝ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ሆነ::

በነባሩ ህግ እንደሁለተኛ የጋብቻ ማስረጃ ተደርጎ የተወሰደው "የባልና የሚስትነት ሁኔታ መኖር" ማስረዳት ነው:: የባልና ሚስትነት ሁኔታ ማለትም "ተጋቢዎቹ ባልና ሚስት ነን እየተባባሉ አብረው የሚኖሩ እንደሆነና ቤተ ዘመዶቻቸውና ሌሎችም ሰዎች በዚሁ ሁኔታ መኖራቸውን ሲያረጋግጡላቸው ነው" ተብሎ በህጉ ትርጓሜ ተሰጥቶታል::[135] ይህም በአራት ምስክሮች የሚረጋገጥና በአራት ምስክሮች ማስተባበል የሚቻል ነበር::[136] ይህ ሁኔታ ሁለት ሰዎች ባልና ሚስት ነን እየተባባሉ መኖራቸው ከታወቀ ጋብቻ ለመኖሩ በቂ ማስረጃ እንደሚሆን የሚያመለክት ሲሆን በሌላ በኩል ግን ሁሉም ባልና ሚስት ነን ብለው ራሳቸውን የሚቆጥሩ ሰዎች ሁሉ በህጉ እምነት ግን ባልና ሚስት ላይሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ ሊታወቅ ይገባል:: አንድ ወንድና አንዲት ሴት ተጋብተውም ሆነ ሳይጋቡ ለመጋባትም ሃሣብ ሳይኖራቸው ባልና ሚስት የሚፈጽሙትን ተግባራት እያከናወኑ ሲኖሩ በሚታዩበት ወቅት በአካባቢያቸው ያለው ሰው የሚወስደው ግምት ባልና ሚስት ናቸው የሚለውን ነው:: ስለሆነም በጋብቻና በጋብቻ ሳይኖር በግብረስጋ ግንኙነት አብሮ መኖር መካከል ያለው

[135] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 699(2)
[136] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 700



ልዩነት ለመገንዘብ አስቸጋሪና የህግ ተርጓሚውን ህሊና የሚፈታተን ጉዳይ ሆነ:: በውጤቱም የአራት ምስክሮችን አመስካከር ብቻ በመቀበል የሚሰጥ ውሳኔ ባልና ሚስት ያልሆኑትን በማጋባት ወይም የተጋቡትን ባልና ሚስት አይደሉም ከሚለው ውሳኔ ላይ ሲያደርስ ታይቷል::

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ሲዘጋጅ ይህ በአሠራር ውዥንብር የፈጠረ የህግ ክፍል የታወቀ ነበርና በተቻለ መጠን የማስረጃ አቀራረቡ ጋብቻንና ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን በሚለይ መልኩ እንዲቀረጽ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል::

በፍትሐብሄሩ ህግ ይህ ምእራፍ "የጋብቻ ማስረጃ" በሚል ርእስ ተቀምጦ የነበረ ሲሆን[137] በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን ይህ ምእራፍ "ጋብቻ ለመፈፀሙ ስለሚቀርብ ማስረጃ" በሚል ተሻሽሎ ቀርቧል:: የህግ አውጪው ሃሳብና ፍላጎት (intention of the legislature) የሚገኘው ከእያንዳንዱ አንቀጽና ንኡስ አንቀጽ ብቻ ሳይሆን ከአዋጁ መግቢያና ከየምእራፎቹ ርእስና አደረጃጀትም ጭምር ነው ከሚል እምነት በመነሣት ለጋብቻ መኖር የሚፈለገውና የሚጠበቀው ማስረጃ "<u>ጋብቻ ለመፈጸሙ</u>" የሚያሳይ ሊሆን እንደሚገባ በምእራፉ ርእስ ላይ ፍንጭ ለማሳየት ተሞክሯል:: በዚህ ብቻም ሳይወሰን የአሁኑ ህግ ተጨማሪ ማስተካከያዎችም ለማከናወን ጥረት አድርጓል::

[137] የፍትህ ሚኒስቴር ባቀረበው ረቂቅ የቤተሰብ ህግም "የጋብቻ ማስረጃ" በሚል ተቀርጾ ነበር



Generated by CamScanner

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ለጋብቻ መኖር ዋናውና ቁልፍ ማስረጃ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ነው። የጋብቻ ምስክር ወረቀት ጋብቻው በተፈፀመበት ዕለትም ሆነ ከዚያ በኋላ በክብር መዝገብ ሹም የሚሰጥ የጋብቻ መፈፀም ማረጋገጫ ሰነድ ነው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው የጋብቻ ምዝገባ መከናወን እንደሚገባ ግዴታ የተጣለ መሆኑን አይተናል፤ ምዝገባውም በክብር መዝገብ ሹም ፊት ለተፈጸሙ ጋብቻዎች ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት ሥርዓትም ሆነ በባህል ሥርዓት ለተፈጸሙ ጋብቻዎች የሚመለከት ነው። መዝጋቢው አካልም ምዝገባ እንዳከናወነ የጋብቻ ምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ግዴታ ያለበት በመሆኑ፤ በየትኛውም ሥርዓት ጋብቻ ቢፈጸምም አንድ ወጥ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይኖራቸዋል ተብሎ ይጠበቃል። በተለይም መዝጋቢው አካል የተጋቢዎቹ መቅረብ ሳይጠበቅ በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ተጋቢዎቹን እያስቀረበ ምዝገባ እንዲያከናውን ሥልጣን ስለተሰጠው የጋብቻ ምስክር ወረቀት የማግኘት እድል ሰፊ ይሆናል የሚል እምነት አለ።[138]

## 5.2 የትዳር ሁኔታ

ይህ ሲባል ግን ሁሉም ጋብቻ የፈፀመ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይኖረዋል ማለት አይደለም። በተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች የጋብቻ ምዝገባ ሳይደረግ ሊቀር፤ የምስክር ወረቀቱም ሊጠፋ፤

[138] የቤተሰብ ህጉ በታወጀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የምዝገባ አዋጅና የምዝገባ ተቋም መደራጀት እንዳለበት በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ አንቀጽ 321(1) የተመለከተ ቢሆንም፤ ይህ ጽሁፍ ሲዘጋጅ ማለት ህጉ በሥራ ላይ ከዋለ ከሁለት ዓመት በኋላም ቢሆን አዋጁም አልወጣም፤ ተቋሙም አልተደራጀም። በመሆኑም በነባሩ ህግ የተፈፀመው ስህተት ተደግሞ እንዳይደገም የሚያስጋ ስለሆነ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ይመስለናል።



ሊቀደድ ወይም ተጋቢዎቹ የምስክር ወረቀቱን ለማቅረብ የማይችሉበት አጥጋቢ ምክንያት ሊያጋጥም ይችላል። ስለሆነም የጋብቻ የምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ በምትክነት የጋብቻ መፈፀም በትዳር ሁኔታ መኖር በማሳየት ማስረዳት የሚቻልበት እድል አለ።

ሆኖም የጋብቻ መፈፀምን ከጋብቻ ምስክር ወረቀት ውጪ በሆነ ማስረጃ ማስረዳት የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ (exception) በመሆኑ በጠባቡ መተርጎም ያለበት ነው። የጋብቻ ምስክር ወረቀት የለኝም ወይም ማቅረብ አልችልም ያለ ሁሉ ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊፈቀድለት አይገባም የጋብቻ ምስክር ወረቀት መያዝ ያልቻለበት ወይም ማቅረብ የማይችልበት ፍርድ ቤቱን ሊያሳምን የሚችል በቂና አሳማኝ ምክንያት ሊያቀርብ ይገባል። ተጋቢዎች የጋብቻ መኖርን ከጋብቻ ምስክር ወረቀት ውጪ በሆነ ማስረጃ በቀላሉ ማስረዳት ከተፈቀደላቸው ጋብቻቸውን ለማስመዝገብና የጋብቻ ምስክር ወረቀት ለመያዝ የሚገፋፋቸው ነገር አይኖርም። ስለሆነም ይህ ዓይነት አሠራር ለቀቅ ያለ ከሆነ ምዝገባን አስመልክቶ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ውጤት አልባ የሚያደርግ ይሆናል። በመሆኑም በዚህ ረገድ ጠበቅ ያለ መመዘኛ ካልተወሰደ የምዝገባ አስገዳጅነትን ብሎም ዋናውን ማስረጃ (የጋብቻ ምስክር ወረቀትን) ፋይዳ ቢስ እንዳያደርገው ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

ሌላው በዚህ ርእስ ሥር መወሳት ያለበት ነጥብ የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ በምትክነት የሚቀርበው ማስረጃ

ምንድን ነው? ሊያስረዳ የሚገባው ጭብጥስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉት ጉዳዮች ማየቱ ጠቃሚ ይመስለናል::

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 95 ሥር እንደተገለጸው የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ የሚቀርበው ማስረጃ "የትዳር ሁኔታ" መኖሩን ማሳየት ሲሆን ይህም ሊያስረዳ የሚገባው ጭብጥ ጋብቻ መፈፀሙን መሆን እንደሚኖርበት ተመልክቷል:: ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልባቸው ሥርዓቶች ቀደም ባሉት ምእራፎች አይተናል:: ስለሆነም ጋብቻ አለኝ ባዩ ቀደም ሲል የጋብቻ ስርዓት ፈጽመናል ማለት እንዳለበትና እንደባልና ሚስት መኖራቸውን እናውቃለን በሚሉ ምስክሮች አማካይነት ብቻ ከመጠቀም አልፎ በአንድ ወቅት ጋብቻ የተፈፀመ መሆኑን በሚያሳዩ ማስረጃዎች አማካይነት መጠቀም መቻል ይኖርበታል::[139]

በርግጥ ወንድየውና ሴቲቱ ራሳቸውን እንደባልና ሚስት ይቆጥራሉ፤ እኛም እንደባልና ሚስት ተቀብለናቸዋል የሚሉ ምስክሮች ሲቀርቡለት ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የህግ ግምት ሊወስድ እንደሚገባ ተመልክቷል::[140] ሆኖም ይህ የህግ ግምት የማስረዳት ሸክሙን ወደሌላኛው ወገን የማስተላለፍ ውጤት

---

[139] በነባሩ የቤተሰብ ህግም ቢሆን የባልና ሚስትነት ሁኔታ የሚለው ፅንሰ ሃሣብ ተከራካሪዎች ቀደም ሲል ከጋብቻ ማስፈፀሚያ ሥርዓቶች ውስጥ አንዱን በመጠቀም ጋብቻ መፈፀማቸው በሚያሳይ መልኩ ሊቀርብና ሊተረጎም እንደሚገባ የአንዳንድ ዳኞቻችን አቋም እንደነበር የፍርድ ቤት መዛግብት ያስረዳሉ:: (የኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ምርጥ ፍርዶች፤ (ሁለተኛ መጽሐፍ) ገጽ 349 - 351 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋኩልቲ መጋቢት 1992)

[140] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 97(1)



ይኖረዋል እንጂ ሌላኛው ወገን ጋብቻ አለመፈጸሙን ማስረዳት ከቻለ ራሳቸውን እንደባልና ሚስት መቁጠራቸውም ሆነ ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እነርሱን እንደባልና ሚስት መቀበሉ ወይም መቁጠሩ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው መኖራቸውን ከማስረዳት በቀር ጋብቻ በመፈፀሙ ረገድ ህጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን ግንዛቤ ሊያገዘበት ይገባል:: ስለዚህ ጭብጡ ዞሮ ዞሮ ቀደም ሲል ጋብቻ ተፈጸመ ወይስ አልተፈጸመም ከሚል የሚያልፍ አይደለም::

ለማጠቃለል ያህልም በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሠረት የጋብቻ ማስረጃ ሲባል ጋብቻ መፈፀሙን ማስረዳት ማለት ነው:: ጋብቻ ለመፈጸሙ ማስረዳት የሚቻለው ደግሞ (ከጋብቻ ምስክር ወረቀት በመለስ) ወንድየውና ሴቲቱ ከጋብቻ ማስፈፀሚያ ሥርዓቶች ውስጥ አንዱን በመከተል ቀደም ሲል ጋብቻ መፈፀማቸው ማስረዳት መቻል ማለት ነው:: ከዚህ ውጪ ግን አንድ ወንድና አንዲት ሴት እንደባልና ሚስት ራሳቸውን መቁጠራቸውና ማህበረሰቡ እነርሱን እንደባልና ሚስት መቀበሉ ለጋብቻ መኖር እንደበቂ ማስረጃ ከተወሰደ በጋብቻና ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር መካከል ልዩነት ስለማይኖር ህግ አውጪው ልዩነት እንዲኖራው አድርጎ የቀረፃቸው ሁለት የተለያዩ ተቋሞች ማደበላለቅ ይሆናል:: ውጤቱም ህግ ያላወቀው ተጨማሪ የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሥርዓት መፍጠር ይሆናል:: ይህ ደግሞ የህግ አውጪነት ሥራ እንጂ የተርጓሚነት ሥራ አይሆንምና ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ይመስለናል:: በተለይም ከዚህ በታች እንደምናየው ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖር



Generated by CamScanner

በፍትሐብሄር ህጉ ውስጥ ከነበረው ጥበቃ ይልቅ በተሻሻለው የቤተሰብ ህጉ ውስጥ የተሻለ ጥበቃ የተሰጠው ስለሆነ ጋብቻ የላቸውም ቢባልም ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብረው መኖራቸው ስለሚታመንና አሉታው ውጤቱ የድሮውን ያህል የከፋ ስለማይሆን በጋብቻ ማስረጃ ረገድ ጠንከር ያለ መለኪያ ማበጀቱ የሚመረጥ ይመስላል።

## ምእራፍ 6.

## ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር[141]

ይህ ምእራፍ በነባሩ የፍትሐብሄር ህግ "ከጋብቻ ውጪ በግብረስጋ ግንኙነት አብሮ መኖር" ይባል የነበረውን የህጉ ክፍል የሚተካው ነው። ከጋብቻ ውጪ በግብረ ስጋ ግንኙነት አብሮ መኖር የሚለው ሃረግ ግንኙነቱን በትክክል የሚገልጽ እንዳልሆነ ግንዛቤ ተወስዷል። ነባሩን የቤተሰብ ህግ ለማሻሻል የሚረዱ ሃሣቦች ለማሰባሰብ በተካሄዱ ተከታታይ አውደ ጥናቶች ሲንፀባረቁ ከነበሩት ሃሳቦች ለመገንዘብ እንደተቻለው በተለይ በአንዳንድ ተሳታፊዎች በኩል የነበረው ግንዛቤ "ከጋብቻ ውጪ" የሚለው ቃል ጋብቻ ፈጽሞ እያለ ከሌላ ሴት ጋር በግብረ ስጋ ግንኙነት አብሮ የሚኖር በሚል እየተተረጎመ ይህ ዓይነት ግንኙነት የህግ እውቅና ሊሰጠው የሚገ አይገባም። እንዲያውም በወንጀል ሊያስጠይቅ ይገባል የሚሉ ሃሣቦች ሲሰነዘሩ ነበር። ይህ ዓይነት ውዥንብር ለመቅረፍ ይቻል ዘንድና የተሻለ ገላጭ ይሆናል ተብሎ በመታመኑ በስያሜው ላይ መሰነኛ ማስተካከያ በማድረግ "ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር" በሚል እንዲተረጽ ተደርጓል።

[141] የፍትህ ሚኒስቴር አዘጋጅቶ ለውይይት ባቀረበው ረቂቅ የቤተሰብ ህግ ውስጥ ይህ ተቋም እንዲካተት አልተደረገም ነበር።



ለነገሩ ችግሩ የስያሜው ብቻ አልነበረም። አንዳንድ ወገኖች ይህ ዓይነቱ ግንኙነት ህገ-መንግስቱ እውቅና የነፈገው በመሆኑ በህግ እውቅና ሊሰጠው አይገባም ቢሰጠውም ህጉ ኢ-ህገመንግስታዊ ይሆናል የሚል አቋም ነበራቸው። ከዚህም አልፎ ለዚህ ዓይነት ግንኙነት የህግ እወቅና መስጠት ሰዎች እንዳይጋቡ መገፋፋት ብሎም የጋብቻን ክቡርነት ዝቅ የሚያደርግ ነው የሚል ክርክርም ቀርቦ ነበር።

በሌላ በኩል ግን ህገ-መንግስት ስለጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ያስቀመጠው ነገር ባይኖርም ግልጽ ክልከላ ግን አላደረገበትም። በዚህ ሁኔታ ደግሞ በመደበኛው ህግ ለዚህ ዓይነት ግንኙነት እውቅና ቢሰጥ ኢ-ህገ-መንግስታዊ አያሰኝ ውም። ዋናው ነገር ደግሞ ህገ መንግስቱ "ቤተሰብ የህብረተሰብ የተፈጥሮ መሰረታዊ መነሻ ነው። ከህብረተሰብና ከመንግስት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው" ይላል። ቤተሰብ ደግሞ በጋብቻ ብቻ የሚገኝ አይደለም። ጋብቻ ሳይኖር ቤተሰብ ይመሠረታል። አንዱ መንገድም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ ወገኖች የሚመሰረት ቤተሰብ ነው። ስለሆነም ለቤተሰብ ከሚሰጥ መንግስታዊ ጥበቃ አንፃር ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር የህግ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው።

ለዚህ ዓይነት ግንኙነት እውቅና መስጠት የጋብቻን ክቡርነት ይቀንሳል ለተባለውም ቢሆን፤ የሚሰጠው እውቅና ከጋብቻ



Generated by CamScanner

ጋር እኩል እስካልሆነ ድረስ ከጋብቻ ጋር ማወዳደር አይቻልም:: የፈለገው ዓይነት እውቅናም ቢሰጠው ሰዎች ከዚህ ዓይነት ግን -ነት ይልቅ ጋብቻን የሚመርጡበት ብዙ ህጋዊ፤ ባህላዊና ሞራላዊ ምክንያቶች እንዳሉ መታወቅ ያለበት ይመስለናል:: በመሆኑም የጋብቻ ክቡርነትን ይቀንሳል የሚለው ክርክርም አሳማኝ አይመስልም::

ጥናቶቹ እንደሚያሳዩት በበለፀጉት አገሮች ማለትም ወንድና ሴት የየራሳቸው አስተማማኝ የገቢ ምንጭ በፈጠሩበት ሁኔታ እንዲህ ዓይነት ግንኙነት ፈጥረው መኖር የተለመደ ነው:: ለመገናኘ ትም ቀላል ለመለያየትም እንዲሁ ቀላል ስለሆነ ብዙዎች ይህን ግንኙነት እንደሚመርጡት ይነገራል::[142] በኢኮኖሚ ረገድ አንዱ ከሌላው የሚጠብቀው ብዙም ነገር ስለማይኖር አንዱ ከሌላው በሚፈልገው ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኩራሉ:: በኛም አገር ቢሆን በከተሞች አካባቢ የሴቶች የራሳቸው ገቢ ባለቤት የመሆን እድል እየሰፋ ሲሄድ፤ በገጠሩም አካባቢ ሴቶች በግላቸው የመሬት ባለይዞታና ተጠቃሚ እየሆኑ ሲመጡ እንዲሁ ዓይነት ግንኙነት ከጋብቻ ይልቅ ተመራጭ አድርገው ሊወስዱት ይችሉ ይሆናል:: ስለዚህ ግንኙነቱን በህግ ለመገዛት የህግ መሠረት እንዲመቻችለት ማድረግ አስፈላጊ ነው::

[142] በበለፀጉት ሃገሮች ይህ ዓይነት ግንኙነት "cohabitation" ወይም "Common law marriage " ወይም "factual marriage" እና ተመሣሣይ አገላለጽ እየተሰጠው እየተስፋፋ በመሄድ ላይ እንደሚገኝ የምርምር ጽሁፎች ያሳዩናል:: ለምሣሌ በካናዳ ከአሥር ጥንዶች አንዱ ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ መሆናቸው ታውቋል::



በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ይህን የተመለከተው ምእራፍ ሲቀረጽ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን አመለካከቶች ተገቢውን ግምት ለመስጠት ጥረት ተደርጓል:: ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ በቀላሉ የማይታዩና የማይቆጠሩ ዜጎች ባሉበት ሃገር ግንኙነቱን ህጋዊ እውቅና መንፈግ ሃቅን ላለማየት አይንን የመጨፈን ያህል ስለሚሆን ግንኙነቱን እውቅና ሊሰጠው አይገባም የሚለው ክርክር ተቀባይነት የሚሰጠው ሆኖ አልተገኘም:: ህጉ እውቅና ሰጠውም አልሰጠው ግንኙነቱ እንደሆነ መቀጠሉ አይቀርም:: በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ግንኙነቱ እየቀጠለ ያለው በህግ በኩል አበረታች ጥበቃ ስለተሰጠው አይደለም:: የራሱ ተጨባጭ መሠረቶች ስላሉት ነው::

ሰዎች ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩት ከጋብቻ ለመሸሽ ነው ተብሎ ብቻ የሚገለጽ አይደለም:: ብዙና የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ:: አንዳንዱ ኢኮኖሚያዊ ነው:: ጋብቻ ለመፈጸም ይብዛም ይነስ ወጪ አለው:: አንዳንድ ወገኖች ለጋብቻ ሊያወጡት የነበረው ወጪ ለትዳራቸው መደጎሚያ ለመጠቀም በማሰብ እንዲሁ ይጠቃለላሉ:: አንዳንዱም ሞራላዊ ነው:: የመጀመሪያ ጋብቻቸው በአንደኛው ተጋቢ ሞት ወይም በፍቺ ምክንያት ሲፈርስባቸው ሌላ ትዳር በጋብቻ ሥርዓት ለማከናወን ባለመፈለግ እንደባልና ሚስት እንዲሁ አብረው ይኖራሉ:: ሌሎችም ዕድሜአችን ከጋብቻ ማስፈፀሚያ እድሜ አልፎብናል "የጋብቻ ስርዓት በኛ እድሜ አያምርም" በሚል ስሜት እንዲሁ አብረው ይኖራሉ:: ብዙዎቹም በጋብቻና ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር መካከል ህግ የፈጠረው ልዩነት



Generated by CamScanner

እንዳለ ካለመገንዘብ እንዲሁ ይኖራሉ፤ ይወልዳሉ፤ ይከባሉ። ስለዚህ በእንደዚህ ያለ የማህበራዊ ኑሮ አጋጣሚዎች ምክንያት የሚፈጠረው ይህ ዓይነቱ ግንኙነት እውቅና አለመስጠት አግባብም ፍትሐዊም አይሆንም።

ይሁን እንጂ ግንኙነቱ የጋብቻ ያህል እውቅናና ጥበቃ ከተሰጠው የራሱ ችግር እንደሚኖረው ይታመናል። ምክንያቱም ጋብቻ መፈጸምና ማስመዝገብ ምንም ዓይነት ህጋዊ ፋይዳ ሳይኖረው ነው። ከዚህም አልፎ ይህ ዓይነቱ ግንኙነት ራሱን የቻለ የጋብቻ ማስፈፀሚያ ስርዓት ሊሆንም ነው ማለት ነው። በመሆኑም ግላዊና የንብረት ግንኙነቱ (personal and pecuniary effect) ጋብቻ ከሚፈጥረው ግላዊና የንብረት ግንኙነት የተለየና ያነሰ እንዲሆን ማድረግ ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ በመነሳትም በህጉ እምነት ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባለና ሚስት አብሮ መኖር ከጋብቻ ጋር ሲነፃፀር ላላ ያለ ግንኙነት ነው። ጋብቻን ለማፍረስ የፍቺ ስምምነት ወይም የፍቺ ጥያቄ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ሲገባ፤ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ግን በማንኛውም ጊዜ ፍርድ ቤትም ጋር መቅረብ ሳያስፈልግ ማቋረጥ ይቻላል። በንብረት በኩልም፤ ጋብቻ ሲሆን ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ የጋራ ንብረት ባለቤትነት የሚፈጥር ሲሆን ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር ሂደት ግን የጋራ ንብረት ባለቤትነት ለመፍጠር ቢያንስ ሦስት ዓመት



ግንኙነቱ ውስጥ መቆየት እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል።[140]

ከዚህም አልፎ በተለያዩ የህግ ዘርፎች ለምሳሌ በጡረታ ህግ በአሠሪና ሠራተኛ የሞት ጉዳት ካሣ፤ ከውል ውጪ በሚደርስ ኃላፊነት የሞት ጉዳት ካሣ መብቱን ለባል ወይም ለሚስት ለይቶ ይሰጣል። ከዚህ ተጠቃሚ ለመሆን ባል ወይም ሚስት መሆንን ማስረዳት ያስፈልጋል ማለት ነው። በመጨረሻም ጋብቻ በወንድየውና በሴትዮዋ የሥጋ ዘመዶች መካከል እንዲሁም በሴትዬዋና በወንድየው የሥጋ ዘመዶች መካከል የጋብቻ ዝምድና የሚፈጥር ሲሆን ይህም ዝምድና ለጋብቻ ክልከላና ቀለብ ለመስጠት ግዴታ መሠረት ሆኖ ያገለግላል። ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ መካከል ግን ለጋብቻ ክልከላ መሠረት ይፈጥራል እንጂ ለወንድየው ወይም ለሴትዬዋ የሥጋ ዘመዶች ቀለብ የመስጠት ግዴታን አያስከትልም። ይህ ሁሉ የሚያሳየው በጋብቻና በጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር መካከል ቀላል የማይባል ህጋዊ ልዩነት እንዳለ ነው።

[140] ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀረበው ረቂቅ ህግ ውስጥ የጋራ ሃብት ለመፍጠር ወንድየውና ሴትዮዋ ቢያንስ ለአምስት ዓመት አብረው የኖሩ ሊሆኑ ይገባል የሚል የነበረ ቢሆንም ህግ አውጪው አምስት ዓመቱን ወደ ሦስት ዓመት ዝቅ አድርጎታል። በአንዳንድ ሃገሮች የጋራ ሃብት ለመፍጠር አብረው የቆዩበት ጊዜ አጭር ቢሆንም ከግንኙነት ውስጥ ልጅ ከተወለደ ግንኙነቱን ቀጣይ ያደርገዋል ተብሎ ስለሚታመን የጋራ ሃብት ለመፍጠር በቂ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። ሆኖም ግንኙነቱ ራሱ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር መሆኑ ሳይረጋገጥ ልጅ ስለተወለደ ብቻ የጋራ ንብረት እንዲፈጠር ማድረግ አላስፈላጊ ውጤት ስለሚኖረው በኛ ደረጃ ተመራጭ አልሆነም። ምክንያቱም ግንኙነቱ ስለመኖሩና ስለቀጣይነቱ ለመወሰን የጊዜ ርዝመት ትልቅ ግምት ሊሰጠው ስለሚገባ ነው።



Generated by CamScanner

በርግጥ ጋብቻና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ተመሳሳይ ህጋዊ ውጤት የሚያስገኙበት ጊዜ አለ:: በጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ አባቱ የሴትዮዋ ባል እንደሆነ የሚገመት ሲሆን ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው እየኖሩ ባሉበት ሁኔታ ልጅ ከተወለደም የልጁ አባት ከሴትዮዋ ጋር በዚህ ግንኙነት የሚገኘው ወንድ እንደሆነ ይገመታል:: ይህ ግን በዋናነት የተወለደውን ልጅ ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል የተደረገ የህግ ግምት እንጂ ግንኙነቱን የጋብቻ ያህል ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው በማሰብ የተደረገ አይመስለንም::

እላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ከጋብቻ ጋር ሲነፃፀር ላላ ያለ ግንኙነት ነው:: በመሆኑም ግንኙነቱንት ለማቋረጥ በተፈለገ ጊዜ በማናቸውም ወገን (በወንድየውም ሆነ በሴትዮዋ በኩል) ሊቋረጥ የሚችል ነው:: በፍትሐብሄር ህጉ ውስጥ የግንኙነቱ መቋረጥ በሴትዮዋ በኩል ምንም ዓይነት ሃላፊነት የማያስከትልባት ሲሆን ግንኙነቱ በወንድየው በኩል ሲቋረጥ ግን "...ርትዕ ሲያስገድድ እጅግ ቢበዛ ለሶስት ወር ለሴትዮዋ ኑሮ የሚበቃ ኪሣራ እንዲከፍል በፍርድ ቤት ሊታዘዝ" እንደሚችል ተደንግጎ ነበር:: ምክንያቱም ግንኙነቱ ሲቋረጥ በነባሩ ህግ የጋራ ንብረት የማይፈጥር ስለነበር ግንኙነቱ ሲቋረጥ በኢኮኖሚው ደካማ አቋም ላይ ትገኛለች ተብሎ የታመነው ሴቲቱን ለመደጎም ታስቦ የተደነገገ እንደሆነ ይገመታል::

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ግን ወንድየውና ሴትዮዋ በዚሁ ግንኙነት ቢያንስ ለሦስት ዓመታት ያህል አብረው ከቆዩ የጋራ



ንብረት ባለቤትነት ስለሚፈጥሩና ግንኙነት ቢቋረጥም ከጋራው ንብረት የየድርሻቸውን ስለሚያገኙ እጅግ ቢበዛ ለሦስት ወር ኑሮ የሚበቃ ለሴትዮዋ የሚሰጥ ድጎማ አስፈላጊ ሆኖ ስላልተገኘ እንዲካተት አልተደረገም:: ከሦስት ዓመት በታች ለቆየ ግንኙነት ግን ግንኙነቱም ራሱ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ስለመሆኑም አጠያያቂ ስለሚሆን ግንኙነቱንት እንዲቋረጥ ያደረገው ወገን ጥፋት ካልፈፀመ በቀር ለሌላኛው ወገን ካሣ እንዲከፍል አይገደድም:: ግንኙነቱ ማቋረጥ በራሱ ደግሞ ጥፋት ነው ሊባል የሚቻል አይደለም::

ሌላው በዚህ ክፍል ሥር መወሳት ያለበት ነጥብ የማስረጃ ጉዳይ ነው:: በፍትሐብሄር ህጉም ሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሠረት በጋብቻ መኖርና አለመኖር ወይም ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሣ እንደሆነ የመወሰን ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው:: ቀደም ሲል እንደተገለፀው በፍርድ ቤቶች አካባቢ ማስረጃዎችን በመመዘን ረገድ ሁለቱን ተቋሞች የማደበላለቅ ጉዳይ አልፎ አልፎ ይታያል:: በህጉ ረገድ ግን ለጋብቻ መኖር መቅረብ የሚገባው ማስረጃ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ ቀደም ሲል ጋብቻ መፈፀሙን የሚያሳይ ሊሆን ሲገባ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን ለማስረዳት የሚቀርብ ማስረጃ ግን የፍሬ ነገር (fact) ጉዳይ በመሆኑ ግንኙነቱን በማሳየት ብቻ ማስረዳት ይቻላል:: በመሆኑም ለጋብቻ ማስረጃነት ፋይዳ የሌላቸው መረጃዎች ለጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ግን ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ::

ጡ-ኔር ዘ ይለያያል ባል ወይም ሚስት ብሎ ማስመዝገብ ለጋብቻ ማስረጃነት ሳይኖራቸው ቢችልም ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ሰዎች ግን የሚፈለገው ማስረጃ ወንዱና ሴትዮዋ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና በተዘመዶቻቸውና ማህበረሰብ እንደ ተጋ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው የሚገምቷቸው መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ እንዲህ ካለ ሰነዶች በመነሣት የቀበሌው ነዋሪዎች ወይም የእድሩ አባላት ይህንን ግምት የሚወስዱበት ሁኔታ ይኖራል ተብሎ ስለሚገመት አግባብነት ሊኖራቸው ይችላል ማለት ነው::

ፍ አዋጅ አንድ

ምዕራፍ አንድ

## ስለ ጋብቻ አፈጻጸም

### ክፍል 1

### ጠቅላላ

**አንቀጽ 1 ልዩ ልዩ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች**

1. ጋብቻ በአንድ የክብር መዝገብ ሹም ፊት ሊፈጸም ይችላል::
2. በአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ቢኖርም ጋብቻ በተጋቢዎቹ ሃይማኖት ወይም ባህል መሠረት ሊፈፀም ይችላል::

**አንቀጽ 2 በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀም ጋብቻ**

ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድ እና ሴት ጋብቻ ለመፈፀም ተስማምተው በክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ ፈቃዳቸውን ሲገልጹና የክብር መዝገብ ሹሙም ይህንኑ ፈቃዳቸውን ሲቀበል ነው::

**አንቀጽ 3 በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት የሚፈፀም ጋብቻ**

ጋብቻ በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሃይማኖታቸው ወይም ከሁለቱ በአንዳቸው ሃይማኖት መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው::

**አንቀጽ 4 በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈፀም ጋብቻ**

ጋብቻ በባህል ሥርዓት መሠረት ተፈፀመ የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት በሚኖሩበት አካባቢ ባህል ወይም ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው::

**አንቀጽ 5 ከኢትዮጵያ ውጭ ስለሚፈፀም ጋብቻ**

በተፈፀመበት አገር የጋብቻ አፈፃፀም ሕግ ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈፀመ ጋብቻ የሕዝብን ሞራል እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ ሕግ ተቀባይነት ይኖረዋል::

# ክፍል 2

## ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

### አንቀጽ 6 ፈቃድ

የሚፀና ጋብቻ ተፈፀመ የሚባለው ተጋቢዎቹ ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው:

### አንቀጽ 7 ዕድሜ

1. ወንዱም ሆነ ሴቷ አሥራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ መፈፀም አይችሉም::
2. አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከባድ ምክንያት ሲያጋጥም ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ የአንዳቸው ወላጆች ወይም አሳዳሪ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት የፍትሕ ሚኒስትሩ ከመደበኛው የጋብቻ ዕድሜ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጊዜ በመቀነስ እንዲጋቡ ሊፈቅድ ይችላል::

### አንቀጽ 8 የሥጋ ዝምድና

1. በቀጥታ የሥጋ ዘመዳሞች (በወላጆችና በተወላጆች) መካከል ጋብቻ መፈፀም ክልክል ነው::
2. ወደጎን በሚቆጠር የሥጋ ዝምድና አንድ ወንድ ከእህቱ ወይም ከአክስቱ እንዲሁም አንዲት ሴት ከወንድሟ ወይም ከአጎቷ ጋር ጋብቻ መፈፀም የተከለከለ ነው::

### አንቀጽ 9 የጋብቻ ዝምድና

1. በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ጋብቻ መፈጸም ክልክል ነው::
2. ወደ ጎን በሚቆጠር የጋብቻ ዝምድና ባል ከሚስቱ እህት ወይም ሚስት ከባሏ ወንድም ጋር ጋብቻ መፈፀም ክልክል ነው::

### አንቀጽ 10 በሕግ ያልተረጋገጠ ልጅነት

የአንድ ሰው ተወላጅነት በሕግ መሠረት ያልተረጋገጠ ቢሆንም እንኳን በማኅበረሰቡ ዘንድ በተወላጅነት የሚታወቅ ከሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ 8 እና 9 እንደተመለከተው ጋብቻን ለማስከልከል በቂ ነው::

### አንቀጽ 11 በጋብቻ ላይ ጋብቻ

ማንኛውም ሰው አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ ይኸው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ መፈፀም አይችልም::



### አንቀጽ 12 ጋብቻን በእንደራሴ መፈጸም የማይቻል ስለመሆኑ

1. ጋብቻ ሲፈፀም ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻው በሚፈፀምበት ጊዜ በግንባር ተገኝተው ፈቃዳቸውን መስጠት አለባቸው::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከባድ ምክንያት መኖሩን እና በእንደራሴ አማካይነት ጋብቻውን ለመፈፀም የሚፈልገው ተጋቢ ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ የገለፀ መሆኑን የፍትሕ ሚኒስትሩ ሲያረጋግጥ ጋብቻው በእንደራሴ ሊፈፀም ይችላል::

### አንቀጽ 13 መሠረታዊ ስህተት

1. በስህተት በተገኘ ፈቃድ ምክንያት የተፈፀመ ጋብቻ አይፀናም::
2. በስህተት ምክንያት ፈቃድ ተጎደለ የሚባለው ስህተቱ መሠረታዊ ሆኖ ሲገኝ ነው::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለፀው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መሠረታዊ ስህተት እንዳለ ይቆጠራል::

ሀ/ በሚያገባው ሰው ማንነት ላይ በመሳሳቱ ምክንያት አገባዋለሁ ብሎ ያላሰበውን ሰው ያገባ ሲሆን፤

ለ/ የሚያገባው ሰው ሊድን የማይችል ከባድ በሽታ ያለበት መሆኑን ሳያውቅ ያገባው ሲሆን፤

ሐ/ ሌላው ተጋቢ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም የማይችል መሆኑን ባለማወቁ ምክንያት ያገባው ሲሆን፤

መ/ ሌላው ተጋቢ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የመፈፀም ልማድ ያለው መሆኑን ባለማወቅ ምክንያት ያገባው ሲሆን፤

### አንቀጽ 14 በኃይል ሥራ የተገኘ ፈቃድ

1. በኃይል ሥራ በተገኘ ፈቃድ ምክንያት የተፈፀመ ጋብቻ አይፀናም::
2. ፈቃድ በኃይል የተገኘ ነው የሚባለው ፈቃዱን የሰጠው ተጋቢ ራሱን ወይም ከወላጆቹ ወይም ከተወላጆቹ አንዱን ወይም ሌላ ለእርሱ የቅርብ ዘመድ የሆነን ሰው ሊፈፀምበት ከተቃረበ ከባድ አደጋ ለማዳን ሲል ፈቃዱን የሰጠ ሲሆን ነው::

### አንቀጽ 15 በፍርድ ስለተከለከለ ሰው ጋብቻ

1. በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር ጋብቻ መፈፀም አይችልም::
2. ስለዚህ ጉዳይ ለፍርድ ቤት የሚቀርበውን ጥያቄ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ሊያቀርበው ይችላል::



Generated by CamScanner

## አንቀጽ 16 በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ

1. አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ካላለፈ በስተቀር እንደገና ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸም አትችልም
2. በዚህአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ሴቲቱ አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ሳይሞላ
   - ሀ/ የወለደች እንደሆነ ወይም
   - ለ/ ጋብቻ የምትፈጽመው ከቀድሞ ባሏ ጋር የሆነ እንደሆነ ወይም
   - ሐ/ እርጉዝ አለመሆኗ በሕክምና የተረጋገጠ እንደሆነ ወይም
   - መ/ በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ እንዳትጠብቅ ፍርድ ቤት የወሰነ እንደሆነ በብቸኝነት ለመኖር ስለተወሰነው ጊዜ የተደነገገው ተፈጻሚ አይሆንም::

### ክፍል 3

### ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወም

## አንቀጽ 17 ስለመቃወም

ጋብቻ ለመፈፀም አስፈላጊ የሆነ ሁኔታ አልተሟላም በማለት ሊፈፀም የታሰበን ጋብቻ እንዳይፈፀም ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል::

## አንቀጽ 18 መቃወም ስለሚችሉ ወገኖች

ጋብቻ እንዳይፈፀም መቃወም የሚችሉት ወገኖች የሚከተሉት ብቻ ናቸው::

- ሀ/ በዕድሜ ምክንያት ሲሆን ወላጆች፣ ዐቃቤ ሕግ ወይም ሌላ ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው
- ለ/ በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ሲሆን የተጋቢዎቹ ወይም የአንደኛው ተጋቢ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፤ 18 ዓመት የሞላቸው ወንድሞች ወይም እህቶች ወይም ዐቃቤ ሕግ፤
- ሐ/ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ሊፈፀም ሲሆን ሌላ ጋብቻ ከሚፈጽመው ሰው ጋር የቀደመ ጋብቻ አለን የሚለው ተጋቢ ወይም ዐቃቤ ሕግ፤
- መ/ በፍርድ መከልከል ምክንያት ሲሆን አሳዳሪው ወይም ዐቃቤ ሕግ፤

## አንቀጽ 19 መቃወሚያ ስለሚቀርብበት ሥርዓትና ጊዜ

1. ጋብቻ እንዳይፈፀም የሚቀርበው መቃወሚያ በጽሑፍ ሆኖ እጅግ ቢዘገይ ጋብቻው ከሚፈፀምበት ከ15 ቀን በፊት ለጋብቻ አስፈጻሚ ባለስልጣን መቅረብ አለበት::



2. ጋብቻ አስፈጻሚ ባለሥልጣን በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የተጋቢዎቹን አስተያየት መቀበል ይኖርበታል::

## አንቀጽ 20 በመቃወሚያ ላይ ስለሚሰጠው ውሳኔ

1. ጋብቻ የሚያስፈጽመው ባለሥልጣን በሚቀርብለት መቃወሚያ ላይ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት::
2. ጋብቻ አስፈፃሚ ባለሥልጣን መቃወሚያውን ባለመቀበል ጋብቻው እንዲፈፀም የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል::
3. ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን መቃወሚያውን የተቀበለው እንደሆነ ጋብቻው እንዳይፈፀም ማድረግ አለበት::
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ውሳኔ የተሰጠ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለውሳኔው ምክንያት ያደረገውን ጉዳይ ተጋቢዎቹ ወዲያውኑ እንዲያውቁት ያደርጋል::

## አንቀጽ 21 ስለይግባኝ

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ሁኔታ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተጋቢዎቹ ወይንም ከተጋቢዎቹ አንዱ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል::
2. ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት የጋብቻ አስፈጻሚውን ባለሥልጣን ውሳኔ የሻረው እንደሆን ባለሥልጣኑ ጋብቻውን ያስፈጽማል::

### ክፍል_4

### በክብር መዝገብ ሹም ፊት ስለሚፈፀም ጋብቻ

## አንቀጽ 22 ሥልጣን ያለው የክብር መዝገብ ሹሙ

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎቹ ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች አንዱ ጋብቻው ከሚፈጸምበት ጊዜ በፊት ቢያንስ ለስድስት ወራት ያህል ሳያቋርጥ በሚኖርበት ቦታ በሚገኘው የክብር መዝገብ ሹም ፊት ይፈጽማል::

## አንቀጽ 23 ጋብቻ ለመፈፀም ጥያቄ ስለማቅረብ እና ስለሚቀርብበት ጊዜ

ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈፀም ማሰባቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን ለመፈፀም ከወሰኑበት ቀን አንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማስታወቅ አለባቸው::

## አንቀጽ 24 ጋብቻ የሚፈፀምበትን ቀን ስለመወሰንና ስለማስታወቅ

የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄው እንዲቀረበለት ከተጋቢዎች ጋር በመነጋገር ከወሰነ በኋላ ጋብቻው የሚፈፀምበትን ቀን በመግለጽ አመቺ በሆነው መንገድ ማስታወቂያ ያወጣል::



Generated by CamScanner

አንቀጽ 25 የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት እና ጋብቻው መፈፀሙን ስለማስታወቅ

1. ጋብቻው ሁለቱ ተጋቢዎች እና ከእያንዳንዱ ተጋቢ በኩል ሁለት ሁለት ምስክሮች በተገኙበት በግልጽ ይፈፀማል::
2. ተጋቢዎቹና ምስክሮቹ ጋብቻ ለመፈፀም አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች አለመጣሳቸውን በቃለ መሐላ ያረጋግጣሉ::
3. ተጋቢዎችና ምስክሮቹ የመሐላ ቃል ከመስጠታቸው በፊት የሚሰጡት ቃል ስለሚያስከትለው ኃላፊነት የክብር መዝገቡ ሹሙ በግልጽ ማስረዳት አለበት::
4. ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈፀም መፍቀዳቸውን ለክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ያረጋግጣሉ::
5. ሁለቱም ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በክብር መዝገቡ ላይ መፈረም አለባቸው::
6. ከዚህ በላይ የተገለጹት ሥርዓቶች የተፈፀሙ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹ በሕጋዊ ጋብቻ የተሳሰሩ መሆናቸውን አስታውቆ ለተጋቢዎቹ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል::

## ክፍል 5

### ሌሎች የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች

**አንቀጽ 26 በሃይማኖት ሥርዓት የሚፈፀም ጋብቻ**

1. በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት እንደሃይማኖቱ ይወሰናል::
2. በዚህ ሕግ ለማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም መሟላት አለባቸው የተባሉት ሁኔታዎች በሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ለሚፈፀም ጋብቻም መሟላት አለባቸው::

**አንቀጽ 27 በባህል ሥርዓት ስለሚፈፀም ጋብቻ**

1. በባሕል ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈፀም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት በአካባቢው ባሕል ይወሰናል::
2. በዚህ ሕግ ለጋብቻ አፈፃፀም መሟላት አለባቸው የተባሉት ሁኔታዎች በባህል ሥርዓት ለሚፈፀም ጋብቻም መሟላት አለባቸው::

## ክፍል 6

### ስለ ጋብቻ ምዝገባ

**አንቀጽ 28 ጋብቻን ስለማስመዝገብ**

1. ጋብቻው የተፈፀመው በማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት



ቢሆንም አግባብ ባለው የክብር ሹም መመዝገብ አለበት::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ምዝገባውን ያከናወነ የክብር መዝገብ ሹም ለተጋቢዎቹ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ይሰጣል::
3. ማንኛውም ጋብቻ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ውጤት ይኖረዋል::

**አንቀጽ 29 የጋብቻ መዝገብ ስለማደራጀት**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተጋቢዎች ጋብቻውን ያላስመዘገቡ ቢሆንም እንኳን የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻ መፈፀሙን ያወቀ እንደሆነ የጋብቻ መዝገብ በሥልጣኑ ያደራጃል::
2. ይህ በሚሆንበት ጊዜ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹና እንደ ነገሩ ሁኔታ ምስክሮች ቀርበው በጋብቻው መዝገብ ላይ እንዲፈርሙ ያደርጋል::

**አንቀጽ 30 የጋብቻ መዝገብ ይዘት**

የጋብቻ መዝገብ የሚመለከተው

ሀ) የተጋቢዎችን ሙሉ ስም የተወለዱበትን ቀንና ቦታ የመኖሪያ አድራሻቸውን
ለ) የምስክሮችን ሙሉ ስም የተወለዱበትን ቀንና ቦታ የመኖሪያ አድራሻቸውን፤
ሐ) ጋብቻው የተፈፀመበትን ሥርዓት ቀንና ቦታ እንዲሁም የተመዘገበበትን ቀን ይሆናል::

## ምዕራፍ ሁለት

### የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት

**አንቀጽ 31 የእድሜ ሁኔታ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እድሜአቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች በሆኑ ሰዎች መካከል የተፈፀመ ጋብቻ በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲፈርስ ይደረጋል::
2. ሕጉ የሚጠይቀው የጋብቻ ዕድሜ ከተሟላ በኋላ ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም::

**አንቀጽ 32 የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና**

በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ጋብቻ እንዳይፈጸም የተደነገገው ክልከላ በመተላለፍ የተፈፀመ ጋብቻ በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲፈርስ ይደረጋል::



Generated by CamScanner

## አንቀጽ 33 በጋብቻ ላይ ጋብቻ

1. በጋብቻ ላይ ሌላ ጋብቻ ተፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ በመጀመሪያው ወይም በሁለተኛው ተጋቢ ወይም በዐቃቢ ሕግ ጥያቄ የኋለኛው ጋብቻ እንዲፈርስ ይደረጋል::
2. ሆኖም የመጀመሪያው ተጋቢ የሞተ እንደሆነ የኋለኛው ጋብቻ እንዲፈርስ መጠየቅ አይቻልም::

## አንቀጽ 34 በፍርድ ክልከላ ምክንያት ጋብቻን ስለማፍረስ

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍርድ ቤት ሳይፈቀድ ጋብቻ ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ጋብቻውን እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል::
2. የተከለከለው ሰው ጋብቻውን እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ክልከላው ከቀረበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር ካለፈ በኋላ ሊቀርብ አይችልም::
3. ጋብቻውን እንዲፈርስ በአሳዳሪው የሚቀርበው ጥያቄ ጋብቻው መፈፀሙን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ከቀረ ሊቀርብ አይችልም::

## አንቀጽ 35 በኃይል ተግባር የተፈፀመ ጋብቻን ስለማፍረስ

1. ማንኛውም ሰው ተገዶ ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል::
2. ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ የኃይል ሥራው ከቀረበት ከስድስት ወር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም::

## አንቀጽ 36 በስህተት ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻን ስለማፍረስ

1. ማንኛውም ሰው ከመሠረታዊ ስህተት በመነሳት ጋብቻ የፈፀመ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል::
2. ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ መሳሳቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም::

## አንቀጽ 37 በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ ስላለመጠበቅ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 16 ንዑስ (1) የተመለከተው በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነው ጊዜ አልተከበረም በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም::



## አንቀጽ 38 የክብር መዝገብ ሹም ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ

የክብር መዝገብ ሹሙ በአንቀጽ 22 ጋብቻውን ያስፈፀመው የክብር መዝገብ ሹሙ በአንቀጽ 22 መሠረት ሥልጣን አልነበረውም በማለት ብቻ ጋብቻው እንዲፈርስ ለመወሰን አይቻልም::

## አንቀጽ 39 የሥነ ሥርዓት አለመጠበቅ

በዚህ ሕግ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (6) የተመለከቱት ሥርዓቶች አልተጠበቁም በማለት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ሊወሰን አይችልም::

## ምዕራፍ ሦስት

## የጋብቻ ውጤት

## ክፍል 1

## ጠቅላላ

## አንቀጽ 40 ሁሉም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ

1. በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት የተፈጸመ ጋብቻ ተመሳሳይ ህጋዊ ውጤት ይኖረዋል::
2. በዚህ ረገድ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ወይም በሃይማኖት ወይም በባህል በታዘዙት ሥርዓቶች መሠረት የተፈፀመም ቢሆን ልዩነት አይደረግበትም::

## አንቀጽ 41 የፍላቢ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም

የፍላቢ ሥጋ ግንኙነት በሰውነት መፈጸሙ ወይም ተፈጽሟል ተብሎ መገመቱ ጋብቻው ለሚያስከትለው ውጤት አስፈላጊ አይደለም::

## አንቀጽ 42 (1) የጋብቻ ውል

1. ተጋቢዎች ጋብቻቸው ንብረታቸውን በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት ጋብቻቸውን ከመፈፀማቸው በፊት ወይም እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸው በሚፈፀምበት ዕለት በውል መወሰን ይችላሉ::
2. እንዲሁም ግላዊ ግንኙነታቸውን በሚመለከት የሚኖሯቸውን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ውል መወሰን ይችላሉ::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ተጋቢዎች የሚያደርጓቸው ውሎች አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሊሆኑ አይችሉም::



Generated by CamScanner

## አንቀጽ 43 (2) የተጋቢዎቹ ችሎታ ማጣት

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው የሚያደርገውን የጋብቻ ውል እርሱ ራሱ ካልፈፀመውና ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም::
2. በሕግ የተከለከለ ሰው የጋብቻ ውል መዋዋልን በተመለከተ ችሎታ እንዳለው ይቆጠራል::

## አንቀጽ 44 (3) የተጋቢዎቹ ችሎታ ማጣት

የጋብቻ ውል በጽሑፍ ካልተደረገና አራት ምስክሮች ሁለት በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ካልሆነ በስተቀር ውጤት አይኖረውም::

## አንቀጽ 45 (4) የ ውሉ ሰነድ ስለሚቀመጥበት

1. የጋብቻ ውሉ አንድ ቅጅ በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል::
2. ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ለማየት በፈለጉ ጊዜ እንዲሁም በፍርድ ቤት ወይም ከተጋቢዎቹ በአንዱ የተፈቀደላቸው ሰዎች የውሉን ሰነድ ለማየት ይችላሉ::

## አንቀጽ 46 (5) ውል ለመዋዋል ስላለው የነፃነት ወሰን

1. ተጋቢዎች በጋብቻቸው ውል ውስጥ በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታ የሚያስከትሉ ስምምነቶችን ማድረግ አይችሉም::
2. እንዲሁም ተጋቢዎቹ ባሕልን ወይም ሃይማኖትን ወይም የአንድን አገር ሕግ በጥቅሉ በመጥቀስ ብቻ ተስማምተናል በማለት የሚያደርጉት የጋብቻ ውል ውጤት አይኖረውም::

## አንቀጽ 47 (6) የጋብቻ ውልን ስለማሻሻል

1. የጋብቻ ውል እንዲሻሻል የቤተሰቡ ጥቅም የሚጠይቅ ሲሆንና ተጋቢዎቹ ሲስማሙ ውሉን በማሻሻል ፍርድ ቤት እንዲያፀድቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ::
2. ፍርድ ቤት በተጋቢዎቹ ተሻሽሎ የቀረበው የጋብቻ ውል የቤተሰቡን ጥቅም የማይጎዳ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተሻሻለውን ውል ተቀብሎ ያፀድቃል::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ወይም ውሉን ያፀደቀው እንደሆነ የተሻሻለው ውል በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል::



## አንቀጽ 48 (7) የሕግ ተፈፃሚነት

የጋብቻ ውል በሌለ ጊዜ ወይም የጋብቻ ውል ቢኖርም በሕግ የጋብቻ ውል ሳይፀና የቀረ እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ::

## ክፍል 2

## ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት

## አንቀጽ 49 መከባበር መተጋገዝ መደጋገፍ

1. ባልና ሚስት እርስበርሳቸው መከባበር አለባቸው::
2. በጋብቻው ውል ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም::

## አንቀጽ 50 የቤተሰብ የጋራ አመራር (1) ጠቅላላ

1. በቤተሰብ አመራር ረገድ ባልና ሚስት እኩል መብት አላቸው::
2. ባልና ሚስቱ በማናቸውም ረገድ የቤተሰቡን ደህንነት ጥቅም ለማስጠበቅ ልጆቻቸውን በመልካም ሰነምግባር እንዲታነፁ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ መተባበር አለባቸው::

## አንቀጽ 51 (2) ከታጋቢዎቹ አንዱ ቤተሰቡን ለመምራት ስላለመቻሉ

1. ከባልና ከሚስት አንደኛው ችሎታ ያጣ የጠፋ ወይም ቤተሰቡን ጥሎ የሔደ ወይም ከመኖሪያ ሥፍራው በመራቁም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት ፈቃዱን ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ በሚገኝበት ጊዜ በአንቀጽ 50 የተመለከተውን የቤተሰብ አመራር አንደኛው ተጋቢ ብቻውን ይፈጽማል::
2. ባልና ሚስት በጋብቻ ውላቸው ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም::

## አንቀጽ 52 ከጋብቻ በፊት ከሌላ ስለተወለዱ ልጆች

1. ከባልና ሚስቱ አንዱ ከጋብቻው በፊት ከሌላ የወለዳቸውን ልጆች መልካም አስተዳደግ በሚመለከት በራሱ አሳብና መሪነት የፈቀደውን ውሳኔ ለማድረግ ሙሉ መብት ይኖረዋል::
2. ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም::

## አንቀጽ 53 አብሮ መኖር

1. ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ይገደዳሉ::



Generated by CamScanner

2. ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስት ከጋብቻ የሚጠበቀውን መደበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አለባቸው።
3. ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም።

## አንቀጽ 54 የመኖሪያ ሥፍራን ስለመወሰን

ባልና ሚስት የሚኖሩበት ሥፍራ በጋራ ይወስናሉ።

## አንቀጽ 55 በስምምነት ተለያይቶ ስለመኖር

1. በዚህ ሕግ በአንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ባልና ሚስቱ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር መስማማት ይችላሉ።
2. ስለዚህ ጉዳይ የተደነገገውን ስምምነት መስጠጥ የማይገባ ካልሆነ በስተቀር ከሁለቱ ተጋቢዎች አንደኛው አስቦ ሊሰርዘው ይችላል።

## አንቀጽ 56 የመተማመን ግዴታ

ባል ለሚስቱ ሚስት ለባልዋ ታማኝ የመሆን ግዴታ አለባቸው።

# ክፍል 3

## ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት

## አንቀጽ 57 የባልና ሚስት የግል ሀብት (1) ያለግብይት የተገኙ ንብረቶች

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው ይቀራሉ።

## አንቀጽ 58 (2) በግብይት የተገኙ ንብረቶች

1. ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤት ሲያፀድቀው ብቻ ነው።

## አንቀጽ 59 የግል ሀብትን ስለማስተዳደር (1)

1. እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ለማስተዳደርና ገቢውንም ለመቀበል ይችላል።
2. እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ሊያገዘበት ነፃነት አለው።



## አንቀጽ 60 (2) የግል ሀብት አስተዳደርን በጋብቻ ውል ስለመወሰን

1. ባልና ሚስት አንደኛው የሌላውን ተጋቢ የግል ሀብት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት እና እንደአስፈላጊነቱ እንዲያዝበት በጋብቻ ውላቸው ሊወስኑ ይችላሉ።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው አኳኋን ንብረት የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ተጋቢ በሌላኛው ተጋቢ ሲጠየቅ ስለንብረቱ አስተዳደር ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ የመስጠት ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 61 (3) ስለውክልና ሥልጣን

ከተጋቢዎቹ አንዱ የግል ሀብቱን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት ለሌላኛው ተጋቢ ውክልና መስጠት ይችላል።

## አንቀጽ 62 የባልና ሚስት የጋራ ሀብት

1. ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ።
2. በዚህ ሕግ በአንቀጽ 58 ንኡስ አንቀጽ (2) መሠረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በስተቀር ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል።
3. በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ቃል በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር በስጦታ ወይም በኑዛዜ ለተጋቢዎች የተሰጧቸው ንብረቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ።

## አንቀጽ 63 የሕግ ግምት

1. አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል።
2. የግል ንብረት መሆኑን ሦስተኛ ወገኖች የሚያውቁት ወይም ሊያውቁት የሚገባ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ ይኸው ንብረት የግል ነው በማለት በሦስተኛ ወገን ላይ መቃወሚያ አድርገው ሊያቀርቡት አይችሉም።

## አንቀጽ 64 ስለባልና ሚስት ገቢ (1) መደበኛ የገቢ አስተዳደር

1. ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው ገቢያቸውን በየራሳቸው ይቀበላሉ።
2. ባልና ሚስት በየግላቸው የሚያገኙትን ገቢ የግል ወይም የጋራ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ማስቀመጥ ይችላሉ።



Generated by CamScanner

3. ከባልና ከሚስት አንደኛው ሲጠየቅ ሌላኛው ተጋቢ ያገኘውን የገቢ መጠን የማስታወቅ ግዴታ አለበት::

አንቀጽ 65 (2) ልዩ ሁኔታ

1. ከባልና ሚስት አንዱ ገቢውን ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልለት ሥልጣን ለመስጠት ሙሉ ነፃነት አለው::
2. ከባልና ከሚስት በአንደኛው ጠያቂነት የአንደኛውን ገቢ ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልለት ለመቀበሉም ደረሰኝ እንዲሰጥ ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል::
3. በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ከባልና ከሚስት የአንደኛው ገቢ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከበር በፍርድ ቤት ሊታዘዝ ይችላል::

አንቀጽ 66 የጋራ ሀብትን ስለማስተዳደር

1. ከባልና ከሚስት አንዱ የጋራ ሀብታቸውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድር ግልጽ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ባልና ሚስቱ የጋራ ሀብታቸውን ያስተዳድራሉ::
2. ከባልና ከሚስት አንዱ ችሎታ የለውም ተብሎ ሲወሰን ወይም ንብረት የማስተዳደር መብቱን ሲገፈፍ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የጋራ ሀብታቸውን ለማስተዳደር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ሌላኛው ተጋቢ የጋራ ሀብቱን የማስተዳደሩን ተግባር ያከናውናል::

አንቀጽ 67 የማስታወቅ ግዴታ

ከተጋቢዎቹ አንዱ ብቻ የጋራ ሀብታቸውን በሚያስተዳድርበት ጊዜ የሀብቱን አስተዳደር በተመለከተ ለሌላኛው ተጋቢ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት::

አንቀጽ 68 (1) የተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ

በሌላ ሕግ የተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ነው::

ሀ) የጋራ የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ለመለወጥ ለማከራየት በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ መብት በማናቸውም ሁኔታ በዚሁ ንብረት ላይ ሌሎች ሰዎች መብት እንዲያገኙ ለማድረግ፤

ለ) ዋጋቸው ከብር 500 (አምስት መቶ) በላይ የሆኑ የሚንቀሳቀሱ የጋራ ንብረቶችን ወይም የገንዘብ ሰነዶች ለመሸጥ ለመለወጥ በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ለማስተላለፍ፤

ሐ) ከብር 100 (አንድ መቶ) በላይ ዋጋ ያለውን የጋራ ንብረት ወይም ገንዘብ ለሌላ ሰው በስጦታ ለማስተላለፍ፤



[illegible] ከብር 500 (አምስት መቶ) በላይ ሲበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሰው ዋስ ለመሆን::

አንቀጽ 69 (2) የስምምነት አለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤት

[illegible] ተጋቢ ከዚሁ በላይ የተመለከተውን ድንጋጌ ባለማክበር የውል [illegible] የተገኘ እንደሆነ ሌላኛው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው [illegible] ግዴታው ሊፈርስ ይችላል::
[illegible] ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው [illegible] ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በሌላ [illegible] ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓምት በኋላ ሊቀርብ [illegible]::

አንቀጽ 70 የባልና የሚስት ዕዳ

[illegible] ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ ዕዳ ከባለዕዳው ተጋቢ የግል ሃብት [illegible] ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሀብታቸው [illegible]::
[illegible] የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ከሆነ ከጋራ ሀብታቸው የጋራ [illegible] ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከባል ወይም ከሚስት [illegible] ሀብት ይከፈላል::

አንቀጽ 71 ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠር ዕዳ

[illegible] ዕዳዎች ለትዳር ጥቅም እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ናቸው፤
[illegible] ለባልና ለሚስት እንዲሁም ለልጆቻቸው የዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት የተገቡ ዕዳዎች፤
[illegible] ባል ወይም ሚስት ቀለብ ለመስጠት ያለባቸውን ግዴታ ለመወጣት የተደረጉ ወጪዎች፤
[illegible] ባልና ከሚስት በአንደኛው ወይም በዕዳ ጠያቂው አመልካችነት ለትዳር ጥቅም ስለመሆኑ ፍርድ ቤት የተቀበለው ሌላ ዕዳ::

አንቀጽ 72 የትዳር ወጪዎችን ስለመሸፈን

[illegible] የትዳራቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው [illegible] ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው::

አንቀጽ 73 በተጋቢዎች መካከል ስለሚደረጉ ውሎች

[illegible] ሚስት ተጋብተው በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው [illegible] ውሎች ፍርድ ቤት ካላፀደቃቸው በስተቀር ውጤት [illegible]::



Generated by CamScanner

## ምዕራፍ አራት

## ስለጋብቻ መፍረስ

**አንቀጽ 74 በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የተቋቋሙ ጋብቻዎች እኩል ስለመሆናቸው**

1. ጋብቻው የተፈጸመበት ሥርዓት ማናቸውም ዓይነት ቢሆን የጋብቻው መፍረስና የሚያስከትለው ውጤት አንድ ዓይነት ነው::
2. ጋብቻው የተፈፀመው በማናቸውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ቢሆንም የጋብቻውን መፍረስ በተመለከተ ማናቸውም ልዩነት አይደረግም::

**አንቀጽ 75 ጋብቻ ስለሚፈርስባቸው ምክንያቶች**

ጋብቻ የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፤

ሀ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥ ወይም

ለ) ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በሕግ መሠረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን ወይም

ሐ) የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ

**አንቀጽ 76 ፍቺ ስለሚወሰንበት ሁኔታ**

ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚችለው፤

ሀ) ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑና ይህንኑ ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም

ለ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ተጋቢዎች በአንድነት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው::

## ክፍል 1

## በስምምነት ስለመፋታት

**አንቀጽ 77 በስምምነት ለመፋታት ስለሚቀርብ ጥያቄ**

1. ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት የወሰኑ እንደሆነ የፍቺ ስምምነታቸውንና ፍቺው የሚያስከትለውን ውጤት በጽሑፍ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍቺው እንዲጸድቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተመለከተው ቢኖርም ተጋብተው ስድስት ወር ያልሞላቸው ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት አይፈቀድላቸውም::
3. ባልና ሚስት ለፍርድ ቤት በሚያቀርቡት የፍቺ ስምምነት ላይ ለመፋታት የወሰኑበትን ምክንያት እንዲገልጹ አይገደዱም::

**አንቀጽ 78 የፍርድ ቤት ሥልጣን**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ድንጋጌ መሠረትየመፋታትጥያቄ ሲቀርብ ለትፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠል ወይም በአንድ ላይ በማስቀረብ ስለጥያቄያቸው ያነጋግራቸዋል፤ እንዲሁም የመፋታት ሀሳባቸውን እንዲለውጡ ይጠይቃቸዋል::
2. ባልና ሚስት የመፋታት ሀሣባቸውን የማይለውጡ መሆኑን የገለጹ እንደሆነ ፍርድ ቤት እንደነገሩ ሁኔታ ከሶስት ወር የማይበልጥ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል::

**አንቀጽ 79 ጉዳዩን እንደገና ስለማንቀሳቀስ**

1. ባልና ሚስቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የማሰላሰያ ጊዜ ቢሰጣቸውም እንኳን በመፋታት ሃሳባቸው የፀኑ እንደሆነ የተሰጣቸው የማሰላሰያ ጊዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጉዳያቸውን እንደገና በማንቀሳቀስ የፍቺ ስምምነታቸውን እንዲያፀድቅላቸው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የስድስት ወር የጊዜ ገደብ ቢኖርም ባልና ሚስቱ አዲስ የፍቺ ስምምነት ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይሆንም::

**አንቀጽ 80 የፍቺ ስምምነቱን ስለማጽደቅ**

1. ፍርድ ቤቱ የፍቺ ስምምነቱን የሚያፀድቀው የባልና ሚስቱ ትክክለኛ ፍላጎት መሆኑን እና ባልና ሚስቱ ፈቃዳቸውን በነፃ የሰጡ መሆኑን እንዲሁም ስምምነቱ ከሕግና ሞራል ጋር የማይቃረን መሆኑን ሲያምን ብቻ ነው::
2. ፍርድ ቤቱ የፍቺውን ስምምነት ያፀደቀው እንደሆነ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉትንም ስምምነት አብሮ ያፀድቃል::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ቢኖርም ባልና ሚስቱ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉት ስምምነት የልጆቻቸውን ደህንነትና ጥቅም በበቂ ሁኔታ የማያስጠብቅ ወይም የአንደኛውን ተጋቢ ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ካገኘው ፍርድ ቤቱ የፍቺው ስምምነት ብቻ በማጽደቅ የፍቺውን ውጤት በተመለከተ ጉድለቶቹ እንዲስተካከሉ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሳኔ ይሰጣል::





Generated by CamScanner

## 1. ክፍል 2
## ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ

### አንቀጽ 81 (1) የፍቺ ጥያቄ ስለማቅረብ

1. ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ::
2. ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍቺ ለመጠየቅ ምክንያት የሆናቸው ጉዳይ መግለጽ ይችላሉ::

### አንቀጽ 82 (2) የፍርድ ቤት ሥልጣን

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 81 መሠረት ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠልም ሆነ በአንድነት በማነጋገር የፍቺው ጥያቄ የሚቀርበትንና አለመግባባቱን በስምምነት ለመፍታት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲችሉ ያግባባቸዋል::
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ሞክሮ ውጤት ያላገኘ እንደሆነ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ውጤት የማያገኝ መስሎ የታየው እንደሆነ ባልና ሚስቱ ከፍርድ ቤት ውጭ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ጉዳያቸውን በዕርቅ እንዲጨርሱ ሊጠይቃቸው ይችላል::
3. ባልና ሚስቱ ጉዳያቸውን በሽማግሌ አማካይነት በዕርቅ ለመጨረስ ያልተስማሙ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከሦስት ወር ያልበለጠ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያስናብታቸው ይችላል::
4. ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተገቢውን ሁሉ አድርጎ ጥረቱ ውጤት ያላስገኘ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የእስታራቂ ለተጋቢዎቹ ሽማግሌዎች ሪፖርት ከደረሰው ወይም እንደሁኔታው ለተጋቢዎቹ በአንድ ወር ጊዜ የተወሰነው የማሰላሰያ ጊዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የፍቺ ውሳኔ ይሰጣል::
5. የፍቺ አቤቱታው እንደቀረበ ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩበትና ስለሚኖሩበት ሁኔታ ስለልጆቻቸው አጠባበቅ ስለሚኖሩበት ስፍራና ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ስለንብረታቸው አስተዳደር ተገቢ መስሎ የታየውን ትእዛዝ ይሰጣል::
6. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(5) በተመለከተው መሠረት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሁለቱ ተጋቢዎች የአንዳቸው ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት የግድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ የባሰ ጉዳት የሚደርስበት ወገን የትኛው መሆኑን እንዲሁም የልጆቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ አመቺ የሚሆነውን ሁኔታ ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል::



### አንቀጽ 83 ፍቺ ውጤቶችን ስለመወሰን

1. በዚህ ክፍል መሠረት ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ፍቺው ስለሚያስከትለው ውጤት እንዲስማሙ ባልና ሚስቱን ይጠይቃቸዋል::
2. ባልና ሚስቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት ለመስማማት ያልፈለጉ ወይም ለመስማማት ሞክረው ስምምነት ላይ ለመድረስ ያልቻሉ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም በሽማግሌዎች ወይም ፍርድ ቤቱ በሚሾማቸው ባለሞያዎች አማካይነት ወይም አመቺ መስሎ በሚታየው በማናቸውም ዘዴ የፍቺውን ውጤት ይወስናል::
3. የፍቺው ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማግሌዎች ወይም በባለሞያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሳኔው ተፈጻሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው::
4. ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ውሳኔ እንደሁኔታው ከፍቺ በኋላ ከ6 ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያዘገየው ይችላል::

### አንቀጽ 84 ስለ ካሳ

ከባልና ከሚስት አንዱ ለፍቺው ምክንያት የሆነውን በደል ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ ለፍትህ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሌላው ተጋቢ ላይ ለደረሰ ጉዳት በዳዩ ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ እንዲከፍል ሊወስን ይችላል::

## ምዕራፍ አምስት

## የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት

### አንቀጽ 85 የባልና ሚስትን ሀብት በስምምነት ስለማጣራት

1. በዚህ ሕግ ስለካሣ ክፍያ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጋብቻው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የፈረሰ እንደሆነ ባልና ሚስቱ የጋብቻቸው መፍረስ በንብረት በኩል የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክተው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በጋብቻ ውላቸው መሠረት ይጣራል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የጋብቻ ውል ወይም ስምምነት የሌለ ወይም በሕግ ፊት የማይፀና ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የባልና ሚስት ሀብት በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሠረት ይጣራል::

### አንቀጽ 86 የግል ሀብትን መልሶ ስለመውሰድ

1. ባል ወይም ሚስት የግሉ መሆኑን በማስረዳት የግል ሀብቱ የሆነውን ንብረቱን መልሶ የመውሰድ መብት ይኖረዋል::
2. ከባልና ሚስቱ አንደኛው የግል ሀብቱ የሆነ ማናቸውም ንብረት ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑን ከዚሁ ግብይት የተገኘውን ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ጋር የተቀላቀለ መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ከዚህ ንብረት



Generated by CamScanner

ጋር ተመጣጣኝ የሆን ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሀብታቸው በትድሚያ የማንሳት መብት ይኖረዋል::

3. ባልና ሚስት የየግል ሀብታቸውን የሚያነሱበት ሁኔታ ሲኖር ሁሉቱም በመጨረሻ ከተገኘው የንብረት መጠን እንደየአስተዋጽኦዋቸው ሊደርሳቸው የሚችለውን ያህል የማንሳት መብት ይኖራቸዋል::

አንቀጽ 87 ስለካሳ

1. በዚህ ሕግ መሠረት የጋራ ንብረቱን ወይም የሌላኛውን ተጋቢ ንብረት በብቸኝነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የተሰጠው ተጋቢ ከተሰጠው ሥልጣን ውጪ በፈጸማቸው ድርጊቶች ምክንያት ወይም ከብልሹ አስተዳደር የተነሳ ወይም የካሣ ጠያቂውን መብት በማታለል ድርጊቱ የጎዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በተበዳይ ጥያቄ ሲቀርብለት ተገቢ የጉዳት ካሳ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ የካሳ ጥያቄ ተፈጸመ የተባለው ድርጊት ጋብቻው ከመፍረሱ ከአምስት ዓመት በፊት የሆን እንደሆን ተቀባይነት አይኖረውም::

አንቀጽ 88 ያለአግባብ ስለመበልጸግ

ባልና ሚስት ተቃራኒ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር ከባልና ሚስት የአንደኛው የግል ሀብት ከሆን ንብረት የሌላኛው የግል ሀብት ወይም የጋራ ሀብታቸው ያለአግባብ መበልጸጉን ያስረዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ካሣ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል::

አንቀጽ 89 የዕዳ ጠያቂዎችን መብት ስለማክበር

ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ በፍርድ የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም የመኑት ዕዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆን ይኸው ዕዳ የባልና ሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል ይሆናል::

አንቀጽ 90 (1) የጋራ ሀብት ስለመከፋፈል

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን የባልና ሚስት ሀብትን በስምምነት ስለማከፋፈል የተደነገገት እንደተጠበቁ ሆነው የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ይሆናል::



አንቀጽ 91 የባልና ሚስት ሀብት በዓይነት የሚከፋፈል ስለመሆኑ

1. በመሠረቱ እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ የጋራ ሀብቱ በዓይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው አኳኋን እኩል ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆን ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ ይደረጋል::
3. የሀብት ክፍፍሉ በሚደረግበት ጊዜ እያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸውን ንብረቶች እንዲያገኝ ለማድረግ ጥረት መደረግ ይኖርበታል::

አንቀጽ 92 ለማከፋፈል አዳጋች ስለሆኑ ንብረቶች

1. ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆንና ባልና ሚስቱን ንብረቱ ከሁለቱ ለአንዳቸው እንዲሰጥ ለማስማማት ሳይቻል የቀረ እንደሆን ንብረቱ ተሸጦ የተገኘ ውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ ይደረጋል::
2. ስለአሻሻጡ ሁኔታ ባልና ሚስቱ ሳይስማሙ ቀርተው አንደኛው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆን ሽያጩ የሚደረገው በጨረታ ይሆናል::

አንቀጽ 93 ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ከባልና ሚስት ስለሚጠየቅ ዕዳ

1. ጋብቻው ከፈረሰና የባልና ሚስት ሀብት ከተከፋፈለ በኋላ የሚጠየቅ ዕዳ በጋራ መከፈል የነበረበት በሆን ጊዜ ስለዕዳው እስኪፈል ሁለቱም በደርሻቸው መጠን ተጠያቂ ይሆናል::
2. ዕዳው የሚመለከተው አንደኛውን ተጋቢ በሆን ጊዜ የዕዳው ክፍያ ሊጠየቅ የሚችለው ባለዕዳ ከሆነው ተጋቢ ብቻ ይሆናል::

## ምዕራፍ ስድስት

### ጋብቻ ስመፈፀሙ ስለሚቀርብ ማስረጃ

አንቀጽ 94 የጋብቻ ምስክር ወረቀት

ጋብቻ መፈፀሙን ለማስረዳት የሚቻለው ጋብቻው በተፈፀመበት ዕለት ወይም ከዚያ በኋላ በሕጉ መሠረት ተዘጋጅቶ የተሰጠውን የጋብቻ የምስክር ወረቀት በማቅረብ ነው::

አንቀጽ 95 የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ

የጋብቻ ምዝገባ ሳይደረግ የቀረ ወይም መዝገቡ በመጥፋቱ ምክንያት ጋብቻ መፈፀሙን በጋብቻ ምስክር ወረቀት ለማስረዳት ያልተቻለ እንደሆነ ጋብቻ ለመፈፀሙ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል::



Generated by CamScanner

## አንቀጽ 96 የትዳር ሁኔታ መኖር (1) ትርጓሜ

አንድ ወንድና አንዲት ሴት የትዳር ሁኔታ አላቸው የሚባሉት ራሳቸውን እንደባልና ሚስት የሚቆጥሩና የሚኖሩ ከመሆናቸውም በላይ ቤተዘመዶቻቸውና ማኅበረሰቡ እንደባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሆነው ሲገኙ ነው::

## አንቀጽ 97 ጋብቻ ለመፈፀሙ የትዳር ሁኔታ መኖሩን ስለማስረዳት

1. ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት አንድ ሰው በራሱና ከእራሱ ጋር ጋብቻ አለኝ ከሚለው ወገን ጋር የትዳር ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ግምት ጋብቻው አለመፈፀሙን ማናቸውንም ዓይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ለማፍረስ ይቻላል::

### ምዕራፍ ሰባት

### ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር

## አንቀጽ 98 (1) ትርጓሜ

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ማለት አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሕግ በሚፀና አኳኋን ጋብቻ ሳይፈጽሙ በትዳር መልክ የኖሩ ሲሆን ነው::

## አንቀጽ 99 (2) ማብራሪያ

1. ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ኖሩ ለማለት ወንድየውና ሴትየዋ የሚያሳዩት ሁኔታ በሕግ እንደተጋቡ ሰዎች ዓይነት መሆኑ አስፈላጊና በቂ ነው::
2. ለሶስተኛ ወገኖች እንደተጋቡ ሆነው መቅረብ አስፈላጊ አይደለም
3. አንድ ወንድና አንዲት ሴት በታወቀና በተደጋገም ሁኔታ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀማቸው ብቻ በሁለት መካከል ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት ግንኙነት አላቸው ለማለት በቂ ምክንያት አይደለም::



## አንቀጽ (100) የጋብቻ ዝምድና የማያስከትል ስለመሆኑ

1. ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር በወንድየውና በሴቲቱ የሥጋ ዘመዶች መካከል እንዲሁም በሴትየዋና በወንድየው የሥጋ ዘመዶች መካከል አንዳችም የጋብቻ ዝምድና አያስከትልም::
2. ሆኖም የጋብቻ ዝምድና ባለ ጊዜ ጋብቻን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ባለጊዜም ተፈጻሚ ይሆናሉ::

## አንቀጽ 101 የጋራ ኑሮ ወጪዎችን ስለመሸፈን

ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች የጋራ ኑሮአቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው::

## አንቀጽ 102 ስለ ጋራ ሀብት

1. የንብረት አስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ከሶስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ እያሉ ያፈሩዋቸው ንብረቶች የጋራ ሃብቶቻቸው ይሆናሉ::
2. ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ አብረው በመኖር እያሉ የሚኖርዋቸው ንብረቶች በግንኙነት ውስጥ የተፈሩ ሃብቶች ተደርገው ይቆጠራሉ::
3. ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት የሚገኙቸው ዕዳዎች አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ለጋራ ኑሮአቸው ወይም ከግንኙነቱ የተወለዱ ልጆችን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል የተገቡ እዳዎች ሲሆኑ ለእዳዎቹ አከፋፈል ሁለቱም በአንድነትና በነጠላ ኃላፊዎች ይሆናሉ::

## አንቀጽ (103) የጋራ ንብረት ስለሚያስከትለው ውጤት

በዚህ ሕግ አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት የጋራ ሀብት በሚፈጠርበት ጊዜ ስለንብረቱ አስተዳደር የሶስተኛ ወገን ዕዳ አከፋፈልና ንብረት ማጣራት ሂደት በዚህ ሕግ በጋብቻ ስለሚፈጠር የጋራ ንብረትና የማጣራት ሂደት የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል:: (አንቀጽ 75 - 93)

## አንቀጽ 104 የልጆች መወለድ

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ ወንድና ሴት የተወለዱት ልጆች ተወላጅነታቸው የሚረጋገጠው በዚህ ሕግ ስለመወለድ በተባለው ምዕራፍ ውስጥ በተደነገገው መሠረት ይሆናል::



Generated by CamScanner

### አንቀጽ 105 የግንኙነት መቋረጥ

1. ጋብቻ ሳይፈጸሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት በማንኛውም ጊዜ ግንኙነታቸው እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላሉ።
2. በዚህ ሕግ አንቀጽ 102 ስለጋራ ሀብት የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ያደረገው ወገን ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ካሳ እንዲከፍል አይገደድም።

### አንቀጽ 106 የግንኙነት ማስረጃ

1. ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የግንኙነት ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል።
2. አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ይኖራሉ የሚባለው ምንም እንኳን በሕግ የተጋቡ ባይሆንም የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ሰዎች ናቸው ብለው ሲገምቷቸው ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ሁኔታ መኖሩን እንደኛው ወገን ለማስረዳት የቻለ እንደሆን ፍርድ ቤቱ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ናቸው ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል።
4. ከዚህ በላይ የተመለከተውን የሕግ ግምት ማናቸውንም ዓይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ግንኙነት ያለመኖሩን በማስረዳት መፍረስ ይቻላል።

### አንቀጽ 107 ጋብቻ ሳይፈጸም የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች

1. ከጋብቻ ሥርዓት ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ውጪ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች በሕግ ፊት ምንም ውጤት አይኖራቸውም።
2. በዚህ ሕግ ስለ ጉዲፈቻ ልጅ ወይም ልጅነትን ስለመቀበል የተወሰኑት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከእንደዚህ ያለ ግንኙነት የተወለዱ ልጆች ከእናታቸው በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር ማናቸውም ዓይነት ህጋዊ ግንኙነት አይኖራቸውም።



## ምዕራፍ ስምንት

## በጋብቻ እና ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን

## ክፍል 1

## ጠቅላላ

### አንቀጽ 108 ተፈጻሚነት ስለሚኖረው ሕግ

በዚህ ሕግ የተመለከቱት የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ሕግ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ ክርክሮች የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

### አንቀጽ 109 የባልና ሚስትነት ሃብት ስለማጣራት የተደነገጉት ተፈጻሚ ስለመሆናቸው

1. ጋብቻ የፈረሰው በፍቺ ባይሆንም የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ከዚህ በላይ በምዕራፍ 5 የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።
2. በተለይም ጋብቻው የፈረሰው በሞት በሆነ ጊዜ በሕይወት ባለው ተጋቢ እና በሟች ወራሾች መካከል የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ክርክር የተነሳ እንደሆነ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት በዚህ ህግ በምዕራፍ 5 የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

### አንቀጽ 110 የባልና ሚስት ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታ

ፍርድ ቤት የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል ሊያነጋግር ወይም ጉዳዩን ሊመረምርና ምስክር ሊሰማ በዝግ ያስችላል።

### አንቀጽ 111 ስለ ውሳኔ አሰጣጥ

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍቺ በሚወስንበት ጊዜ የተጋቢዎቹን ወይም የቤተዘመዶቻቸውን መልካም ስም ለመጠበቅ ዝርዝር ጉዳዮች ከመተቸት በመቆጠብ ፍቺውን ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ብቻ በውሳኔው ላይ ሊያሰፍር ይችላል።



Generated by CamScanner

**አንቀጽ 112 ስለ ይግባኝ**

ፍርድ ቤቱ ፍቺ መወሰኑን ብቻ መሠረት በማድረግ ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም።

**አንቀጽ 113 የልጆችን አጠባበቅና አያያዝ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ስለሚሰጠው ውሳኔ**

1. ፍርድ ቤቱ ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወስን ልጆች ከማን ጋር ሊኖሩ እንደሚገባ ስለትምህርታቸው እና ስለጤናቸው አጠባበቅ ስለቀለባቸውና ባጠቃላይ ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ወላጆችና ልጆቻቸው ለመጠየቅ ስላላቸው መብት መወሰን አለበት።
2. ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ የወላጆችን የገቢ የዕድሜ የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የልጆቹን እድሜ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማገናዘብ ይኖርበታል።
3. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ መሠረት ስለልጆች አያያዝና አጠባበቅ የሚሰጠው ውሳኔ የሁኔታዎች መለወጥን ምክንያት በማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል።

**አንቀጽ 114 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር**

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል 2

## ስለ ፍርድ ቤት ሥልጣን

**አንቀጽ 115 የሚጸና ጋብቻ ስለመኖሩ**

ጋብቻ የተፈፀመ ወይም የሚፀና ስለመሆኑ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው።

**አንቀጽ 116 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር**

በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው።



**አንቀጽ 117 ስለፍቺና ፍቺ ውጤቶች**

ፍቺን የመወሰን ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ 83 በተደነገገው መሠረት የፍቺ ውጤቶች በተመለከተ ውሳኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው።

**አንቀጽ 118 በጋብቻ ውስጥ ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶች**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 117 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ባልና ሚስቱ በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ይወሰናሉ።
2. ሽማግሌዎቹ በሚሰጡት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል።
3. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ ሽማግሌዎቹ የሰጡትን ውሳኔ ሊያፀና ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ይችላል። የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

## ክፍል 3

## ስለ ዕርቅ

**አንቀጽ 119 አስታራቂ ሽማግሌዎችን ስለመምረጥ**

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 82(2) መሠረት ባልና ሚስት ጉዳያቸውን በዕርቅ ለመጨረስ በወሰኑ ጊዜ አመቺ ሆኖ በሚያገኙት መንገድ አንድ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሽማግሌዎችን በመምረጥ ሽማግሌ እንዲመርጡ ከተነገራቸው ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ የሽማግሌዎቹን ስም ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት የሽማግሌዎቹ ስም ዝርዝር ሲቀርብለት ወይም ሽማግሌዎቹ እንደተሰየሙ ወዲያውኑ መዝግቦ ዕርቅ የሚከናወንበትን የመፍትሔ አቅጣጫ የሚጠቁም ምክርና መመሪያ በመስጠት ወይም እንዲደርሱበት በማድረግ የዕርቁ ወይም የዕርቁ ሙከራ ውጤት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብለት ያዛል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የዕርቁ ሂደት የደረሰበትን ደረጃ በየጊዜው ለመመርመርና ወቅታዊ ሪፖርት እንዲቀርብለት ማዘዝ ይችላል።

**አንቀጽ 120 ስለተጨማሪ ጊዜ**

ከዕርቅ ሙከራው ሂደት አኳያ ባልና ሚስት ያለመግባባታቸውን በዕርቅ ሊጨርሱ ይችላሉ የሚል ግምት ያለው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 119 በተመለከተው ጊዜ ላይ ተደርቦ ከአንድ



Generated by CamScanner

ወር ላልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት የዕርቅ ሙከራው እንዲቀጥል ሊያዝ ይችላል።

<u>አንቀጽ 121 የባልና ሚስት ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታ</u>

1. አስታራቂ ሽማግሌዎች ባልና ሚስቱ የመፋታት ሃሳባቸውን እንዲተዉና ጉዳያቸውን በመግባባት እንዲጨርሱ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለባቸው።
2. አስታራቂ ሽማግሌዎች ጉዳዩ ከፍቺ በመለስ ሊፈታ እንደማይችል የተረዱ እንደሆነ ተጨማሪ ጊዜ ሳያስፈልጋቸው ስለደረሱበት ውጤት ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።
3. አስታራቂ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ከፍቺ በመለስ በመግባባት ለመፍታት ከመጣር አልፈው ባልና ሚስቱን የሚመለከት ማናቸውንም ትዕዛዝም ሆነ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አይኖራቸውም።

<u>አንቀጽ 122 የሪፖርት አሰማቅረብ</u>

1. በዚህ ሕግ አንቀጽ 119 እና 121 መሠረት አስታራቂዎቹ ሪፖርት ሳያርቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋዋል።
2. መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው ጉዳያቸውን በዕርቅ አለመጨረሳቸውንና ሪፖርቱ በወቅቱ ያልቀረበበትን ምክንያት በመግለጽ ጉዳያቸው እንዲንቀሳቀስላቸው የጠየቁ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥያቄያቸው ተገቢ ሆኖ ካገኘው መዝገቡን በመክፈት በህጉ መሠረት የራሱን ውሳኔ ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጠው መዝገቡን የመዝጋት ውሳኔ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው አዲስ አቤቱታ በማቅረብ ጉዳያቸው እንዲታይላቸው ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይሆንም።



አባሪ - ሁለት

<u>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ</u>

<u>ምዕራፍ 1</u>

<u>ስለ ሥጋና ስለጋብቻ ዝምድና</u>

<u>አንቀጽ 1 የሥጋ ዝምድና</u>

1. የሥጋ ዝምድና ከመወለድ ይገኛል።
2. በወላጆችና በተወላጆች መካከል በቀጥታ መስመር የሚቀጠር የዝምድና መተሳሰር ይኖራል።
3. ካንድ አባት እና እናት በተወለደ ወይም በአንድ ወላጅ ብቻ በሚገናኙ ሰዎች መካከል ወደጎን የሚቆጠር የትውልድ መስመር ነው።

<u>አንቀጽ 2 የሥጋ ዝምድና ደረጃ</u>

1. የሥጋ ዝምድና ደረጃ ሁለት ትውልዶችን የሚያገናኝ የትውልድ ሐረግ ነው።
2. በሁለት ሰዎች መካከል ወደጎን የሚኖር የሥጋ ዝምድና ደረጃ የትውልድ ሐረጎች በመቁጠር ይሆናል።
3. ወደጎን የሚቆጠር የሥጋ ዝምድና ከአምስተኛው ደረጃ በኋላ ጋብቻን በሚመለከት ውጤት አይኖረውም።

<u>አንቀጽ 3 የጋብቻ ዝምድና</u>

1. የጋብቻ ዝምድና ከጋብቻ ይገኛል።
2. ባል ከሚስት ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ታች ከሚቆጠሩ ተወላጆች ጋር ሚስት ከባሏ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደታች ከሚቆጠሩ ተወላጆች ጋር ቀጥታ የሆነ የጋራ ዝምድና አላቸው።
3. ባል ከሚስቱ የጎን ዘመዶች ሚስት ከባሏ የጎን ዘመዶች ጋር ወደጎን የሚቆጠር የጋብቻ ዝምድና አላቸው።
4. ወደጎን የሚቆጠር ጋብቻ ዝምድና ከሦስተኛው ደረጃ በኋላ ውጤት አይኖረውም።

<u>አንቀጽ 4 አጥፍ የጋብቻ ዝምድና</u>

1. ባል ከሚስቱ ወንድም ሚስት፤ ወይም ከሚስቱ እህት ባል፤ ሚስት ከባልዋ ወንድም ሚስት፤ ወይም ከባልዋ እህት ባል፤ ጋራ አጥፍ የሆነ የጋብቻ ዝምድና አላቸው።
2. ይኸው አጥፍ የሆነ የጋብቻ ዝምድና ተራ እንደሆነው የጋብቻ ዝምድና ውጤቶች አሉት።



Generated by CamScanner

አንቀጽ 5 የጋብቻ ዝምድና የማይቀር ስለመሆኑ

ዝምድና ያስገኘው ጋብቻ ቢፈርስ እንኳን በጋብቻው የተገኘው ዝምድና መተሳሰር እንደፀና ይኖራል::

አንቀጽ 6 የቀጥታ ዝምድና በደረጃ ስላለመሆኑ

በቀጥታ መስመር የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና በደረጃ አይወሰንም::

አንቀጽ 7 የጉዲፈቻ ዝምድና

የሥጋና የጋብቻ ዝምድና በዚህ ሕግ በምዕራፍ 9 እንደተደነገገው በጉዲፈቻ ሊመሰረት ይችላል::

ምዕራፍ 2

ስለመተጫጨት

አንቀጽ 8 ትርጓሜ

1. መተጫጨት ማለት እጮኛውና እጮኛይቱ በመካከላቸው ለወደፊቱ ጋብቻ ለመፈጸም የሚያደርጉት ስምምነት ነው::
2. የመተጫጨት ስምምነት በእጮኛውና በእጮኛይቱ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ካልሆነ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም::

አንቀጽ 9 መተጫጨትን የሚከለክል ምክንያት

የእጮኛዎቹን ጋብቻ የሚከለክል ሕጋዊ ምክንያት ያለ እንደሆነ መተጫጨቱ ህጋዊ ውጤት አይኖረውም::

አንቀጽ 10 የመተጫጨት ስርዓት /ፎርም/

የመተጫጨት ሥርዓት መተጫጨቱ በሚደረግበት ቦታ በልማድ ወይም በዕሁፍ ሊፈፀም ይችላል::

አንቀጽ 11 የመተጫጨት ማስረጃ

1. መተጫጨት የተደረገው በፅሁፍ በሆነ ጊዜ የመተጫጨት ስምምነት መኖሩን ማስረዳት የሚቻለው ይህንኑ የፅሁፍ ማስረጃ በማቅረብ ነው::
2. ጽሑፍ በሌለ ጊዜ መተጫጨት መኖሩን ማስረዳት የሚቻለው ሁለት ምስክሮች በማቅረብ ወይም በማናቸውም ገላጭ ማስረጃ ነው::

አንቀጽ 12 መተጫጨቱ የሚቆይበት



መተጫጨቱ ሲደረግ የጋብቻ ሥርዓት የሚፈጸምበት ጊዜ በስምምነቱ ያልተወሰነ እንደሆነ መተጫጨት ስምምነት በተደረገ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጋብቻው መፈጸም ይኖርበታል::

አንቀጽ 13 የመተጫጨት መፍረስ

1. እጮኛው ወይም ዕጮኛይቱ መዘግየታቸውን ወይም እንቢተኛነታቸውን የሚያስረዳ በቂ ምክንያት ሳይኖር ጋብቻውን እንቢ ያሉ እንደሆነ መተጫጨቱ ፈራሽ ይሆናል::
2. እንዲሁም ወይም ዕጮኛይቱ ለመተጫጨቱ በሁኔታ ወይም በጠባይ /በምግባር/ ጋብቻው እንዳይፈጸም የሚያደርግ ፈራሽ ይሆናል::

አንቀጽ 14 የመተጫጨት መፍረስ የሚያስከትለው ውጤት /1/ ወጪና የተበላትን ማጫ ስለመመለስ

1. ለመተጫጨቱ መፍረስ ኃላፊ የሆነው ሰው በመተጫጨት ምክንያት የተደረጉትን ወጪዎች ሁሉ መክፈል ይኖርበታል::
2. በመተጫጨት ምክንያት የተቀበለውን ስጦታ ለመተጫጨቱ መፍረስ ኃላፊ የሆነው ሰው እና ስጦታ የተቀበለ የቤተሰብ አባል መመለስ አለባቸው::

አንቀጽ 15 (2) የሕሊና ጉዳት

1. የመተጫጨቱ መፍረስ ስለሚያስከትለው የሕሊና ጉዳት ለመፍረሱ ኃላፊ ላልሆነው ዕጮኛ ወይም ለዕጮኛይቱ በሕሊና ግምት ተገቢ የሆነ ካሣ ሊሰጥ ይችላል::
2. የዚህን ካሣ መጠን ለመወሰንና ካሣውንም ለመጠየቅ የሚችለውን ሰው ዳኞች ርትዕን መሠረት አድርገው ይከተላሉ::
3. ስለ ሕሊና ጉዳት እንዲከፈል የሚደረገው ኪሣራ ከአስር ሺህ የኢትዮጵያ ብር የበለጠ ሊሆን አይችልም::

አንቀጽ 16 የመተጫጨት መቅረት

1. መተጫጨት ከወደፊት ተጋቢዎች አንድ በሞት ሲለይ ወይም ጋብቻን ለመፈፀም የማያስችል በቂ ምክንያት ሲያጋጥም ወይም በሁለቱ ስምምነት ቀሪ ሊሆን ይችላል::
2. እንዲህ በሆነ ጊዜ ሁለቱም ወገኖች የተቀበሏቸውን ስጦታዎች መመለስ አይኖርባቸውም::



Generated by CamScanner

አንቀጽ 17 ይርጋ

በመተጫጨት መፍረስ ላይ ተመስርተው የሚቀርቡት ክሶች ሁሉ መተጫጨቱ ከፈረሰበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ውስጥ ካልቀረቡ በይርጋ የሚታገዱ ይሆናሉ::

## ምዕራፍ 3

## ስለ ጋብቻ አፈጻጸምና አከባበር

### ክፍል 1

### የጋብቻ አስፈላጊ ሁኔታዎች

አንቀጽ 18 ዕድሜ

1. ወንዱም ሆነ ሴቷ አሥራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ ለመፈጸም አይችሉም::
2. ከባድ ምክንያት ሲያጋጥም ወላጆቻቸው ወይም አሳዳሪዎቻቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ፍ/ቤት ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጊዜ በመቀነስ እንዲጋቡ መፍቀድ ይችላል::

አንቀጽ 19 ዝምድና

1. ጋብቻ የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የተከለከለ ነው::
2. ጋብቻ የጋብቻ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የተከለከለ ነው::
3. ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ልጅ ተወላጅነቱ በህግ የታወቀለት ባይሆንም እንኳ ከዚህ በላይ ባሉት ሁለት ቁጥሮች እንደተመለከተው ጋብቻውን ለማስከልከል በቂ ነው::

አንቀጽ 20 ፈቃድ

ተጋቢዎች እያንዳንዳቸው ጋብቻው በሚፈጸምበት ጊዜ ለመጋባት ፈቃዳቸውን መስጠት ይኖርባቸዋል::

አንቀጽ 21 ጋብቻን በእንደራሴ መፈጸም የተከለከለ ስለመሆኑ

ጋብቻን በእንደራሴ መፈጸም የተከለከለ ነው::

አንቀጽ 22 በፍርድ የተከለከለ ሰው

1. በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍ/ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር ጋብቻ ለመፈጸም አይችልም::
2. ስለዚህ ጉዳይ ለፍ/ቤት የሚቀርበውን ጥያቄ በፍርድ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ለማቅረብ ይችላል::



አንቀጽ 23 በጋብቻ ላይ ጋብቻ

አንድ ሰው አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ ጋብቻው እስካለ ድረስ ሁለተኛ ጋብቻ ለመፈጸም አይችልም::

አንቀጽ 24 በኃይል የተገኘ ፈቃድ

1. በኃይል የተገኘ ፈቃድ አይፀናም::
2. ፈቃድ በኃይል ተሰጠ የሚባለው ፈቃዱን የሰጠው ሰው ሊደርስ ይችላል ተብሎ ከሚገመት ከባድ አደጋ ራሱን ወንድሙን ወይም ከወላጆቹ አንደኛውን ወይም ከተወላጆቹ አንዱን ወይም እህቱን ለማዳን ሲል ፈቃዱን የሰጠ እንደሆነ ነው::
3. በወላጆቹ ወይም በሌላ በማናቸውም ሰው አክብሮት በመገፋፋት የተሰጠ ፈቃድ በሃይል እንደተሰጠ አይቆጠርም::

አንቀጽ 25 በጋብቻ ላይ ጋብቻ

1. አንደኛው ተጋቢ ፈቃዱን መሠረታዊ የሆነ ስህተት በመፈጸም ከሰጠ ፈቃዱ የተጓደለ ይሆናል::
2. መሠረታዊ ስህተት ተፈጽሟል የሚባለው:-
   ሀ. አገባዋለሁ ብሎ ያሳሰበውን ሰው አግብቶ ሲገኝ፤ ወይም
   ለ. በሚያገቡት ሰው ሃይማኖት መሳሳት ይኸውም ያገባው ሰው ሃይማኖት የእርሱን ሃይማኖት ያልመሰለ ሲሆን፤ ወይም
   ሐ. ያገባው ሰው የቤተሰብ ኃላፊነትን ለመወጣት የማያስችል የአዕምሮ መታወክ ያለበት ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም
   መ. የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን ለመፈጸም የማይችል ሆኖ ሲገኝ ወይም
   ሠ. ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት የመፈጸም ልማድ ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው::

### ክፍል 2

### ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወምና ስለመከልከል

አንቀጽ 26 ጋብቻን ስለመቃወም

ለጋብቻ አስፈላጊ ከሆኑ ሁኔታዎች አንዱን በመተላለፍ ሊፈጸም የታቀደን ጋብቻን እንዳይፈጸም መቃወም ይቻላል::

አንቀጽ 27 መቃወም የሚችሉ ወገኖች

ጋብቻ እንዳይፈጸም ለመቃወም የሚችሉ ወገኖች፤



Generated by CamScanner

1. በዕድሜ ምክንያት ሲሆን እናት ወይም አባት ወይም እነርሱ በሌሉ ጊዜ አያቶቻቸው ወይም አካለመጠን ያልደረሰው ወገን አሳዳሪ ፤
2. በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ሲሆን ዐቃቤ ሕግ፤
3. በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሟል በማለት ምክንያት ሲሆን የቀደመ ጋብቻ አለኝ የሚለው ወገን ወይም ዐቃቤ ሕግ፤
4. በፍርድ መከልከል ምክንያት ሲሆን አሳዳሪው ወይም ዐቃቢ ሕግ ይሆናሉ::

## አንቀጽ 28 መቃወሚያ የሚቀርብበት ፎርምና ጊዜ

የጋብቻ ተቃውሞ በጽሁፍ ሆኖ ማስታወቂያ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ለክብር መዝገብ ሹሙ መቅረብ ይኖርበታል::

## አንቀጽ 29 በተቃውሞ ላይ የሚሰጥ ውሣኔ

1. የክብር መዝገብ ሹሙ በቀረበው ተቃውሞ ላይ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ውሣኔ መስጠት ይኖርበታል::
2. በዚህ ሕግ በምዕራፍ 4 የተጻፈው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻው እንዲፈጸም የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል::

## አንቀጽ 30 ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመከልከል

1. የክብር መዝገብ ሹሙ በራሱ አነሳሽነት ወይም ነገሩ የሚገባው ወገን በሚያቀርበው ተቃውሞ መሠረት ማንኛቸውም ለጋብቻ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች መጣሳቸውን ካረጋገጠ ጋብቻው እንዳይፈጸም ማድረግ ይኖርበታል::
2. እንዲህ ሲሆን የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻው እንዳይፈጸም የከለከለበትን ምክንያት ለተጋቢዎቹ በጽሁፍ ወዲውኑ ያስታውቃል::
3. የክብር መዝገቡ ሹም ጋብቻው እንዳይፈጸም ከከለከለ ከተጋቢዎቹ አንዱ ለፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል::

# ክፍል 3

# ስለ ጋብቻ አከባበር

## አንቀጽ 31 መሠረቱ

ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በእኩልነትና ፈቃደኝነት ቤተሰብ ለማቋቋም የሚመሠርቱት ጸምረት ነው::



## አንቀጽ 32 የጋብቻ አፈጻጸም

1. ጋብቻ በአንድ የሕዝብ ክብር መዝገብ ሹም ፊት ወይም እርሱ ውክልና በሚሰጠው ሰው ፊት ይፈጸማል::
2. ጋብቻ ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት የክብር መዝገብ ሹም ፊት ቀርበው ፈቃዳቸውን በፊርማቸው ሲያረጋግጡና የክብር መዝገብ ሹሙም ተቀብሎ ሲመዘግበውና በሕግ ስም ሲያስታውቅ ነው::

## አንቀጽ 33 ሥልጣን ያለው የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም

1. ጋብቻ ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎቹ ወላጆቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አያቶች አንዱ ከጋብቻው ጊዜ በፊት ቢያንስ አንድ ዓመት ሳያቋርጥ በሚኖሩበት አጥቢያ በሚኖር የክብር መዝገብ ሹም ፊት መፈጸም ይኖርበታል::
2. የክብር መዝገብ ሹሙ ፊት ያልተፈጸመና በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ያልተመዘገበ ጋብቻ ውጤት አይኖረውም::

## አንቀጽ 34 ጋብቻን ለመፈጸም የሚቀርብ ጥያቄ

1. ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈጸምካቀዱበት ቀን ቢያንስ ከአንድ ወር አስቀድሞ ለክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::
2. የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄ ሲቀርብለት ለጋብቻ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች አለመጣሳቸውን ያረጋግጣል::

## አንቀጽ 35 ጋብቻ የሚፈጸም መሆኑን ስለማስታወቅ

1. የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄ እንደቀረበለት የጋብቻውን መፈጸም የሚቃወሙ ወገኖች ቢኖሩ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ እንዲቀርቡ ተገቢ በሆነው መንገድ ማስታወቂያ ያወጣል::
2. የጋብቻ አስፈላጊ ሁኔታዎች ካለተጣሱና ተቃውሞ ካልቀረበ የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻው የሚፈጸምበትን ቀን ከታጋቢዎቹ ጋር በመስማማት ይወስናል::

## አንቀጽ 36 የጋብቻ አከባበር ስርዓት

1. ጋብቻ ሁለት ተጋቢዎችና በእያንዳንዱ ተጋቢ በኩል ሁለት ምስክሮች በተገኙበት በይፋ መፈጸም ይኖርበታል::
2. ተጋቢዎችና ምስክሮቹ ለጋብቻ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች አለመጣሳቸውን በመኃላ ያረጋግጣሉ::
3. ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻ ለመመስረት መፍቀዳቸውን ለክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ያረጋግጣሉ::



Generated by CamScanner

4. ከዚህ በላይ የተገለጹት ሁኔታዎች ከተሟሉ በኋላ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹ በጋብቻ የተሳሰሩ መሆናቸውን በሕግ ስም አስታውቆ ወዲያውኑ ጋብቻውን በመዝገብ ጽፎ ለተጋቢዎቹ የምስክር ወረቀት ይሰጣል::

አንቀጽ 37 በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ

1. ሴቲቱ አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረበት ጊዜ በኋላ መቶ ሰማንያ ቀን ካላለፈ በቀር እንደገና ለማግባት አትችልም::
2. ሴቲቱ አብሮ መኖር ከተቋረጠ በኋላ ልጅ የወለደች እንደሆነ ከዚህ በላይ ያለው ኃይለ ቃል ውሣኔ የፀና አይሆንም::
3. በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነው ጊዜ እንዳትጠብቅ ፍ/ቤት ሊፈቅድላት ይችላል::

አንቀጽ 38 ያለማግባት ስምምነት

1. አንድ ሰው አላገባም ብሎ ወይም እንደገና አላገባም ብሎ ቃሉን ቢሰጥ በፍትሐብሔር በኩል ውጤት የለውም::
2. የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹሙም ይህንን ነገር አይመለከትም::

ምዕራፍ 4

<u>የጋብቻ ሁኔታዎች ባለመጠበቃቸው ምክንያት ስለሚያስከትለው ውጤትና ኃላፊነት</u>

ክፍል 1

የጋብቻ መፍረስ

አንቀጽ 39 የዕድሜ ሁኔታ

1. በአንቀጽ 18 ንዑስ ቁጥር 2 የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜአቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ወንድም ሆነ ሴት የፈፀሙት ጋብቻ በማናቸውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲፈርስ ሊወሰን ይችላል::
2. ሕጉ በሚያስገድደው መሠረት ለጋብቻ የተወሰነው የዕድሜ ልክ ተሟልቶ የተገኘ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም::

አንቀጽ 40 ዝምድና

በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ያለው ክልከላ በመጣስ ጋብቻ ተደርጎ የተገኘ እንደሆነ ማናቸውም ባለጉዳይ ወይም ዐቃቤ ሕግ በሚያቀርበው ጥያቄ ጋብቻው እንዲፈርስ ይደረጋል::



አንቀጽ 41 በጋብቻ ላይ ስለሚደረግ ጋብቻ

በጋብቻ ላይ ጋብቻ የተደረገ እንደሆነ የመጀመሪያውን ጋብቻ ያደረገው ሰው ወይም ኋለኛውን ጋብቻ በቅን ልቦና ያደረገው ተጋቢ ወይም ዐቃቤ ሕጉ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ጋብቻው ይፈርሣል::

አንቀጽ 42 ችሎታ የሌለው ሰው ጋብቻ

1. ችሎታ የሌለው ሰው የፈፀመው ጋብቻ እንዲፈርስ አካለመጠን ያላደረሰ ሰው ወይም በአእምሮው መናወጽ ምክንያት የተከለከለ ወይም የተከለከለው ሰው አሳዳሪ ፍ/ቤትን መጠየቅ ይችላል::
2. ችሎታ ያጣው ሰው ጋብቻው እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ችሎታ ማጣቱ ከቀረ 6 ወር በኋላ ለማቅረብ አይችልም::
3. ለዚሁ ጉዳይ ሌሎች ሰዎች የሚያቀርቡት ጥያቄ ጋብቻው መኖሩን ካወቁ ከ6 ወር በኋላ በሌላ በማናቸውም ምክንያት ሲሆን ደግሞ አካለ መጠን ያላደረሰው ወይም የተከለከለው ሰው ችሎታ ማጣት ከቀረ በኋላ ሊቀርብ አይችልም::

አንቀጽ 43 የኃይል ሥራ

1. ማናቸውም ሰው በኃይል ተገዶ ጋብቻ የፈፀመ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስ ፍ/ቤትን መጠየቅ ይችላል::
2. ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ የኃይል ስራው ከተቋረጠ ከስድስት ወር በኋላና በማናቸውም አኳኋን ጋብቻው ከተፈፀመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም::

አንቀጽ 44 ስህተት

1. ማንም ሰው ከመሠረታዊ ስህተት የተነሣ ጋብቻ ያደረገ እንደሆነ ጋብቻው እንዲፈርስለት ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል::
2. ስለዚሁ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ ስህተቱን ካወቀበት ቀን አንስቶ በሚቀጥለው 6 ወር ውስጥና በማናቸውም አኳኋን ጋብቻ ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም::

ክፍል 2

የወንጀል ቅጣት

አንቀጽ 45 <u>የጋብቻ ሁኔታዎች እና የአፈጻጸም ደንቦች በመጣሳቸው</u> <u>የሚቀጡ ወገኖች</u>

የህዝብ የክብር መዝገብ ሹም እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው፤



Generated by CamScanner

ለ) የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸውን ሴትና ወንድ ጋብቻ ያስፈፀመ እንደሆነ፤
ሐ) ከዚህ በፊት በጋብቻ የተሳሰረ/ች ሰውን ጋብቻ ያስፈፀመ እንደሆነ፤
መ) በፍርድ የተከለከለውን ሰው ጋብቻ ያስፈፀመ እንደሆነ፤
ሠ) በኃይል ሥራ የተደረገ ጋብቻን ያስፈፀመ እንደሆን ፤
ረ) በአንቀጽ 37 ሥር እንደተደነገገው በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነው ጊዜ ከማለቁ በፊት ያገባቱን ሴት ጋብቻ ያስፈጸመ እንደሆነ፤
ሰ) በአንቀጽ 33 ሥር ስለመኖሪያ ሁኔታ የተደነገገውን በመተላለፍ ጋብቻ ያስፈፀመ እንደሆነ፤
ሸ) በጋብቻ ላይ የተደረገውን ተገቢ የሆነውን መቃወም በማቃለል ጋብቻ ያስፈፀመ እንደሆነ፤
ቀ) የጋብቻን አፈፃፀም የሚመለከቱ ውሣኔዎችን /ደንቦችን/ ጠብቆ ጋብቻ ያላስፈፀመ እንደሆነ፤

እንዲሁም በጋብቻው ላይ ምስክሮች የነበሩ፤ እንደአግባብነቱም ተጋቢዎቹ በወንጀል ህግ መሰረት ይቀጣሉ:: ሆኖም የጋብቻን አፈፃፀም የሚመለከቱትን ውሣኔዎች /ደንቦች ባለመጠበቅ የተፈፀመ ጋብቻ እንዲፈርስ ሊጠየቅ አይችልም::

## ምዕራፍ 5

## የጋብቻ ውጤቶች

## ክፍል 1

## ጠቅላላ ደንቦች

### አንቀጽ 46 የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም

ጋብቻው ለሚያስከትለው ውጤት የሩካቤ ስጋው ግንኙነት መፈፀሙ ወይም በግምት ተፈጽመዋል መባሉ አስፈላጊ አይደለም::

### አንቀጽ 47 የጋብቻ ስምምነት

1. ተጋቢዎች በገዛባቸው በኩል ጋብቻቸው ስለሚያስከትለው ውጤት ጋብቻቸውን ከማድረጋቸው በፊት ሊስማሙ ይችላሉ:: እንዲሁም በዚህ ስምምነት ውስጥ በመካከላቸው ስላለው ግንኙነት አንዱ ለአንዱ ይችላል:: ያለብትን ግዴታዎችና ያሉትን መብቶች ሊያረጋግጡ ይችላል::
2. ተጋቢዎች የሚያደርጉት ስምምነት አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን የሚቃረን መሆን አይችልም::

### አንቀጽ 48 ከባልና ሚስት የአንደኛው ችሎታ ማጣት



2 ተጋቢዎች የሚያደርጉት ስምምነት አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን የሚቃረን መሆን አይችልም::

አንቀጽ 48 ከባልና ሚስት የአንደኛው ችሎታ ማጣት

1. አካለ መጠን ያላደረሰ ሰው በአንቀጽ 18/2 መሠረት ለሚያደርገው የጋብቻ ስምምነት ራሱና የሞግዚቱ ፈቃድ አስፈላጊ ነው::
2. በፍርድ የተከለከለ ሰው የሚያደርገውን የጋብቻ ስምምነት እርሱው ራሱ ሊፈፅም ይገባዋል ሆኖም ፍ/ቤት ካላፀደቀው ፈራሽ ነው::
3. በህግ የተከለከለን ሰው የሚመለከቱ የችሎታ ማጣት ድንጋጌዎች በዚህ በጋብቻ ስምምነት መዋዋል ተፈጻሚነት አይኖራቸውም::

### አንቀጽ 49 የስምምነት ስርዓት /ፎርም/

የጋብቻው ስምምነት በጽሁፍ ካልሆነና አራት ምስክሮች፤ ሁለቱ በባልየው ወገን ሁለቱ በሚስቲቱ ወገን የፈረሙበት ካልሆነ በቀር ፈራሽ ነው::

### አንቀጽ 50 የስምምነት ጽሁፍ የሚቀመጥበት ቦታ

1. የስምምነቱ አንድ ግልባጭ ውል ለማፈራረም ስልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ ይቀመጣል::
2. ተጋቢዎቹ ለማየት በፈለጉ ጊዜ እንዲሁም ፍ/ቤት ወይም ተጋቢዎቹ የፈቀዱላቸው ሰዎች የስምምነቱን ጽሁፍ ለማየት ይችላሉ::

### አንቀጽ 51 ስምነት ለማድረግ ስላለው የነፃነት ወሰን

1. የጋብቻ ስምምነት በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ ማንኛውንም ግዴታ ሊያስከትል አይችልም::
2. የጋብቻው ስምምነት በቀጥታ ወይም ያለ ሀተታ በአገር ልማድ ተጋብተናል በማለት ብቻ ለመመሪት አይችልም::

### አንቀጽ 52 የጋብቻ ስምምነት ስለመለወጥ

1. የቤተዘመድ ጥቅም የሚጠይቅ በሆነ ጊዜ ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንደኛው ጠያቂነት ስምምነት ሊለወጥ ይችላል::
2. የጋብቻው ውል እንዲለወጥ ሁለቱ ተጋቢዎች በማይስማሙበት ጊዜ ጉዳዩ ለፍ/ቤት ቀርቦ ይወሰናል::
3. የስምምነቱን ስርዓትና ምዝገባ በሚመለከት የተገለፁት ድንጋጌዎች ውሉ በሚለወጥበት ጊዜም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል::



Generated by CamScanner

## አንቀጽ 53 በባልና ሚስት መካከል የሚደረግ ስምምነት

1. ባልና ሚስት ተጋብተው በሚኖሩበት ጊዜ በሁለቱ መካከል የሚደረገውን ስምምነት ፍ/ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ዋጋ የለውም።
2. በዚህ ሕግ ስለ ጋብቻ ስምምነት በግልፅ ተለይተው የተነገሩት ድንጋጌዎች የተጠበቁ ናቸው።

## አንቀጽ 54 ሕጋዊ አስተዳደር/ ስርዓት/

በአንቀጽ 47 መሠረት የተደረገ የጋብቻ ስምምነት የሌለ እንደሆነ ወይም በአንቀጽ 53 መሠረት በባልና ሚስት መካከል የተደረገው ስምምነት ሳይፀና የቀረ እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ይፈጸማል። ስምምነት ቢኖርም እንኳን ቀጥሎ የተመለከቱት አስገዳጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው።

# ክፍል 2

# ጋብቻ በተጋቢዎች ማህበራዊ ግንኙነት ላይ የሚኖረው ውጤት

## አንቀጽ 55 ባልና ሚስት እኩል ስለመሆናቸው

ተጋቢዎቹ በጋብቻ አፈፃፀም፤ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው።

1. ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው መከባበር መተጋገዝና መተማመን አለባቸው።
2. ይህን ደንብ በጋብቻ ስምምነት መለወጥ አይቻልም።

## አንቀጽ 56 የቤተሰብ አመራር

ባልና ሚስት የቤተሰባቸው ጥቅም እንዲጠበቅ ልጆቻቸው በመልካም ጠባይ ታንፀው እንዲያድጉ ተገቢ ትምህርት እንዲያገኙና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች እንዲሆኑ ለማድረግ መተባበር ይኖርባቸዋል።

## አንቀጽ 57 ከባልና ሚስት የአንዱ መታወክ

1. ከባልና ሚስት አንደኛው ችሎታ ማጣት የደረሰበት እንደሆነ ወይም በስፍራው የማይገኝ ወይም ቤተሰቡን በመተው ምክንያት



የተፈረደበት እንደሆነ ከዚህ በላይ በተመለከተው ቁጥር ያለውን ስልጣን አንደኛው ብቻውን ይፈፅማል።
2. ከሁለቱ አንዳቸው የአንድነት ኑሮውን በፈቃዱ ትቶ የሄደ እንደሆነ ወይም ከመኖሪያ ስፍራው በመራቁም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት የፈቃደኝነት አሳቡን ለመግለፅ በማይቻልበት ሁኔታ በሚገኝበት ጊዜም በዚሁ ዓይነት ይፈፀማል።
3. የጋብቻው ስምምነት ከዚህ በላይ ያሉትን ስርዓቶች አፍራሽ ሊሆን አይችልም።

## አንቀጽ 58 ከጋብቻ በፊት ከሌላ ስለተወለደ ልጅ

ከባልና ሚስቲቱ አንዱ ከጋብቻው በፊት ከሌላ ስለወለዷቸው ልጆች ማሳደግና ማስተማርን በሚመለከት ተጋቢዎች ከጋብቻ በፊት ወይም ከጋብቻ በኋላ ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ።

## አንቀጽ 59 አብሮ መኖር

1. ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ይገደዳሉ።
2. ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስት ከጋብቻ የሚጠበቀውን ደንበኛውን የሩካቤ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ይኖርባቸዋል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን የሚቃረን የስምምነት ቃል ሁሉ ፈራሽ ነው።
4. ለጤና አደገኛ በሆንና ከደንበኛው የሩካቤ ስጋ ግንኙነት ተቃራኒ በሆነ መንገድ የፈፀመ ተጎጂው በሚያቀርበው መሠረት በወንጀል ሕግ ይቀጣል።

## አንቀጽ 60 የመኖሪያ ስፍራን ስለመወሰን

1. ባልና ሚስት የሚኖሩበትን ስፍራ በስምምነት ይወስናል።
2. ባልና ሚስት ያልተስማሙ እንደሆነ ሥፍራው በፍርድ ቤት ይወስናሉ
3. ፍርድ ቤቱም የመኖሪያ ስፍራቸውን የሚወስነው የቤተሰቡን ጥቅም መሠረት በማድረግ ይሆናል።

## አንቀጽ 61 በስምምነት ስለመለያየት

1. በአንቀጽ 59 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባልና ሚስት ሳተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር ስምምነት ለማድረግ ይችላሉ።
2. ስለዚህ ጉዳይ የተደረገውን ስምምነት የመሰረዙ ጉዳይ የማይገባ ካልሆነ በቀር ከሁለቱ አንደኛው ወገን እስከ ሊሰርዘው ይችላል።



Generated by CamScanner

አንቀጽ 62 የቁጥጥርና የጥበቃ ተግባር

ለኑሮአቸው መልካም ጥቅም ከሆነ ባል ሚስቱ የምታደርገውን እንዲሁም ሚስት ባልዋ የሚያደርገውን ግንኙነት ለመቆጣጠርና የየጠባያቸውንም አመራር ለመጠበቅ ይችላሉ::

አንቀጽ 63 የባልና የሚስት የሞያ ሥራ

1. ከተጋቢዎቹ እያንዳንዱ የመረጠውን የሞያ ሥራ ወይም የጥበብ ስራ ለማከናወን ይችላል::
2. ከሁለቱ የአንደኛው ሥራ ለትዳራቸው ለቤተሰባቸው መልካም አኗኗር የማይጠቅም እንደሆነ ያንደኛውን የተወሰነ ስራ ወይም ሞያ ለመቃወም ይችላል::

ክፍል_3

ጋብቻው በንብረት በኩል ያለው ውጤት

አንቀጽ_64 የባልና ሚስት የግል ሀብት

1. በጋብቻቸው ጊዜ የነበራቸው የባልና ሚስት ሀብቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ ያገኙአቸው ሀብቶች ለየራሳቸው የግል ሀብቶቻቸው ሆነው ይኖራሉ::
2. እንዲሁም ከተጋቡ በኋላ ከባልና ሚስት አንዱ በገንዘቡ የገዛቸው ሀብቶች የግል ሀብቶች ናቸው:: ይኸውም የሚሆነው ሀብቱ የተገኘው በግል ገንዘቡ የገዛው ሲሆንና ወይም የግል ገንዘቡ በሆነው ነገር ልውጫ ያገኘው ሀብት የሆነ እንደሆነ ነው::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በመጨረሻ ኃይለ ቃል የተመለከተው ድንጋጌ ግን በዚህ ዓይነት የተገኘው ሀብት የግል ይሁንልኝ ብሎ አንደኛው ያቀረበውን ጥያየቄ ፍ/ቤቱ ካላፀደቀው ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም::

አንቀጽ_65 የግል ሀብትን ስለማስተዳደር

1. ከተጋቢዎች አንዱ የግል ንብረቱን ለማስተዳደርና ገቢውንም ለመቀበል ይችላል::
2. ይህንንም የግል ንብረቱን በራሱ ሊያገዘበት ነፃነት አለው::

አንቀጽ_66 የአንደራሴነትን ስልጣን

ከባልና ከሚስቱ አንዱ ላንደኛው የንብረቱን አስተዳዳሪነት ወይም ከግል ሀብቱ ያንዱን ንብረት ጠባቂነትና አስተዳዳሪነት ስልጣን ለመስጠት መብት አለው::



አንቀጽ 67 የጋራ ሀብት

1. የባልና ሚስት ደመወዝ፤ ከግል ሀብት የሚገኙ ገቢዎችና ፍሬዎች የጋራ ሀብቶቻቸው ናቸው::
2. እንዲሁም ባልና ሚስቱ ከተጋቡ በኋላ በገንዘብ የገዟቸው ሀብቶችና ንብረቶች ሁሉ የሁለቱ የጋራ ሀብቶች ናቸው::
3. በስጦታ ውል ወይም በኑዛዜ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ለሁለቱ ተጋቢዎች በስጦታ ወይም በኑዛዜ የተሰጡት ንብረቶች የጋራ ሀብቶች ናቸው::

አንቀጽ_68 የግል ሀብትን ስለማስተዳደር

1. አንደኛው ወገን የግሉ መሆኑን በበቂ ማስረጃ ካላረጋገጠ በቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛውም ወገን ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም የጋራ ንብረት እንደሆነ ይቆጠራል::
2. የግል ንብረት መሆኑን ሶስተኛ ወገኖች የሚያውቁት ወይም ሊያውቁት የሚገባ ካልነበረ በቀር፤ ባልና ሚስቱ ንብረቱ የግል ነው በማለት በሶስተኛ ወገን ላይ መከላከያ አድርገው ሊያቀርቡት አይችሉም::

አንቀጽ_69 ደመወዝና ገቢ_(1)_ደንበኛ_አመራር

1. ተጋቢዎቹ እያንዳንዳቸው ደመወዛቸውንና ገቢያቸውን ይቀበላሉ::
2. ከሁለቱ በአንደኛው ጠያቂነት ከደመወዝና ከንብረት ገቢ ያገኘው ገንዘብ ልክ መግለፅ አለበት::

አንቀጽ_70_(2)_የባልና_ሚስት_መብት

1. ከባልና ከሚስት አንዱ የሌላኛውን ደመወዝ ወይም ገቢ እንዲቀበል ስልጣን ሊሰጠው ይችላል::
2. ፍ/ቤት ከባልና ሚስቱ በአንደኛው ጠያቂነት ከሁለቱ የአንደኛውን ደመወዝ አንዱ እንዲቀበልና ለመቀበሉም ደረሰኝ እንዲሰጥ ለመወሰን ይችላሉ::
3. ፍ/ቤቱ ከባል ወይም ሚስት ደመወዝ ወይም ገቢ ላይ የአንደኛው በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከበር ለመፍቀድ ይችላል፤

አንቀጽ_71 የጋራ ሀብትን ስለማስተዳደር

1. አንደኛው ወገን በሙሉ ወይም በከፊል የጋራ ንብረትን እንዲያስተዳድር የግል ስምምነት ከሌለ በቀር ባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸውን በአንድነት ያስተዳድራሉ::!
2. ከባልና ሚስቱ አንደኛው ችሎታ የለውም ተብሎ ሲወሰን ወይም ከቤተሰቡ አስተዳደር መብቱን ሲገፈፍና ወይም በቂ በሆነ ምክንያት የጋራ ንብረቱን አብሮ ለማስተዳደር ሳይችል ሲቀር ወይም

የማይችልበት ሁኔታ ላይ ሲገኝ የጋራ ንብረት አስተዳደሩን ለሌላው ወገን ብቻውን ያከናውናል።

አንቀጽ 72 የማስታወቅ ግዴታ

እተጋቢዎቹ አንዱ በጋራ ሀብቶች ላይ የአስተዳደር ተግባር ሲያከናውን ሌላኛው ወገን መግለጽ ወይም ማስታወቅ አለበት።

አንቀጽ 73 የባልና የሚስት የዕለት ጉዳይ ስራዎች

1. በዚህ ምዕራፍ አንቀጽ 72 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጋቢዎቹ የቤተሰባቸውን ጥቅም በማይጎዳና የገቢያቸውን መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለዕለት ከዕለት ጉዳዮች ለሚያወጡት ወጪ አንዱ የሌላውን ፈቃድ መጠየቅ አያስፈልጋቸውም፤
2. የባልና ሚስት የዕለት ከዕለት ጉዳይ ስራዎች፤
   ሀ) የጋራ ንብረት መሸጥን ወይም በዕዳ ማስያዝን፤
   ለ) ከቤተሰቡ የገቢ አቅም በላይ ገንዘብ መበደር ወይም ማበደርን
   ሐ/ ስጦታ ማድረግንና ወይም ለሌላ ሰው ዕዳ ዋስ መሆንን አይጨምርም።

አንቀጽ 74 የባልና የሚስት ዕዳ

1. ከባልና ከሚስት ከአንደኛው የሚጠየቀው ዕዳ ከግል ሀብት ላይ ሊጠይት ይችላል የግል ሀብት በማይኖርበት ጊዜ ዕዳው ከባለዕዳው ድርሻ ከሆነው ከጋራ ሀብታቸው ሊጠየቅ ይችላል፤
2. ዕዳው የመጣው ለቤተሰባቸው ጥቅም በሆነ ጊዜ እንደ አንድነት ዕዳ ተቆጥሮ ከባልና ከሚስቱ በአንደኛው የግል ሀብት ላይ ወይም በጋራ ሀብታቸው ላይ ሊጠየቅ ይችላል፤

አንቀጽ 75 ለቤተሰብ ጥቅም እንደተደረገ ስለሚቆጠር ዕዳ

ለቤተሰብ ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠረው ዕዳ

ሀ) የባልና ሚስትን ወይም የልጆቻቸውን ምግብና መተዳደሪያ ለማዘጋጀት የተደረጉ ዕዳዎች፤
ለ) ባልየው ወይም ሚስትየዋ ቀለብ የመስጠት ግዴታቸውን ለመወጣት ያደረጓቸው ዕዳዎች፤
ሐ) ከባልና ከሚስቱ በአንደኛው ወይም በገንዘብ ጠያቂው አመልካችነት ዕዳው የደረሰው ለቤተሰብ ጥቅም መሆኑን ፍ/ቤት አውቆ የተቀበለው ሌላ ዕዳ ሲሆን ነው።



<u>አንቀጽ 76 ለትዳራቸው ወጪ ባልና ሚስት ስለሚያደርጉት መረዳዳት</u>

ባልና ሚስት የትዳራቸውን ወጪ ለማደራጀት እያንዳንዳቸው ባላቸው ችሎታና አቅም መጠን እርስ በርሳቸው መረዳዳት አለባቸው።

<u>ምዕራፍ 6</u>

<u>ስለ ጋብቻ መፍረስ</u>

<u>ክፍል 1</u>

<u>ጋብቻ የሚፈርስበት ምክንያት</u>

<u>አንቀጽ 77 ልዩ ልዩ ምክንያቶች</u>

1. ጋብቻ የሚፈርሰው ከተጋቢዎቹ አንደኛው በሞተ ጊዜ፤
2. እንዲሁም ከጋብቻው ሕግ አንደኛው በመጣሱ ምክንያት ዳኛ ጋብቻው ቀሪ እንዲሆን የፍርድ ውሳኔ በሰጠ ጊዜ፤
3. ፍቺ ሲኖር ነው።

<u>አንቀጽ 78 አልፈልግም ስለማለት</u>

ሚስት ባልዋን ወይም ባል ሚስቱን አልፈልግም በማለት ጋብቻ አይፈርስም።

<u>አንቀጽ 79 በስምምነት የሚደረግ መፋታት</u>

1. በባልና ሚስት ስምምነት የሚደረግ መፋታት በሕጋዊ መንገድ ካልተፈጸመ በቀር አይፈቀድም፤
2. በዚህ ሕግ ድንጋጌ ላይ ከተመለከተው ውጪ በሆነ አፈጻጸም መፋታትን ለመወሰን አይቻልም፤

<u>አንቀጽ 80 ለመፋታት የሚቀርብ ጥያቄ</u>

1. ለመፋታት የሚቀርበውን ጥያቄ ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱ በአንድነት ሆነው ለፍ/ቤት ሊያቀርቡ ይችላሉ፤
2. ሌላ ማናቸውም ሰው የመፋታትን ጥያቄ ሊያቀርብ አይችልም፤
3. የመፋታቱ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ከባልና ከሚስቱ የአንደኛው መሞት ስለ መፋታት የቀረበውን አሠራር ያስቀረዋል።

<u>አንቀጽ 81 ከባድ ምክንያቶችና ሌሎች ምክንያቶች</u>

በፍቺው የሚወስንባቸው ሁኔታዎችን የሚያስከትሏቸው ውጤቶች መፋታቱን የሚጠይቀው ተጋቢ ለእርሱ/ለእርሷ በሚጠትም ሁኔታ ከባድ ምክንያት መኖሩን በሚያስረዳበት መጠን የሚለዩ ናቸው፤



Generated by CamScanner

አንቀጽ 82 በከባድ ምክንያቶች የሚደረግ የመፋታት ውሳኔ

መፋታትን የሚጠይቀው ወገን ጋብቻውን ሊያፈርስ የሚችል ከባድ ምክንያት ካቀረበ የመፋታቱ ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤት በአንቀጽ 89 እና 93 ላይ በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት ውሳኔ ይሰጣል

አንቀጽ 83 መፋታትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ከባድ ምክንያቶች /1/ ከባልና ሚስት የአንደኛው ጥፋት

ከባልና ከሚስት በአንደኛው ጥፋት መፋታትን ለማስከተል የሚችሉ ከባድ ምክንያቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) ባል ወይም ሚስት የዝሙት ተግባር የፈፀመ እንደሆነ ወይም
ለ) ቢያንስ ለአንድ ዓመት ጊዜ ቤተሰቡን ጥሎ ከሄደ፤ ወይም
ሐ) አንዱ በሌላው ላይ የጨካኝነት ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፤

አንቀጽ 84 /2/ ከባልና ከሚስት በአንዱ ጥፋት የሆነ መፋታትን የሚያስከትል ከባድ ምክንያት

መፋታትን የሚያስከትል ከባድ ምክንያት አለ የሚያሰኘው፡-

ሀ) ከባልና ከሚስት አንዱ እጅግ ቢያንስ ለሁለት ዓመት ጊዜ አእምሮው የተናወጠና የእብድ መጠበቂያ ስፍራ ተዘግቶበት የቆየ እንደሆነ፤
ለ) ከባልና ከሚስት የአንደኛው መጥፋት በፍርድ ውሳኔ ተገልጾ እንደሆነ ነው፡፡

አንቀጽ 85 ከባድ ምክንያት ስለሚቀርብበት ሁኔታ

1. ከባልና ሚስት አንደኛውን በጥፋት የሚያስጠይቅ ከባድ ምክንያት ሌላው ወገን ይቅርታ ካደረገለት እንደ ምክንያት መቆጠሩ ይቀራል፡፡
2. ማናቸውም ተቃራኒ ማስረጃ ቢቀርብም እንኳን ጥፋተኛው ተጋቢ የጥፋት ተግባሩን መፈጸሙን ካወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ሶስት ወር ድረስ ሌላው ተጋቢ የፍቺ ጥያቄ ያላቀረበ እንደሆነ ይቅርታ እንዳደረገ ይቆጠራል፡፡

አንቀጽ 86 ሌሎች ምክንያቶች

1. ከባልና ከሚስት በአንደኛው የተጠየቁት ሌሎች የመፋታት ምክንያቶች እንደ ከባድ የመፋታት ምክንያቶች አይቆጠሩም፤
2. ስለሆነም ከዚህ በታች በሚከተሉት ቁጥሮች በተወሰኑት ሁኔታዎች ጊዜዎች መሠረት መፋታቱ እንዲወሰን የሚያበቁ ምክንያቶች ናቸው፡፡



አንቀጽ 87 የፍቺ ጥያቄ ተቀባይነት ስለማይገኝበት ሁኔታ

ባልና ሚስት አብሮ ለመኖር የማያስችል ከባድ ሁኔታ ካጋጠመ በቀር ሚስቲቱ ነፍሰ ጡር በሆነችበት ጊዜ ወይም ወልዳ ስድስት ወር ከማለፉ በፊት ባለየው የሚያቀርበው የፍቺ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 88 ለጊዜው ስለሚሰጡ ውሳኔዎች

1. ባልና ሚስቱ የፍቺ አቤቱታቸውን ለፍ/ቤት እንዳቀረቡ ፍ/ቤት ወዲያውኑ ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩበት ሁኔታ፤ ስለ ልጆቻቸው አጠባበቅና ስለሚኖሩበት ስፍራ ስለንብረታቸውም አስተዳደር ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ጊዜያዊ ትዕዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡
2. ፍ/ቤቱ ለጊዜው የሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም ሰው በሚያቀርበው ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊቀር ይችላል፡፡

አንቀጽ 89 የቤተ ዘመድ ሽማግሌዎች ተግባር

1. በማናቸውም ምክንያት ቢሆን የፍቺ አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት ባልና ሚስቱ እንዲታረቁ ሙከራ እንዲደረግ ጉዳዩን ለቤተ ዘመድ ሽማግሌዎች ይመራዋል፡፡
2. ጉዳዩ የተመራላቸው ሽማግሌዎች ባልና ሚስቱን በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለማስታረቅ ጥረት ያደርጋሉ፤
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው የጊዜ ገደብ በቤተዘመድ ሽማግሌዎች ጠያቂነት ለ3 ወር ጊዜ እንዲራዘም ፍ/ቤቱ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. የቤተ ዘመድ ሽማግሌዎች በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ባልና ሚስቱን ለማስታረቅ ያደረጉትን የሙከራ ውጤት ለፍ/ቤቱ በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

አንቀጽ 90 የቤተዘመድ ሽማግሌ ስለመምረጥ

1. ባልና ሚስቱ እያንዳንዳቸው ሁለቱ ወይም በጋራ ስምምነት አምስት ሽማግሌዎች መምረጥ ይኖርባቸዋል፡፡
2. የቤተዘመድ ሽማግሌዎች እስከተቻለ ድረስ በጋብቻቸው ጊዜ የነበሩት ሰዎች ይሆናሉ፤
3. የባልና ሚስቱ ጉዳይ በቤተ ዘመድ ሽማግሌዎች እንዲታይ ከታዘዘበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ አንደኛው ወገን ሽማግሌዎችን ሳይመርጥ ቢቀር ወይም ሁለቱም ወገኖች ሽማግሌዎች ለመመረጥ ካልቻሉ እንደነገሩ ሁኔታ ሌላው ወገን በመረጣቸው ወይም ፍ/ቤቱ በሚመርጣቸው ሽማግሌዎች እንዲታረቁ ሙከራ ይደረጋል፡፡



Generated by CamScanner

## አንቀጽ 91 የቤተዘመድ ሽማግሌ ስለመተካት

የተመረጠው የቤተዘመድ ሽማግሌ በበቂ ምክንያት የማስታረት ተግባሩን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ በመረጠው ወገን ወይም በፍርድ ቤት ሌላ ሽማግሌ መተካት ይችላል፤

## አንቀጽ 92 ለቤተዘመድ ሽማግሌዎች አበል ስለአለመከፈሉ

1. የቤተዘመድ ሽማግሌዎች ባልና ሚስቱን ለማስታረት ለሚሰጡት አገልግሎት አበል አይከፈልም፤
2. ሽማግሌዎች ተግባራቸውን ለማከናወን አስፈላጊና ተገቢ ወጭዎችን ባልና ሚስቱ እንዲከፍሉ ወይም ሽማግሌዎች የከፈሉት እንዲተካላቸው ፍ/ቤት ሊያዝ ይችላል፤

## አንቀጽ 93 የፍርድ ቤቱ ሥልጣን

1. ጉዳዩ የተመራላቸው የቤተዘመድ ሽማግሌዎች በአንቀጽ 89 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባልና ሚስቱን ለማስታረት ሳይችሉ ከቀሩ ፍ/ቤቱ ከሦስት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የፍቺ ውሳኔ ይሰጣል::
2. ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ ጋብቻው የሚፈርስበትን ምክንያትና ለጋብቻው መፍረስ ምክንያት የሆነውን ወገን ለይቶ ማመልከት ይኖርበታል::
3. የፍቺው ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ የባልና ሚስቱን የቤተሰብ ሚስጢርና በተለይም የልጆቹን ጥቅም ማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ክርክሩን በዝግ ችሎት መስማት ይችላል::

## አንቀጽ 94 አካለ መጠን ስለአልደረሱ ልጆች አጠባበቅ

1. የልጆቹን ደህንነት፤ መልካም አስተዳደግና ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት አካለ መጠን ላልደረሱ ከጋብቻ የተወለዱ ልጆች ከወላጆቻቸው በማናቸው እንደሚጠበቁና እንደሚያዙ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይሰጣል::
2. ተቃራኒ ውሳኔ የሚያሰጥ ከባድ ምክንያት ከሌለ በቀር እድሜአቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ከእናታቸው ጋር መቆየት ይኖርባቸዋል::

## አንቀጽ 95 ውሳኔውን ስለማሻሻል

ከጋብቻ ስለተወለዱ አካለመጠን ስላልደረሱ ልጆች አጠባበቅና አያያዝ የተሰጠ ውሳኔ በአባት ወይም በእናት ወይም በሕግ መብት በተሰጣቸው ሌሎች ሰዎች ጠያቂነት በማናቸውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል::



# ክፍል 2

## የጋብቻ መቅረት ወይም መፍረስ

## በንብረት ላይ የሚያስከትለው ውጤት

## አንቀጽ 96 የስምምነት ተፈጻሚነት

1. ከተጋቢዎቹ አንደኛው በሞተ ጊዜ የሀብታቸው ክፍያ ጉዳይ የሚጣራው በጋብቻቸው ስምምነት ላይ በተመለከተው የስምምነት ቃል መሠረት ወይም በተጋቢዎች መካከል በተደረገው ስምምነት ነው::
2. የዚህ ዓይነት ስምምነት የሌለ እንደሆነ ወይም ይህ ስምምነት በሚፀና አኳኋን ሳይደረግ ቀርቶ እንደሆነ የተጋቢዎቹ ሀብት ክፍያ ሥርዓት የሚፈጸመው በዚህ ክፍል ላይ በተደነገገው ደንብ መሠረት ነው::

## አንቀጽ 97 የግል ሀብትን መልሶ ስለመውሰድ

ከተጋቢዎቹ እያንዳንዱ የግል ሀብቱ መሆኑን አስረድቶ የራሱን የግል ድርሻ ሀብት በዓይነቱ መልሶ ለመውሰድ መብት አለው::

## አንቀጽ 98 የጋራ ሀብትን በየድርሻው ስለመውሰድ

ከተጋቢዎቹ አንዱ የግል ንብረቱ የነበረው ነገር ተሸጦ ዋጋው ወደ ጋራ ንብረት ውስጥ የተደባለቀ መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ከጋራ ሀብቱ ውስጥ ለዚሁ የግል ገንዘቡ ተመጣጣኝ በሚሆነው መጠን ቀንሶ ዋጋውን ለራሱ ድርሻ ለመውሰድ ይችላሉ::

## አንቀጽ 99 ስለ ካሣ /1/ መሠረቱ

ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ወይም የሂሳብ ማስተካከል መተማመኛ ቢኖርም እንኳ በሠራቸው ሥራዎች የጋራ ሀብቶችን ወይም ያንደኛውን የግል ሀብት በጎዱት ሥራዎች ምክንያት ከተጋቢዎች አንዱ ለአንደኛው ኪሣራ እንዲከፍለው ለማድረግ የሚቻለው፤

ሀ) ሥራውን የፈጸመው ይህንን ለማድረግ ሥልጣን ያልነበረው እንደሆነ፤

ለ) የሀብት ጠባቂነት ተግባር መጥፎ ዓይነት አስተዳደር የሆነ እንደሆነ ወይም በከሣሹ ላይ የማጭበርበርን ተግባር ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ነው፤



Generated by CamScanner

አንቀጽ 100 /2/ ጥያቄን ስለአለመቀበል

ጋብቻው ከመፍረሱ ከ3 ዓመት በፊት በተሠሩት ሥራዎች ምክንያት ከዚህ በላይ በተጻፈው ቁጥር ላይ የተመሠረተው የኪሣራ ጥያቄ ሊደረግ አይችልም።

አንቀጽ 101 ያለአግባብ ስለመበልፀግ

ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር አንደኛው ወገን ከሌላኛው የግል ሀብት ወይም ከጋራ ሀብት ላይ ራሱን ያለአግባብ ያበለጸገ መሆኑ የተረጋገጠበት እንደሆነ ሌላኛው ወገን ካሣ መክፈል ይኖርበታል።

አንቀጽ 102 የጋራ ሀብት ክፍያ

1. ከዚህ በላይ በተጻፉት ቁጥሮች የተመለከቱት ድንጋጌዎችና በጋብቻቸው ስምምነት ወይም ተጋቢዎቹ በሚዐና አኳኋን የተፈራረሙት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ክፍያ የሚፈጸመው እኩል ነው።
2. የክፍያን ሥርዓት ክፍያ ከተደረገ በኋላ በጋራ ወራሾች መካከል ያለውን ግንኙነት ክፍያ ከተደረገ በኋላ የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት ስለመጠበቅ ጉዳይ በውርስ ሕግ በተነገረው ድንጋጌ የባልና የሚስት የጋራ ንብረት በማካፈልም ጊዜ በተመሳሳይነት ተፈጻሚ ይሆናል።

አንቀጽ 103 ጠቅላላ ደንብ

1. ከዚህ በታች ከተመለከቱት ቁጥሮች ውስጥ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተጋቢዎች በተፋቱ ጊዜ የገንዘባቸው ግንኙነት የሚጣራው ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ከሁለቱ አንዱ በሞተ ጊዜ ለሚደረገው የንብረት ክፍያ በተሰጠው ደንብ ዓይነት ነው።
2. ከዚህ በታች በተመለከተው ቁጥሮች የተመለከቱ ድንጋጌዎች በጋብቻም ስምምነት ሆነ የጋብቻቸውን ስምምነት ከማፍረሳቸው በፊት ተጋቢዎቹ በሚያደርጉት በሌላ ዓይነት ስምምነት እንዲቀር ለማድረግ አይቻልም።

አንቀጽ 104 ስጦታዎችና የጋብቻ ጥቅሞች

1. ስጦታ የሰጡ ወይም ወራሾቻቸውም በጠየቁ ጊዜና አስፈላጊ መሆኑ የተገመተ እንደሆነ ፍ/ቤት ተጋቢዎቹ የጋብቻቸውን ስርዓት በፈፀሙ ጊዜም ወይም ጋብቻቸው በመኖሩ ምክንያት አንዱ ለአንዱ የሰጠው ስጦታ ወይም ከሁለቱ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ከሌላ ሶስተኛ ወገኖች ያገኙትን ስጦታ እንዲመልሱ ያዛል፤
2. በጋብቻው ጊዜ ወይም በጋብቻው ምክንያት ከተጋቢዎች ለአንዳቸው ወይም ለሁለቱ ከ3ኛ ወገን ተሰጥቶ የነበረው ስጦታ ወይም ለሚስቱ ወይም የነበረውን የስጦታ ተስፋ ቃል ወይም ባልየው ለሚስቱ ወይም



ሚስት ለባልዋ የተሰጣጡትን ወይም ለመስጠት የገቡበትን የተስፋ ቃል መሠረዝ አስፈላጊ መስሎ የታየ እንደሆነ ፍ/ቤት ሊያስቀረው ይችላል።

አንቀጽ 105 በንብረት ክፍያ ስለማበላለጥ

1. ፍ/ቤት ከተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት አብዛኛውን ክፍል ወይም አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሙሉውን በደል ለተፈጸመበት ወገን ሊሰጥ ይችላል፤
2. ፍ/ቤት ከተጋቢዎቹ የአንደኛውን የግል ንብረት ለአንደኛው ድርሻ እንዲሆን ለመወሰን ይችላል፤ ይሁን እንጂ ይህ ለአንደኛው እንዲሰጥ የሚወሰነው የግል ንብረት ከባልየው ወይም ከሚስትየዋ ከሚወሰደው ጠቅላላ ሀብት ሲሶ (1/3) በላይ መብለጥ የለበትም፤

አንቀጽ 106 የመፋታቱ ኃላፊነት /1/ ከባድ ምክንያት

1. መፋታቱ የተወሰነው የአንደኛው ወገን ጥፋት በሆነ ከባድ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ከዚህ በላይ በተፃፉት 2 ቁጥሮች የተመለከቱት ቅጣቶች በተባለው ጥፋተኛ ላይ ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፤
2. አጥፊ ባልሆነው በአንደኛው ተጋቢ ላይ እኒህ ቅጣቶች ተፈጻሚዎች ሊሆኑ አይችሉም፤
3. መፋታቱ የተወሰነው የሁለቱም ወገኖች ጥፋት ባልሆነ ከባድ ምክንያት የሆነ እደሆነ የተባሉት ቅጣቶች በሁለቱም ላይ አይፈጸምባቸውም፤

አንቀጽ 107 ከባድ ምክንያት ስላለመኖሩ

1. መፋታቱ የተወሰነው ከባድ ባልሆነ ምክንያት ከሆነ ከዚህ በላይ በተጻፉት ቁጥሮች የተመለከቱት ቅጣቶች ፍቺውን በጠየቀው ተጋቢ ላይ ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፤
2. ሆኖም ፍቺው የተወሰነው ፍቺውን ባልጠየቀው ወገን ጥፋት መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳው እንደሆነ ፍቺ የጠየቀውን ወገን ከላይ ከተጠቀሱት ቅጣቶች ነጻ እንደሆነ ፍቺ የጠየቀውን ወገን ከለ
3. ከተጠቀሱት ቅጣቶች ነጻ ማድረግ ይችላል። ፍቺውን ባልጠየቀው ተጋቢ ላይ እኚህን ቅጣቶች እንዲፈፅሙ ለማድረግ አይቻልም፤

Generated by CamScanner

አንቀጽ 108 መሪ የሆኑ ሀሳቦች

1. ፍርድ ቤቱ የሚወስናቸው ቅጣቶች ከዚህ በላይ በተገፉት ቁጥሮች የተመለከቱትን ነው፤
2. ስለሆነም በማናቸውም ጊዜ እነዚህኑ ለመወሰን ወይም ላለመወሰን እንዲሁም ተፈጻሚ የሚሆኑበትን መጠን ለመወሰን ፍ/ቤቱ ሙሉ ሥልጣን አለው
3. ለጉዳዩ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ለጉዳዩ ምክንያት የሆነውን ነገር በተለይም መፋታትን ያስከተለውን የተጋቢዎቹን ጥፋት ከባድነትና በሕሊናም በኩል /በሞራል/ የፍቺው ጥያቄ የሚያስወቅስበትን መጠን መመርመር አለበት::
4. ፍ/ቤቱ የጋራ ንብረት ክፍያን የሚመለከተው ውሳኔ የሚሰጠው የፍቺ ውሳኔ በተሰጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት::

አንቀጽ 109 መሪ ደንቦች

1. የጋብቻን ሁኔታዎች ከማንደል የተነሣ ጋብቻውን መፍረስ ፍ/ቤት በሚወስንበት ጊዜ መፍረሱ የሚያስከትለውን ውጤት በርትዕ ይወስናል፤
2. ጋብቻው ፈራሽ በሆነ ጊዜ በተጋቢዎቹ መካከል ያለውን የገንዘብ ግኙነት ለማጣርት በተደነገጉት ደንቦች ፍ/ቤት ይመራል
3. በተለይም ፍ/ቤቱ የሚመለከተው የተጋቢዎቹን በቅን ወይም በመጥፎ ልቦና መሆን ሩካቤ ሥጋ መፈጸሙን ወይም አለመፈጸሙን ያሉም እንደሆን ከፈረሰው ጋብቻ የተወለዱት ልጆች ጥቅምና በቅን ልቦና የሆኑትን የሶስተኛ ወገኖች ጥቅም ነው::

ምዕራፍ 7

የጋብቻ ማስረጃ

አንቀጽ 110 የጋብቻ መኖር ማስረጃ

1. ጋብቻ መኖሩን ማስረዳት የሚቻለው የጋብቻ የምስክር ወረቀት ወይም የጋቻው መዝገብ የተረጋገጠ ግልባጭ በማቅረብ ነው፤
2. ከዚህ በታች በአንቀጽ 111 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በቀር የጋብቻን መኖር ለማረጋገጥ ሌላ ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም፤

አንቀጽ 111 ምስክር መስማት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ

1. የጋብቻው መዝገቡ በመጥፋቱ ወይም በመውደሙ የመዝገቡ የተረጋገጠ ግልባጭ ማቅረብ ካልተቻለ የጋቻው መኖር ጋብቻው ሲፈጸም በነበሩ ወይም መፈጸሙን በሚያውቁ ምስክሮች ማረጋገጥ ይቻላል::



2. ጋብቻ መፈጸሙን በምስክሮች ማስረዳት የሚፈቀደው የጋብቻው መዝገብ መጥፋት ወይም መውደም በቅድሚያ ከተረጋገጠ በኋላ መሆን ይኖርበታል::

አንቀጽ 112 የጋብቻ መፍረስ ማስረጃ

ጋብቻ በፍርድ ቤት የፈረሰ መሆኑ ማረጋገጥ የሚቻለው ፍ/ቤት የሰጠውም ውሳኔ ግልባጭ በማቅረብ ይሆናል::

Generated by CamScanner

# ስለ አዘጋጁ

የዚህ ስሁፍ አዘጋጅ በህግ ትምህርት የባችለርና የማስትሬት ዲግሪ ያለው ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በህግ ፋኩልቲ በመምህርነት በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ በፍትህና የህግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ሥር በተቋቋሙት የፌደራል ህጎች ማሻሻያ የሥራ ቡድኖች በአንዱ በተለየም ይሀን የቤተሰብ ህግ ባረቀቀው የአራት ሰዎች ኮሚቴ ውስጥ በትርፍ ሰዓት ሥራ ከ1990 - 1993 ዓ.ም በአባልነት አገልግሏል፡፡

ረቂቁ የቤተሰብ ህግ በፍትህ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ቀርቦ በተከታታይ ሲምፖዚየሞች ውይይት ከተደረገበት በኋላ የመጨረሻ ቅርፁ እንዲይዝ ወደዚህ ኮሚቴ ስለተመራ ይህ አዘጋጅ የረቂቁን የእለት ተእለት አካሄድ በቅርበት የመከታተል እድል አጋጥሞታል፡፡

በረቂቅ የየቤተሰብ ህጉ ላይ በተካሄዱት ተከታታይ ሲምፖዚየሞች አዘጋጁ በፅሁፍ አቅራቢነት፣ በሰብሳቢነት እንዲሁም በአወያይነት በተለያዩ መድረኮች ተሳታፊ ሆኗል፡፡ በመጨረሻም ረቂቁ የቤተሰብ ህጉ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግና የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴዎች ለጋራ ውይይት ሲቀርብ በአስረጅነት ተገኝቷል፡፡ ከዚህም አልፎ ረቂቁ የቤተሰብ ህግ ለህዝባዊ ውይይት ሲቀርብ እንዲሁ በአስረጂነት ተገኝቶ ማብራሪያዎችና አስተያየቶች የመስጠት በአንፃሩም ጥያቄችና አስተያየቶችን የማስተናገድ እድል አጋጥሞታል፡፡

ዋጋው ብር 28.00

ሬቂት ማተሚያ ቤት
0911-697470

Generated by CamScanner